# መግባትና እና መውጣት

*(ከአስተናጋጁ ማስታወሻ የተቀነጨበ)*

በዕውቀቱ ሥዩም

ሚያዝያ 2005 ዓ.ም

# ምዕራፍ አንድ

አዲሳባ ውስጥ የሚኖሩ ወይም የሚቆዩ ጀርመኖች ያቋቋሙት ትምህርት ቤት አለ:: በትምህርት ቤቱ ሥር ቤተ መጻሕፍት፣ ቤተ ሰገራ እና ሽንት ቤት እንዲሁም ቤትሆቨን በተባለ ያገራቸው ሰው የተሰየመ ካፍቴሪያ ይገኛል:: ወደ ካፍቴሪያው የተለያዩ ሰዎች ይመጣሉ፤ በተለይም ጀርመኖች፣ ጀርመንኛ ቋንቋ የሚማሩ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች እንዲሁም ‹ጀርመኖች በሚገኙበት ካፌ ስለ ገቡ ብቻ ጀርመን አገር የገቡ የሚመስላቸው ቦዘኔዎች› ይመጣሉ(አባባሉ የጓደኛዬ የምዑዝ ነው):: ወደ ቤትሆቨን ካፌ የሚመጡ ኢትዮጵያውያን ወንዶች እና ሴቶች የአንድ አገር ልጆች አይመስሉም:: ምነው ቢሉ፣ ሴቶቹ እንኳን ዐይናቸው መነጽራቸው የሚያማልልላቸው፣ ያነገቡት ግዙፍ ቦርሳ እና የለበሱት ልብስ የሚያምርባቸው፣ ትኩረትን ሁሉ በቁጥጥር ሥር የሚያውል ዐምባገነን ቂጥ የሚከተላቸው፣ ሲያወሩ እና ሲሥቁ በራስ መተማመን የሚታይባቸው ናቸው:: ወንዶቹ በበኩላቸው፣ እንኳን ሱሪያቸው ቆዳቸው የሰፋባቸው፣ ምቾታቸው ኀቡእ የገባባቸው፣ እምብዛም የማይሥቁ፣ ሳት ብሏቸው ከሣቁ እንኳ ሳል የሚያደናቅፋቸው፣ አገጫቸውን እጃቸው ላይ



አስደግፈው ለረጅም ጊዜ ስለሚቆዝሙ፣ ራሳቸው ባንገታቸው ሳይሆን በእጃቸው ድጋፍ የቆመ የሚመስልባቸው ናቸው::

በቤትሆቨን ካፍቴሪያ ውስጥ ጠዋት የማስተናገድ ሥራ እየሠራሁ፣ ከሰዓት የጀርመን መንግሥት በፈቀደልኝ መሠረት በነጻ የቋንቋ ትምህርት እየተማርሁ ትንሽ እንደ ቆየሁ ጆሮዬን ያመኝ ጀመር:: ሕመሙ እንደ ጀመረኝ ጆሮዬ የወትሮ ልምዱን ትቶ አዲስ አሠራር አመጣ:: በል ሲለው አዛብቶ ይሰማል፤ ካፍቴሪያው ግድግዳ ላይ በተንጠለጠለው ቴሌቪዥን የቢቢሲ ዜና ስከታተል ጆሮዬ "Horn of Africa" የሚለውን "Horny Africa" ብሎ ይሰማል፤ "የG-Eight" አገሮች የሚለውን "የG-spot" አገሮች ብሎ ይተረጉማል:: አንዳንዴ ደሞ ባከራዬ ቤት ጣራ ላይ ከጭስ ማውጫው አጠገብ እንደ ተሰቀለው የወሬ መግላሊት(ዲሽ) መረጃ ከሩቅ ይጠልፋል::

ሕመሙ በጀመረኝ ሰሞን ካንገት በላይ ሕክምና ወደሚሰጥበት ማእከል ሄድሁ:: ዶክተሩ ጓንቱን አጥልቆ፣ በጆሮዬ ቀዳዳ አጮልቆ፣ አእምሮዬን የሚሰልል ይመስል ግማሽ ሰዓት ተለግቦ ቆየ:: ሲጨርስ ራሱን ነቅንቆ፣ ጓንቱን አውልቆ እስኪርቢቶ ካነሣ በኋላ «የሰገራ ምርመራ ያስፈልግሃል፤. . .ቀጣዩ ክፍል ሄደህ ሁለት መቶ ብር ከፍለህ ናሙና ስጥ!» አለኝ::

«ጆሮዬን ከሰገራዬ ጋራ ምን አገናኘው?» ብዬ ጠየቅሁት:: ከሚጽፍበት ቀና ብሎ ዛቻ በሚያህል አስተያየት ላፍታ ካተኩረብኝ በኋላ፣ መልስ ሳይሰጠኝ መልሶ አቀረቀረ:: በዚህ ጊዜ ዕቃ ለማሰናዳት ወደ ምርመራ ክፍሉ የገባች ነርስ ፈገግ ስላለችልኝ፣ የልብ ልብ ተሰምቶኝ፣ «ንገረኛ! . . .ሰገራዬን ከጆሮዬ ጋራ ምን አገናኘው?» ብዬ ደነፋሁ:: ይሄኔ ዶክተሩ ዘና ባለ'ድምፅ፣ «Well . . . ሰገራ በነካ ጣትህ ጆሮህን የጎረጎርህበት አጋጣሚ ካለ ብዬ ነው!» ብሎ

መለሰልኝ:: ነርሲቱ በጣም ሣቀች:: እኔ ግን እጅግ አዘንሁ:: ግዴለም የሰገራ ናሙና መስጠት እሰጣለሁ፤ ግን ለናሙና ሁለት መቶ ብር መክፈሌ ምን የሚሉት ነው? በቀበሌያችን የተመደበ የፍሳሽ መኪና እንኳ ለሙሉ ሽንት ቤት ማስመጠጫ ያን ያህል አያስከፍልም::

ቢቸግረኝ ያለሁበትን ሁኔታ ለታታሪው ተስተናጋጅ ለምዑዝ አዋየሁት:: «በልጅነትህ አባትህ ጆሮ ግንድህ ላይ በጥፊ መትቶህ ያውቃል?» ሲል ጠየቀኝ - አንድ ቀን:: ለማስታወስ ሞከርሁ::

የእንጀራ አባቴ በጣም ጥሩ ሰው ነበር:: በሕይወቱ አንድ ጊዜ ብቻ ነው የመታኝ:: እሱም እንዴት ነበር?. . .እም፤በልጅነቴ ልጅነት አታሎኝ በጎችን በግጦሽ መስክ ላይ በማሰማራት ፈንታ፣ ከጓደኞቼ ጋራ ኳስ በምንጫወትበት ሜዳ ጠርዝ ላይ አሰማርቻቸው - ርቀው ለመሄድ ሲሞክሩ ግብ ጠባቂነቴን ትቼ የግቡን ችካል ነቅዬ እየመለስኋቸው - በጎቹም ቢጨንቃቸው - የሚግጡት ነገር ቢቸግራቸው - ኳስ እንመልከት ብለው - ኳስ ጨዋታ ሲመለከቱ ውለው - ሲመሽ መራባቸውን አባቴ እንዳያስተውለው - በድብቅ ነድቻቸው ጉሮኗቸው ውስጥ አስገብቼ ዘጋሁባቸው::

የበጎች ቅንነት በወንጌል ውስጥ ብቻ ነው:: ጉሮኗቸው ውስጥ ቢገቡም፣ ‹ተርበናል› ለማለት አፋቸውን ወደ እንጀራ አባቴ መኝታ ቤት አነጣጥረው የሮሮ በእእታቸውን አቀለጡት:: የእንጀራ አባቴ፣ ለበጎቹም የሣር አባታቸው ነውና፣ ክሳቸውን ሰምቶ፣ ከወገቡ በታች ጋቢ አገልድሞ ከመኝታ ቤቱ ወጥቶ «በጎች እየጮሁ ነው!» አለኝ በቀዘቀዘ ድምፅ፣ «እየሰማኋቸው ነው!» አልሁት::

«መጮሃቸው ምንን ይገልጻል?» ቀጠለ፤



«ያው፣ መጮህ እንደሚችሉ ይገልጻል!» ብዬ መለስሁለት::

ወዲያው በእንጀራ አባቴ ፊት ላይ ንዴት ተሥሎ ሳይ፣ ለመሮጥ እግሬን አቀባብዬ ስጠባበቅ፣ እሱ ወደ መጣበት ዞር ብሎ ተራመደ፤ ይሄኔ ንዴቱን በእንቅልፍ ለማሳለፍ ቆርጧል ብዬ ስዘናጋ ድንገት ዞር ብሎ፣ ክንዴን ለቀም አድርጎ ከያዘ በኋላ አንዴ በኀይል መታኝ:: ነገሩ ብዙ ዘመን ስላለፈው ምኔን እንደ መታኝ ረስቼዋለሁ:: ታዲያ እኔ ከረሳሁት ለምን ራሱን አልጠይቀውም ብዬ የእንጀራ አባቴ ወደሚኖርበት ደብረ ማርቆስ ለመሄድ አውቶብስ ተሳፈርሁ:: ደጀን ላይ ስደርስ ግን ቂጤን በካልቾ እንደ መታኝ ትዝ አለኝ፤ ተመለስሁ::

ቀጥዬ ችግሬን ያዋየኋት፣ በአስተናጋጅነት አብራኝ የምትሠራውን ጓደኛዬን መክሊትን ነው:: «ተማሪ በነበርህበት ጊዜ አስተማሪህ ጆሮ ግንድህ አካባቢ በጥፊ መትቶህ ያውቃል?» አለችኝ::

በፍጹም፣ መምህሮቼ ለምን ይመቱኛል? በትምህርት ሰነፍ አልነበርሁም:: እንዲያውም እነሱ ከጠየቁኝ በላይ ጨምሬ እመልስ እንደ ነበር አገር ያውቃል፤ ለምሳሌ:- *የምድር ልኬት መምህሬ*፣ «የራስ ዳሽን ተራራ ቁመት ስንት ነው?» ብለው የጠየቁኝ እንደሁ፣ «ሰሞኑን ረዝሞ ካልሆነ በቀር፣ ያለፈው መጋቢት ከባሕር ጠለል በላይ አራት መቶ ሜትር ከፍታ ነበረው፤» ብዬ እመልስላቸዋለሁ:: አቅፈው ይስሙኛል:: ትንሽ የሚያዳግቱኝ የትምህርት ዐይነቶች ቢኖሩ መዝሙር እና ስፖርት ናቸው:: በእነዚህ ትምህርቶችም ቢሆን ጆሮ ግንዴን በጥፊ እስከ ማስመታት የሚያደርስ ውጤት አልነበረኝም:: የመዝሙር መምህሬ አንድ

ቀን ሳንጎራጉር በጥሞና ከሰሙኝ በኋላ፣ ተሰጥኦዬ የጉሮሮ ሳይሆን የመዳፍ መሆኑን ገልጠው፣ ጓደኞቼ በኅብረት ሲዘምሩ እኔ በጭብጨባ ብቻ እንድሳተፍ መከሩኝ።

ስፖርት አስተማሪያችን በበኩላቸው ወደ መስክ ይዘውን ይወርዱና በተሸበለለ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ወዲያ ማዶእየጠቆሙ፣ ‹‹ያን ግራር ዞራችሁ ተመለሱ!›› ይሉናል። ግራሩ ላይ ደርሰን እስክንመለስ እሳቸው የእለቱን ርእስ አንቀጽ የማንበቢያ ፋታ ያገኛሉ። እኔ ብዙ አቅም አልነበረኝምና ትንሽ ሮጥ ሮጥ እንዳልሁ ከቀበቶ ማሰርያዬ ግድም ያደፈጠ ውጋት ጠቅ ያደርገኝና እጆቼን ወገቤ ላይ አኑሬ እቆማለሁ። መምህሩ ይህን ቢያዩ፣ ተማሪዎች በሁለተኛው ዙር ሩጫ ግራሩን ትተው እኔን ዞረው እንዲመጡ ሐሳብ አቀረቡ።

በዚህ አይነት የቤተሰብ እና የትምህርት ቤት ትዝታዬን መርምሬ ጆሮዬ ላይ የሚያደርስ ነገር ባጣበት ሌላ መላ ፍለጋ ሄለን ዘንድ ሄድሁ። ሄለን፣ ጀርመንኛ የምትማር የካፌያችን ደንበኛ ናት። ‹‹ከባድ የጦር መሣርያ በቅርብ ርቀት ጮሆብህ ያውቃል?›› ብላ ጠየቀችኝ። ይህ ጥያቄ ከጦርነት ጋራ የተቆራኘውን ትዝታዬን ያሳስበኛል።

አሥራ ሁለተኛ ክፍል ስደርስ፣ ካንዲት ተማሪ ጋራ ያይን ፍቅር ያዘኝ። ልጅቱን መጠየቅ መምህራንን እንደ መጠየቅ ስላልቀለለኝ ዝም ብዬ ስደናበር ማትሪክ ወደቅሁ። ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ አገራችን በድንበር ውዝግብ ምክንያት ከጎረቤት አገር ጋራ ጦርነት ውስጥ ስለ ገባች በእግረኛ የጦር ክፍል ለመዝመት ተመዘገብሁ። ለምን ለመዝመት እንደ ወሰንሁ እስከ አሁን በውል አልተገለጠልኝም። ምናልባት ማትሪክ በመውደቄ ያጣሁትን ክብር በአርበኝነት ክብር ለማስመለስ ይሆናል። እናቴ ለመዝመት ማቀዴን ስትሰማ በድንጋጤ ትወድቃለች ብዬ ስላሰብሁ፣ ከኋላ ደግፎ የሚያስቀራት ሰው ሁሉ አሰናድቼ ነበር። እናቴ እግሬ ላይ



ወድቃ፣ ጎረቤቱን አገሩን አስተባብራ ታስቀረኛለች ብዬ ተስፋ አድርጌያለሁ። እንዲያ ከሆነ፣ «ሊዘምት ፈልጎ ነበር! ነገር ግን የእናቱ ፍቅር ከዘመቻ አስቀረው!» ተብዬ የእናትንም የእናት አገርንም ፍቅር ጠቅልሎ የያዘ ስመ ጥርነት እቀዳጃለሁ ብዬ አሰብሁ። ይሁንና ያሰብሁት አልሆነም።

ሕዝቡ በጠቅላላ አገር እንድለቅ ሰበብ ሲፈልግልኝ እንደ ቆየ የገባኝ የመዝመቴ ነገር እንደ ተሰማ ሁሉም የሽኝት ድግስ ለማሰናዳት ሲሯሯጥ ሳይ ነው። እናቴ በድንጋጤ በመውደቅ ፈንታ ለስንቅ የሚሆን ዳቦ ቆሎ ለመቁረጥ ስታቅድ፣ የቀኝ ጎረቤታችን ሊጥ፣ የግራ ጎረቤታችን መቀስ ለማዋጣት ተስማሙ። ገብስ ከጥይት የሚከላከል ይመስል፣ አጎቴ አንድ ከረጢት በሶ ለማበርከት ቃል ገባ።

በመሸኛው ቀን እየተበላ፣ እየተጠጣ ወታደራዊ ምክር ይዋጣ ጀመር። ከኮርያ ጦርነት ያለግራ እግር የተመለሱ ጡረተኛ ሽማግሌ፣ «ዋናው ነገር በግራ በኩል ወደ ጠላት ምሽግ ዘልለህ መግባት ነው! ጠላት እንዲህ ያለ ዱብ ዕዳ ሲገጥመው የያዘውን ጥሎ መፈርጠጡ አይቀርም!» አሉኝ። ኮንጎ ዘምተው የተመለሱ ሽማግሌ ግን ወደ ጠላት ምሽግ በመዝለሌ ነጥብ ላይ መስማማታቸውን ገልጸው፣ ይሁን እንጂ፣ «በግራ በኩል ሳይሆን በቀኝ በኩል ቢዘል ይሻላል!» የሚል ሐሳብ አቀረቡ። ወዲያው በግራ በኩል ይዝለል ወይስ በቀኝ በኩል የሚለው ሐሳብ ለአንድ ሰዓት ያህል አከራከረ። ክርክሩ መቋጫ ሳይገኝለት ስለ መሸ፣ ሽማግሌዎችም ስለ ደከማቸው በተመቸኝ አቅጣጫ በኩል እንድዘል ወስነው ወደ የቤታቸው ሄዱ። በመጨረሻ ላይ ሲሰናበቱኝ ባንገቴ ዙሪያ እንደ ቡዳ መድኃኒት ተጠምጥመው ያለቀሱት መሪር ለቅሶ፣ የምሄድበት ዘመቻ ወደ ምሽግ ከመዝለል የከፋ

ነገር እንዳለበት እመለከተኝና እኔም ጦሽ ብዬ አለቀስሁ።

አንባቢ ሆይ፣ እኔ አገሬን እወዳለሁ። አገር ሲኖር ነው የሻይ ማለቢያ ማሽን የሚኖረው፤ የሻይ ማለቢያ ማሽን ሲኖር ነው አስተናጋጅም፣ ተስተናጋጅም የሚኖረው። ያም ሆኖ የአገርን ሉዐላዊነት በደም ማስጠበቅ በሚለው አላምንም፤ ከሚገረዝበት ቀን በቀር የወንድ ልጅ ደም እንዲፈስ አልፈልግም። እንዲህ ስል ግን የአገር ዕጣ ፈንታ የሚወሰነው በማሽነፍ እና በመሸነፍ መሆኑን ዘንግቼ አይደለም፤ ግጭት አይኑር የሚል ደደብም አይደለሁም። ቦታ ከጠበበው እንኳን አገር እና አገር ብርጭቆ እና ብርጭቆም ይጋጫል። እኔ የምለው የተሻለ የመሸናነፊያ መንገድ ይኑር ነው። ለምሳሌ፡- ሁለት አገሮች በድንበር ቢጣሉ ከአወዛጋቢው ድንበር አርባ ሁለት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወታደሮቻቸውን ያሰልፉና ወደ ድንበሩ አቅጣጫ እንዲሮጡ ይዘዟቸው፤ ቀድሞ ሮጦ ወደ ድንበሩ የደረሰውን ወታደር ያሰለፈች አገር አወዛጋቢውን መሬት ትወሰድ፤ የለም፣ ያለጠብ አይሆንም ከተባለ ደሞ ወታደሮች ከባድ መሣርያቸውን ትተው ትግል እንዲገጥሙ ይደረግ። ብዙ ወታደር የተዘረረባት አገር አወዛጋቢውን መሬት አሳልፋ እንድትሰጥ ይሁን። መቼም ይህን አሰብሁት እንጂ ለባለሥልጣኖች አልተናገርሁትም። ይህን ከመናገር ይልቅ ወደ ማሠልጠኛ ጣቢያ ይዞን ከሚሄደው የጭነት መኪና ላይ ወደ መሬት መዝለል ቀለለኝ። ያኔ መሬት ያረፍሁት በጆሮ ግንዴ በኩል ይሆን እንዴ?



# ምዕራፍ ሁለት

በቤትሆቨን ካፌ ውስጥ ጠዋት ባስተናጋጅነት እየሠራሁ፣ ተሲዓት በኋላ የጀርመን መንግሥት በፈቀደልኝ መሠረት ጀርመንኛ ቋንቋ እየተማርሁ ትንሽ እንደ ቆየሁ ጆሮዬን ያመኝ ጀመር። ሕመሙ በፈጠረብኝ ጭንቀት ምክንያት የሦስት ቀናት ፈቃድ ለመጠየቅ ሥራ አስኪያጃችንን ደጅ ጠናሁ።

ሥራ አስኪያጁ ዕድሜው በግምት ኀምሳ ዓመት የሚጠጋው ጎልማሳ ነው። ጀርመን አገር ተምሮ ከመጣ ወዲህ የጀርመኖች ታታሪነት ተጋብቶበት፣ በቀሪው ሕይወቱ አንዲት ሰከንድ ላለማባከን ቃል ገብቷል ይባላል። ለምሳሌ፡- የሚለብሰው ሹራብ በፊትም በጀርባም ኪስ አለው፣ ምክንያቱም አዙሬ ለበስሁት አለበስሁት የሚለውን በማጣራት ጊዜ እንዳያባክን ነው። ሽንት ቤት ሲገባ እንኳ የጀመረውን ሥራ ይዞ ይገባል፤ ታዲያ የሽንት ቤቱ በር ሲንኳኳ መጸዳጃ ቤት ውስጥ መሆኑን ዘንግቶት፣ «ይግቡ ብሎ ይጋብዛል!» ይባላል። ከዕለታት አንድ ቀን ባለቤቱ፣ «የኔ ውድ! ምነው የሻይ ሰዓት እንኳ የሰህም?» ብትለው፣ «በሻይ ንግድ እንጂ በሻይ ሰዓት የከበረ ሕዝብ የለም!» ብሎ መልሶላታል ይባላል። ከሳምንት አንድ እሑድ ለሁለት ሰዓታት ያህል ዕረፍት ያደርጋል። በዚህ ጊዜ የሚወደው የጊዜ ማሳለፊያ እጁን ወደ ኋላ

ሽርባ በእግር መንሸራሸር ነው፤ ታዲያ በእግሩ እየተንሸራሸረም ሥራ እንዳይፈታ፣ «ርምጃዎቹን ይቆጥራል» ይባላል::

ሥራ አስኪያጁ ቢሮ ገብቼ፣ ጉዳዬን በጥቂት ቃላት አስረድቼ ከቋጨሁ በኋላ ውሳኔውን ጥበቃ ዐይን ዐይኑን ማየት ጀመርሁ:: መልስ ሳይጠኝ ከፊቱ የነበረውን የስልክ እጀታ አንሥቶ ቁጥር ከመታ በኋላ፣ ለእሱ ከካፌ ማኪያቶ እንዲላክለት አዝዞ፣ ወደ እኔ ፊቱን መልሶ፣ "Was Möchten Sie?" (ምን ትወስዳለህ?) ብሎ ጠየቀኝ:: መቼም በአማርኛ ሊጠይቀኝ ይችል ነበር:: ግን ይህ ሰው ምንም ነገር ማባከን አይፈልግም፤ ባንድ ዐረፍተ ነገር ግብዣ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን ጀርመንኛ መፈተን እንደሚቻልም ያምናል::

ዳቦ እና ሻይ እንዲጋብዘኝ ፈልጌ ነበር፤ ግን ዳቦ እና ሻይ በጀርመንኛ ምን ማለት እንደ ሆነ አላወቅሁም፤ አላዋቂነቴን ከማጋለጥ ዳቦ እና ሻዩን ማጣት መርጬ፣ "Wasser (ውኃ)» ብዬ መለስሁ:: እነሆ እሱ ማኪያቶውን እያጣጣመ፣ እኔ ጉንጭ የሚቆረጥም ቀዝቃዛ ውኃ እየተጋትሁ ቁጭ ብለናል::

በነገራችን ላይ ባንድ ዐረፍተ ነገር ሁለት ሐሳብን ስለ መግለጽ ስናገር ሌላ ነገር ትዝ አለኝ:: «ባንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ» ይላል ያገራችን አዳኝ፤ «ባንድ ክፍለ ጊዜ ሁለት የትምህርት ዐይነቶች» ይላሉ የሦስተኛ ክፍል የስፖርት መምህሬ፤... ትዝ ይለኛል፣ ሦስተኛ ክፍል ስደርስ ብዙ መምህራን ወደ ሱዳን ስለ ተሰደዱ በትምህርት ቤታችን ውስጥ ከነበሩት መምህራን ይልቅ ዘበኞቹ በቁጥር ይበልጡ ነበር:: የመምህራን እጥረት ለመቋቋም አንድ መምህር ሁለት የትምህርት ዐይነቶችን እንዲያስተምር የሚያዝዝ ደንብ ወጣ:: በዚህ ደንብ መሠረት የስፖርት መምህራችን



የመዝሙር መምህርም እንዲሆኑ ተወሰነ:: በመጀመርያው ክፍለ ጊዜ ያስሮጡናል፤ በሁለተኛው ክፍለ ጊዜ ደግሞ «አጥንቴም ይከስከስ» የሚለውን መዝሙር ያዘምሩናል:: ከጊዜያት በኋላ ግን ሁለት ክፍለ ጊዜ ማስተማር ስለ ታከታቸው ስፖርትን እና መዝሙርን ባንድ ክፍለ ጊዜ ለማጣቃለል ወሰኑ:: እናም፣ «አጥንቴም ይከስከስ» የሚለውን መዝሙር እየዘመርን እንድንሮጥ ሐሳብ አቀረቡ::

ወደ ቀደመ ነገራችን ስንመለስ፣ ሥራ አስኪያጁ ማኪያቶውን እየጠጣ የሆነ ነገር በወረቀት ላይ ጽፎ አቀበለኝ:: ለሦስት ቀናት የሚቆይ ፈቃድ ማግኘቴን የሚገልጽ ወረቀት ነው፤ ላመስግነው ብድግ አልሁ፤ ግን ምስጋናዬ ጊዜውን እንዳያባክንበት ሰግቼ በቀጥታ ወደ በሩ አመራሁ:: ወዲያው ግን ምናለ የመታከሚያ ገንዘብ ቢሰጠኝ የሚል ምኞት መጣብኝ:: ምኞቴ ተስፋ ሆነና ከአሁን አሁን ይጠራኛል በማለት አረማመዴን እያዘገየሁ ተራመድሁ:: እውነትም የበሩን እጀታ እንደ ጨበጥሁ ከኋላዬ ጠራኝ::

«አቤት!»

«ሃያ ሁለት ማዞሪያ የሚገኘውን ሶፍ ዑመር ባንክ ታውቀዋለህ?» ሲል ጠየቀኝ::

«አዎ!» አልሁ፣ ባንድ በኩል ፈገግታዬን በቁጥጥር ሥር ለማዋል እየሞከርሁ፣ በሌላ በኩል ከጠረጴዛው ላይ የቼክ ደብተር በዐይኔ እየፈለግሁ::

«ከባንኩ አጠገብ ዘመናዊ ክሊኒክ ተከፍቷል፤ እዚያ ብትሄድ ጥሩ ነው» አለኝና ወደ ስሌት ማሺናው አቀረቀረ:: በጣም

አዝኜ ወጣሁ:: ለነገሩ ጥፋቱ የእኔ ነው:: ጥፋቴ፣ ተስፋን የሙጥኝ ማለቴ:: በውነቱ፣ ተስፋ የገቢ ምንጭ የሚሆነው ለሎተሪ አዟሪዎች ብቻ ነው:: ግን ምነው መተዛዘን ጠፋ? «ሁለት ኮት ያለው አንደኛውን ኮት ለባልንጀራው ይስጥ፤» ተብሎ በወንጌል ተጽፏል፤ ታዲያ ዛሬ ይህን የሚተገብር ይኖራል? አንባቢ ሆይ፣ በዚህ ዘመን፣ አበበ ሁለት ኮት ካለው አንደኛውን ኮት ለከበደ ከሰጠው፣ ከበደ ላውንደሪ ቤት አለው ማለት ነው::

የቤትሆቨን ካፌን ግቢ እንደ ለቀቅሁ፣ ጎዳናው ዳር ቆሜ ሚኒባስ መጠበቅ ጀመርሁ:: ድንገት ዞር ስል አንድ ትዕይንት ዐይኔን ያዘው:: ግራ እጁ የተቆረጠ ጠብደል ለማኝ በቀኝ እጁ ገጀራ ይዞ እየነቀነቀ፣ «ኧረ ስለ ገብሬል፤ ኧረ ስለ ገብሬል፤. . .እኔ ተናግሬያለሁ ስለ ገብሬል!» በማለት ይጮሃል:: አላፊ አግዳሚውም ገብርኤልን ሳይሆን ገጀራውን ፈርቶ ምጽዋቱን ያዥጎደጉደዋል:: ድንገት ከዬት መጣ ያልተባለ የፌዴራል ፖሊስ አባል ተጠግቶት፣ «ገጀራውን ለምን ያዝከው!» ብሎ አፈጠጠበት:: ለማኙ አንገቱን ደፍቶ፣ «. . .በግጦሽ መሬት ምክንያት በተከሠተ ግጭት ግራ እጄን ያጣሁት በዚህ ገጀራ ስለሆነ ለመታሰቢያነት ይዤው እዞራለሁ፤» አለና፣ «ኧረ ስለ ገብሬል!. . .» ብሎ ወደ አልፎ ሂያጆች ዞረ::

ቀጥሎ ምን እንደ ተከሠተ አላየሁም:: ከላይ ሲጋልብ የመጣ ሚኒባስ ባጠገቤ ሽው ብሎ አዳፋ የጎርፍ ውሃ ከላይ እስከ ታች አከናንቦኝ ሄደ:: ዝቅ ብዬ ባይ አስፋልቱ ላይ የተቋጠረ ጎርፍ የለም፤ ታዲያ ውኃው ከዬት መጣ? ምናልባት የሚኒባሱ ሾፌር በባሊ ደፍቶብኝ ይሆን?

ቀኑ ደመናማ በመሆኑ፣ ፀሐይዋ ያለውትሮዋ በመራቋ፣ አውሮፕላን ጀርባ ላይ ካልተሰጣ በቀር የረጠበው ልብሴ



እንደማይደርቅ ገባኝ:: ይሁን እንጂ ወዲያው ብልሃት መጣልኝ:: መንገዱ ዳር ወደሚገኝ ካፌ ገብቼ ትኩስ ነገር ለመውሰድ አሰብሁ:: ሆዴ በጣም ከሞቀ ቢያንስ ከናቴራዬ ይደርቃል:: ገባሁና አስተናጋጁን ጠርቼ ጦመኛ ስለ ሆንኩ ሻይ እና ችብስ እንዲያመጣልኝ ነገርሁት:: አሻግሬ ወደ ውጭ መመልከት ጀመርሁ:: ማዶ ካለው አሮጌ አጥር ሥር አንድ መጽሐፍ አዟሪ ጎረምሳ ብልቱን በጳውሎስ ኞኞ መጽሐፍ ጋርዶ ሽንቱን ይሸናል:: እየሸና ሰው ዐየኝ አላየኝ ብሎ ሲገላመጥ ከእኔ ጋራ ተገጣጠምንና በእጄ ምልክት ጠራሁት:: ሽንቱን ሳይቋጭ ተንደርድሮ ገባ:: አንዱን መጽሐፍ እየመዘዝሁ፣ «በቢንላደን ላይ መጽሐፍ ጽፈውበት ነው?» ብዬ ጠየቅሁት::

«ቢንላደን አይደለም፤ኦሾ ነው!» አለኝ አዟሪው እየሣቀ:: ከኦሾ መጽሐፍ ለናሙና ሁለት አንቀጽ አንብቤ የእግዜርን ህልውና ስለ ተጠራጠርሁ፣ አስተናጋጁ ችብሱን ትቶ ጥብስ እንዲያመጣልኝ ነገርሁት:: ጥብሱ በጣም ጥሩ ነበር:: ብዙ ሬስቶራንቶች ውስጥ እንደሚታየው በጥብሱ ውስጥ ፀጉር አላገኘሁም:: ጥብሱን ያዘጋጀው ሼፍ መላጣ ሳይሆን አይቀርም::

ከካፍቴሪያው ከወጣሁ በኋላ ሳልፈልግ ራሴን ከአስተናጋጁ ጋራ ማነጻጸር ጀመርሁ:: ልጁ በመልኩ እና በዩኒፎርሙ ጥራት ይበልጠኛል:: በተጨማሪም ኮካ በትከሻው ላይ አስቀምጦ መክፈት ይችልበታል:: በርግጥ ኮካን ትከሻህም ላይ ክፈተው፣ ጠረጴዛ ላይ ጣዕሙን አይቀይረውም:: ግን በቃ፣ ተስተናጋጁ ኮካ አዝዞ የሰርከስ ትርኢት ይመረቅለታል:: ያ አስተናጋጅ በዚህ ረገድ ሊደነቅ ይገባል:: በሒሳብ ግን አይደርስብኝም፤ የእኔን ጨምሮ የሦስት ደንበኞችን ሒሳብ ሲሳሳት አይቻለሁ:: ይህ ሰው በባቄላ ፍሬ ሲያሰላ ያደገ ሳይሆን አይቀርም ብዬ አሰብሁ፡፡ ጓደኛዬ ምዑዝ እንደ ነገረኝ

የጥንት ኢትዮጵያውያን በጦርነት የተሞላ ኑሯቸው የሒሳብ ዕውቀታቸውን ለማዳበር ጊዜ ስላልሰጣቸው መደመር እና መቀነስን የሚሠሩት የባቄላ ፍሬን በመጠቀም ነበር። ነገሩ እውነት ከሆነ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የባቄላ ዝምድና ከአተር ጋራ ብቻ ሳይሆን ከካልኩሌተር ጋራ ጭምር ነው።

* * *

ወደ ቤት መጣሁ። በግቢው ውስጥ አበባ ሲከባከቡ የቆዩት አከራዬ ወይዘሮ ይርገዱ፣ በቀን ያለወትሮዬ ግቢ ውስጥ ቢያዩኝ ተገርመው፣ «ምነው?» ብለው ጠየቁኝ፣

«ትንሽ አሞኝ ነው!» አልኳቸው።

«በል ግባና ጋደም በል፤ መጥተን እንጠይቅሃለን፤» አሉኝ፣ ከእጃቸው ላይ አቧራቸውን እያራገፉ።

«ግዴለም ሕመሜ የሚያስተኛ ዐይነት አይደለም!» አልኳቸው።

«ቢሆንም ለመጠየቅ እንዲያመቸን ገብተህ ብትተኛ ይሻላል!»

ማምለጫ ስለሌለኝ ገባሁና አልጋዬን አነጠፍሁ። አከራዮቼ፣ በእኔ ጤንነት አሳብበው የቤቱን ጤንነት ለመሰለል ስለሚመጡ እንደ አቅሜ ክፍሉን አሰማመርሁ - ፖፖዬን እና ጫማዬን አልጋው ሥር ደበቅኋቸው። ከዚያ ሬዲዮኔን አውጥቼ፣ ከክክ ጋራ ተሰጥቶ የዋለውን ባትሪዬን አጉርሼ ኤፍ.ኤም ከፈትሁ። በሬዲዮኑ ውስጥ ጋዜጠኛው ባለሥልጣኑን፣ ሰሞኑን ስለሚታየው የመብራት መጥፋት ጉዳይ እየጠቃቸው ነበር። አዲስ አበባ ሰሞኑን



ማታ ማታ በጥቂት በርታ፣ በብዙ ጠፍታ ፊልም የተጀመረባት ግዙፍ ሲኒማ ቤት ትመስላለች። አሁን ቅድም የገባሁባት ካፌ ውስጥ ነዋይ ደበበ በኪቦርድ ሳይሆን በጄኔሬተር ድምፅ ታጅቦ ሲዘፍን ነበር። ጄኔሬተሩ ቴፑን አጅቦ ያለማቋረጥ ደቅ. . ደቅ. . ደቅ ስለሚል፣ ድምፃዊው በስቱዲዮው ውስጥ ሳይሆን በሄሊኮፕተር ውስጥ ሆኖ የሚዘፍን አስመስሎታል።

አሁን እንግዲህ ከሬዲዮኔ ውስጥ ያለው ጋዜጠኛ፣ «በቅርቡ ኀይል ቆጣቢ አምፖሎች ለኅብረተሰቡ እንደሚታደሉ ተገልጿል። ይሁን እንጂ የኀይል ቆጣቢ አምፖሎች ለወትሮ ከምንጠቀምባቸው አምፖሎች ጋራ ሲነጻጸሩ የብርሃን መጠናቸው አነስተኛ ነው የሚል አስተያየት አለ፤ እርስዎ ምን ይላሉ?. . .» ሲል ጠየቀ።

«Well. . .ኀይል ቆጣቢ አምፖሎች የብርሃን መጠናቸው አነስተኛ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም፤» አሉ ባለሥልጣኑ፣ ቀጠሉና፣ «አምፖሎቹ ደብዛዛ ቢሆኑም ገረዳችንን ከሚስታችን ለመለየት የሚያስችል በቂ ብርሃን ይኖራቸዋል።»

ጋዜጠኛውም፣ «በኀይል ቆጣቢ አምፖሎች መጽሐፍ ማንበብ ይቻላል?»

«Well. . .» አሉ ባለሥልጣኑ፣ «የብሬል መጽሐፍ ማንበብ ይቻላል።»

ይህን ያደረሰኝ ሬዲዮ ነው ወይስ የተቃወሰ ጆሮዬ? የሚለውን መመለስ አቅቶኝ ሬዲዮኔን ስዘጋ የቤቴ በር ተከፍቶ አከራዮቼ ፊት እና ኋላ ተከታትለው ገቡ።

# ምዕራፍ ሦስት

አሁን ደሞ ጥቂት ስለ አከራዮቼ - ስለ አቶ ተሻገር እና ስለ ባለቤታቸው ስለ ወይዘሮ ይርገዱ - ልናገር::

አቶ ተሻገር ከዓመታት በፊት እንጦጦ ጫካ ውስጥ ይኖር የነበረን ብቸኛ ዋልያ ለቱሪስቶች በማስጎብኘት ይተዳደሩ ነበር:: ዋልያው እንጦጦ ጫካ ውስጥ እንዴት እንደ ገባ ለእንስሳት ታሪክ ተመራማሪዎች እተወዋለሁ:: «አዝማሪዎችን ተከትሎ ከጎንደር ወደ አዲሳባ መጥቶ ነው፤» የሚሉ አሉ:: ከዬትም ይምጣ ከዬት፣ ዋልያው ለቱሪዝም ከፍተኛ ገቢ ካስገባ በኋላ ገደል ገብቶ ስለ ሞተ አቶ ተሻገር ሥራ ፈትተው ለጥቂት ጊዜ ከተቀመጡ በኋላ የዋልያውን መካነ መቃብር ለቱሪስቶች እንዲያስጎበኙ ተወሰነላቸው:: ከጊዜ በኋላም በሥራቸው የላቀ ትጋት ስላሳዩ ወደ መካከለኛው ሙዚየም ተሸጋግረው ጥንታዊ ቅርሶችን ለልጆች ማስጎብኘት ጀመሩ:: ይህን ሥራ በቅንነት እና



በትጋት ቢሠሩም መካከለኛው ሙዝየም የበጀት እጥረት ስለ ገጠመው ሊቀንሳቸው ወሰነ:: ይሁን እንጂ አንድን ሠራተኛ ዝም ብሎ ከማባረር ሰበብ ፈልጎ ማባረር፣ ላባራሪውም ለተባራሪውም ስለሚቀል፣ «የሙዚየሙን ዕቃዎች ለግላቸው ጥቅም አውለዋል፤» የሚሉ ክሶች እንዲቀርቡባቸው ተደረገ::

ከክሶቹ መካከል፣ «ከኀምሳ ዓመት በላይ ያስቆጠረውን የራስ ተፈሪን ቦላሌ ለዘመን መለወጫ በዓል ለብሰው ታይተዋል፤» የሚል ይገኝበታል:: አቶ ተሻገር ይህን ክስ ውድቅ ያደረጉት በእሳቸው እና በራስ ተፈሪ መካከል ያለውን የቁመት ልዩነት በማንሣት ነው፤ «እንደምታዩኝ እኔ በጣም ረጅም ነኝ፤» አሉ ለገምጋሚዎች፣ «ራስ ተፈሪ ደግሞ ከእኔ ጋራ ሲተያዩ ድንክ ናቸው:: ስለዚህ የእሳቸው ቦላሌ ለእኔ ሙታንታ ቢሆነኝ ነው:: ታዲያ በዘመን መለወጫ ለምን ታሪካዊ ሙታንታ እለብሳለሁ?»

ገምጋሚዎች የአቶ ተሻገር መከራከርያ አሳማኝ ሆኖ ቢያገኙትም፣ ለክርክር የተጠቀሙበት አማርኛ ራስ ተፈሪን የሚያጣጥል ሆኖ ስላገኙት፣ «ታላላቅ የታሪክ ሰዎችን ስም እና ዝና በማዋረድ» በሚል ክስ ከሥራ እንዲሰናበቱ ወሰኑባቸው::

አቶ ተሻገር ከመሥሪያ ቤታቸው ቢቀነሱም በሞት ካልሆነ በቀር ወደማይቀነሱበት ቤታቸው ተመልሰው ክፍሎቻቸውን እያከራዩ፣ ከዚያም የቀረውን የግቢያቸውን መሬት በአትክልት ያለሙት ጀመር:: ሰው በዕድሜው ሲገፋ ከሥራዎቹ ሁሉ አትክልተኝነት ይዋጣለታል፤ ምክንያቱም ሰውነቱ ስለሚጎብጥ ለማረም እና ለመኮትኮት ይመቸዋል:: አቶ ተሻገር ዕፀዋትን አጥብቀው ከመውደዳቸው የተነሳ በባልዲ ይዘውት የሚዞሩት ለማዳ ድንክ ዛፍ ነበራቸው:: ከሥራቸው ውጭ በዕፀዋት እና በእርሻ ላይ ያተኮሩ ጽሑፎችን እና ፖስት ካርዶችን ይሰበስባሉ::

እንዲያውም ባንድ ወቅት በእርሻ ላይ የሚያተኩር መስሏቸው *«የአረም እርሻ»* የተባለ የፖለቲካ መጽሐፍ ገዝተዋል።

ሚስታቸው ወይዘሮ ይርገዱ ለእኛ ዕድለኛ ተከራዮች እንደ እመ ብርሃን ናቸው። እሳቸውም፣ «እኔ ቤት የተከራየ ሰው ባስከሬን መጫኛ መኪና ካልሆነ በቀር ግቢውን አይለቅም፤» የሚሉት እውነታቸውን ነው። ምን ጎድሎብን እንወጣለን? በተለይ በግራ በኩል ያለው ተከራይ ጎረቤቴ፣ ቤቱን እጅግ ተመውደዱ የተነሳ፣ የቤት ቁጥሩን ጀርባው ላይ ተነቅሶታል፤ የእኔማ አይነሣ። ባከራዮቼ ለምጄ፣ ያደርሁበት ሁሉ የእኔ ስለሚመስለኝ፣ አልቤርጎ ከተከራየሁ እንኳ ግድግዳው ላይ ፎቶዬን መስቀል ያምረኛል። በርግጥ ያከራይ መልካምነት አንድ መልካም ያልሆነ ጎን አለው - ከኑሮ ያዘናጋል። ጓደኛዬ ምዑዝ እንደሚለው፣ *«መልካም አከራይ ያለው ሰው፣ ቤት ሳይሠራ ይሞታል።»*

ወይዘሮ ይርገዱ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጀምረው ያቋረጡት ጥንት፣ በዶሮ ላባ በሚጻፍበት ዘመን ነው። ታዲያ በቅርቡ፣ «ለትምህርት መቼም አይረፍድም፤» በሚል መፈክር ተመርተው መማር ስለ ጀመሩ ባለቤታቸው ሴት አስጠኚ ቀጠሩላቸው። አስጠኚዋ እና አጥኚዋ ከመገናኘታቸው ተላምደው፣ አፋቸው እስኪዝል ድረስ አውርተው፣ ፀጉራቸውን በየተራ ተሠራርተው ከመለያየት በቀር የመጀመርያውን መልመጃ እንኳ ስላልሠሩ፣ አቶ ተሻገር ነገሩ አሳስቧቸው፣ እሳቸው በታዛቢነት በሚገኙበት እኔ እንዳስጠናቸው ተወሰነ። እነሆ በየማታው ከወይዘሮ ይርገዱ አጠገብ ሶፋ ላይ ተቀምጬ፣ «በጨጓራ ውስጥ የሚገኘ ው ኢንዛይም ምን ተብሎ ይጠራል?» ብዬ እጠይቃለሁ።

«በጨጓራ ውስጥ የሚገኘው ኢንዛይም ነው፤ ያልኸኝ?»



«አዎ!»

«በጨጓራ ውስጥ የሚገኘው ኢንዛየምማ እንግዲህ. . ቆይ ላመጣልህ ነው. . . አደራ እንዳትነግረኝ እኔው ራሴ እመልሰዋለሁ. . .!» ይሉና በመከላከል ዐይነት ግራ እጄን አጥብቀው ይይዙታል። ጠብቄ፣ ጠብቄ አልሆን ሲል፣ «ፔፕሲን ይባላል፤» እላለሁ ጊዜ ለመቆጠብ።

«አ . .ኦ ፔፕሲን!» ይላሉ ወይዘሮ ይርገዱ እኔ የተሳሳትሁ ይመስል እጃቸውን በልበ ሙሉነት አወናጭፈው።

«እንግዲህ በጨጓራ ውስጥ የሚገኘው ኢንዛይም ምንድን ነው? ብዬ ከዚህ በፊት ሦስት ጊዜ ጠይቄዎት ረስተውታል። ለማስታወስ የሚቸግርዎት ከሆነ ያጠናን ዘዴ ልንገርዎት። ፔፕሲን የሚለውን ቃል ፔፕሲ ከሚለው ጋራ አቆራኝተው ይያዙት። ለምሳሌ፡- ቤትሆቨን ካፌ ገብተው ፔፕሲ አዝዘው ሲጠጡ በሐሳብዎ ይታይዎት!»

«ኢ. . . .ሁን ጥሩ ዘዴ አመጣህ፤» ይሉኛል ወይዘሮ ይርገዱ፤ ጄኔሬተር የዋጡ ይመስል ዐይናቸን በርቶ፣ «የካፌውን ስም ማን አልኸኝ?»

«ቤትሆቨን»

«ይህን ደግሞ ከምን ጋራ አቆራኝቼ ልያዘው?»

«ባይዙትም ችግር የለም። ዝም ብለው ካፌ ገብቼ ብለው ይያዙት፤»

«እውነትህን ነው፤ እንግዲህ ካፌ ገብቼ ፔፕሲ አዝገ6 . .

.፣ካፌ ገብቼ አዝዤ . . . ፔፕሲን!»

«ል. . . ክ ነዎት፤»

«ጥሩ! አሁን እንግዲህ ጠይቀኝ፤»

«በጨንራ ውስጥ የሚገኘው ኢንዛይም ምን ተብሎ ይጠራል?»

«ካፌ ገብቼ ኮካ አዝዤ፣ ካፌ ገብቼ ኮካ አዝዤ . . . ኮክሲን፣ ኮክሲን ተብሎ ይጠራል::»

እኔ እና ወ/ሮ ይርገዱ በዚህ ዐይነት ጥቂት ዕውቀት ብዙ ስሕተት ስንለዋወጥ፣ አቶ ተሻገር ከፊት ለፊት ባለ ሶፋ ላይ ጉብ ብለው፣ «ከምታጠኑት ውስጥ ለእኔ የሚሆን ተባራሪ ዕውቀት አይጠፋም ብዬ ነው፤» በሚል ሰበብ በተጠንቀቅ ይጠብቁናል:: ሚስታቸው፣ «ሲደክሙ ነው የዋሉ፣ ወደ ውስጥ ገብተው ይተኙ፤» ቢሏቸውም ባልየው፣ ሚስታቸውን ለብዳ ጥለው ለመሄድ አይደፍሩም:: ሽንታቸው እንኳ ቢመጣባቸው በተወካይ ይሸኑታል እንጂ ከተቀመጡበት ሶፋ ንቅንቅ አይሉም:: ይሁን እንጂ ጊዜው ሲገፋ እንደ ተሰቀለ ሰው አንገታቸውን ደረታቸው ላይ ደፍተው ማንኳረፍ ይጀምራሉ::

በጥናታችን መሀል ወ/ሮ ይርገዱ፣ «እኮ ፔፕሲን!» ብለው ሲጮሁ አቶ ተሻገር ብንን ብለው ይነሡና በሸለብታቸው መሀል የተካሄደ ነገር መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ወደ ሚስታቸው ቀሚስ እና ወደ እኔ ቀበቶ እያፈራረቁ ይመለከታሉ:: እውነት ለመናገር፣ አቶ ተሻገር እኔን በሚስታቸው የሚጠረጥሩበት ምክንያት ያለ አይመስለኝም:: በርግጥ ሚስታቸው ወይዘሮ ይርገዱ ወፍራም ናቸው:: ከወፍራምነታቸው ባሻገር ደስ የሚል



ነገር አላቸው:: ደስ ከማለታቸውም ባሻገር ጥናት ከመጀመራችን በፊት የሚቀበሉት የዘጠኝ መቶ ብር ሽቶ አላቸው:: እኔ ግን የሽቶው ዋጋ የሁለት ወር ደመወዜን እንደሚያህል ካወቅሁ ጊዜ ጀምሮ መዓዛው ፍትሕ አልባነትን እንጂ ፍትወትን አያሳስበኝም::

* * *

ይኸው አስቀድሜ እንደ ተናገርሁት፣ እኒህ አከራዮቼ ወደ ቤቴ ገብተው ካልጋዬ ፊት ለፊት ባለው ወንበር ላይ ተቀምጠው እየጠየቁኝ ይገኛሉ:: ወይዘሮ ይርገዱ በፔርሙስ ይዘውት የመጡትን የአጃ አጥሚት በመርቲ ጣሳ ሞልተው እያቀበሉኝ፣ «ትኩስ ትኩሱን ጠጣው፤ ያበስልልሃል፤» አሉኝ:: ከሕመሜ ጋራ ባይገናኝም አጥሚት ከጠጣሁ ብዙ ዘመን ስላለፈኝ ተቀብዬ እፍ እፍ ብዬ እንዲበርድ ጠረጴዛ ላይ ካስቀመጥሁት በኋላ፣ «እንዲያው ዝም ብላችሁ ነው የተቸገራችሁ፤» ብዬ ጀመርሁና ምኔን እንደ ታመምሁ፣ ባልተሳካ ሕክምና ከሁለት መቶ ብር በላይ እንደ ከሰከስሁ ተናገርሁ::

«አዬ! የዛሬ ገንዘብ ምን ዋጋ አለው ብለህ ነው?» አሉ ወ/ሮ ይርገዱ፤ «እኔ ራሴ ባለፈው ሳምንት ለጆሮዬ አንድ ሺሕ ብር አውጥቻለሁ::»

«እርስዎም ጆሮዎትን አምዎት ነበር?» አልሁ::

«ምን ያማታል፤. . . አዲስ ጉትቻ ገዝታ ነው፤» አሉ አቶ ተሻገር እየሣቁ::

ይሄኔ በር ተከፈተና የግራ ጎረቤቴ በላቸው ሁለት ሙዝ እና ሁለት ብርቱካን እንዲሁም አምስት ማካከለኛ ዱባዎች በፌስታል

አንጠልጥሎ ገባ። ወዲያው ለአከራዮቼ የተናገርሁትን ለእሱም ደግሜ የሚለውን መጠባበቅ ጀመርሁ።

እንባቢ ከፈቀደልኝ፣ አሁን ደግሞ ስለ አብሮ ተከራዬ ስለ በላቸው ኑሮ ጥቂት ልናገር። በላቸው ዕድሜው ለሥራ ሲደርስ ባንድ ትልቅ መጽሐፍ መደብር ውስጥ ተቀጥሮ ይሠራ ነበር። የመደብሩ ባለቤት ብዙ መጻሕፍትን ከሕንድ ቢያስገባም አንባቢውን አብሮ ስላላስገባ ለኪሳራ ተዳረገ። ጨርሶ ከመንኮታኮቱ በፊት ግን መደብሩን ወደ ምግብ ቤት ለመቀየር ወሰነ። ይሁን እንጂ ከመጽሐፍ መደብር ወደ ምግብ ቤት የሚደረገው ሽግግር በጣም ሥር ነቀል እንዳይሆን ስለ ፈራ በመካከል አንድ መሸጋገርያ እንዲኖር አደረገ። በመጽሐፍ መደብር እና በምግብ ቤት መካከል ያለው ብቸኛ መሸጋገርያ በምግብ ላይ ያተኮረ መጽሐፍ ነው። በዚህ መሠረት ሊቃውንት የጻፏቸውን 102 Spicy Dishes, An Abyssinan Cook Book, The End of food, Eat Caribbean, The Confession of a Chinese Chef - የሚሉ ይገኙበታል። ቀጥሎ ፖስተሮች እና የአገር ካርታዎች በሚንጠለጠሉበት ቦታ ጭልፋዎችን እና ትሪዎችን ደረደረ፤ በኋላም "Book for life" የነበረውን የመደብሩን መጠሪያ "Cook for life" ብሎ በማሸጋሸግ የሬስቶራንቱን ሥራ በይፋ ጀመረ።

በላቸው በመጽሐፍ መደብሩ ውስጥ የነበረው ሥራ የሚወጣ የሚገባውን መፈተሽ ሲሆን ከለውጡ በኋላ ደግሞ በሥጋ ቆራጭነት ተመድቦ ማገልገል ጀመረ። በራሱ አባባል ከሰው ሽንጥ ወደ በሬ ሽንጥ ተሸጋገረ ማለት ነው። በላቸው ምኞቱ ትልቅ፣ ደመወዙ ትንሽ የሆነ ሠራተኛ በመሆኑ ይህን ለማካካስ የብልጠት መላዎችን ይከተላል፤ ይባላል። ለምሳሌ፦ አንድ ደንበኛ ወደ ሥጋው ሱቅ ይመጣና፣ «አንድ ኪሎ



ቁረጥልኝ፤» ብሎ ያዘዋል። በላቸው በቢላዎው ወደ ምግብ ቤቱ በር እየጠቆመ፣ «ግቡ፤ ይመጣልዎታል፤» ይላል። ደንበኛው ከፍሎ ወደ ውስጥ ሲዘልቅ፣ በላቸው ሩቡን ኪሎ ጎምዶ ለራሱ ያስቀራል። ከጊዜ በኋላ ደንበኞች እንደተታለሉ ሲገባቸው እዚያው ቆመው ማስመዘን ጀመሩ። በላቸው ስልቱን ቀየረ። ከሥጋው ትንሽ ቆረጥ አድርጎ ሚዛኑ ላይ ካስቀመጠ በኋላ፣ ሚዛኑ እንዲደፋ ጉልጥምት የሚያህል አጥንት ጣል ያደርግበታል። አጥንቱ ሲያልቅ ቢላዎውን ከሥጋው ጋራ አብሮ ይመዝነዋል።

አሁን እንግዲህ በላቸው ችግሬን ከሰማ በኋላ፣ «ግዴለህም፣ አንድ በጣም የታወቁ የባህል ሐኪም አሉ፤ እሳቸው ጋራ ሄደህ ትታከማለህ፤» አለኝ እኔን ትቶ አጥሚቴን እየተመለከተ።

«ጎበዝ ሐኪም ናቸው?» አሉ አቶ ተሻገር፤

«በ . . . ጣም፤» ቀጠለ በላቸው፣ «ሽጎሌ የሚኖረውን አጎቴን ታውቁታላችሁ፤ መቼም በየሳምንቱ ፀጉሩን ሲስተካከል፣ ፀጉር አስተካካዩ በአጎቴ ጆሮ ውስጥ የፀጉር ብናኝ እንዳይገባ ለማገድ ጥጥ አድቦልቡሎ ይወትፍበታል። መቼም አሁን አሁን ከሽማኔዎች ቀጥሎ ጥጥን በብዛት በመጠቀም የሚታወቁት ፀጉር አስተካካዮች ናቸው። እንግዲህ ያ ጥጥ ወደ ውስጥ እየገባ እየገባ አጎቴ «ረ» የተባለችውን ፊደል እንዳይሰማ ይከለክለዋል። ከፊደላት መሀል «ረ»ን መግደፍ ብዙ ጣጣ እንዳለው የማውቀው እኔ ነኝ። አጎቴ ባንድ ወቅት ጠጅ ቤት ውስጥ አንድ ጎረምሳ፣ «በወጣትነትም በፈረስ እሽቅድድም አሸንፈዋል የሚባለው እውነት ነው?» ብሎ ቢጠይቀው ካልተደባደብሁ ብሎ ነድማ በታኝ መኪና ነው የተገላገለው።»

ታዲያ አጎቴ ችግሩ ሲጠናበት እኒህ ሐኪም ዘንድ ይሄዳል።

ሐኪሙ በነገራችን ላይ በቴሌቪዥን ስኬት ፕሮግራም ላይ ከጆሮ መብሳት ተነሥተው የጆሮ ሕመምን ማከም እንደ ጀመሩ ተናግረዋል:: ታዲያ እኒህ ሐኪም የአጎቴ ሕመም የጥጥ መስረግ ችግር መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ በርጩማ ላይ እንዲቀመጥ አድርገው፣ መንጋጭላው ላይ በጥፊ ቿ አድርገው ሲመቱት. . .ይገርማችኋል. . . ይህን የሚያህል ልቃቂት(ወደ አጥሚቴ ጣሳ እየጠቆመ) ከጆሮው ፈትለክ ብሎ ዱብ አለ::»

«እውነት?» አሉ ወይዘሮ ይርገዱ ቅንድባቸው በጥርጣሬ ከፍ አድርገው::

«ቁልቢ ይድፋኝ፤» አለና በላቸው በገዛ ወሬው ተመሥጦ አጥሚቴን አንሥቶ ተጎነጨ::

«ሐኪሙ የውጭ አገር ሰው መሆን አለበት፤» አሉ አቶ ተሻገር ለመሳተፍ ያህል::

«በፍጹም» ቀጠለ በላቸው:: «በነገርዎ ላይ፣ የአገራችን ሐኪሞች ከውጭ አገር ሐኪሞች ጋራ ሲነጻጸሩ ጋዎን የለበሰ እግዜር ማለት ናቸው:: ይገርምዎታል፤ የእኛ ቤት ደንበኛ የሆነ አንድ ታካሚ ውጭ አገር ተኝቶ ሲታከም ኩላሊቱን ሰረቁት:: ኩላሊቱ የነበረበት ቦታ ባዶ ከሚሆን ብለው ደባል ሆድ አስገቡለት:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እንደ ወፍጮ እህል ከማመላለስ በቀር ሌላ ሞያም የለው:: ይገርማችኋል፤ የግንበኝነት ሥራ እየሠራ መንታ ሆዱን ማስተዳደር ስላቃተው ከሱፐር ማርኬት ጊዜ ያለፈባቸው እሽግ ምግቦች በነጻ እንዲበረከትለት እስከ መጠየቅ ደርሷል:: ተው ጤናህ ይጓደላል፤ ብንለው፣ «የሰው እንጂ የእህል Expired date የለውም፤» ብሎ እምቢ አለ:: አዬ! መቼም ባዳ ባዳ ነው:: እኒያ ፈረንጅ ሐኪሞች ተጨማሪ ሆድ ሲያስገቡለት ምነው በልኩ



ቢያስገቡለት፤ የሀብታም ዐረብ ሆድ አስገብተውለት አበሳውን ያያል!»

«ሆዱ የዐረብ ሆድ መሆኑ በምን ታወቀ?» አሉ ወ/ሮ ይርገዱ::

«እንጃ!! ብቻ ያለልምዱ ቴምር ሲበላ ሳየው እንዲያ ቢሆን ነው ብዬ ጠርጥሬ ነው፤» አለ በላቸው:: እንዲህ ሲያወራ ከቆየ በኋላ ይዞት የመጣውን ፍራፍሬ ብድግ አድርጎ፣ «በሉ እስረኛ ስለምጠይቅ እንዳይመሽብኝ በጊዜ ልሂድ፤» ብሎ ተነሥቶ ወጣ::

# ምዕራፍ ስራት

አዲሳባ ውስጥ ያልገባሁባቸው ሁለት ሆስፒታሎች ይቀሩኛል:: በመጀመርያው ሆስፒታል ውስጥ ያገኘሁት ዶክተር ቸኮል፣ ግራ ጆሮዬ ቀዶ ሕክምና እንደሚያስፈልገው ገልጾ፣ ለቀዶ ሕክምናው የሚሆን አምስት ሺሕ ብር ይዤ እንድመጣ ነግሮ አሰናበተኝ:: ለአማራጭ ያህል ወደ መጨረሻው ሆስፒታል ለመሄድ ወስኜ ሚኒባስ ብሳፈር ዶክተር ቸኮል በኮንትራት ታክሲ ቀድሞኝ አገኘሁት:: ለካ፣ በሁለቱም ሆስፒታሎች ውስጥ በተመላላሽነት የሚሠራው ራሱ ነው:: ገብቼ ከፊት ለፊቱ ካለው ወንበር በሰያፍ ስቀመጥ፣ «ይህን ጆሮ የሆነ ቦታ አውቀዋለሁ፤. . .ወይ ደንበኛዬ ነህ ወይ ጆሮ ጠቢ ነህ!» በማለት አቀባበል ካደረገልኝ በኋላ መድኃኒት ስለሚያስፈልገኝ ለመድኃኒት መግዣ የሚሆን አምስት ሺሕ ብር ይዤ እንድመጣ ነግሮ አሰናበተኝ:: እንግዲህ ይህ ምን ማለት ነው? እኔ ጤና እንደ ጎደለኝ፣ ዶክተር ቸኮልም በኑሮው ውስጥ አምስት ሺሕ ብር ጎድሎታል ማለት ነው:: እንግዲህ የት ልሂድ? ደቡብ አፍሪካ ለመሄድ አውሮፕላን ብሳፈር ዶክተር ቸኮል በጀት ቀድሞ ስለሚጠብቀኝ አላመልጥም::

በክኒናም ሆነ በቀዶ ሕክምና የምፈልገው ፈውስ ነውና አምስት ሺሕ ብር ለማጠራቀም ወሰንሁ:: ብር ማጠራቀም



የምችለው በሁለት መንገዶች ብቻ ነው:: የመጀመርያው፣ መንገድ ለመንገድ የማወጣውን ወጭ መቀነስ ነው:: በአካባቢዬ የሚገኙ አሽከርካሪዎች እንዲያፈናጥጡኝ (ሊፍት እንዲሰጡኝ) ልምምጥ ጀመርሁ:: ይሁን እንጂ በመንደራችን ከሚኖር አምቡላንስ ነጂ በቀር ማንም ሊተባበረኝ አልፈለገም:: ቀጠልሁና፣ ሚኒባስ ብቻ ሳይሆን ከፋይ እየጠበቅሁ መሳፈር ጀመርሁ:: ታክሲ መቆሚያው ላይ ሆኜ፣ ሚኒባስ አጠገቤ መጥቶ ሲቆም በበሩ አንገቴን አስገብቼ የማውቀው ሰው መሳፈር አለመሳፈሩን አጣራለሁ:: ወያላዎቹ ደግሞ ከፋታቸው፣ ታክሲው የት እንደሚሄድ እንጂ በውስጡ ማን እንደሚሄድ አይናገሩም::

ይህ አላዋጣ ሲል ሌላ ብልሃት ሞከርሁ:: በሚኒባስ ተሳፍሬ ሳልከፍል እወርዳለሁ፤ ወያላው ተከትሎኝ ይወርድና ባንድ እጁ የሚኒባሱን በር ይዞ ሌላኛው እጁን ይዘረጋልኛልና፣ «ፈጠን በል፤» ይለኛል:: እኔ ሳምሶናይቴን በዝግታ እከፍታለሁ:: ከሳምሶናይቴ ውስጥ የሚገኘውን አሮጌ ጋቢ ገለጥ አድርጌ ፌስታል እፈልጋለሁ:: ከፌስታሉ ውስጥ አንድ ትንሽ ቦርሳ፣ ከቦርሳይቱ ውስጥ ድፍን መቶ ብር አውጥቼ እዘረጋለታለሁ:: ወያላው፣ ጊዜውን ስላባከንሁበት በጣም ይናደድና በወላጆቹ ዙሪያ የሚያጠነጥን አምስት ስድብ ሰድቦኝ፣ ፍራንኩን ሳይቀበለኝ ይሄዳል:: ድሮ በብር ከጎምሳ የምሄደውን መንገድ አሁን በአምስት ስድብ እሄደዋለሁ ማለት ነው:: ብቻ አልፎ አልፎ የወያላው ስድብ ጠንከር ሲል ስድቡን ለመርሳት አንድ ሁለት መለኪያ ካቲካላ መጠጣት ስላለብኝ፣ ያው ወጪ ማውጣቴ አልቀረም::

ሁለተኛውን የገንዘብ መሰብሰቢያ መንገድ መሞከር ሊኖርብኝ ነው:: እሱም በደንብ አስተናግጄ ጉርሻ መሰብሰብ:: እስከ አሁን ጉርሻ የሚባል ነገር አግኝቼ አላውቅም:: እኔ ጥሩ አድርጌ

ካስተናገድሁ ጉርሻውን አብራኝ ለምታስተናግደው ለመክሊት ይሰጧታል። በሕይወቴ አንድ ቀን ብቻ በቢል መሰብሰቢያው ላይ ድፍን ዐሥር ብር ተቀምጦ አግኝቻለሁ። አመስግኜ ሳልጨርስ፣ ተስተናጋጁ እየሮጠ ገብቶ፣ «ዐሥር ብር ረስቼ ሳልሄድ አልቀረሁም፤ አግኝተሃል?» ብሎ አፋጠጠኝ።

ይኸው፣ በነበርሁበት በቤትሆቨን ካፌ ውስጥ መሥራቴን ቀጥያለሁ። የካፌው ደንበኞች እና አብልቶ አደሮች(አስተናጋጆች) ጥንት በነበሩበት ቦታ ሆነው አገኘኋቸው። ጥግ ላይ ሄለን እና ምዑዝ ፊት ለፊት ቁጭ ብለው እያወሩ ነው። ሄለን ከኋላዋ ያጠራትን ካናቴራ ዐሥሬ ወደ ታች እየጎተተች፣ በከፊል የተራቆተ ዳሌዋን እና ከጅንስ አምልጦ ብቅ ያለውን ፓንቷን(ከብርድ ወይስ ከዐይን?) ለመጋረድ ጥረት ስታደርግ አያታለሁ። ከፊት ለፊቷ የተቀመጠው ምዑዝ ሄለንን ለማማለል እየተፍጨረጨረ እንደ ሆነ ዐውቃለሁ። አለወትሮው በጥንቃቄ ይንቀሳቀሳል። ብቻውን ሲስተናገድ ዝርክርክ እንደ ሆነ እኔ እና መክሊት እናውቃለን። ከዝርክርክነቱ የተነሳ ያልተከፈተ ኮካ ይንጠባጠብበታል። ብዙ ጊዜ ሳንቡሣ እየገመጠ ስለሚያነብ፣ በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት ዐረፍተ ነገሮች የሚቋጩት በአራት ነጥብ ሳይሆን በምስር ፍሬ ነው። አሁን ግን ደረቱን ነፍቶ፣ ብርጭቆውን በቄንጥ ብድግ አድርጎ፣ ለሌላ ሰው የሚያቀብል ይመስል በክንዱ ልክ አርቆ ከያዘው በኋላ ሳይጠጣበት መልሶ አስቀመጠው። ከዚያ እጁን በሄለን ጅንስ ለበስ ጭን ላይ አስቀምጦ፣ «ሰሞኑን ብቸኝነት ምናባቴ እንደሚያደርገኝ እንጃ!» ሲል ሰማሁት። «ምንም አያደርግህ፤» አለች ሄለን እጁን ከጭኗ ላይ እያስወገደች።

ቀጠለችናም፣ *«ካስት አወይን አይተኸዋል?»* ብላ ጠየቀችው።



«አይቼዋለሁ፤»

«በዚያ ፊልም ውስጥ ቶም ሐንክስ፣ ለብዙ ዓመት ባንድ ደሴት ውስጥ ለብቻው ይኖራል፤» ስትለው ምዑዝ መልሶ፣

«ለነገሩ ቶም ሐንክስ ብቻውን አልነበረም፤ቢያንስ ዳይሬክተሩ እና የካሜራ ባለሞያዎች አብረውት ነበሩ፤» አላት።

«እሬ ባክህ?» አለች ሄለን እየሣቀች፤

«ሙች፤» አለና የተገፋውን እጁን መልሶ ጭኗ ላይ አስቀመጠው።

ቀጥሎ የሚከናወነውን ለማወቅ ጓጉቼ ሳለ፣ አንድ ጠንካራ እጅ ጎተተኝ፤ ዞርሁ፤ ጠጉሩ ላይ ላባ የሰካ ተስተናጋጅ፣ «እኔን ያማትታዘዘኝ የአናሳ ብሔር አባል ስለሆንሁ ነውን?» አለኝ። «እሬ ስላልሰማሁህ ነው፣» አልሁት፤

«ነው?. . .እኔኮ *የፐጋፔ* ብሔር አባል ስለሆንሁ ንቀህ የዘለልኸኝ መስሎኝ በጣም ተናድጄ ነበር። በል፣ የግመል ወተት አምጣልኝ፤» አለኝ። በካፌው ውስጥ የግመል ወተት ስላልነበር የግመል ሥዕል በተሣለበት ብርጭቆ የላም ወተት አመጣሁለት። እርሱም ወተቱን ፉት እያለ የፐጋፔን ብሔር ታሪካዊ አመጣጥ አጫወተኝ።

የፐጋፔ ብሔር በዐጤ ምኒልክ ኀይሎች እስኪወረር ድረስ ለብዙ ሺሕ ዓመታት ያህል የግመል ወተት እንደ ልቡ እየጠጣ በነጻነት መኖሩን አጫወተኝ። እንደ ሰውዬው ምስክርነት ከሆነ፣ የብሔሩ አባላት በተፈጥሮ በጣም ብሩህ አእምሮ እና በጣም ሰፊ

ጀርባ ታድለዋል:: በዐጤ ምኒልክ ዘመን፣ ጠረጴዛ ወደ ኢትዮጵያ ስልላገባ፣ የዐጤ ምኒልክ ጭፍሮች ጠጅ ሲጠጡ ብርሌያቸውን የሚያስተምጡት በፐ.ጋፔ ብሔር አባላት ጀርባ ላይ ነበር:: በኋላ ግን የብሔሩ ወጣቶች ተደራጅተው ይህን ግፍ በመዋጋታቸው የማታ ማታ በገዛ ጀርባቸው የማዘዝ ሙሉ መብትን ተጎናጸፉ:: በአሁኑ ጊዜ የብሔሩ አባላት አምስት ሲሆኑ አምስቱም ፓርላማ እንዲገቡ ተፈቅዶላቸዋል:: ይህ ተስተናጋጅ ወተቱን እና ታሪኩን አከታትሎ እንደ ጨረሰ፣ «የፐ.ጋፔ ብሔር የኢኮኖሚ ምንጭ ምንድን ነው? ግመል ነው ወይስ ቡና ነው?» ብዬ ጠየቅሁት::

«በአብዛኛው የኢኮኖሚ ምንጫችን የፎቶ ግራፍ ጥበብ ነው!» አለኝ::

«የፎቶ ግራፍ ጥበብ ስትል . . .?»

«ቱሪስቶች ፎቶ ግራፍ ያነሡንና ሁለት ብር ይሰጡናል፤ ያንን ማለቴ ነው!»

ይህን ሰምቼ ወደ ሌሎች ተስተናጋጆች ስሄድ፣ ከላይ ግዙፍ ወይባ ፀጉር፣ ከታች ግዙፍ ሳምሶናይት የተሸከመ ጀርመናዊ ሽማግሌ፣«ጉትንታግ» እያለ ከገባ በኋላ፣ የእነ ሄለንን ወንበር ሲቀላቀል ዐየሁ:: መክሊት ከዬት መጣች ሳልላት ከጠረጴዛው አጠገብ ደርሳለች::

«ሻይ አለ?» ብሎ ጠየቃት ጀርመኑ፤

«አለ፤» አለች መክሊት፤

«ቀሽር አለ?»



«አለ፤»

«እንግዲያውስ ቡና አምጭልኝ!»

መክሊት ሣቀችና የታዘዘችውን አመጣችለት:: ጀርመኑ ከላይ ያሉትን ነገሮች የዘረዘራቸው ለሄለን እና ምዑዝ አማርኛ እንደሚችል ለማሳየት ነው:: ትዝ ይለኛል፣ ለመንፈቅ ያህል «እግዜር ይስጥልኝ!» ከሚለው የለማኝ ማባረርያ ሐረግ በስተቀር ሌላ አማርኛ አያውቅም ነበር:: አሁን ግን በተለይ ሴትን እና ልማትን የሚመለከቱ ቃላትን እና ሰዋስው ጠንቅቆ ያውቃል::

መክሊት ከቆይታ በኋላ እንደገና ሳትጠራ ተመለሰችና ንጹሑን ጠረጴዛ ትወለውል ጀመር:: እየወለወለች፣ ትልልቅ ጡቶቿን ለጀርመኑ ታስጎበኘዋለች፤ ጀርመኑም ታዛቢ መኖር አለመኖሩን ግራ እና ቀኝ ሰልሎ ካረጋገጠ በኋላ ጡቷን በከፍተኛ ትጋት መመልከት ይጀምራል:: አስተያየቱ ደሞ ከመጥባት አይተናነስም:: አንዳንዴ ካፌው ጭር ሲል ጀርመኑ መክሊትን ይጠራትና፣ «ማኪያቶ አምጭልኝ!» ብሎ ካዘዛት በኋላ ዞር ስትል፣ «ነጣ ይበል ታዲያ፤» ይልና ከማኪያቶው ንጣት ጋራ የሚያያዝ ይመስል ቂጧን በጥፊ ቸብ ያደርገዋል::

እኔ ከሥራዬ በቀር ሴት ቀና ብዬ አይቼ አላውቅም:: አንድ ቀን ብቻ ማንኪያ ወድቆብኝ ለማንሣት ባጎነበስሁበት እግረ መንገዴን ወደ መክሊት ቂጥ ተመለከትሁ:: ያኔ በጣም ከመደነቁ የተነሣ ማንኪያው ከወለሉ፣ ዐይኔ ከመክሊት ቂጥ ላይ ሳይነሣ ብዙ ጊዜ በማለፉ ሥራ አስኪያጁ መጥቶ አቃናኝ::

እኔ እና በዚህ ማስታወሻ ላይ በዝርዝር የማላካትታቸው ሌሎች ሁለት ተስተናጋጆች ወዲያ ወዲህ ስንዋከብ፣ መክሊት

ግድግዳ ተደግፋ እና ፈገግ ብላ ወደ ጀርመኑ ትመለከታለች::

«ከፈረንጁ ጋራ መውጣት ትፈልጊያለሽ?» አልኳት አንድ ቀን::

«ከዚህ አገር መውጣት እፈልጋለሁ!» አለችኝ በሚያሳዝን ድምፅ::

«ሁላችንም ካገር መውጣት እንፈልጋለን ከምዑዝ በቀር፤» አልኳት::

«አንተ ትፈልጋለህ?»

«ሞክሬ አልተሳካልኝም፤»

«መቼ? ለምን?»

*           *           *

ከጥቂት ዓመታት በፊት ወደ ሥልጠና ጣቢያ ከሚሄድ የዘማች መኪና ላይ ዘልዬ ካመለጥሁ በኋላ፣ አዲስ አበባ መጥቼ፣ ወደ አሜሪካ ለመሄድ አመልክቼ በቀጠሮው ቀን ኤምባሲ ተገኘሁ:: ከጎን እና ከጎኔ ሌሎች ሁለት ደጅ ጠኚዎች(አንዲት አሮጊት እና ሌላ ንዴታም ጎልማሳ) ቁጭ ብለው ወረፋቸውን ይጠብቃሉ::

አሮጊቷ አሁንም አሁንም፣ «አንተ ታውቃለህ ገብሬል፤. . .ካሳካህልኝ ጃንጥላህን አስገባልሃለሁ፤» እያሉ ይለማመናሉ:: አሮጊቷ፣ ገብሬል አሜሪካን በጃንጥላ እንዲለውጣቸው ሲደራደሩት አጠገቤ ያለው ጎልማሳ እየሰማ መተቸት እና ማማረር ጀመረ:: «የኤምባሲውን አጥር ልብ ብለህ ተመልክተኸዋል?» አለ ወደ እኔ ዞሮ፤ «መጀመርያ ግንብ፣ ቀጥሎ ሌላ ግንብ፣ ቀጥሎ የኤሌክትሪክ አደገኛ ሽቦ፣ ቀጥሎ ቦዲጋርድ፣ ግን ምን ዋጋ አለው? ግንቦች ሁሉ ተደራርበው ሞትን አይመልሱትም:: እኛም ሆነ አሜሪካኖች ከሞት ያለን ርቀት አንድ ነው:: ምናልባት ግንቡ የሚያመለክተው የፍርሃታቸውን ብርታት ነው:: የለየላቸው ጡርቄዎች ናቸው ስልህ! ወንድሜ፣ ለመሆኑ ያሜሪካ ወታደር



ሲዋጋ አይተኸው ታውቃለህ? የማይሸከመው የጦር ዕቃ ዐይነት የለም:: እውነቴን ነው የምልህ፣ ምሽጉን ተሸክሞ ቢሄድ አይጠላም፤» ይሥቅ ጀመር:: አሮጊቷ ማነብነባቸውን ቀጠሉ::

«ሠለስቱ ደቂቅን ከሳት ያወጣሃቸው፣ እኔንም ከዚች አገር እንደ ሽንኩርት ነቅለህ አውጣኝ:: ገብሬልዬ ምን ይሳንሃል?»

ንዴታሙ ጎልማሳ አሮጊቷን ገላመጣቸውና ወደ ኤምባሲው ዘበኞች ዞረ:: ዘበኞቹ በጣም ወፍራም መሆናቸውን ለመጀመርያ ጊዜ አስተዋልሁ:: ኢትዮጵያ ውስጥ ወፍራም ዘበኛ ማግኘት ባለቀንድ ፈረስ እንደ ማግኘት ይቆጠራል:: ዘበኞቹ ለጌቶቻቸው በጣም ታማኞች ናቸው:: ሲፈትሹ ደግሞ እንኳን ብረት የያዘ የብረት ንጥረ ነገር ያለበት ምግብ የበላ ሰው አያልፋቸውም:: ቀበቶዬን ሁለት ጊዜ አስወለቁኝ:: መጀመርያ ላይ «አውልቅ!» ሲሉኝ የብልት መጠን ምርመራ ይኖራል ብዬ ጠረጠርሁ:: በሁለተኛው ቀበቶዬን አውልቄ እጄን ወደ ላይ ስዘረጋ፣ ሱሪዬ እንደ አልቦ በቁርጭምጭሚቴ ዙሪያ ተገኘ:: ከጎኔ የተሰለፈው ሰውዬ፣ «ቀበቶህን አውልቅ!» ሲባል፣ «ምነው፣ እንቀን እንዳንገላችሁ ነው?» ብሎ መለሰ:: ምን ዐይነት ነገረኛ ሰው ነው? ጢሙን ቤቱ አስቀምጦ የመጣ ቢንላደን መሆን አለበት ብዬ አሰብሁ::

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቪዛ የምትሰጥ እና የምትነፍግ አሜሪካዊት በመስተዋት ውስጥ ተሸሽጋ አሮጊቷን ደጅ ጠኚ ማናዘዝ ጀመረች::

«በፌስታሉ ውስጥ ምንድን ነው የያዙት?»

«መጽሐፍ ቅዱስ ነው፤» መለሱ አሮጊቷ፤

«ምን ሊያደርጉ ያዙት?»

«አይ!. . .ሄጄ አልቀርም፣ እመለሳለሁ፤ የሚለውን በመሐላ ለመግለጽ ነው፡፡»

«የባንክ ደብተር ይኖርዎታል?»

«የለኝም! የመሠረተ ትምህርት ደብተር ግን አለኝ፡፡»

መስተዋቱ ውስጥ ያለችው ወሰን ጠባቂ አሜሪካዊት ከኮምፒዩተሯ ጋራ ስትመካከር ከቆየች በኋላ፣ «አልተፈቀደልዎትም!» አለችና ፊታቸው ላይ የወረደውን ድንጋጤ ሳለማየት የፈለገች ይመስል ፊቷን በፍጥነት ወደ ኮምፒዩተሯ መለሰች፤ እሮጊቷ ወደቁ፡፡

ይህን ሁሉ ትዕይንት ፊቱን አኮማትሮ ሲመለከት የቆየው ንዴቷም ሰውዬ ቀጥሎ ወደ ወሰን ጠባቂዋ አሜሪካዊት ሄደ፡፡

«አሜሪካ የምትሄደው ምን ለማድረግ ነው?»

«ጓደኞቼ እንዝናና ብለው ጋብዘውኝ ነው፤» አለ ሰውዬው አሜሪካዊቷን ሳለማየት ወደ ጣራው አንጋጦ፡፡

«አግብተሃል?»

«የኔ ማግባት ወይም አለማግባት አሜሪካ ከመግባት ጋራ ምን ያገናኘዋል? ወይስ አሜሪካ ሲገቡ የወንደላጤ እና የባለትዳር በር የተለያየ ነው?»

«የጠየቅሁህን በቀጥታ ብትመልስ!»



«እሺ፤»

«አግብተሃል?»

«አላገባሁም፤»

«በቅርቡ ለማግባት ታስባለህ?»

«ምነው? በትርፍ ጊዜሽ የሠርግ ዘፈን ትዘፍኝለሽ? ወይስ ልታገቢኝ አሰበሽል?»

የሴትየዋ አፍንጫ ቀላ፡፡ ይሁን እንጂ ንዴቷን ተቆጣጥራ ቀጠለች፤

«መኖርያ ቤት አለህ?»

«የለኝም፤ ዛፍ ላይ ነው የምኖረው!»

«ዛፉ የግልህ ነው ወይስ የተከራየኸው?»

«የግሌ አይደለም፤ ካንድ ጉሬዛ ጋራ ተዳብዬው ነው!»

«ከዚህ በፊት ሌላ አገር ሄደህ ነበር?»

«አዎ!»

«የት?»

«ጎጃም»

ሰውዬው እንደ ተባረረ እኔ እያመነታሁ ወደ መስተዋቱ ተጠጋሁ፡፡ አሜሪካዊቷ በንዴት እንዳቀረቀረች ገና ኮቴዬን ስትሰማ፣

«ወደ አሜሪካ ለመግባት አልተፈቀደልዎትም!!» ብላ ጮኸችብኝ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ «ዕጣ ፈንታህ ካንተ ቀጥሎ የተሰለፈው ሰውዬ ነው!!» የሚል ጥቅስ ግድግዳዬ ላይ ሰቀልሁ::



# ምዕራፍ ስምንት

በአስተናጋጅነት አብራኝ የምትሠራው መክሊት ቆንጆ ሳትሆን አትቀርም፤ ምክንያቱም ወጣት ወንድ ተስተናጋጆች ይወዷታል:: እኔ ፈገግታዬን እንደ ደጋን ለጥጬ አጠገባቸው ስቆም በትከሻዬ በኩል አሳልፈው እሷን ይጠሯታል:: እኔን ገና ሲያዩኝ እንደ ምስር ለቃሚ ጠረጴዛቸው ላይ ያቀረቀራሉ:: እሷ ግን ስትሳሳት እንኳ ስሕተቷን እንደ ሽልማት ይቀበሉታል:: ባለፈው አንዱ፣ “Well...ፓስታ አምጭልኝ ነበር ያልሁሽ ግን አንቺ ቡና ነው ያመጣሽልኝ!» አለ ከማያባራ ፈገግታ ጋራ ሽቅብ እየተመለከታት::

«ውይ ይቅርታ፤. . .ልቀይርልህ?» አለችው፤

«ችግር የለም፤ ያው ነው!» አለ ሰውዬው::

ፓስታ እና ቡና ያው የሚሆነው እንዴት ነው?

መክሊት ቆንጆ ሳትሆን አትቅርም፤ ምክንያቱም ሴት ተስተናጋጆች(ከሄለን በቀር) ያዋክቧታል:: መጀመርያ ማኪያቶ እንድታመጣላቸው ያዝዟታል:: ማኪያቶ ስታመጣ፣ ማኪያቶውን ትተው ጡቷን ከጡታቸው ጋራ አለካክተው፣ «ምነው ነጣ ያለ ማኪያቶ ማለት ይህ ነው እንዴ?» ብለው ይጮሁባታል:: እንደገና

አስተካክላ ስትመጣ ደሞ፣ «ውይ፣ ይሄማ ቡና በወተት ነው ልጄ፤ በይ ቀይሪ፤» ብለው ይመልሷታል።

መክሊት ከአስተናጋጅነት ለመውጣት ብዙ ትመኛለች፤ ግን አቃታት፤ «ለምን መሰለህ?» ትለኛለች፤ «ዋናው ምክንያቴ አለመሰልቸቴ ነው። በሥራዬ የማገኘው ገንዘብ ቋሚ መጠን የለውም። ባለፈው ወር ያገኘሁት ብዙ ነው። በዚህ ወር ደግሞ በጣም ብዙ ሊሆን ይችላል። በሚቀጥለው ወር ደግሞ ምንም አይኖር ይሆናል። በየወሩ የማይለዋወጥ ደመወዝ ቢኖረኝ ኖሮ ሥራዬ ይሰለቸኝ ነበር። ለምን አንድ ሚልዮን ብር አይሆንም! አሁን ግን ከጉርሻ የማገኘው ፍራንክ ስለሚዋዥቅ እንደ ቁማር ሱስ አስይዞኛል። ብዙ ጊዜ ሥራ ስለ መለወጥ አስቤያለሁ። ግን ይኸው እስከ አሁን አቢሁ ...

## ስለ ትምህርት

መክሊት ከጀርመናዊው ሽማግሌው ጋራ ከተዋወቀች በኋላ ከኛ ጋራ አብራ ጀርመንኛ መማር ጀመረች። ይሁን እንጂ ጥቂት ሞክራ አቋረጠችው። «ለመግባቢያ የሚሆነኝን ያህል ዐውቄያለሁ። ከዚህ በኋላ አንድ ሺሕ ዓመት ብማር እንኳ ለመፋቀርያ የሚሆን ጀርመንኛ ላውቅ አልችልም፤» ትላለች። በሌላ ጊዜ እንዲሁ የግል ኮሌጅ ውስጥ ገብታ ለሦስት ወራት ከተማረች በኋላ ወጣች፤ «ምን ያደርግልኛል ብዬ ነው ጊዜዬን የማቃጥለው?» አለች፤ እኔ እና ምዑዝ ስንቆጣት፣ «. . .ሥራው እና ገንዘቡ ሁሉ ያለው በወንዶች እጅ ነው። ወንዶቹ ደግሞ ቁመና እንጂ ‹CV› አያዩም። ባለፈው የአውሮፕላን ውስጥ አስተናጋጅ ለመሆን ተወዳድሬ ቁመቴ ትንሽ አጠር ስላለ ጣሉኝ። ኮሌጆች ደሞ ቁመት የሚያስረዝም የትምህርት ዐይነት የላቸውም፤»



ልንከራከራት አልቻልንም።

## ስለ እጮኛዋ

አንድ ቀን ሁሉም ተስተናጋጆች ከሄዱ በኋላ ዩኒፎርማችንን ስንቀይር ስለ ቀድሞው እጮኛዋ የሚከተለውን ተረከችልኝ። «የኔ ፍቅር ሳሚ፣ በ. . .ጣም የታወቀ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ግብ ጠባቂ ነበር። ያኔ በደጎናው ጊዜ ነው ታዲያ. . . አሁንማ እንደምታውቀው ኳስ በስታዲዮም መሆኑ ቀርቶ በስቱዲዮ ሆኗል። ሳሚዬ እንዴት ግብ ጠባቂ እንደ ሆነ ነግሬሃለሁ? ይኸውልህ በልጅነቱ ባደገበት መንደር የልጆች ኳስ መጫወቻ አልነበረም። ልጆች ኳስ መጫወት ሲያምራቸው በየበረንዳቸው ይጫወታሉ። ከኳስ ፍቅራቸው የተነሣ ይድቦልቦል እንጂ በተገኘ ው ነገር - በጥቅል ጎመን ሳይቀር - ይጫወታሉ።

ብዙ ጊዜ የሳሚ ቡድን ግብ የእነ ሳሚ ቤት በር ይሆናል። እናልህ፣ ከተቃራኒ ቡድን የተለጋ ኳስ አንዳንዴ ጓዳ ድረስ ይገባና ድስት ምናምን ይሠብራል። ሳሚዬ ታዲያ የራሱን ቡድን ከሽንፈት ለማዳን ብቻ ሳይሆን የእናቱን ድስት ከሥብራት ለማዳን ጭምር ተግቶ ይጠብቃል። ደስ አይልም? ለመሆኑ ሳሚዬን ያፈቀርሁት ጨዋታ ላይ አይቼው መሆኑን ነግሬሃለሁ?... ለምሳሌ፣ የኢትዮጵያ ቡድን ከኡጋንዳ ቡድን ጋራ ሲጫወት ያዲሳባ ሕዝብ ኡጋንዳዎችን ሊበላቸው ይደርሳል። እኔ ግን ውስጥ ውስጡን ዑጋንዳን ነበር የምደግፈው፤ ምክንያቱም ኡጋንዳዎች እያጠቁ ወደኛ ግብ አካባቢ ካልመጡ እኔ ሳሚዬን የማየት ዕድል አላገኝማ!! ታዲያ ሳሚ ራሱ እኔ ከተመልካቹ መካከል መኖሬን ስለማያወቅ. . .ብቃ ይቁነጠነጣል። አንዳንዴ እንዲያውም ኳሷ ከእንግዳው ቡድን ሜዳ አልወጣ ስትል እና ሳሚ ትኩረት አለማግኘቱ ሲሰማው

መሀል ሜዳ ድረስ በስታይል እየሮጠ ይመጣና <ብርቱ!> ብሎ እየሮጠ ይመለሳል። አይ ሳሚ!. . . በጣም እወደው ነበር።»

እውነቷን ነው፣ በጣም ትወደው ነበር። ደመወዝ በተቀበልን ቁጥር መክሊት ለሳሚ ጫማ ለመግዛት ይዛኝ ትወጣለች። አንድ የጎዳና ማእዝን ላይ ስንደርስ፣ ከተደረደሩት የኮንትሮባንድ ጫማዎች መካከል አንዱን ብድግ አድርጋ፣ «እስኪ ይህን ለካው፤» ትለኛለች። ጎዳና ላይ ጫማ ማውለቅ በጣም ያሸማቅቀኛል፤ ምክንያቱም ከጎዳናው ዳር የሚነሣው የሽንት ሽታ ከእግሬ እንደ ተነሣ አድርጎ የሚገምት አልፎ ሂያጅ አይጠፋም። መክሊት እጮኛዋን እንዴት ብትወደው ነው ከዚህ ዐይነቱ መሸማቀቅ የገላገለችው? በመክሊት ብር እና በእኔ እግር አማካይነት የተገኘው ስኒከር ተጫምቶ ይዘንጣል። በርግጥ አንዳንዴ ሰው ነኝና ይሰማኛል። መመኪያ ታደርገኛለች ብዬ ስጠብቅ መለኪያ ስላደረገችኝ አዝናለሁ።

ከዕለታት አንድ ቀን ከእጮኛዋ ጋራ መጣላቷን ስሰማ ግን ኀዘኔ ወደ ግልገል ተስፋ ተቀየረ። በእጮኛዋ ቦታ የመግባት ዕድል እንዳለኝ ገመትሁ። ከእጮኛዋ ጋራ ቢያንስ በእግር መጠን እንመሳሰላለን። ግን ምን ያደርጋል? እኔ ሳመነታ አንዱ ከጀርመን መጥቶ ቀደመኝ።

መክሊት የምትኖረው በአንድ ክፍል ቤት ውስጥ ከወንድሟ ጋራ ነው። ወንድሟ ከኮምቦልቻ እስከ አዲስ አበባ በሚሠራው የመንገድ ሥራ ላይ ቻይናዎች ቀጥረውት ለጥቂት ጊዜ እንደ ሠራ ጥሎት ወደ አዲስ አበባ በመመለስ ከእኅቱ ጋራ አብሮ መኖር ጀመረ።

እናም በአንድ ክፍል ውስጥ፣ በጥቂት ርምጃዎች ርቀት



በተዘረጉ ሁለት አልጋዎች ላይ ማዶ ለማዶ ሆነው ይተኛሉ። ጠዋት ወደ ካፌ ከመምጣቷ በፊት ቁርሱን ሠርታ ትራሱ አጠገብ አስቀምጣለት ትሄዳለች። ስትመለስ ካልጋው ሳይወርድ ይጠብቃታል። ልብስ ለመቀየር ወይም ለመታጠብ ስትፈልግ፣ «ወደ ቀጣዩ ክፍል ግባ፤» ትለዋለች። በእሷ እና በወንድሟ ቋንቋ ወደ ቀጣዩ ክፍል ግባ ማለት «ወደዚያ ዙር» ማለት ነው። ወደ ሌላ አቅጣጫ ዞሮ እንደ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ይገተራል። ወንድሟን ብዙ ላለማስቆም በችኮላ እና በስጋት ትለባብሳለች። ወንድሟ ከክፍሉ መውጣት ሞቱ ነው። አንዳንዴ ብቻዋን መሆን ስትፈልግ፣ «እስኪ ዞር ዞር ብለህ ና፤» ትለዋለች። በረንዳው ላይ ዞር ዞር ብሎ ይመለሳል።

እጮኛዋ ሳሚ ወንድሟን በጣም ይጠላው ነበር። ለምሳሌ አንድ ቀን፣ እጮኛዋ የወንድ እና የሴት ነገር ለማድረግ ወደ ቤቷ መጣ፤ ወንድምዬው ግን አይገባውም። ፀጉሩን እያፍተለተለ አልጋው ላይ ከመጎለቱም በላይ ከእጮኛዋ ጋራ የፍልስፍና ውይይት ለመጀመር ሁሉ ቃጣው። ቢጠብቁት፣ ቢጠብቁት አልወጣ ስላለ መክሊት ሳሙና ገዝቶ እንዲመጣ ጠየቀችው። ወንድሟ ግን፣ «ይኸው ሳሙና» ብሎ አንድ ደርዘን ከአልጋው ሥር አወጣ። ቢጨንቃት አሞ እንዲገዛ ላከችው። ወንድሟ ተነሥቶ ከመውጣቱ መክሊት እና እጮኛዋ ተያይዘው አልጋ ላይ ወደቁ። ይሁን እንጂ የሚፈልጉትን ያህል አልተደሰቱም። ወንድምዬው ካሁን አሁን ይመጣብናል ብለው ስለ ሰጉ፣ ወሲቡን አጣድፈው ጨረሱት። ወንድምዬው ግን አነወትሮው ዘግይቶ፣ በዝናም በስብሶ ገብቶ ጠፈጠፉን ከፀጉሩ ላይ እያራገፈ፣ ጠሉን ከፊቱ ላይ እየጨመቀ ጥግ ፈልጎ ቁጭ አለ። መክሊት ገና እንዳየችው ፊቷን በመዳፏ ውስጥ ቀበረች። ለወሲብ ስትል ከቤቷ አጣድፋ ስላስወጣችው እና ዝናም ስለ አስመታችው ወንድሟ

እንዳዘነባት ገብቷታል፤ ለወንድሟ ስትል ወሲቡን አሳግባብ ስላጣደፈችው እጮኛዋም ተቀይሟታል - ከሁለት ያጣች በመሆኗ አዘነች።

«ወንድምሽ አሁን ምንም አይሠራም?» አልኳት አንድ ቀን ብርጭቆ ስናጥብ።

«ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ የሚናገር ተውኔት ለመሥራት እያጠና ነው!» አለችኝ። «ተውኔቱን እኔ ራሴ አንብቤዋለሁ። *ትራጀ - ኮሜዲ* ነው። ትራጀ - ኮሚዲ ታውቃለህ?»

«አላውቅም!»

«ባንድ ጊዜ የሚያስለቅስም፣ የሚያሥቅም ትርኢት ማለት ነው።»

ገባኝ። በሕይወቴ መድረክ ላይ የወጣሁት አንድ ጊዜ ብቻ ነው፤ ትዝ ይለኛል። ደብረ ማርቆስ ውስጥ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን ስማር በዕረፍት ሰዓት የትምህርት ቤታችንን አጥር ከሚያዋስነው የበቆሎ እርሻ ውስጥ ገብቼ አንድ ራስ የበቆሎ እሸት ሰረቅሁ። ባለበቆሎው ደካማ ሽማግሌም ቢሆን እግር ከልጆቹ የተበደረ ይመስል አባርሮ ያዘኝና ለርእሰ መምህራችን አስረከበኝ። ርእሰ መምህራችን ባንዲራ ከተሰቀለ በኋላ የሰረቅሁትን በቆሎ ባፌ አንጠልጥዬ መድረክ ላይ እንድቆም አደረጉኝ። ተማሪዎቹ በጣም ሣቁብኝ። እኔ ግን አለቀስሁ። እንግዲህ *ትራጀ - ኮሚዲ* ማለት ይሄ መሆን አለበት። ልክ ነው። ትራጀ ኮሜዲ ማለት ተዋናዩ ሲያለቅስ ተመልካቹ የሚሥቅበት ትርኢት ማለት ነው።



# ምዕራፍ ስድስት

አንድ ቀን ከመክሊት ጋራ ስናወራ፣ «ወንድምሽ እንደ ዐጤ ቴዎድሮስ ሆኖ ለመተወን ጥናት ላይ መሆኑን ነግረሽኛል!» አልኳት።

«አዎ!» አለችና በረጅሙ ተንፍሳ ቀጠለች፤ «ወንድሜ ተውኔቱን በትጋት ሲያጠና ያድራል። አንዳንዴ ሌሊት የተኛ ሁበትን አልጋ ይገፋል። ብንን ብዬ ምን እያደረግህ ነው? ብዬ ስጮህበት በተውኔቱ ውስጥ ሴባስቶፖል የሚባል መድፍ ስለምገፋ ያን ስሜት ለማምጣት ብዬ ነው ብሎ ይመልስልኛል፤ እና ይኸውልህ በምዕራብ ተኝቼ በምሥራቅ እነቃለሁ፤ ሆሆ. . .ታዲያ ምን ዋጋ አለው? እንዲህ ሲያጠና ኖሮ. . .ኤጭ ተወኝ ባክህ!»

«ምን ተፈጠረ?»

«በተውኔቱ ውስጥ እንደ እቴጌ ተዋበች ሆና የምትተውነው ሴትዮ ወደ ቤሩት ተሰደደች፤»

«በጄ፤»

«ከዚያማ በቃ በሄደችው ልጅ ምትክ ሌላ ተዋናይት ተፈልጋ እንድታጠና ይደረጋል። ይቺ ልጅም እንዲሁ ለአራት ወር ያህል ተውኔቱን ስታጠና ቆይታ ድንገት በዲቪ ወደ አሜሪካ ው. . . ልቅ ትላለች። ምን ታደርገዋለህ?»

«ይህን ያህል የሴት ተዋናይ ችግር ካለ፣ ደራሲው ለምን ሌላ አማራጭ አይፈልግም?» አልኳት፤

«ምን ዐይነት አማራጭ?»

«ለምን ዐጤ ቴዎድሮስ በወንደ ላጤነታቸው ጊዜ የፈጸሙትን ታሪክ አይጽፈውም፤»

«እንደሱ ይሻላል ብለህ ነው?»

«ይሻላል፤. . .ለእሱም ቢሆን ዐጤ ቴዎድሮስ የሚለውን ‹ላጤ ቴዎድሮስ› ብሎ ማሽጋሸግ ይቻላል።»

መክሊት ባመነጨሁት የመፍትሔ ሐሳብ ላይ አስተያየት ሳትሰጥ ቀጠለች። «ይኸውልህ እንግዲህ፣ ወንድሜ በዚህ መልኩ በእኔ ላይ ተጣብቆ ይኖራል። መቼም ዕድሉ በጣም ያሳዝነኛል። አልፎ አልፎ ያመዋል።. . . አንዳንዴ ምን እንደማስብ ታውቃለህ? ለምን ወንድሜ ሆነ እላለሁ፤ ለምን ከጎረቤታችን አብራክ አልተገኘ ም እላለሁ፤ አንዳንዴ ደሞ ምናለ ያለወላጅ ተገኝቼ ቢሆን እላለሁ። ሰው እንደ ዛፍ ለብቻው ከመሬት ብቅ ማለት ቢችል እንዴት



ጥሩ ነበር።»

ከጥቂት ጊዜ በኋላ መክሊት የዓመት ፈቃዷን ወሰደች፤ መክሊት ከካፌው ከቀረች በኋላ ጀርመኑም መምጣት አቆመ። አንድ ቀን ከሥራ በኋላ ተቀጣጥረን ከጀርመኑ ጋራ ለመሰንበት እንደ ወሰነች ነገረችኝ፣ እናም ከዚህ በኋላ ባንድ ጊዜ ሁለት ቤቶችን ማስተዳደር ስለማትችል ወንድሟን ለማሰናበት እንደ ቆረጠች ነገረችኝ። ወንድሟን አፍ አውጥታ ውጣ ለማለት ስለማትደፍር የማሰናበቱን የቤት ሥራ እኔ እንድወስድ ተማፀነችኝ። የተሰጠኝ የቤት ሥራ ለእኔ የሚከብድ አልነበረም። እርሷን የሚያስደስታት ከሆነ፣ ወንድሟን፣ እንኳን ከቤቷ ከምድሪቷ ማሰናበት አይከብደኝም።

በማግሥቱ አነጋግ ላይ፣ እነ መክሊት ቤት ገብቼ በወንድሟ አልጋ አጠገብ ቁጭ ብያለሁ። ወንድምዬው አጭር ነው ወይስ ረጅም? ብሎ የሚጠይቅ አንባቢ አይጠፋም። ጥሩ ጥያቄ ነው። አልጋው ላይ ቁጭ ብሎ ስለነበረ የቁመቱን ሁኔታ ማወቅ አልቻልሁም። ይሁን እንጂ ከግርጌው የተሰቀለውን ግዙፍ ሱሪ በማዬት ረጅም መሆኑን መገመት ይቻላል። መክሊት እንደ ነገረችኝ ወንድሟ በጣም ብስጩ ነው። ለዚህ ሳይሆን አይቀርም እንኳን ፀጉሩ ባርኔጣው መሸበት ጀምሯል።

ተዋውቀን ትንሽ ከቆየን በኋላ፣ «ምነው በጠዋቱ?» ሲል ጠየቀኝ፤

«ሥራ ከመግባቴ በፊት የምነግርህ ብርቱ ጉዳይ አለኝ፤» አልሁት።

«መርዶ እንዳይሆን ብቻ፣ ዛሬለማልቀስ አልተዘጋጀሁም፤»

እንዴት መጀመር እንዳለብኝ ስላላወቅሁ ዝም ብዬ ግድግዳውን ማዬት ጀመርሁ። ግድግዳው ላይ ግዙፍ ፍሬም ያለው ፎቶ ተሰቅሏል። በፎቶ ግራፉ ውስጥ መክሊት ለስዊዘርላንዱ አምባሳደር ቦምቦሊኖ እና ሻይ ስታቀርብ ትታያለች። ከሩቅ እኔ የሻይ ማለቢያ ማሽኑን ስወለውል እታያለሁ።

«ዐየህ፣ ባሁኑ ጊዜ መክሊት. . .!» ብዬ ጀምሬ ቆምሁ። ወንድምዬው ለማስታረቅ የመጣሁ ሳይመስለው አልቀረም። ከመታረቁ በፊት ትንሽ ለመግደርደር ያህል፣ «የመክሊትን ነገር ተወው፤» ካለ በኋላ እንድቀጥል ዐይን ዐይኔን ያየኝ ጀመር።

«መክሊት እና አንተ በዚህ ቤት ውስጥ በመረዳዳት አብራችሁ ቆይታችኋል፤ መክሊት ሥራ ትሠራለች፤ ምግብ ታበስላለች፤ ልብስ ታጥባለች፤ ገበያ ትሄዳለች፤ ከገበያ ትመለሳለች። አንተም በበኩልህ ያከናወንሃቸው ተግባሮች ብዙ በመሆናቸው ልዘርዝራቸው ብል ጊዜ አይበቃኝም፤»

«የእኔ ሲሆን ጊዜ አይበቃህም!» አለኝ ቱግ ብሎ።

ይቺን ይወዳል! እኔ እንዳላስደነግጠው ብዬ ዳር ዳር ስል ጭራሽ ሊወዘገብ ይፈልጋል? ቻለው እንግዲህ! ድምፄን አጠብድዬ ገባሁበት፣ «. . .ለማንኛውም መክሊት ከአዲሱ እጮኛዋ ከአቶ ያን ጋራ አብራ መኖር ጀምራለች። ስለዚህ አንተ ከዚህ ቤት. . .»

«ልውጣ?»

«ነጻ ውጣ፤»

ወንድምዬው ለአጭር ጊዜ ፊቱን በእጆቹ ቀብሮ ሲተክዝ ከቆየ በኋላ የሚከተለውን ተናገረ። «ገጠር ሄጄ ለመሥራት



ሞከርሁ፣ ግን በቃ ልወደው አልቻልሁም። ገጠር ውስጥ ምን ታገኛለህ?. . .ተራራ - ድንጋይ እንደ ኪንታሮት የወረሰው ደረቅ ሜዳ - የተረሳ ጃንጥላ የመሰለ ብቸኛ የግራር ዛፍ - ከዚያ አለፍ ስትል ድልድይ - ዝቅ ብለህ ስታይ በድልድዩ ውስጥ የሚያልፍ ውኃ የለም፤. . . ታዲያ ድልድዩ ምን ሊሠራ እዚያ ተገኘ? እንጃ። ምናልባት የወንዝ መካነ መቃብር ይሆን? . . .ለመሆኑ ወደ ገጠር ሄደህ ታውቃለህ?»

«እኔ ራሴ የገጠር ልጅ ነኝ፤» አልሁ በኩራት።

«ገጠር መወለድ እና ገጠርን ማወቅ የተለያዩ ነገሮች ናቸው፤» ቀጠለ ወንድምዬው፤ «ገጠር ስገባ፣ ወደ ድሮ የተወረወርሁ ነው የመሰለኝ። ታሪክ ጸሐፊዎች በድሮ እና በዘንድሮ መካከል ያለውን ልዩነት በጊዜ መጠን ሲለኩት ይገርመኛል። እንደኔ እንደኔ ካዲስ አበባ መቶ ኪሎ ሜትር ስትርቅ ድሮን ቁጭ ብሎ ታገኘዋለህ። በድሮ እና በዘንድሮ መካከል ያለው ርቀት መቶ ኪሎ ሜትር ነው።. . .ለጥቂት ጊዜ ከቻይናዎች ጋራ አብሬ ለመሥራት ሞከርሁ፤ ቻይናዎች ባሕር ተሻግረው መጥተው አገሬን ሲያለሙ ስመለከት እልህ ያዘኝ። ቁታዬን ለብሼ ድንጋይ መፍለጥ፣ ጠጠር ማጠብ፣ ባሬላ መሸከም ጀመርሁ፤ ደስ አለኝ። ቁርጠኝነት ወደ ልቤ ዘለቀ።

ሆኖም አንዳንድ ቀን ድንጋይ ከምፈልጥበት ቀና ብዬ ከፊት ለፊቴ ያለውን ግብዳ ተራራ ስመለከት አሞቴ ፍስስ ይላል። ይህን ለመለወጥ ብዙ ሺሕ ዓመት ያስፈልጋል እላለሁ። እንኳንስ ቻይናዎች፣ በረፍት ጊዜያቸው ላሊበላን የፈለፈሉ መላእክት እንኳ ቢወርዱ አይችሉትም እላለሁ። ግን እንዲያም ሆኖ ጥርሴን ነክሼ፣ እንዲት ጎጆ ተከራይቼ መሥራቴን ቀጠልሁ። ይገርምሃል፣ የምኖርበት ጎጆ ባይጥ ስለ ተሞላ ላብራቶሪ እንጂ ቤት

አይመስልም::

በዚህ መሀል ሌላ ሐሳብ ይደቀንብኛል:: አዲሳባ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች የክፍለ ሀገር ነዋሪዎች እንዳይሻሟቸው ራሳቸውን በተራራ ከልለው ሲበሉ፣ ሲጠጡ፣ ሲባልጉ እንዲሁም ሲዝናኑ ሲታዩኝ እበሽቃለሁ:: እኔም ጊዜው ሳይመሽ ከበረከቱ ለመቃመስ እመኛለሁ:: እናም ወደ አዲስ አበባ መጣሁ:: ከእኅቴ ጋራ መኖሬ የተስማማኝ ይመስልሃል?. . .አትሳሳት፤ አስታጣቢ ይመስል የሰው እጅ እያዩ መኖር ቀላል እንዳይመስልህ:: በቴአትር ሞያ እንጀራ ለማግኘት የዐጤ ቴዎድሮስን ታሪክ ለአራት ዓመት ያህል ሸምድጃለሁ:: ዐጤ ቴዎድሮስ መሳፍንትን ለማጥፋት እንኳን ይህን ያህል ጊዜ አልፈጀባቸውም:: ከመክሊት ጋራ ስኖር ተሸማቅቄ ነው:: አንድ ቀን ቤት ሆኜ ቦይፍሬንዷ መጣ:: ሰው ርቦኝ ስለነበር ገና ሳዬው ተጠመጠምሁበት:: እርሱ ግን ገፈተረኝ:: ከዚያ በፍልስፍና ሐሳቦች ላይ መወያየት ፈልጌ፣ ስለ ነጻ ፈቃድ ያለህ አስተያየት ምንድን ነው? አልሁት:: እርሱ ግን ምን ብሎ እንደ መለሰልኝ ታውቃለህ? «ነጻ ፈቃዱን ትተህ ለምን መንጃ ፈቃድ አታወጣም?» አለኝ:: መክሊት እንዳሁኑ እንዳንተ ሣቀች:: ትንሽ ቆይተው እንደ ሕፃን ልጅ አሞ እንድገዛ ላኩኝ:: ወጣሁና ዝም ብዬ መራመድ ጀመርሁ፤ ወዲያው ዝናም መጣ:: ለመጠለል አልፈለግሁም:: ኀፍረቴን እንዲያጥብልኝ በዝናሙ እየበሰበስሁ መንገዴን ቀጠልሁ:: ምነው ፈጣሪ በዚያ ሰዓት የጨው ሐውልት ቢያደርገኝ - ታጥቤ እንዳልቅ፤. . .እኅቴን እና ቦይፍሬንዷን ስለ ጠላኋቸው ቢያንስ ለሳምንት ወደ ቤቴ ላለመመለስ ቃል ገባሁ፤ ትንሽ ቆይቼ ግን ሳምንቱን ወደ ሦስት ቀን አሸጋሸግሁት:: እየመሸ ሲሄድ ብርዱ እና ረኀቡ ከኩራቴ በላይ ሆነ:: ይቅር ለእግዜር ብዬ ወደ ቤት ተመለስሁ::



በርግጥ መክሊት ባለውለታዬ ናት:: ካባቴ የወረስሁት ነገር ቢኖር የስኳር ሕመም ብቻ ነው:: የዚህ ዓለም ነገር አይገርምም? አንዱ ካባቱ የስኳር ፋብሪካ ሲወርስ ሌላው የስኳር ሕመም ይወርሳል:: አዲሳባ ውስጥ ያለመክሊት ርዳታ የማደርገው ነገር ቢኖር ራሴን ማጥፋት ብቻ ነው:: አሁን ትላንት ማታ ራበኝ፣ ብቸኝነትም ተሰማኝ:: ሁሉ ነገር ባዶ ሲሆንብኝ ኮረንቲ ጨብጬ ለመገላገል ወሰንሁ. . .ግን ባጋጣሚ መብራት ተረኛ ስለነበርን. . . ያሰብሁትን ለማሳካት አልቻልሁም::

ከዚህ በኋላ የምቆይበት ምክንያት አይኖረኝም:: ልሂድ፤ ለነገሩ ዕድሜዬም እየሄደ ነው:: ወደ ገጠር ልሂድና ድንጋይ እየፈለጥሁ፣ ባሬላ እየተሸከምሁ ቻይኖችን ላግዝ:: ከመምጣትህ በፊት ያጤ ቴዎድሮስን ታሪክ ሳነብ፣ ንጉሡ ከግንበኞች ጋራ ሆነው መንገድ ይሠሩ እንደ ነበር አነበብሁ:: እሳቸው እንዲያ ከሠሩ እኔ ለምን አልሠራም? እሄዳለሁ ግ . . .ጥም አድርጌ እሄዳለሁ::»

ወንድምዬው በንግግሩ መሀል ረጃጅም እጆቹን አሁንም አሁንም እንደ ተደባዳቢ ስለሚያወናጭፋቸው ፊቴን በክንዴ እየመከትሁ ማዳመጥ ነበረብኝ:: ከራስጌው በነበረው ጠረጴዛ ላይ የተደረደሩት መጽሐፎች፣ የሲጃራ ማኅደሮች፣ ክብሪቶች እና የዓመድ ቋቶች ተራ በተራ እየወደቁ ወለሉን ሞሉት:: የሆነ ሰዓት ላይ እንዲያውም ጠረጴዛው ራሱ ወደቀ:: ወንድምዬው ንግግሩን እንደ ጨረሰ ያደረገውን ተመልክቶ፣ «ይቅርታ አድርግልኝ፤ ልማዴ ነው፤. . .የፊጥኝ ካልታሰርሁ በቀር ባፌ ብቻ ሐሳቤን መግለጽ አልችልም፤» አለኝ::

ከጥቂት ዝምታ ቆኋላ ሲጃሯውን ለኩሶ አንድ ጉንጭ ከወረወረ በኋላ፣ «በውሳኔዬ ላይ ምን ትላለህ?» ሲል ጠየቀኝ::

ምን ልበለው? የሚከተለውን ልበለው? «ውሳኔህ ጥሩ ነው:: ከመንገድ ሥራ ይልቅ የቴአትር ሥራን የመረጥኸው ስመ ጥርነትን ፈልገህ ነው:: ሲመስለኝ፣ ‹ስም ከመቃብር በላይ ይውላል› የሚለው ተረት እና ምሳሌ አታሎሃል:: ድሮ እንደዚያ ሊሆን ይችላል:: ዛሬ ግን ሟች ስለ በዛ ከመቃብር በላይ የሚለው ስም ሳይሆን የሌላ ሰው መቃብር ነው:: የስም ጉዳይ የሚያሳስብህ ከሆነ በሚሠራው አስፋልት ላይ ሬንጁ ሳይደርቅ ስምህን ቅረጽበት:: እንደኔ እንደኔ ስም ብዙ ዋጋ የለውም:: አንድ ሰው ወደ እኛ ካፍቴሪያ ገብቶ ወተት ከጠጣ በኋላ የጠጣበትን ሒሳብ እንጂ ስሙን አንጠይቀውም::

በአሁኑ ሰዓት ለአገራችን የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ሥራዎች ሦስት ናቸው - ገበሬነት፣ አስተናጋጅነት እና ሐኪምነት፤ ገበሬው ምግብ ያመርታል:: አስተናጋጁ ምግብ ያቀርባል:: ምግቡ ታይፎይድ ሲያመጣ ሐኪሙ ያክማል:: አለቀ:: ተዋናይ ለምን ይጠቅማል? ገበሬ መሆን እንጂ መምሰል ላገራችን ምን ይጠቅማል? ብሔራዊ ቴአትር ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ብዙ ሰዎች እንደ በሬም፣ እንደ ገበሬም እየሆኑ ተጫውተዋል:: «ከብሔራዊ ቴአትር አንድ ኩንታል ጤፍ ተጭኖ ሲወጣ ዐየሁ፤» የሚል ሰው ግን የለም:: ተዋናዮች መድረክ ላይ ሙዝ መብላት የሚያስፈልጋቸው ከሆነ እውነተኛ ሙዝ ነው የሚበሉት:: የሙዝ ዛፍ ሲተክሉ ግን የይምሰል ነው:: ለዚች አገር የውሸት እየሠሩ የምር መብላት አይቻልም:: ሁላችንም መሥራት አለብን:: አጎቴን ውሰድ:: የከባድ ተሳቢ መኪና ሾፌር ነው:: የሚነዳው መኪና በጣም ረጅም በመሆኑ ተሳቢው የሸዋን መሬት ሳይለቅ ዋናው መኪና ጎጃም ይገባል:: እና አጎቴ ቴዎድሮስን ሆኖ መተወን አቅቶት ነው? እንትህ መክሊት የሰው ፊት እያጠናፈራት አስተናጋጅነት የምትሠራው ቴዎድሮስን ሆና ለመተወን አቅቷት



ይመስልሃል? እንዲያውም ለሹሩባ የሚሆን በቂ ፀጉር ስላላት ዐጤ ቴዎድሮስን ሆና ለመተወን ካንተ ትሻላለች::»

ይሁንና ይህን በማለት ፈንታ መክሊት እንድሰጠው አደራ ያለችኝን አምስት መቶ ብር ከኪሴ አውጥቼ ሰጠሁት::

«አልቀበልም፤»አለ፣ «እግዜር ይስጥልኝ፤. . .እስከ አሁን ላደረገችልኝ ሁሉ እግዜር ይክፈላት:: ከዚህ በኋላ ግን አምስት ሳንቲም ከእሷ አልቀበልም፤» ብለው ብሠራው እምቢ አለ::

*   *   *

እሑድ ጠዋት ልሸኘው፣ በዚያውም የምር መሄዱን ለማረጋገጥ አውቶብስ ተራ ድረስ አጀብሁት:: ወረፋ ይዤ ተጋፍቼ አውቶብስ ውስጥ ከገባን በኋላ፣ እንግዲህ አይዞህ፤ በርትተህ ሥራ፤ አልሁና እጄን ሰድጄ ማጅራቱን አሻሸሁለት:: ያለቅስ ጀመር::

«ዐየህ፣ ገጠሩን ከአዲሳባ የሚያገናኘው አስፋልት መሠራት አለበት:: በደንብ ካሰብኸው ለኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን ለተውኔትም ይጠቅማል:: ገጠር የሚገኙ የቴአትር አፍቃሪዎች ወደ አዲሳባ መምጣት የሚችሉት አስፋልት መንገድ ሲሠራ ነው::»

ወንድምዬው ግን ማጽናኛዬ አልበጀውም:: በአውቶብሱ መስተዋት አሻግሮ እየተመለከተ አጥብቆ ያለቅስ ጀመር፤ አሳዘነኝ፤

«መርዶ ሰምቶ ነው?» አሉኝ ከኋላ የተቀመጡ አሮጊት ተሳፋሪ:: ትንሽ ካለቀሰ በኋላ በረጅሙ ተንፍሶ፣ «አዎ፤ ጠንክሬ እሠራለሁ፤» አለ።

«እንዲያ ነው ወንድ ማለት» አልሁት፤

«አዎ፣ አራት መቶ ኪሎ ሜትር አስፋልት በደሜ እና በላቤ ይሠራል፤»

«እሰይ!» አልሁና ክንዱን ጨበጥ አድርጌ ያዝሁት።

«አዎ፣ በላቤ እና በደሜ የመሠረትኩሽ ኢትዮጵያ እናቴ ቀለሜ . . .»

«ምን አልህ?»

«አይ ተወው፤. . . ቃለ ተውኔቱ ጣልቃ ገብቶብኝ ነው፤» አለኝ በሚያሳዝን ድምፅ። ወዲያው ዳግመኛ ለማልቀስ ማሟሟቅ ጀመረ። ቀስ ብዬ ለመውረድ ወደ አውቶብሱ በር ስጠጋ፣ «የባለፈውን ፍራንክ ይዘኸዋል?» አለኝ እየተናፈጠ።

«አዎ፣. . . ልስጥህ?»

ራሱን ባዎንታ ነቀነቀ፤

ሰጠሁትና ወረድሁ።



# ምዕራፍ ሰባት

ትዝ ይለኛል። ምዑዝ ወደ መማሪያ ክፍላችን ሲመጣ ጀርመንኛ ቋንቋ መማር ከጀመርን አንድ ሳምንት አልፎን ነበር። በመጀመርያው ቀን ለሃያ ደቂቃ አርፍዶ፣ በሩን በርግዶ፣ ሹርባ የለበሰ ጭንቅላቱን ብቅ ሲያደርግ ያዩት መምህራችን፣ *«ቪ ሃይሰን ዚ?»* (*ስምህ ማን ነው?*) ብለው ጠየቁት     ። ምዑዝ ባንድ እጁ የበሩን እጄታ እንደ ጨበጠ በሌላው እጁ *«ጀርመንኛ በሠላሳ ቀን»* የሚል መጽሐፍ ከኪሱ አውጥቶ ለጥያቄው መልስ ለመፈለግ ስለ ሞከረ ሣቅንበት። ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ግን ምዑዝ በተራው በእኛ ላይ መሣቅ ጀመረ። ጀርመናዊው መምህራችን ከባድ ጥያቄ ሲያወርዱብን አገራችንን ያዋረድን ያህል አፈርን፤ ከእፍረታችን እንዲያስጥለን ዞረን ምዑዝን በዐይናችን እንፈልገዋለን። ጥቂት ሳምንታት ሲጨመሩ ይግረማችሁ ብሎ ከጀርመናዊው መምህራችን ጋራ በሰዋስው ጥራት ዙሪያ ይሟገት ጀመር። እንግዳ የሆነ የሰዋስው አገባብ ሲያመጣባቸው መምህሩ፣ «ከዬት አመጣኸው?» ብለው ሲጠይቁት፣ «ይህን ሐረግ እገሌ ከሚባለው ጀርመናዊ ባለቅኔ አገኘሁት፤ ይህን ደግሞ እገሌ ከሚባል ኦስትርያዊ ደራሲ ተደበርሁት፤» ብሎ ይከራከራል።

ትንሽ ቆይተን ምዑዝ ከእንግሊዝኛ ባሻገር ፈረንሳይኛ እና ጣልያንኛ እንደሚያውቅ ስንሰማ፣ ይህ ሰው ማን ነው? የሚል ጥያቄ ተጠናወተን። አንዲቱ ተማሪ፣ «የቤተ መንግሥት አስተርጓሚ ነው፤» አለች ሌላው ደሞ፣ «ሞሳድ ያሠለጠነው ፈላሻ ነው፤» ብሎ ተሟገተ።

ብዙም ሳይቆይ፣ የክፍላችን ሴት ተማሪዎች ምዑዝን የጥናት ጓደኛ ለማድረግ ይራኮቱ ጀመር። ወደው አይደለም። ከጥቂት ወራት በኋላ የሚሰጠውን ፈተና በጥሩ ውጤት ካላለፉ የጀርመን ኤምባሲ የይለፍ ደብዳቤ(ቪዛ) አይሰጣቸውም። ስለዚህ ምዑዝን በጀርመን አገር በር ላይ ቁልፍ ይዞ የቆመ መልአክ አድርገው ሳይቆጥሩት አልቀረም። ዘወትር ቤትሆቨን ካፌ ገብቶ፣ ሳምቡሣ በልቶ፣ ሻይ ጠጥቶ «ቢል» ብሎ ሲጮህ፣ «ተከፍሏል» ብዬ እንደምመልስለት ያውቃል። ይሄኔ፣ «እንዲጋብዙኝ ማን ፈቀደላቸው?» የሚል ይመስል፣ አጥንታም ፊቱን ቅጭም አድርጎ፣ የጋባዡን ስም እንኳን ሳይጠይቅ ብድግ ብሎ እየነጠረ ይወጣል፤ ወይም ሌላ ተጨማሪ ነገር ያዝዛል።

ከመከሊት ፍቅረኛ ከአቶ ያን ጋራ ምሳ ሲበላ ግን የራሱን ብቻ ሳይሆን የጀርመኑንም ሒሳብ ይከፍላል። ጀርመኑ መጀመርያ ላይ ካላጋጨን ብሎ ይግደረደር ነበር። በኋላ ግን፣ ከኪሱ የብር ቁንጣን የያዘው ቦርሳ ለይስሙላ ያህል ያወጣና ምዑዝ እስኪከፍል ድረስ ዐይን ዐይኑን እያዬ ይጠብቃል።

ምዑዝ፣ ጀርመናዊውን ሽማግሌ ሁልጊዜ የሚጋብዘው ለምንድን ነው? ያገራችንን ገጽታ ለመለወጥ ነው? ምክንያቱን አንድ ቀን እንደሚነግረኝ ተስፋ አደረግሁ። ገና ከመጀመርያው፣ ምዑዝን ጓደኛ የማድረግ ፍላጎት አደረብኝ። ምን ያግደኛል? ጠዋት ባስተናጋጅነቴ ዝቅ ብዬ ባስተናግደውም፣ ከሰዓት



በተማሪነቴ ከጎኑ እቀመጣለሁ። ያም ሆኖ የከበበውን የሴት ቀለበት ሠብሬ ለመግባት ጊዜ ፈጀብኝ። አንድ ረፋድ ላይ፣ ካፌ ውስጥ ሻይ እየጠጣ መጽሐፍ ሲያነብ ሳምቡሣውን አጠገቡ ካስቀመጥሁለት በኋላ ለመግባቢያ ያህል አፌ ላይ የመጣልኝን ተናገርሁ። ምን አልሁ? «አገር ቤት እያለሁ ዳገት ላይ ቁጭ ብዬ ልቦለድ ማንበብ እወድ ነበር፤» አልሁ። ምዑዝ ቀና ብሎ በሚያባባ አስተያየት ከተመለከተኝ በኋላ፣ «ልቦለዱን እኔ ላውስህ እችላለሁ፤ ዳገቱን ደግሞ ሌላ ሰው ይተባበርህ፤» ብሎ አሳገጠብኝ። ትንሽ ቆይቶ ግን ጸጸት ተሰማው መሰል፣ የአንድ ብር ጉርሻ አስቀምጦልኝ ወጣ።

የአናዛዥነት ተሰጥኦ ነበረኝ፣ የቀረብኋቸው ሰዎች ከተላመድኋቸው በኋላ ከምድር ተነሥተው ምስጢራቸውን ይዘከዝኩልኛል። ከምዑዝ ጋራ ጓደኛ ከሆን ከጥቂት ጊዜ በኋላም የሆነው እንዲህ ነበር።

አንድ ቀን ምዑዝ የካፌው ሽንት ቤት ውስጥ ገብቶ ወዲያው ተመልሶ ከመጣ በኋላ፣ «ሽንት ቤቱ ውስጥ ሶፍት የማታስቀምጡት ለምንድን ነው?» አለኝ።

ጀርመኖች ናፕኪናቸውን፣ አበሾች ጋዜጣቸውን ይዘው ስለሚገቡ ሽንት ቤቱ ውስጥ ተጨማሪ ሶፍት ማስቀመጥ እንደማይጠበቅብን ነገርሁት።

ትንሽ ከተንጎራደደ በኋላ ወደ ጆሮዬ ቀርቦ፣ «የማትፈልገው ወረቀት ይዘሃል?» ሲል ጠየቀኝ። ኪሴ ውስጥ ገብቼ ብዙ የተጣጠፉ ወረቀቶች አወጣሁና ጠረጴዛ ላይ ከመርሁለት። «ይህ ወረቀት የእግረኛ ማኅበር አባል ሆኜ ስመዘገብ የተሰጠኝ ጊዜያዊ መታወቂያ ነው፤» አልሁት።

«የእግረኞች ማኅበር የሚባል ደሞ አለ?» አለኝ ኮስተር ብሎ። እኔም ትንሽ ለማብራራት ተገደድሁ። ነገሩ እንዲህ ነው።

- ባዲስ አበባ የሚኖሩ እግረኞች አስፋልት ለማቋረጥ ሲፈልጉ፣ ባለመኪኖች መኪኖቻቸውን አስቁመው አያሳልፏቸውም። ብልሽት ገጥሞት ካልሆነ በቀር ዜብራ ላይ ሲደርስ መኪናውን የሚያቆም አሽከርካሪ አይገኝም። ይህን እና መሰል ችግሮችን ለመቅረፍ ያዲሳባ እና የአካባቢዋ እግረኞች ተደራጅተው ለመታገል ተስማሙ። ማኅበሩ ከሚታገልላቸው ዓላማዎች መሀል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ነበሩ፤

- የዜብራ መሥመሮች በቂ ስላልሆኑ ከዜብራ መሥመሮች አጠገብ መኪና አስከልካይ ዘበኞችን ማቆም፤

- ባለመኪኖች ለወንዶችም ሊፍት እንዲሰጡ ማግባባት፤

- የእግረኛ መንገዶች በሚጨናነቁበት ጊዜ ወደ መሥሪያ ቤት የሚሄዱ እግረኞች ለሽርሽር ከሚራመዱ እግረኞች ቅድሚያ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

- የአገራችን እግረኞች በበለጸጉ አገሮች ከሚኖሩ እግረኞች ልምድ የሚያገኙበትን መድረክ መፍጠር፤. . .ወዘተ።

ይህን ዓላማችንን ከግብ ሳናደርስ የማኅበራችን ሊቀ መንበር ቮልስ ገዝተው ማኅበራችንን ከድተው የባለመኪኖችን ግንባር ተቀላቀሉ።

ምኑዝ ይህን ማብራሪያዬን ከመ ጤፍ ሳይቆጥር ወረቀቴን አፍተልትሎ ወደ ኪሱ ከጨመረ በኋላ ወደ መጸዳጃ ቤት ተመለሰ።



ከዚያም አንድ ድርቀት የያዘው ሰው ከሚፈጅበት ሰዓት በላይ ቆይቶ ከሽንት ቤት ከተመለሰ በኋላ፣

«ምን ዋጋ አለው?» ብሎ ተከዘ።

«ምነው?» አልሁት።

«ጀርመኖች ሽንት ቤታችን ውስጥ ሲገቡ እንዴት ይንቁን!. . .የላሊበላ ሕንፃችንን ክብር የተጨማለቀ ሽንት ቤታችን ይጋርደዋል። እኔ ከቅድም እስካሁን፣ አምስት ባሊ ውኃ እያመላለስሁ ሦስት የመጸዳጃ ቤት መቀመጫዎችን አጸዳሁ። ጀግና አይደለሁም? አምስት ባሊ ውኃ ማፍሰስ ዐድዋ ላይ ደም ከማፍሰስ የማይተናነስ ብሔራዊ ተግባር ነው። አይመስልህም?»

ከጥቂት ዝምታ በኋላ ቀጠለ፤ «ከነገሩ ሁሉ የምጠላው ስለ አገሬ ማሰብ ነው። አገሬን ሳስብ ደስታዬን አበላሻለሁ። በተለይ የውጭ አገር ሰው ካየሁ ሳልፈልግ አገሬን ካገሩ ጋራ ማነጻጸር እጀምራለሁ። ስለዚህ በተቻለኝ መጠን ዙሪያዬን በፋሲል ፖሊሲ አጥሬ ማንም ፈረንጅ ወደ ሕይወቴ ሰርጎ እንዳይገባ ለማገድ እጥራለሁ።»

«ፈረንጅ ማዬት ካልወደድህ ለምን ወደዚህ ቤት ትመጣለህ?» አልሁት።

«ሴቶችን ፈልጌ!» ሲል መለሰልኝ «ዐየህ፣ ካገር ፍቅር የሚገኘው ደስታ በየዘመኑ ይለያያል። ምንጅላቶቻችን በአክሱም ሥልጣኔ ጊዜ ይሰማቸው የነበረው የአገር ፍቅር ስሜት ለእኛ አይሰማንም። በአክሱም ሥልጣኔ ዘዜ የነበረው የሴት ገላ ጣዕም ግን አሁንም አለ።. . . በረጅም ጊዜ ልምዴ፣ ቆንጆ ቆንጆ ሴቶች

የት እንደሚገኙ ዐውቃለሁ። የቋንቋ ትምህርት ቤት ቆንጆ ሴቶችን እንደ ማግኔት ይስባል። ፈረንጅ በይፍሬንድ ለማጥመድ ያቀዱ ሴቶች እዚያ ይከማቻሉ። እና የፈለጉትን ፈረንጅ እስኪያገኙ ድረስ አብሯቸው የሚያዘግም ቢያገኙ አይጠሉም። ሁለተኛ፣ እንደ ሄለን ያሉ በውጭ አገር ባል ያላቸው፣ ከባላቸው ጋራ ለመቀላቀል ቋንቋ የሚማሩ ሴቶች አሉ። እነሀ ሴቶች ለጊዜው ብቸኛ ስለሆኑ በብቸኝነታቸው መግባት ትችላለህ። ከእኒህ ሴቶች ጋራ ያን ነገር ብትጀምር ባላቸው ራቁቴን በምወራጭበት ሰዓት መኝታ ቤት ድረስ ገብቶ በሽጉጥ ያዳፍነኛል ብለህ አትሰጋም። ሴቶቹ ጉዳዩን በጥናት ስለሚያሳብቡት፣ ለሸውከኛ ትዝብት የተጋለጡ አይደሉም። በዚያ ላይ፣ እኒህ ሴቶች በኢኮኖሚም በስሜትም ባንተ ላይ ጥገኛ አይሆኑም። ለቋንቋ ትምህርት የሚከፍሉት ገንዘብ ካላቸው ድሃ አይደሉም። ሌላው፣ እንደምታውቀው ፍቅር ሲውል ሲያድር ጭቆና ይሆናል። እኒህ ሴቶች ግን ለጥቂት ጊዜ አብረውህ ቆይተው ወደ ውጭ ይሻገራሉ። ገላቸውን እና ጸጸታቸውን ይዘው ይሄዱልሃል። በዚያ ላይ ብዙ ያበሻ ወንድ የሴቶችን ያህል ቋንቋ ስለማይማር ያን ያህል ተፎካካሪ አይኖርብህም። እንግዲህ ይህን ምስጢር ለብቻዬ ስለማውቅ ከብዙ ቤላ አቢሲኒያዎች ጋራ በሞኖፖል ተደስቻለሁ። ግን ምን ዋጋ አለው? ደስታ በጎተራ አይጠራቀምም። እንግዲህ ተመልከት፤ ሴት ፍለጋ ጣልያንኛ እና ፈረንሳይኛ ተምሬያለሁ። አሁን ጀርመንኛ እየሞከርሁ ነው። ነገ ስዋሂልኛ ከመማር ምን ያግደኛል?»

ሣቁን ድንገት ብልጭ አድርጎ ቀጠለ። «የቋንቋ ትምህርት እንዲህ ዐይነቱን ደስታ ቢያመጣልኝም ደባል ሐዘን አለው። ከፈረንጅ ጋራ ያገናኘኛል። ፈረንጅ ሳይ ለራሴ ያለኝ አክብሮት



እንዲህ ዐይነቱን ደስታ ቢያመጣልኝም ደባል ሐዘን አለው። ከፈረንጅ ጋራ ያገናኘኛል። ፈረንጅ ሳይ ለራሴ ያለኝ አክብሮት ፈተና ውስጥ ይገባና ደስታዬ ይደፈርሳል።

. . .ከእማማ የወረስሁት አሪፍ ቤት ውስጥ እኖራለሁ። ግን ምን ዋጋ አለው? ለእኔ ዐይነት አኗኗር አይሆንም። በየቀኑ ሴት ይዤ ስመጣ ጎረቤቶቼ በየመስኮታቸው አንገታቸውን አሾልከው ያፈጡብኛል። ባለፈው አንድ ሰውዬ ከሁለተኛ ፎቅ ላይ ሆኖ ሲያፈጥ ወድቆ ወገቡ ተሠበረ። በማግሥቱ በዊልቸር ላይ ተቀምጦ እንደገና ማፍጠጡን ቀጠለ. . . አቤት! ደሞ ባስተያየታቸው ውስጥ ያለውን ሳንሱር ብታዬው. . . አንዳንዴ ሳስበው አብርሃም በድንኳን ውስጥ ለመኖር የመረጠው ወዶ አይደለም። ጎረቤቶቹ ሲደብሩት ቤቱን በቦርሳው አጣጥፎ ከትቶ ወደ ሌላ ቦታ መሄድ ይችላል። እንዲህ ዐይነት ልዩ ነጻነት ስላገኘ ጤናው ተጠብቆ አምስት መቶ ዓመታት ኖረ። እኔ ግን የገዛ መንደሬ እስረኛ ነኝ፤. . .ትላንት ማታ እስኪጨላልም ድረስ ጠብቄ አንዷን ይዤ ወደ ቤት እየመጣሁ ነው። እና ድንገት በጨለማው መሀል አንድ ድንጋይ እንደ ሌሊት ወፍ ውልብ ብሎ ጀርባዬ ላይ ዐረፈ። ማን የመታኝ ይመስልሃል? ሚስቱን ያባለግሁበት አበሻ ከበርሊን ድንጋይ ወርውሮብኝ እንዳይመስልህ፤ አይደለም።

ከጎረቤታችን ከሚኖሩ ጎረምሶች አንዱ ነው። ይህ ሰው የሴት ደስታን አያውቅም። የሴት ብልት እንኳን ያየው የጎጂ ልማድ አስወጋጅ ኮሚቴ በሚያሳየው የግርዛት ቪዲዮ ላይ ነው። ታዲያ በድንጋይ ቢወግረኝ ይገርምሃል?»

* * *

ዘወትር ከሰኞ እስከ ዐርብ ከቀኑ ስድስት ተኩል ጀምሮ

ተማሪዎች ከቋንቋ መማሪያ ክፍሎች ወጥተው ወደ ካፌው ከመጡ በኋላ ምሳ ያዝዛሉ:: ያዘዙት እስኪመጣ ድረስ አንድ ቦታ ተጠራቅመው እንደ ወፍ ጫጫት መንጫጫት ይጀምራሉ:: ሴቶች ደብተራቸውን ገልጠው በአንድ ቃል ዙሪያ ትንሽ ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ ከመ ቅጽበት ርእስ ለውጠው፣ አንዲቱ ተማሪ ይዛው የመጣችውን የፎቶ ግራፍ ነዶ እየበዘበዙ ማድነቅ ይጀምራሉ፤ «ወይኔ እዚህ ጋ እንዴት አ - ባሽ አድርገሽ ነው የምታምሪው!» የሚል ልስልስ የሴት ድምፅ ይሰማል::

ከሴቶች ጫጫታ የተረፈውን ክፍተት ለመጠቀም ወንዶች መሻማት ይጀምራሉ:: «እኔን አስጨርሰኛ!» የሚል የዛቻ እና የልመና ቅልቅል ይወረወራል:: ወሬውን ለግማሽ ሰዓት ተቆጣጥሮት የቆዬ ወጣት፣ «የኢትዮጵያ ሕዝብኮ. . .» ብሎ የጀመረውን ሐረግ ሳይቋጭ ሞባይሉ ይጮህበትና ሞባይሉን አንሥቶ ከወሬው መንበር ለጊዜው ይሰናበታል:: ይሄኔ ሌላው እንዲያዳምጥ ብቻ ተፈርዶበት የቆዬ ጭቁን አድማጭ፣ ባለሞባይሉ ስልክ የሚያወራበትን አጋጣሚ ተጠቅሞ የወሬውን ጭብጥ ቀይሮ ስለ ፋሽን ማውራት ይጀምራል:: በቅርቡ ወደ አገር ቤት ስለ ገቡ የጣልያን ጅንሶች ጥሩ እየተነተነ ሳለ በሞባይሉ ሲያወራ የቆየው ወጣት ስልኩን አጣድፎ ዘግቶ፣ «እና እንዳልኳችሁ የኢትዮጵያ ሕዝብኮ. . .» ብሎ ወሬውን ይቀለብሳል::

ይህ ሁሉ ሲሆን ምዑዝ ጸጥ ብሎ ይቀመጣል:: ተናጋሪዎች የእሱን ትኩረት ፍለጋ እጁን ሲጎትቱት፣ አንዳንዴም እንደ ፀጉር ከርካሚ አገጩን በየአቅጣጫው ሲያሧዙሩት አንድ ቃል ሳይተነፍስ ይታገሣል:: መስማቱን እና መስማማቱን ለመግለጽ ለዚህኛው ተናጋሪ ራሱን እየናጠ፣ ለዚያኛው የዐይን ጥቅሻ እያበረከተ ይቆያል፡፡ «ተማሪዎች ምሳ ከመብላታቸው በፊት ለማውራት



እንጂ ለማዳመጥ ዝግጁ አይደሉም፤» ይላል::

እውነትም ምሳ ከተበላ በኋላ ጸጥታ ይሰፍናል:: አዳሜ ጥርሱን በስቴኪኒ እየጎረጎረ፣ ቡናውን ፉት እያለ፣ ጨዋታ ለዳይጀሽን ይጠቅመው ይመስል፣ «ተጫወቱ እንጂ!» እያለ አጠገቡ ያለውን መማጠን ይጀምራል:: ይሄኔ ምዑዝ በዙሪያው ያሉት በሙሉ የወሬ ዝናራቸው ባዶ መቅረቱን ስለሚያውቅ ያለምንም ተሻሚ ንግግሩን ያዥጎደጉደዋል::

«ብታምኑም ባታምኑም አንድ ነገር ልነግራችሁ እፈልጋለሁ!» ይላል ከፊት ለፊቱ የተቀመጡትን ተራ በተራ እየቃኘ:: በዚህ ኮርስ ማጠናቀቂያ ላይ አሪፍ ነጥብ ያስመዘገበ ተማሪ የጀርመን መንግሥት ስኮላርሽፕ ይሸልመውና ወጪውን ችሎ ያስተምረዋል:: በኮርሱ መጨረሻ ተወዳድሬ አንደኛ እንደምወጣ አትጠራጠሩ! ያኔ ስኮላርሺፑን ሲሰጡኝ እምቢ አልቀበልም እላለሁ:: Aufuhr! አብዮት ይሏል ይሄ ነው:: እንግዲህ አውሮፓ ውስጥ መኖር የማይፈለግ ኢትዮጵያዊ መኖሩን ለዓለም ማሳዬት ራሱን የቻለ ሬቮሉሽን አይደለም?

«የኔ ቆንጆ እንደምትገምቺው(ወደ አንደኛዋ ተማሪ ዞሮ)፣ አንድ አሜሪካዊ ወደ ጀርመን ለመግባት ጀርመንኛ መማር አይጠበቅበትም:: ባሰኘው ሰዓት ይገባል:: ኢትዮጵያዊ ግን ጀርመንኛ እንዲማር ይገደዳል:: ለምን ብትል(ወደ ሌላው ተሰብሳቢ ዞሮ)፣ ያው በፈተና መውደቅን ሰበብ አድርገው ወደ አገራቸው እንዳይገባ ለማገድ ነው:: የአርበኝነት ስሜታችንን ለጊዜው ገሸሽ አድርገን ብናወራ አውሮፓውያን ጉልበታቸውን እና ብልጠታቸውን ተጠቅመው ወደ አገራቸው እንዳንገባ የሚያደርጉን የመኖር ሕግ ስለሚያስገድዳቸው ነው:: አውሮፓ ውስጥ ባላገሮቹ

መሬት ላይ አልዓዛራቸው[1] እስኪረግብ፣ እንትናቸው እስኪነትብ እየተሳረሩ ይቀፈቅፋሉ:: ይህን ዝም ብሎ ማለፍ እንዴት ይቻላል? ባላገሮች ሰደተኞችን፣ ‹ይህች የምትኖሩባት አገር አባቶቻችን ያቀኑት ምድር ነው፤› ብለው ሲሏቸው ሰደተኞች እና እንግዶች ግን፣ ‹ምድር የእግዜር ነው፤› ይላሉ:: ይህች ፈሊጥ የርስት አልባ ሰዎች ብልጠት ናት - ከምድራዊው አባት ያልተገኘውን ርስት በሰማያዊው አባት ስም ለመካፈል ነው::

. . እስኪ አስቡት፣ አውሮፓውያን በቅኝ ግዛት ምድራችንን ለመውረስ ጠመንጃ ይዘው ሲመጡ ጋሻ እና ጦር ይዘን ወጥተን አልተጋፈጥናቸውም? Ja! የኛም ነገር ከዚህ አይለይም፤ ዐየህ በታሪክ እንደተመለከትነው፣ ጀግናው ተዋግቶ ደካማው ተራብቶ የሌሎችን አገር ይቀማል:: ጀግና በደሙ፣ ወላድ በስፐርሙ አገር ያቀናል:: Well. . .ለምን ይሄን ትተን ስለሌላ ነገር አናወራም::»

ምዑዝ ስለ ሌላ ነገር የሚለው ስለ ሴት ነው:: ከአገር ወሬ ለማምለጥ ስለ ሴት ማውራት ይጀምራል:: ግን ስለ ሴት እያወራ ሳያውቀው ስለ አገር ማውራቱን ይቀጥላል:: ለካ ሴት የአገር ቁራኛ ኖራለች:: ሁለቱ ተቆላልፈው የምዑዝን ጠረጴዛ ሲዞሩት ቆዩ::

* * *

ብዙ ሰዎች ምዑዝ በኔ ሕይወት እና ጠባይ ላይ ጫና ያሳደረ ይመስላቸዋል:: ይህን ጉዳይ በተወሰነ መንገድ እውነት ነው፤ ግን ከምንቀራረብበት የምንለያይበት ይበዛል:: ይህን በተሻለ መንገድ ለማብራራት አንድ ትዝታ ልጨምር፤. . .

[1] አልዓዛር:- ምዑዝ ለወንድ ብልት የሰጠው ስያሜ ነው:: ሞቶ የመነሣት ባሕርይውን ለመጠቆም ሳይሆን አይቀርም::



አንድ ቀን ቁጭ ብዬ ሳስብ፣ የመክሊት ፍቅረኛ አቶ ያን አባቴ እና ምዑዝ ባንድ መሥመር ተገናኝተው አገኘኋቸው::

አቶ ያን በቴምብር ውስጥ ካልሆነ በቀር በዱር ውስጥ እምብዛም የማይገኙ የዱር እንስሳት ተከባካቢ ድርጅት ውስጥ ይሠራል:: እንዲህ ዐይነቱ ነገር የዘመኑ ፋሽን ነበር:: እኔ በምኖርበት ሠፈር እንኳ በዱር እንስሳት ዙሪያ የሚሠሩ ብዙ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይገኛሉ:: ለምሳሌ፤ አሳዳጊ አልባ ግልገል ነብሮች ጡጦ አጥቢ ድርጅት፣ የአንበሳ ጋማ አበጣሪ ድርጅት፣ ሽልምልማቸው የደበዘዘ የሜዳ አህዮች ቀዳ አድማቂ ድርጅት፣ የቀጭኔዎች አንገት ርዝመት ደረጃ መዳቢ ድርጅት፣ የተሰደዱ ወፎች ናፋቂ ድርጅት. . . ወዘተርፈ::

ከነዚህ ሁሉ በብልጽግና ብልጫ ያለው ጀርመን በቀል የሆነው አቶ ያን የሚሠራበት ድርጅት ነው ይባላል:: የአቶ ያን ድርጅት ለእንስሳት በጣም ከማሰቡ የተነሳ፣ «ኢትዮጵያ ውስጥ ድርቅ ቢከሠት ሣር በል እንስሳትን ወደ ኬንያ ወይም ወደ ኮንጎ በመውሰድ አስግጦ ሲጠግቡ ወደ አገራቸው በመርከብ የመመለስ አቅም አለው፤» ይባላል::

አቶ ያን ካፌው ውስጥ ቡና እየጠጣ፣ ዶክተር ሰሎሞን ይርጋ የተባሉ ምሁር የጻፉትን «አጥቢዎች» የተባለ መጽሐፍ ያነባል:: መጽሐፉ ውስጥ ስለ አጋዘን፣ ስለ ድኩላ፣ ስለ ኒያላ፣ ስለ አንበሳ፣ ስለ ሳላ፣ ስለ ጅብ፣ ስለ ዝሆን ስለ ሌሎችም አጥቢ እንስሳት የቀረቡ ጥናቶች እና ሥዕሎች ይገኛሉ:: አቶ ያን የዚህን መጽሐፍ አንድ ቅጅ ገዝቶ ሲያበረክትልኝ የሕይወቴን አንድ ክፍል የሚያሳስብ ነጥብ አገኘሁበት::

ከዛሬ ብዙ ዓመታች በፊት እናቴ እኔን ነፍሰ ጡር ሳለች፣

«የአንበሳ ሥጋ አማረኝ፤» ብላ አባቴ እንዲያመጣላት አጥብቃ ለመነችው፡፡ አባቴ ሐሳቧን እንድትቀይር በማግባባት ወይም በማስፈራራት ፈንታ ለእሷ ያለውን ፍቅር ለማሳየት አሮጌ ቼኮዝ ጠመንጃውን ተሸክሞ ለአደን ይወጣል፡፡ ለአደን የመረጠው ቦታ በጊዜው በደብረ ማርቆስ የሚገኝ የእንስሳት መደብር የነበረ ውትርን በተባለ ወንዝ አጠገብ የበቀለ ጫካ ነበር፡፡ አባቴ እዚያ ገብቶ መጀመርያ ሳላ የተባለውን ሣር በል ገደለ፤ ከዚያ የሳላውን በድን በደረቅ ግንድ ላይ አጋድሞ አንበሳው የሳላውን ሥጋ አነፍንፎ ሲመጣ ለመግደል ይጠባበቅ ጀመር፡፡ ቢጠብቅ፣ ቢጠብቅ አንበሳው ብቅ ሳይል ጀንበር ወደ ጎሬዋ መንሸራተት ጀመረች፡፡ በአንበሳው ፈንታ ድንኳን ሠባሪ ጥንብ አንሣዎች በግዳዩ በድን ላይ መራኮት ጀመሩ፡፡ አባቴ በጣም ነዶት፣ ጥንብ አንሣዎቹን አንድ ባንድ በጥይት ነድፎ እየጣለ በሳላው ዙሪያ ጎዘጎዛቸው፡፡ ደርዘን ሙሉ ጥንብ አንሣ ከገደለ በኋላ ግን ጥይት መጨረሱን ተገነዘበ፡፡ ይሄኔ ዱር ውስጥ ሆኖ የአባቴን ጥይት መጨረስ በደመ ነፍስ የተረዳው አንበሳ እየተጎማለለ ወጥቶ ሳላውን እየዘነጠለ ማጣጣም ጀመረ፡፡ አባቴ ምንም ማድረግ አልቻለም፡፡ ቼኮዝ ጠመንጃውን እንደ ከዘራ እየተመረኮዘ ወደ ቤቱ መመለስ ጀመረ፡፡ ቤቱ ሊደርስ ጥቂት ምዕራፎች ሲቀሩት ግን ከኋላው ጅብ እንደ ተከተለው ተመለከተ፡፡

አደጋው በተከሠተ በማግሥቱ የመንደራችን ዕድር ያደራጃቸው ወጣቶች በመንደራችን ውስጥ የሚኖሩ ጅቦችን በአጠቃላይ በቁጥጥር ሥር አውለው፣ አባቴን ገድሎ የበላውን ጅብ ለመለየት መላ መቱ፡፡ በወፍጮ ቤት የእህል ሚዛን ላይ ምርኮኛ ጅቦችን ተራ በተራ በማውጣት መዘኗቸው፡፡ አንድ ጅብ በአማካይ ስሦንት ኪሎ ይመዝናል፡፡ አባቴ ስድሳ ኪሎ ይመዝን ስለ ነበር በወቅቱ ስድሳ ስምንት ኪሎ መዝኖ የተገኘ ጅብ ያባቴ



ገዳይ እንደ ሆነ ተደርሶበት ተረሸነ፡፡ ጅቡን የገደሉት ለበቀል አልነበረም፡፡ የአባቴን ቀብር ለማስፈጸም የግድ ይሄ መደረግ ነበረበት፡፡ ባንድ በኩል ጅቡ ያባቴ አስከሬን መክተቻ ሆኖ አገለገለ፡፡ በሌላ በኩል አባቴ እና ጅቡ ባንድ መቃብር ውስጥ በጅምላ ተቀበሩ፡፡ ከአብማ ቤተ ክርስቲያን ጓሮ የሚገኘውን ይህን የጋራ መቃብር ቀን ቀን ያባቴ ቤተሰቦች፣ የጅቡ ቤተሰቦች ማታ ማታ ይጎበኙታል፡፡

ይህን ከመንደራችን የፈለቀ የጀርባ ታሪክ ከሰማሁ በኋላ በልጅነቴ ያባቴ ሞት ጸጸት ሆኖብኝ ነበር፡፡ እናቴ እኔን ባታረግዝ ኖሮ፣ የአንበሳ ሥጋ አያምራትም፤ አባቴም አጉል አይሞትም፤ ብዬ በመረገዜ ተጸጸትሁ፡፡

እያደግሁ ስሄድ ግን ጸጸቴ ወደ እፍረት ተቀየረ፡፡ በጀግኖች አገር ውስጥ በጅብ የተበላ አባት ልጅ መሆኔን ማወቄ አሸማቀቀኝ፡፡ ምናለ አባቴን የበላው ጅብ መሆኑ ቀርቶ የንግሥና ምልክት የሆነው አንበሳ በሆነ፤ ምናለ ሳላው በቀንዱ በዘከዘከው፤ እያልሁ ተጸጸትሁ፡፡ በቅርቡ አቶ ያን በሰጠኝ «አጥቢዎች» በተባለው መጽሐፍ ስለ ጅብ የተጻፈውን ሳነብ አንዳች የክብር ምልክት አጣሁበት፡፡ ይባስ ብሎ ባንድ የመጽሐፉ ክፍል አንድ ጅብ ከገዛ ክብደቱ ስምንት በመቶ የሚያህል ሠገራ እንደሚጥል አነበብሁ፡፡ አቤት ግፍ! ይህን ያህል ለማራት በእግዜር አምሳል የተፈጠረውን አባቴን መብላት ፍትሐዊ ነው? እያልሁ ተከዝሁ፡፡

መጽሐፉን እንደ ያዝሁ በሐሳብ ስባክን የተመለከተኝ ምዑዝ፣ ጥራዙን ከእጄ ወስዶ ማንበብ ጀመረ፡፡ በማግሥቱ መጽሐፉን ሲመልስልኝ የወደዳቸውን አንቀጾች አሥምሮባቸው ነበር፡፡ ስለ ሳላ በተጻፈው ውስጥ የሚከተለውን በቀይ አስክርቢቶ

አሥምሮበታል።

*«...ሳሳ - በሥሪያ ጊዜ በመጀመርያ ወንድየው ከኋላ በኩል ያሸታል። ሆኖም እሷ ከኮርማው በስተኋላ ለመሆን በምታደርገው ጥረት ዑደት ያደርጋሉ። ወንድዬው ከፊት ለፊት ከመጣባት ራሷን ትከላከላለች። እንዲህ በክብ ከተሿሿሩ በኋላ በርከክ ብላ ትሸናለች። ሽንቷን የሚያሸተው ወንድ በርግጥ መሞቋን ካወቀ የፊት እግሩን እያነሣ መከተሉን ይቀጥላል። ከዚያ በኋላ እግሮቿን አጠፍ ካደረገች እና ጭራዋን ወደ ጎን ፈቀቅ ካደረገች ወንድየው ይወጣባታል። ግንኙነት ይፈጽማሉ።»*

በመጽሐፉ ውስጥ ስለ ዝሆን በቀረበው ጥናት ደግሞ፣ «የወንዱ ዝሆን ብልት እስከ 27 ኪሎ ግራም ይመዝናል» የሚለውን አሥምሮበታል። ስለ ጅብ ከተጻፈው መሀል ምዑዝን ያሳሰበው በወንዱ ጅብ እና በሴቷ ጅብ መካከል ያለው መመሳሰል ነው። የሚከተለውን በቀይ እስኪቢርቶ አድምቆታል፤

*«. . .የሴት ጅብ ቂንጥር የወንድ ብልት ያህል ማደጉ፣ በጮማ የሞላው የሴቷ ላት የቆለጥ ከረጢት የወንድ መምሰሉ የውንዠንብር መንሥኤ ነው።»*

ከአቶ ያን የተዋስሁት ስለ አጥቢ እንስሳት የሚያትተው ይህ መጽሐፍ ለኔ ውርደትን፣ ለምዑዝ ሽፍደትን እንዳመጣብን ዐይቼ ተገረምሁ፤ የልዩነታችንን መጠንም ተረዳሁ።



# ምዑዙፍ ስምንት

ከሌሎች እንደ ሰማሁት፣ ራሱም እንደ ነገረኝ ከሆነ፣ ምዑዝ ጭንቅየለሽ ኑሮ ይኖራል። ከሁለተኛ ባለቤታቸው ጋራ በአሜሪካ የሚኖሩ እናት አሉት። እናቲቱ ወደ አሜሪካ ሊወስዱት ቢሞክሩም እርሱ ግን፣ «ከአገሬ አልወጣም፤» ብሎ ድርቅ አለ። ከዩኒቨርሲቲ ከተመረቀ ዓመታት ተቆጥረዋል፤ ግን ሥራ አልያዘም። እንዴት ይኖራል? «ሁለተኛ ዲግሪዬን እየሠራሁ ነው፤» ብሎ ለእናቱ ስለ ነገራቸው በየወሩ ዶላር ሲልኩለት ቆዩ። ከዕለታት አንድ ቀን፣ «ይህ ሁለተኛ ዲግሪ ማለቂያ የለውም እንዴ?» ብለው በስልክ ጠየቁት። ሲያስበው ለካ ጊዜው ነጉዷል። «. . .እ! ሳልነግርሽ ፒ.ኤች. ዲዬን በዚያው ቀጠልሁ፤» ብሎ ዶላር መመንዘሩን ቀጠለ። ያም ሆኖ ገንዘብ አይበቃውም ነበር።

አንድ ቀን እንዲህ አለኝ፤ «. . .የምትችል ከሆነ ከአንዲት ሴት ጋራ ተማምነህ ኑር። ነቢያት ‹አታመንዝሩ› ብለው ያዘዙት ከኢኮኖሚ አንጻር የሚያመጣውን ኪሳራ አይተውት ነው። እንዲያውም አንዳንዴ ሳስበው ‹መነዘረ› የሚለው ቃል ‹አመነዘረ› ከሚለው ግስ የተገኘ ይመስለኛል። እኔ ብቻ እንዳልመስልህ አባቴም የዚህ ሰለባ ነበር።

ነፍሱን ይማርና አባቴ ወደ ውሽማው ሲሄድ ለእጅ መንሻ አንድ ኩንታል ከሰል ያስጭናል። ከውሽማው ወደ እማማ ሲመለስ ደግሞ ጸጸት ስለሚሰማው ጠቦት በግ አስጭኖ ይመጣል። ምን ልበልህ! እኛ ቤት በር ላይ በግ ታስሮ ካየሁ አባዬ ሌላ ሴት ጋራ ሄዶ እንደ መጣ ይገባኛል።»

«ሁልጊዜ በግ መግዛት ትንሽ አይከብድም?» አልሁት።

«ሁልጊዜ አይደለም። አባዬ በግ የሚያመጣው ከውሽማው ጋራ ከተኛ ብቻ ነው። ከተሳሳመ ደግሞ ዶሮ ያመጣል።»

አባካኙ ምዑዝ፣ ሴቶችን ባጭር ጊዜ ለማማለል የማያስችል ፓስወርድ እንዳለው ቢናገርም፣ ፓስወርዱ ወደ ሄለን ሊያስገባው አልቻለም። ለመጀመርያ ጊዜ ምዑዝ ሄለንን ሲቀርባት የደረሰበት ነገር ትዝ ይለኛል። ሄለን ወደ ካፌው ገብታ፣ ተጋሪ አልባ ወንበር መርጣ ከተቀመጠች በኋላ ሰላጣ እንዳመጣላት አዘዘችኝ። ያዘዘችውን ይገፍ መጥቼ ከጠረጴዛዋ ላይ ሳስቀምጥላት፣ «ሁልጊዜ አትክልት ስትበይ ነው የማይሽ፣» የሚል ድምፅ ተሰማ። ዞር ስል ምዑዝ ነው። ሳያስፈቅድ ከፊት ለፊቷ ቁጭ ካለ በኋላ፣ «ቬጂቴሪያን ለመሆን ምን አነሣሣሽ?» ሲል ሰማሁት።

ሄለን፣ አድርቆ በሚጥል አስተያየት ከገረመመችው በኋላ ምንም ሳትመልስለት የጨዉን ብልቃጥ አነሣች። እኔ እንዲህ ዐይነት አጋጣሚ ቢገጥመኝ በእፍረት ሥራዬንም አገሪቱንም ለቅቄ እሄድ ነበር። ምዑዝ ግን ባፈጠጠ ድርቅና ጥያቄ እየጠየቀ፣ ለጥያቄው ራሱ መልስ እየሰጠ «ይተረተር» ጀመር።

«Well. . .ለነገሩ ሳይንቲስቶች ቅጠላቅጠል እና ፍራፍሬ መብላት ዕድሜን እንደሚያስረዝም አረጋግጠዋል። ግን ምን ዋጋ አለው? በእኛ አገር ብዙ ሰው የሚሞተው በመኪና አደጋ



ነው። መኪና ደግሞ አትክልት የበላውን ሰው ካልበላው ለይቶ አይገጭም። ምናልባት *ቬጂቴሪያን* የሆንሽው ለእንስሳት ያለሽን ፍቅር ለመግለጽ ይሆን? እዚህ ላይ እውነት አለሽ፤. . .እንስሳት እንደ ሰዎች ደኅንነታቸው ሊጠበቅ ይገባል። ይገርምሻል! ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት *ሾፐንሀወርን* በጀርመንኛ እያነበብሁ ነበር። እንስሳት ከሰዎች የሚለዩበትን ነገር ለማብራራት ዐሥር ገጽ ሙሉ ይዘበዝባል. . .፤ ይቺን ታህል አላሳመነኝም!! እንደኔ እንደኔ ሰውን ከእንስሳት የሚለየው የፓርክ አጥር ነው። እውነቴን ነው የምልሽ፣ አንድ በሬ ዕድሉን ካገኘ እንደ ኤንሽታይን ከመሆን ምን ያግደዋል? እኔ ለምሳሌ፣ ዓለም አቀፍ ግኝቶችን ያበረከቱ ሁለት ኢትዮጵያውያንን ዐውቃለሁ። አንደኛው፣ የቢላሃርዚያን መድኃኒት ያገኘው አክሊሉ ለማ ሲሆን ሌላው ቡናን ያገኘው ፍየል ነው። እኛ ሰዎች ግን አድሏዊ ስለሆን ግኝቱን ለፍየሉ ሳይሆን ለእረኛው ሰጠነው!. . .እና የእንስሳትን ደኅንነት ለመጠበቅ የምታደርጊው ነገር በሙሉ ድጋፍ ያስፈልገዋል ባይ ነኝ።

በእምነትሽ መግባት አይሁንብኝና ቬጂቴሪያኒዝም አንድ ስሕተት አለው። ተክሎችን ከግምት አያስገባም። ዐየሽ፣ ለጠቦት በጎች የምንራራውን ያህል ለጥቅል ጎመኖች መራራት ይገባናል። ዞርዐ ያዕቆብ እንዳለው ዕፀዋትም ነፍስ ያላቸው ይመስለኛል። እውነቴን ነው የምልሽ፣ እግሩ ባይታሰር ኖሮ ጎመን ሰው ሲያይ ሮጦ ያመልጥ ነበር። እንዲያው ቬጂቴሪያን ከሆንሽ ስንት ጊዜ ሆነሽ?»

«ቬጂቴሪያን አይደለሁም!» አለች ሄለን ሳሕኗን ይዛ እየተነሣች። ምዑዝ የጨው ብልቃጧን ይዞ እየተከተላት፣ «ታዲያ ሰላጣ የምታዘወትሪው ሽምንድን ነው?»

«ሁዳዴን ስለ ምጾም ነው!»

በሌላ ቀን ምዑዝ ወደ ካፌው ገባና ባይኑ ሰው መፈለግ ጀመረ። ይሄኔ እንደ ልማዷ ብቻዋን ቁጭ ብላ ስታጠና ስላያት፣ እየነጠረ ሄዶ አጠገቧ ከተቀመጠ በኋላ፣ «. . .ዛሬ የልደት ቀኔ ስለሆነ ይህን ስጦታ አበረክትልሻለሁ፤» ብሎ ይዞላት የመጣውን ትልቅ ጥቅል ሰጣት። « . . . አ! Vielel Danke (በጣም አመሰግናለሁ!) አለችና እየሣቀች እቅፍ አደረገችው። የስጦታው ጥቅል ሲፈታ ባለ ሦስት ጣት የሻማ ማብርያ መቅረዝ ሆነ። ከተሰነባበቱ በኋላ ለምን አበባ እንዳላመጣላት ስጠይቀው፣ «አንተ ስለ ሴት ምን ታውቃለህ?» ብሎ ጀመረ። «ይቺ ልጅ በቀላሉ የምትበገር አይደለችም። አበባ ባመጣላት ነገ ትረሳዋለች። አእምሮዋ ውጭ ባለው በይፍሬንዷ ናፍቆት እና በትምህርቷ ሐሳብ ተሞልቷል። በዚያ መሀል ተጋፍቼ ከፊቷ ለመቆም ለየት ያለ ነገር ያስፈልገኛል። ዐየህ፣ ሰሞኑን በሳምንት ሦስት ቀን መብራት ይጠፋል። እና ሻማ ባበራች ቁጥር ቢያንስ በሳምንት ለሦስት ምሽት ታስበኛለች። ከብርሃን ጋራ አቆራኝታ ስለምታስበኝ ፍቅር በልቧ ይፀነሳል፤ ምናለ በለኝ፤ ታያለህ! ብቻ ሄለንን በእጄ ሳላስገባ መብራት ኀይል አሠራሩን እንዳያሻሽል ጸልይልኝ!»

በማግሥቱ ምዑዝ ለብቻው ትልቅ ወንበር ላይ ተንፈራጦ አጠገቡ ለመቀመጥ የሚቃጣውን ሁሉ፣ «ሰው አለ!» እያለ እያባረረ ሄለንን ይጠብቃል። ሄለን ከጥቂት ጊዜ በኋላ ገባችና፣ ለምዑዝ የተድበሰበሰ ፈገግታ አሳይታው አልፋው ሌላ ቦታ ተቀመጠች። «ስጦታው እንዴት አልሠራም?» አልሁት ጠረጴዛው ላይ ሻይ እያስቀመጥሁለት።

«ምን አውቃለሁ!» አለኝ ባኮረፈ ድምፅ፤ «እኔ ሻማ ማብርያ



መቅረዝ ሳበረክትላት ሌላው በጎን ጀኔረተር አበርክቶላት ይሆናል!»

* * *

በሌላ ቀን የጀርመንኛ ቋንቋ ተማሪዎች እና ጥቂት ከውጭ የመጡ ተስተናጋጆች ካፌውን ሞልተው አትሌቶቻችን የሚያደርጉትን ውድድር በቴሌቪዥን እየተመለከቱ ነው። ምዑዝ ለአትሌቲክስም ሆነ ከአትሌቲክስ ለሚገኘው ብሔራዊ ድል ደንታ እንደሌለው ሲነግረኝ ቆይቷል። ያም ሆኖ፣ አሁን ከተመልካቾች መሀል ቁጭ ብሎ የቴሌቪዥኑን ስክሪን እና የሄለንን ፊት እያፈራረቀ ሲመለከት ያዝሁት። ውድድሩ ሊጠናቀቅ ሁለት ዙር ሲቀረው፣ ቀነኒሳ በቀለ ከተወዳዳሪዎች መካከል አፈትልኮ ሲወጣ ምዑዝም ከተመልካቾች መካከል አፈትልኮ በመውጣት ከሄለን አጠገብ ቁጭ አለ። ሄለን በስሜት ውስጥ ሆና የምታደርገውን ሳታውቅ የሌላ ሰው የሻይ ስኒ አንሥታ ጠጣች። ቀነኒሳ የመጨረሻው ዙር ፍጻሜ ላይ ሲደርስ፣ ካፌው ተደበላለቀ። ብርጭቆዎች እና ጠርሙሶች ከቀነኒሳ ሪከርድ ጋራ አብረው ተሠባበሩ። ሄለን ብድግ ብላ ስትጮህ፣ ምዑዝ ዘልሎ ከተጠመጠመባት በኋላ በግርግር መሀል ሩብ ከንፈሯን፣ ግማሽ ጉንጯን ይስም ጀመር።

ቀጥሎ የተደረገውን ለማየት አልቻልሁም። ሳይፈቀድለት ወደ ካፌው የገባ ሎተሪ አዟሪ በደስታ አብዶ፣ ቀነኒሳን ያገኘ ይመስል እኔን ከነትሪዬ ተሸክሞ ወደ ደጅ አወጣኝ። በማግሥቱ ምዑዝ፣ ሄለንን እየጠበቀ ለእኔ እና ለመክሊት የሚከተለውን ተናዘዘልን።

«ሄለንን ማሳመን ከቻልሁ ሕይወቴ ወደ ሌላ ምዕራፍ ይሸጋገራል። ይኸው እናንተ ምስክሮች ናችሁ - መንዘላዘል

አቆማለሁ፤ ሥራ እይዛለሁ። አዎ፣ ለምን ወፍጮ ቤት ውስጥ አይሆንም! . . .ለገንዘቡ አይደለም! በቃ ለሞራል!!»

ከጥቂት ዝምታ በኋላ ኑዛዜውን ቀጠለ፤ «አንድ ሰው በመጨረሻ ሰዓቱ ላይ፣ ‹ምን አደረግሁ?› ብሎ ሲጠይቅ በኑሮ ውስጥ ያደረገውን ጥረት፣ በቁጥር እና በሥፍር ማስቀመጥ አለበት። አራት መሥርያ ቤቶች ውስጥ ሠራሁ፤ ኀምሳ ከብቶችን አደለብሁ፤ ሁለት ሕንፃ ገነባሁ፤ ዘጠኝ ልጆችን ወለድሁ ማለት አለበት። በልኬት የማይታወቅ ሕይወት ዋጋ ቢስ ነው። እኔ ግን ደስታን ስፈልግ ኖርሁ። በመጨረሻ ሰዓት ምን እላለሁ? ደስታ አይሠፈርም። ይህን ያህል ኪሎ ደስታ ተደሰትሁ ማለት ይቻላል? ባንድ ወቅት የማወጣቸውን ሴቶች የጡት ማስያዣ የማጠራቀም «ሆቢ» ነበረኝ። አርባ የጡት ማስያዣ ከሰበሰብሁ በኋላ ምን ማድረጌ ነው? አልሁ። ለካ አርባ ደስታ ተደስቻለሁ ብዬ ራሴን ለማሳመን ያደረግሁት ነው። ደስታን ለመቁጠር የተደረገ የመጨረሻ ሙከራ! . . .አያሳዝንም? እስኪ አስቢው መከሊትዬ፤ ጣልያንኛ፣ ፈረንሳይኛ ተምሬያለሁ ግን ምን አደረግሁበት? ባለፈው ቋንቋው ዝም ብሎ እንዳይባክን የመጀመርያ ፍቅረኛዬ የጻፈችልኝን ደብዳቤ ወደ ጣልያንኛ ተረጎምሁት፤» ብቻውን ይሥቅ ጀመር።

«በምታደርገው ነገር ሁሉ በላይ ቤት ትጠየቅበታለህ!» አለችው መከሊት። ምዑዝ ንቀት በተቀላቀለበት ፈገግታ ለጥቂት ሰከንዶች ሲመለከታት ከቆየ በኋላ፣ «ይህ እንግዲህ ከሞት በኋላ ባለው ነገር የሚወሰን ነው። Well . . .ሰው ነኝና ጉዳዩ ያሳስበኛል። ባለፈው ለሁለት ቀን ያህል ቤቴን ዘግቼ ከሞት ቀጥሎ ምን አለ የሚለውን ጥያቄ አንሥቼ ተመራመርሁ። በመጨረሻም መልሱ መጣልኝ። ከሞት ቀጥሎ ያለው የቀብር ሥነ ሥርዐት ነው።»



# ምዕራፍ ዘጠኝ

Also Sprach Müz(ምዑዝ እንዲህ ሲል ተናገረ)፤ «ፍልስፍና አይመቸኝም፤ ከሜታፊዚክስ ይልቅ ሜታ ቢራን እመርጣለሁ፤ ከየት መጣን? ወዴት እንሄዳለን? የሚለው ጥያቄ ይህን ያህል ከባድ አይደለም። የመጣነው ከእናታችን ማሕፀን ሲሆን የምንሄደው ወደ አሜሪካ ነው። ሴ ፊኒ(አለቀ)። ዶስቶቭስኪ፣ *‹እግዜር ከሌለ ሁለት ነገር ማድረግ ይፈቀዳል!›* ይላል። እኔ ደግሞ እላለሁ፤. . .እግዜር ባይኖርም የፌዴራል ፖሊስ ይኖራል፣ እና ካፌ ገብቶ ሳንቡሳ በልቶ ሳይከፍሉ መውጣት አልተፈቀደም። ሌላ የሚያፈላስፍ ምን የቀረ ነገር አለ? ምናልባት ሞት። ሞት የሚያፈላስፈው ሕይወት ብርቅ በነበረችበት ዘመን ላይ ነው። ዛሬ ግን ሰዎች በኑሯቸው ደስታ ስላጡበት በሞት ማዘን አቁመዋል። ወደ የሴፍ ቤተ ክርስቲያን ለቀብር ሄደህ ታውቃለህ? እንባ የሚያፈስ ሰው አታይም። እንዲያውም፣ የእኛ ሰፈር ዕድር ከዚህ በኋላ ሰው ሲሞት አስለቃሽ ጭስ ለመከራየት ዐቅዷል።

የገባኝን ያህል እንድናገር የሚፈቅድልኝ ማኅበረሰብ የለኝም።

የስምንተኛ ክፍል የታሪክ መምህሬ አንድ ቀን፣ ‹የሠራተኛው መደብ ከከበርቴው መደብ በምን ይለያል?› ብለው ጠየቁኝ፤ እንደ ገባኝ መለስሁላቸው፤ ‹የሠራተኛው መደብ ከጭቃ የተሠራ ሲሆን አልፎ አልፎ አገዛ ጣል ይደረግበታል› አልኋቸው:: ትንሽ ሲሥቁ ከቆዩ በኋላ ለአርባ ደቂቃ ያህል አንበረከኩኝ:: እሺ፣ ተሳሳትሁ እንበል፤ ግን ቢያንስ ስላዝናናኋቸው ምናለ ቢምሩኝ::»

በሌላ ጊዜ ደግሞ ምዑዝ እንዲህ አለ፤

«. . ፈላስፎች፣ መሪዎች እና ደራሲዎች ዓለምን ለመለወጥ ቃል ይገባሉ:: የሚቻል ነው? ይሄ ነገር(ወደ ቴሌቪዥኑ እየጠቆመ) ከዐሥር ደቂቃ በፊት በአልጀዚራ ጣቢያ በኩል የጋዛን ጦርነት ሲያሳየን ነበር:: መክሊት ወደ ኀብረ ትርኢት ፕሮግራም ቀየረችው:: መክሊት ልክ ናት:: የሰው ልጅ የቴሌቪዥኑን ቻናል እንጂ ዓለምን መቀየር አይችልም::»

"*Contra Aristotle* - የሰው ልጅ ተገንጣይ እንስሳ ነው:: ባለፈው አንዱ ‹*ያዲሳባ ልጅ*› የሚል ጽሑፍ ያለበት ቲ-ሸርት ለብሶ ታዩ፤ ወዲያው ብዙ ሰዎች እንደ እሱ መልበስ ሲጀምሩ ተገንጥሎ ‹*የሸሮ ሜዳ* ልጅ› የሚል ጽሑፍ ያለበት ቲ-ሸርት ለበሰ:: ብዙ የሰፈሩ ልጆች እንደ እሱ መልበስ ሲጀመሩ ተገነጠለና ‹*የእኛ ቤት*› ልጅ የሚል ጽሑፍ ያለበት ቲ-ሸርት ለበሰ:: በመጨረሻም ወንድሞቹ እንደ እሱ መልበስ ሲጀምሩ ተገንጥሎ ‹*ታላቁ ልጅ*› የሚል ጽሑፍ ያለበት ቲ-ሸርት ለበሰ::»

አንድ ቀን እንባብያን በሌሉበት ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ተቀምጠን ሳለ ምዑዝ እንዲህ አለ፤

«. . ስለ መጻሕፍትም እናገራለሁ፤ መጽሐፍ የደስታ



ምንጭ የሚሆነው ስታነበው አይደለም፤ ስትሸጠው ነው:: ያም ሆኖ ልክፍት ሆኖብኝ አነባለሁ፤ የአማርኛ ልቦለዶች በጣም አዝጋሚ ታሪክ ስላላቸው ላነባቸው ስፈልግ ታክሲ ውስጥ እገባለሁ:: ከደራሲው ያጣሁትን ፍጥነት ከሾፌሩ አገኛለሁ:: የውጭ አገር መጻሕፍትን በተመለከተ የቋንቋ ዕንቆቅልሽ አለ:: ጎረምሳ ሳለሁ የትርጉም ሥራዎችን አነብ ነበር:: አሁን በቅርቡ ኦርጅናሌዎችን አግኝቼ ሳስተያያቸው ልዩነታቸው ገረመኝ:: ዐየህ፣ የቪክቶር ኢጎ ልቦለድ እኛ ዘንድ ከመድረሱ በፊት ከፈረንሳይኛ ወደ እንግሊዝኛ ፣ ከእንግሊዝኛ ደግሞ ወደ አማርኛ መተርጎም ነበረበት:: ከኦርጅናሌው ጋራ ያለውን ልዩነት እንዴት ብዬ ላስረዳህ? የትርጉም ትርጉም ማንበብ ሁለት ኮንዶም ደርቦ እንትን እንደ ማድረግ ነው::

## ምዑዝ እና አቶ ያን

አቶ ያን በየወሩ ሰባ ሺሕ የኢትዮጵያ ብር እንደሚያገኝ ይነገራል:: ያም ሆኖ በየቀኑ ፈጣን ሎተሪ ሲፍቅ ዐየዋለሁ::

አቶ ያን ፎቶ ማንሣት ይወዳል:: ለነገሩ ብዙ ፈረንጆች ከንጣታቸው ቀጥሎ ያለው መለዮአቸው ካሜራቸው ነው:: ባለፈው መጸዳጃ ቤት ተቀምጬ ግድግዳ ላይ የሚከተለው ማሳሰቢያ በፓርከር ተጽፎ አነበብሁ:: እንዲህ ይላል፤ *«በሽንት ቤት ውስጥ ስውር ካሜራ ስለሚገኝ ፈገግ ብለው ይጸዳዱ::»* የፈረንጆችን መፍቅሬ ካሜራነት የሚያውቅ ተንኮለኛ ተማሪ የጻፈው ሳይሆን አይቀርም::

በዚህ ጉዳይ ሌላም ትዝታ አለኝ:: በእኛ ሰፈር የበጎ አድራጎት ተቋም የከፈተ ጴጥሮስ መርፊ የተባለ ባለጸጋ የአየርላንድ ሰው ነበር:: አቶ መርፊ በየዓመት በዓሉ ቮጎዳና ተዳዳሪ ልጆችን ሰብስቦ

ራት ያበላል:: በየዓመት በዓሉ ጥሪ የተደረገላቸው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጋዜጠኞች ራት ግብዣውን ቀርጸው ለሕዝብ ያስተላልፋሉ:: ባንድ ራት ግብዣ ላይ ችግር አመዳይ ያለበሳቸው የጎዳና ልጆች በጠረጴዛቸው ዙሪያ የጠመኔ ሐውልት መስለው ተደርድረው እንዲበሉ እስኪታዘዙ ድረስ ይጠብቃሉ፤ ምግቡ ቢቀርብም አቶ መርፊ ከካሜራ ጀርባ ቆሞ "Action" ብሎ እስኪያዛቸው መታገሥ አለባቸው:: በዚያ ምሽት የኢ.ቴቪ ጋዜጠኞች ቢጠበቁ ቢጠበቁ ብቅ ሳይሉ ቀሩ:: አቶ መርፊ፣ ጋዜጠኞች መቅረታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ወደ ጎዳና ልጆቹ ዞሮ፣ «ልጆች፣ ዛሬ ካሜራ ስለሌለ ነገ ትበላላችሁ!» ብሎ አሰናበታቸው::

ወደ ቀደመው ነገሬ ልመለስ:: አንድ ቀን ምዑዝ ካፌ ውስጥ ቁጭ ብሎ ሄለን ከክፍል እስክትወጣ ድረስ እየተቁነጠነጠ ይጠብቃታል:: ከጥቂት ቆይታ በኋላ መጥታ አጠገቡ ቁጭ አለች:: ምዑዝ ሊያወራት ሳይሆን ሊሸከማት የተዘጋጀ ይመስል ኮቱን አወለቀ፤ የሸሚዙን እጅጌም ሰበሰበ:: የሆነ ነገር ለመናገር አፉን እያሟሟቀ ሳለ ከኋላ ድምፃቸውን አጠብድለው በኅብረት የሚያወሩ ተስተናጋጆች ድምፁን ዋጡበት:: ዞሮ ገላመጣቸው፤ በዚያች ቅጽበት ባለሥልጣን ቢሆን ኖሮ ከሄለን ጋራ አውርቶ እስኪጨርስ ካፌውን ያሳሽገው ነበር:: ወዲያውኑ የወትሮ ጓደኛው አቶ ያን፣ ግዙፍ ሳምሶናይቱን አንጠልጥሎ ከገባ በኋላ አጠገባቸው ሲደርስ፣ «ጨዋታ ይዛችኋል መሰለኝ!» ብሎ አንድ ወንበር አልፎ ሊቀመጥ ሲቃጣ ሄለን፣ «ችግር የለም፤ አብረኸን ልትሆን ትችላለህ!» ብላ ወንበር ሳበችለት::

አቶ ያን አመስግኖ ሲቀመጥ ምዑዝ ፊቱን ሲያኮማትር ተመለከትሁት:: ወዲያው አቶ ያን ከሳምሶናይቱ ካሜራ አውጥቶ በወለሉ ላይ ያለውን ወፍራም ዝንብ ሁለት ጊዜ ፎቶ አነሣው::



ሄለን የእንግዳ ተቀባይ ፈገግታ አሳየችው:: ምዑዝ ግን ጣራ ጣራውን እያየ ሹርባውን ማከክ ጀመረ:: የጠብ ሰበብ እየፈለገ እንደ ሆነ ያስታውቃል:: ጀርመናዊው ካሜራውን ወደ ቦታው መልሶ በምትኩ ስኒ ካወጣ በኋላ ቡና እንዳመጣለት አዘዘኝ::

«ምንድን ነው እሱ?» አለ ምዑዝ፤

«ስኒ ነው!» አለ ጀርመኑ፤

«ስኒማ ስኒ ነው:: ለምን ያዝኸው? አበሻ በነካው ስኒ መጠጣት ቀፈፈህ?»

«እንደሱ አይደለም!» አለ ጀርመኑ፤

«ካልሆነ ታዲያ እንደ ጠንቋይ ስኒ ይዞ መዞርን ምን አመጣው?. . .እኛ የነካነው ነገር የሚደብራችሁ ከሆነ እንደ ስኒው ቡናውንም ለምን ባገራችሁ አታመርቱም? እ?. . .ለነገሩ ነጮች ስትባሉ ባጠቃላይ ልባችሁ አይገኝም:: እኛ በኬሚካል የተቀመመ ምግባችሁን ተቀብለን ስንበላ እንኳ አልደበረንም:: በዚህ ነገር ገና ትጠየቁበታላችሁ፤ እንዲያውም ልንገርህ? አዲሱ ትውልድ ቁመቱ ያጠረው የርዳታ ስንዴ መብላት ከጀመረ ወዲህ ነው::»

«አልገባህም!» አለ ጀርመኑ ልጁን የሚያባብል አባት ይመስል ምዑዝን በየዋህ ፈገግታ ቁልቁል እያዩው፤ ቀጠለናም፣ «በእውነቱ፣ ይህን ስኒ የያዝሁበት ምክንያት ሴት አያቴ . . .»

«. . .እኮ ሴት አያትህ አበሻ በነካው ስኒ እንዳትጠጣ ብለው ከለከሉህ? . . .እ?» አለና ምዑዝ ድፉፍ ፍለጋ ወደ ሄለን ዞረ::

«ከሴት አያቴ ያገኘሁት ስጦታ ስለሆነ አልፎ አልፎ እጠጣበታለሁ ማለቴ ነው፤» አለ ጀርመኑ::

አጭር ዝምታ. . .

ሄለን፣«ልክ አይደለህም፤» በሚል ዐይን ምዑዝን ገረመመችው:: ወዲያው ነገሩን ለማለባበስ የፈለገች ይመስል ከጀርመኑ ጋራ ሞቅ ያለ ወሬ ጀመረች:: ምዑዝ እንዳኮረፈ ሕፃን አገጩን ጠረጴዛው ላይ አስደግፎ ከሞባይሉ ጋራ መጫወት ጀመረ:: ጥቂት ደንበኞችን አስተናግጄ ካጠገባቸው ስመለስ ሄለን እንዲህ ስትል ሰማኋት::

«. . .በጀርመንኛ ካፌ፣ በእንግሊዝኛ ኮፊ ተብሎ መጠራቱ ቡና ከፋ ውስጥ እንደ ተገኘ በቂ መረጃ ነው::»

«ያ! ያ! ያ!» አለ ጀርመኑ ራሱን እየናጠ::

«በዚህ ሎጂክ መሠረት የቡና ማፍያ የተገኘው ከጣልያኑ ማፍያ ነው፤» አለ ምዑዝ::

«አንተን አስተያየት የጠየቀህ የለም፤» ሄለን መለሰች::

«ይሄ ብቻ አይደለም፤» ሲል ቀጠለ ምዑዝ፣ «. . .ሥርወ ቃሉ እንደሚጠቁመው ከሆነ ጅብ ለመጀመርያ ጊዜ የተገኘው ጅቡቲ ውስጥ ነው::»

ሄለን እና ጀርመኑ የተመካከሩ ይመስል ሰዓታቸውን እኩል አይተው በአንድ ጊዜ ብድግ አሉ:: አብረው ትንሽ ከተራመዱ በኋላ ጀርመኑ አንድ ነገር ሲናገር ሄለን ወደ ኋላ ቀርታ ከወገቧ ታጥፋ በጣም ሣቀች:: ምዑዝ ለማጥናት የፈለገ ይመስል ጥቂት



ወረቀቶችን አውጥቶ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠ፤ ግን ወዲያው በንዴት በረጅሙ ሲተነፍስ፣ ወረቀቶቹ በእስትንፋሱ ኀይል ተገፍተው ከበሉ:: ጥቂት ቆይቶ ወጥቶ ሲሄድ ከደብተሩ ጋራ ሚኖውን ደርቦ ይዞት እንደ ሄደ ገባኝ::

# ምዕራፍ 10

ሰው ሁሉ መለዮ ለባሽ ነው። መለዮውን እስከ ወዲያኛው አይቀይርም። ደብረ ማርቆስ ሳለሁ የወዛደሩ ፓርቲ ጽንፈኛ አባል በመሆን የምትታወቅ አንዲት ሴት ነበረች። ሴትዮይቱ፣ በየቤቱ እየዞረች፣ «ለሌኒን ሐውልት ማሠርያ የሚሆን መዋጮ አምጡ!» በማለት ድሆችን ታስመርር ነበር። የሕዝብ ሐዘን ከባድ ነውና እሷ በአባልነት የታቀፈችበት መንግሥት ከጥቂት ዓመታት ቆይታ በኋላ ተገረሰሰ። ይሄኔ ሴትዮይቱ በቀድሞው ሥራዋ ተጸጽታ ከወዛደሩ ፓርቲ ወጥታ ጽንፈኛ ሃይማኖተኛ ሆነች። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን በየቤቱ እየዞረች፣ «ለቤተ ክርስቲያን ማሠርያ የሚሆን መዋጮ አምጡ!» በማለት ድሆችን ማስመረሯን ቀጠለች።

በ«ቶማስ ወንጌል» እንደ ተጻፈው ከኢየሱስ በስተግራ በኩል የተሰቀለው ሌባ በመስቀል ላይ ሆኖ ከኢየሱስ ግራ ኪስ አምስት ብር ሰርቋል።

የሦስተኛ ክፍል አስተማሪያችን ጋሽ ዐወቀ ከመሞታቸው ጥቂት ቀናት አስቀድሞ ለጥቁር አንበሳ የጤና ኮሌጅ ተማሪዎች



ማስተማርያ እንዲሆን አስከሬናቸውን በኀምሳ ሺሕ ብር ሸጡት። ዛሬ የሕክምና ተማሪዎች የሰው ቅልጥም ከዬት ጀምሮ የት ላይ እንደሚያበቃ ለመረዳት ሲሹ የጋሽ ዐወቀን አስከሬን እንደ ብራና ይገልጣሉ። ጋሽ ዐወቀ ድሮ ቆመው፣ ዘንድሮ ተጋድመው ያስተምራሉ።

የምዑዝ መለዮ ሴት አውልነት ነው። ከሞተ በኋላ ዐመሉ ይቀየር ይሆን? አይመስለኝም። ከጥቂት መቶ ዓመታት በኋላ በመካነ መቃብሮቻችን ላይ የግንባታ ሥራ ቢካሄድ በምዑዝ መቃብር ላይ የሚገነባው አልቤርጎ ነው። በሄለን መቃብር ላይ ፋርማታ፣ በእኔ መቃብር ላይ ሆስፒታል ይገነባል።

ባለፈው ቤት አከራዬ ወይዘሮ ይርገዱ የወደቀ ቦርሳ አግኝተው፣ ቤቴን አንኳኩተው፣ «ይሄ ያንተ ነው?» አሉኝ። ከግቢያችን ተከራዮች ሁሉ ቦርሳው የእኔ እንደ ሆነ እንዴት እንደ ገመቱ ጠየቅኋቸው! «ምክንያቱም በውስጡ ነጭ ሸንኩርት እና ፓራሲታሞል ስላገኘሁበት ነው!» ብለው መለሱልኝ።

ምዑዝ አንድ ቀን፣ «ኮከብህ ምንድን ነው?» ብሎ ጠየቀኝ። «ካንሰር» እንደ ሆንሁ ነገርሁት። ካንሰርነቴን በልፋት እና በድካም ያገኘሁት ይመስል ባድናቆት ከጨበጠኝ በኋላ፣ «ከማደንቃቸው ታላላቅ ሰዎች መካከል አብዛኞቹ ካንሰር ናቸው። ዝርዝሩን ለማዬት ከፈለግህ ኢንተርኔት ገብተህ ተመልከት!» አለኝ። ይህ አነጋገር ወደ ፊት ታላቅ የመሆን ተስፋ ስላሳደረብኝ እኛ ሰፈር በሚገኘው ኢንተርኔት ካፌ ገብቼ ነገሩን ለማረጋገጥ ፈለግሁ። እንደሚታወቀው አዲስ አበባ የቡና እና ኢንተርኔት አገልግሎት የሚሰጡ ቤቶች አሉ! ግን ከኢንተርኔታቸው ቡናቸው ይፈጥናል። ይህ ተስፋ ሳያስቆርጠኝ በጎግል ሣጥን ውስጥ «Cancer» እና

«Famous men» የሚሉ ቃላት ከትቼ ዝርዝሩን እንዲያቀርቡልኝ ጠየቅሁት:: ኮምፒዩተሩ ግማሽ ሰዓት ያህል ሲማስን ከቆየ በኋላ፣ "Do you mean famous men who died of cancer;" ብሎ ጠየቀኝ:: አከራዬ ወይዘሮ ይርገዱና ኮምፒዩተሩ ተባብረው የእኔ መለዮ የሕመምተኛ እንጂ የዝነኛ እንዳልሆነ ነገሩኝ::

* * *

ሄለን ለሁለት ቀናት ያህል ወደ መማርያ ክፍላችንም ሆነ ወደ ካፌው አልመጣችም:: ምዑዝ ወደ ክፍል ሳይገባ በቤተ መጻሕፍት እና ካፌ ውስጥ ብቻ ጊዜውን ማሳለፍ ጀመረ:: አንድ ቀን አለወትሮው የጡት ማስያዣ የሚያህል ትልቅ ጥቁር መነጽር አድርጎ ከገባ በኋላ ጥግ ይዞ ተቀምጦ፣ «ወንደላጤነት እንዴት እንደ መረረኝ ልነግርህ አልችልም!» አለኝ አጠገቡ ስደርስ፣ «ወንድ ብቻውን ምንም መሥራት አይችልም:: ማታ ያወለቅሁትን ፓንት ጠዋት ለማግኘት ቢያንስ ለግማሽ ሰዓት ያህል መፈለግ አለብኝ:: በዚያ ሰፊ ክፍል ውስጥ ፓንት ከመፈለግ፣ አዲስ አበባ ውስጥ ሥራ መፈለግ ይቀላል:: Well. . .የፓንት መጥፋት የማያስቸግርህ ከሆነ ወይ በጣም ጥንቁቅ ሰው ነህ፣ ወይ ፓንት የለህም::»

ጥቂት አስተናግጄ ወደ ተቀመጠበት ስመለስ አቀርቅሮ ይጽፋል:: ምን እንደሚጽፍ ስጠይቀው፣ «ለሄለን የፍቅር ደብዳቤ ልልክላት ነው!» አለኝ::

«የሞባይል ሚሴጅ እና ኢ - ሜይል ባለበት ዘመን በእጅ የተጻፈ የፍቅር ደብዳቤ መጻፍ ትንሽ ኋላ ቀርነት አይሆንም?» አልሁት::

«አንተ ስለ ሴቶች ምን ታውቃለህ?» አለኝ እንደ ልማዱ



በንቀት ፈገግ ብሎ ሽቅብ እያየኝ::

«. . .ዐየህ፣ የተተየበ የፍቅር ደብዳቤ ለታይፒስቷ እንጂ ለተፈቃሪዋ አይጠቅምም:: የተተየበ የፍቅር ደብዳቤ እና በእጅ የተጻፈ የፍቅር ደብዳቤ ልዩነታቸው ያፅምና የሙሉ አካል ያህል ነው:: ከዐፅም ክምር መሀል መቶ አለቃ እገሌን ከዶክተር እገሌ መለየት ከባድ ነው - ሟቾች ከነዩኒፎርማቸው ካልተቀበሩ በቀር:: በእጅ የተጻፈ የፍቅር ደብዳቤ ያፍቃሪው መልእክት ብቻ ሳይሆን ሥጋ እና መንፈስ ይሠፍርበታል:: ዐየህ፣ በሥጋ እና በነፍስ ስገለጥ ምዑዝ ነኝ፤ ፊደል እና ነጥብ ለብሼ ስገለጥ ደግሞ የፍቅር ደብዳቤ ነኝ::

«ሌላው ምንድን ነው፤ በእጅ የተጻፈ የፍቅር ደብዳቤ ለሴቶች የአእምሮ ጨዋታ ይሰጣቸዋል:: እኔ ደብዳቤ ስጽፍ ቁልጭ አድርጌ አልጽፍም:: ጥቂት ዐረፍተ ነገሮችን ሆን ብዬ እሰርዛለሁ፤ እደልዛለሁ:: ሄለን የተደለዙ ዐረፍተ ነገሮችን ለማንበብ ከመኝታ የተነሳ ሁለት የራስጌ መብራት እና አንድ ትልቅ ጧፍ አስተባብራ እንደምትጠቀም ዐውቃለሁ:: በመጀመርያ ከልቡ የወጣው ቃል ምንድን ነው? በኋላ ለምን ሰረዘው? በሁለቱ ሐሳቦች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? እያለች መመራመሯ አይቀርም:: አንዲት ሴት ከተሰረዘ ዐረፍተ ነገር ጀርባ ያለውን ሐሳብ ለማወቅ የምታደርገው ጥረት በጎረቤት መታጠቢያ ቤት ውስጥ ወንድን አጮልቆ እንደ ማየት ያለ ደስታ ይሰጣታል::

«ብቻ ምን ልበልህ? በእጅ የተጻፈ ደብዳቤ ብዙ ምትሀት አለው:: አባቶች በፊደል ላይ ድግምት የሚሠሩት ይህ ምስጢር ስለ ተገለጠላቸው ይመስለኛል:: እስኪ ሻይ አምጣልኝ::»

ወደ ደብዳቤው አቀረቀረ፤

ደብዳቤው በሄለን የክፍል ጓደኛ በኩል ተላከ:: በማግሥቱ ሄለን ራሷ ወደ ካፌው መጥታ፣ «ለምዑዝ ስጠው፤» ብላ ገርበብ ያለ ፖስታ አቀበለችኝና ወደ ክፍሏ እየተጣደፈች ገባች::

ምዑዝ ከሰዓት በኋላ መጣና ፖስታውን በችኮላ ከፍቶ ተመለከተው:: ራሱ ከላከው ወረቀት በቀር ሌላ ነገር አልነበረም:: የፖስታውን አፍ ዘቅዝቆ ዘጠኝ ጊዜ አራገፈው፤ ምንም ጠብ የሚል ነገር የለም:: በመጨረሻም የራሱን ደብዳቤ ለጥቂት ደቂቃ ሲያጠና ከቆየ በኋላ መልሶ አቀበለኝ::

«በወረቀቱ ላይ ምን አዲስ ነገር ዐየህ?» አለኝ በግራ ዐይኑ እየጠቀሰኝ:: «ምንም» በሚል ዐይነት ትከሻዬን ሰበቅሁ::

«በወረቀቱ ጠርዝ ላይ ጥቂት ነጠብጣቦች አይታዩህም?;»

ወረቀቱን እንደገና ስመለከተው እውነትም አተር የሚያካክሉ ጥቂት ነጠብጣቦች ወድቀዋል::

«እንባዋ ነው!» አለ ምዑዝ በጣም ስሜታዊ በሆነ ድምፅ፤ «እያለቀሰች ነው ያነበበችው!» ወረቀቱን ቀስ ብዬ ወደ አፍንጫዬ አስጠጋሁት፤ ጠብታው የምስር ወጥ እንደ ሆነ ለማወቅ ጊዜ አልፈጀብኝም::

«እንደኔ እንደኔ ራቷን እየበላች ነው ያነበበችው፤» አልሁት::

«እዎ፣ ራቷን እየበላች፣ እያለቀሰች ነው ያነበበችው፤» አለኝ ምዑዝ ፍዝዝ ብሎ አሻግሮ እያዬ:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቀጠለ፣ «እስኪ ንገረኝ፣ እጮኛዋን እንዴት ብታፈቅረው ነው ሦስት ዓመት ሙሉ ከሌላ ወንድ ጋራ ሳትወጣ የምትጠብቀው? ስሙ ማን ነበር? በጣም ስለ ጠላሁት ዐሥር ጊዜ ነግራኝ ዐሥር



ጊዜ ረስቼዋለሁ:: አዎ፣ ገረመው ነው፤ ምን ዐይነት አስገራሚ ሰው ቢሆን ነው እንዲህ ያለ ጽናት ያላት ሴት የጠበሰው? እንዳልኩህ፣ እሱ ጀርመን ከገባ ጊዜ አንሥቶ ሄለን ወሲብ አልፈጸመችም:: አንድ ምሽት ላይ ብቻ «ፎን ሴክስ» ለማድረግ ተስማሙ:: እያደረጉ፣ እያደረጉ እያለ እርሱ ሊጨርስ ትንሽ ስከንድ ሲቀረው ሞባይሉ ቀድሞ ካርድ ጨረሰ:: ይህን የነገረችኝ ራሷ ሄለን ናት(አላመንሁትም)::

«ሰሞኑን ጥሩ እየተሳካልኝ ነበር፤ አስጠናኋት፤ ብዙ ነገር ገለጥሁላት፣ እሷም እየወደደችኝ መጣች:: ፊልም እንይ አለችኝ:: የቋንቋ ማስተማርያ ፊልሞች የሚታዩበት ክፍል ገብተን *«ካስት ኧወይ»* የተባለውን ፊልም አሳየችኝ:: ከዚህ በፊት ባዬውም ለእሷ ስል ደግሜ ዐየሁት:: ከዚያ ስንወጣ በቲ-ሸርቷ ዘልቄ ወገቧን ዳበስሁት:: ዝም አለችኝ:: ከዚህ በፊት ከብዙ ሴቶች ጋራ ብዙ ነገር አድርጌያለሁ:: የሄለንን ወገብ ዝም ብሎ መንካት ግን ከሁሉ የበለጠ ተኣምር ሆነብኝ:: ደስታዬን እንዳላረክሰው ፊርቼ ቤቴ እስክገባ ድረስ ማንንም አልጨበጥሁም::

«በማግሥቱ የሄለን እጮኛ በኒዎ ናዚዎች ተደብድቦ ሆስፒታል ገባ:: ይሞታል ብዬ ጠብቄ ነበር:: አውሮፓ ውስጥ ሞት ቀርቷል መሰለኝ አልሞተም::

«ብአጠቃላይ እኛ ኢትዮጵያውያን የድመት ነፍስ ነው ያለን፤ በቀላሉ አንሞትም አልሁት፤

«እንዴት?» አለኝ፤

«ለምሳሌ:- እዚህ ጎረቤታችን በቅርቡ በፖሊስ የታሸገ ምግብ ቤት አለ:: ምግብ ቤቱ በርበሬ ነው ቁያለ የሽክላ ወጥ ለደንበኞቹ

ያቀርብ ነበር፡፡ ብዙ ኢትዮጵያውያን ሸክላ በልተው ማሰሮ ቢጸዳዱም የሞተ ግን አልነበረም፡፡

ምዑዝ ቸል ብሎኝ ቀጠለ፤

«. . .ሄለን የእጮኛዋን መደብደብ ስትሰማ ከመጠን በላይ ወደደችው፤ ከመጠን በላይ ናፈቃት፡፡ ምን አደረጋቸው? ለምን ይደበድቡታል? ብላ ትከሻዬ ላይ ፊቷን አስደግፋ አለቀሰች፡፡ ተናድጄ ስለ ነበር፣ ከነጭ ሴቶች ጋራ ሲዳራ አይተውት ካልሆነ በቀር አይደበድቡትም ነበር፤ አልኳት፡፡»

«እንዴት እንዲህ ትላለህ?» ብዬ ሙሁኩበት፡፡

«ልክ ነኝ፣. . .ነጭ ወጣቶች ከጥቁር ወጣቶች ጋራ ያላቸው ቅራኔ የሚመነጨው ከርእዮተ ዓለም ልዩነት አይደለም፤ ከPenis *envy* ነው፡፡ እንደኔ እንደኔ፣ አንድ ጀርመናዊ ፖሊስ ጥቁርን ሲደበድብ የተገኘን ነጭ ወጣት በቁጥጥር ሥር ካዋለ በኋላ በመጀመርያ ሊመረምር የሚገባው የብልቱን መጠን ነው እንጂ አስተዳደጉን ወይም አመለካከቱን አይደለም! ያም ሆኖ ወጣቱ ‹የሙርጤ መጠን ባሳደረብኝ ዝቅተኝነት ተነሣስቼ ጥቁሩን ወጣት አጠቃሁት› አይልም፡፡ ጠቡን ወደ ፖለቲካ ከፍ ያደርገዋል፡፡ ነገሩን ከፓንት ወደ ባንዲራ ያሻግረዋል፡፡ ይህን ስነግራት ሄለን፣ አሁን ደግሜ ልናገራቸው የማልፈልጋቸውን ስድቦች አወረደችብኝና ጥላኝ ሄደች፡፡»

«ታዲያ አሁን ምን ይሻላል?» አልሁት፡፡

«ሄለንን መርሳት ይሻላል፡፡ በቃ ከዚህ ደቂቃ ጀምሮ ስሟን አላነሣም፡፡ አንተም ስሟን እንዳታነሣብኝ፡፡ እንዲያውም ስሟን



ያነሣ ሰው ኀምሳ ብር ይቀጣል፡፡ ትስማማለህ;»

«እግኝቼ ነው፤»

ተጨባበጥን፡፡

ምዑዝ ሄለንን ካፉ ማውጣት እንደሚከብደው ስለማውቅ በውርርዱ ለቤት ኪራይ የሚሆን ጥሪት እንደምሰበስብ ገባኝ፡፡ ጥቂት ደንበኞችን አስተናግጄ ወደ ምዑዝ ተመልሼ መጣሁና «ከዚህ በኋላ አትገናኙም ማለት ነው?» ስል ጠየቅሁት፡፡

«ከማን ጋራ?» አለኝ፡፡

«ከሄለን ጋራ፤»

«ኀምሳ ብር አለብህ!» አለኝ፡፡ ድንጋጤዬ ሲያልፍልኝ የባጥ የቆጡን አውርቼ ካዘናጋሁት በኋላ «ግን ከልብህ ነው የምትወዳት;» አልሁት፡፡

«ማንን ነው ከልብ የምወዳት;» አለኝ፡፡

«ልጅቷን ነዋ!» አልሁት ስሟን እንደ ፈንጂ ወረዳ በጥንቃቄ እያለፍሁት፡፡

«ልጅቷ ማን ናት;» አለኝ፡፡

«ይቺ አንኳ ጎረድረድ ያለች፣ በጣም ደስ የሚል አጭር ፀጉር ያላት፣ ቁጭ ስትል የዳሌዋ ጥቂት ክፍል ከጅንስዋ ብቅ ብሎ የሚታይ፣ የሚያምር ቀይ ስካርፍ የምትጠመጥም፣ ብዙ ጊዜ ብቻዋን ገለል ብላ መቀመጥ የምትወድ. . .!» አልሁት፡፡

«አ!. . . እሷንማ የምሬን ነበር የምወዳት፤» አለኝ፡፡

የውሻ ልጅ! ጎምላ ብሬን ለማስመለስ ያደረግሁት ሙከራ እንዳልተሳካልኝ ሳውቅ ብሩን ከቦርሳዬ አውጥቼ ዘረጋሁለት:: ይምረኛል ብዬ ተስፋ አድርጌ ነበር::

«በነገራችን ላይ በተገናኘን ቁጥር ስላንተ አውርታ አትጠግብም!» አለኝ ምዑዝ እጁን ወደ ብሬ እየዘረጋ::

«ማ? ሄለን?» አልሁት ሳላስበው::

«ብሩን መቶ አድርገው!» ሲለኝ ሰማሁት::

መቶ ብሬን በተበላሁ በሳምንቱ ጆሮዬን ታመምሁ:: ጉዳዩን ለምዑዝ ባማከረው፣ «በልጅነትህ አባትህ ጆሮ ግንድህን በጥፊ መቶህ ያውቃል?» ብሎ ጠየቀኝ:: ይህን ባለኝ በአምስት ወሩ አንድ ዶክተር በዱቤ ጆሮዬን ቀዶ ሕክምና አደረገልኝ:: ጆሮዬን ቀዶ ሕክምና ያደረገው ዶክተር በጣም ደግ ሰው ስለነበር፣ «ምራቂ ነው!» ብሎ እግረ መንገዱን ጆርባዬ ላይ የነበረውን ዕጢ አወጣልኝ:: ሕክምናውን ካጠናቀቅሁ በኋላ ወደ አገር ቤት ሄድሁ:: ወዲያው፣ የከተማችን ከንቲባ ጆሮዬ ላይ የነበረውን የቢላ ቅርጽ ያለው ጠባሳ ተመልክተው ከሰሜን ዘመቻ ቆስዬ እንደ መጣሁ ስላመኑ በከተማው መውጫ ላይ ያለችው ወንዝ በስሜ እንድትሰየም ወሰኑ::

ወንዟ በስሜ መጠራት ከጀመረች ከጥቂት ሳምንት በኋላ ዝናም ዘነመ! ወንዚቱም ሞልታ ከዳር ሆኖ ሲታጠብ የነበረን ሽማግሌ ከግንድ ጋራ ደባልቃ ወሰደችው:: የሟቹ ሽማግሌ የበኩር ልጅ በጣም ጠበኛ ነው:: እንዲያውም ልጁ በጠብ፣ አባትዬው በመታጠብ ይታወቃሉ:: በዚህ ላይ ልጅዬው ከወዳደቁ ብረቶች የተሠራ ምንሽር አለው:: ምንሽሩ ሲተኮስ ከጥይቱ ጋራ አብሮ



አፈ ሙዙ ይበራል:: ስለዚህ ባለምንሽሩ በዝናሩ ውስጥ ጥይት ብቻ ሳይሆን፣ «ተጠባባቂ አፈ ሙዞች ይዞ ይዞራል!» ይባላል:: እና ይሄ ባለምንሽር ጎረምሳ ያባቱ ቀብር ላይ ባባቱ አስከሬን ፊት እንደ ባለዛር እየተንጎራደደ፣

*«ተለዋዋጭ ቡዳ መጣ ተቀይሮ፣*

*ውዱ አባታችንን በላው በወንዝ አድሮ፣*

*እኔ እሱን አያርገኝ ጉድ ፈላ ዘንድሮ!»*

በማለት ሙሾ ለበስ ፉከራ ካቀረበ በኋላ ከለቀስተኞች መካከል መርጦ ለሃያ ደቂቃ ያህል አተኩሮ ተመለከተኝ:: እንዲህ በተመለከተኝ ማግሥት ወደ አዲስ አበባ ተሳፈርሁ:: በስሜ የተጠራችው ወንዝ ካልደረቀች በቀር ወደ አገሬ እንደማልመለስ ገባኝ::

እነሆ በቤትሆቨን ካፌ ውስጥ ራሴን አገኘሁት:: ከድሮ ደንበኞች መካከል አብዛኞቹ በቦታቸው አልነበሩም:: ምዑዝ ያዘወትረው በነበረው ቦታ ላይ አንድ አብሻቂ ተመጋቢ ቁጭ ብሎ የምላስ ጥብስ ይጎስጉሳል:: ባጠገቡ ሳልፍ ጎተተኝና፣ «ስማ ምላሱን ከመጥበሳችሁ በፊት ማጠብ ነበረባችሁ:: በሬው ከመታረዱ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የበላው ሰርዶ ምላሱ ላይ ተጣብቆ አግኝቻለሁ!» አለኝ:: ይህን ሲለኝ በጣም ተናድጄ ከፊት ለፊቱ የተቀመጠውን የአምቦ ውኃ ጠርሙስ ብድግ አድርጌ . . .ፍሪጅ ውስጥ አስቀምጥሁት::

ከጥቂት ቀናት በኋላ ምዑዝ ወደ ካፌው መጣ:: «አይገርምህም?›› አለኝ ከጥቂት ጭውውት በኋላ፣ «ከሄለን ጋራ

ፍቅር ከጀመርሁ አንድ ዓመት ሞላኝ። ዛሬ ለምን እንደ መጣሁ እስኪ ገምት? ለመጀመርያ ጊዜ በተገናኘንበት ካፌ አንደኛ ዓመት የፍቅር በዓላችንን ለማክበር ተቀጣጥረናል. . .አሁን ሳስበው፣ ሄለንን ከማግኘቴ በፊት የነበረው ሕይወቴ ሕይወት አይደለም። በሃይማኖት ዘይቤ ግለጸው ካልኸኝ፣ ያለፈው ሕይወቴ መካነ ንስሐ ወይም ጣልያኖች እንደሚሉት *Purgatorio* ነው። በሳይንስ ዘይቤ ግለጸው ካልኸኝ ያለፈው ሕይወቴ ቤተ ሙከራ ነው። ያለዘይቤ ግለጸው ካልከኝ ያለፈ ሕይወቴ - ያለፈ ሕይወት ነው»

«ከሄለን ጋራ ከጀመርህ ወዲህ ሌላ ሴት . . .»

ምዑዝ አላስጨረሰኝም።

«ሌላ ሴት? ምነው አንተ! አብደሃል እንዴ? ከዚህ በኋላ እንኳን በውኔ በሕልሜ ሌላ ሴት ላለማዬት ወስኛለሁ። እንዲያውም በሕልምህ ሴት እንዳታይ የሚያግድ ትራስ ዲማ ጊዮርጊስ እንደሚገኝ ሰምቻለሁ። ቤተሰብህን ለመጠየቅ ስትሄድ ታመጣልኛለህ።»

አከታትሎም፣ ጥንት የሚያውቁት ሴቶች ደውለው ሄለንን እንዳይረብሽዋት በማሰብ ሞባይል መያዝ እንዳቆመ ነገረኝ። ከዚያ እያፏጨ ከኪሱ ባለ ብዙ ገበር ቦርሳ አውጥቶ ብር መሳብ ጀመረ። የቦርሳው ልባስ በሄለን ልዩ ልዩ ፎቶዎች እንደ ተገጠገጠ ተመለከትሁ። ሄለን ቆማ፣ ሄለን ተቀምጣ፣ ሄለን ሥቃ፣ ሄለን ተከዛ፤. . .ይሄ ቦርሳ ሊባል አይችልም። ምዑዝ በፎቶ አልበም ውስጥ ገንዘብ ይዞ መዞር ጀምሯል።

ዐሥር ብር አውጥቶ እያቀበለኝ፣ «ሁለት ሻማዎችን ልታስገዛልኝ ትችላለህ;» ሲል ጠየቀኝ። «የምታከብሩት አንደኛ



ዓመት የፍቅር በዓላችሁን መሰለኝ። ሁለተኛው ሻማ ምን ይሠራል?»

«ማታ እቤት ስገባ ምን አበራለሁ? . . .»

ከዚያ ወንበር ፈልጎ ቁጭ አለ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ምዑዝ ከለበሰው ካፖርት ኪስ ውስጥ *«ካፖርቱ»* የተባለ መጽሐፍ አውጥቶ ማንበብ ጀመረ። ሻማውን ገዝቼ ስመጣ ሄለን እና ምዑዝ እንደ ርግብ አፍ ለአፍ ገጥመው ሲያወሩ አገኘኋቸው። ወዲያው ከውጭ የዝናም ሹክሹክታ ተሰማ። ክፍሉ ቀዘቀዘ። ፍቅረኛ ያላቸው ፍቅረኛውን አቀፉ፤ ፍቅረኛ የሌላቸው ኮታቸውን ቆለፉ። ምዑዝ ካፖርቱን አውልቆ ሄለንን አለበሳት። በመስኮቱ በኩል አሻግሬ መመልከት ጀመርሁ። የዝናም ነጠብጣቦች ከመሬት ጋራ እየተጋጩ እዚያው ፈክቶ እዚያው የሚከስም የውኃ አበባ ያመርቱ ጀመር። ዝናሙ እንደ ማባራት ሲል፣ የቤትሆቨን ካፌ ተረኛ አስተናጋጅ አባተ ስለ ተተካልኝ የዚህን ብርሃናዊ ፍቅር መጨረሻ ሳላይ ለመሄድ ተገደድሁ።

በማግሥቱ ምዑዝ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ካፌው መጥቶ ተገናኘን። ከትከሻው ትንሽ ጎብጧል። ሹሩባውን ተቆርጦታል። እንደ ሳምሶን ኀይሉን ከፀጉሩ ጋራ ያራገፈ መሰለኝ።

«ችግር አለ;» አልሁት።

«ትላንት ምሽት ከሄለን ጋራ አብረን አላየኸንም? አንደኛ ዓመት የፍቅር በዓላችንን አክብረን እኔ ቤት ሄደን ለማደር ነበር ሐሳባችን። እንዳየኸው ነገሩ በጣም በጥሩ ሁኔታ እየሄደ እያለ፣ You know የሆነ ነገር ዘባረቅሁ። ምኣድን ነበር ያልሁት? ዛሬ አንቺ ባትደርሽልኝ ኖሮ ብርድ ይገድለኝ ነበር አልሁ። ድንገት

ፊቷ ተለዋወጠ:: ማውራት እና ማዳመጥ አቆመች:: ቤተሰቦቼ ስለሚጠብቁኝ መሄድ አለብኝ አለች:: ያስቀየማትን ነገር ለማወቅ ሞከርሁ:: ዛሬ አንቺ ባትደርሽልኝ ኖሮ ብርድ ይገድለኝ ነበር ማለቴ እንዳስከፋት ጠረጠርሁ:: አባባሉ፣ ሄለንን ከፍቅረኛነት ወደ ብርድ ልብስነት የሚያወርድ አባባል ነው ወይም እርሷ እንዲህ ተርጉማዋለች:: ምን ታደርገዋለህ? ሴቶች ፍቅር ሲይዛቸው ወንዱ የሚናገረውን ተራ ነገር ሳይቀር የአንድምታ ትርጉም ይፈልጉበታል:: ለማስተባበል ሞከርሁ፤ አልተሳካም:: እሷም ለመሄድ ስትነሣ እኔ እፍረት እና ሐሳቧን ትቀይራለች የሚል ስሜት ተባብረው ወንበሬን ላይ ሰፉኝ:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዙሪያ ገባዬን ሳይ ካፌው ባዶ እየሆነ ነው:: እኔ እና ከፊት ለፊቴ ብቻዋን የተቀመጠች ሴትዮ ቀረን:: ሒሳብ ከፍዬ ለመውጣት እጄን ብሰድ ኪሴን አጣሁት:: ሄለን ቦርሳዬን ከካፖርቱ ጋራ ይዛው ሄዳለች:: ምን ልሁን? አስተናጋጆች የሆነ ነገር እንደ ጠፋኝ እንዲረዱልኝ ብቻ የሸሚዜን ኪስ መበርበር ጀመርሁ::

በዚህ መሀል አዲሱ አስተናጋጅ ወደ ጆሮዬ አጎንብሶ፣ ‹ሒሳብ ተከፍሏል› አለኝ፤ ማን እንደ ከፈለልኝ ገምት:: ከፊት ለፊት ቁጭ ብላ መርበትበቴን ስታይ የነበረች ሴትዮ፤. . .ተነሥቼ አጠገቧ ተቀመጥሁና ወግ ጀመርን:: ከዚያ ከካፌው ወጥተን ሌላ ቦታ ገብተን ቢራ ጠጣን:: ወንድ ቀጥሯት እንደ ቀረ ከሴትዮዋ አኳኋን ተረዳሁ:: ወዲያው አብሬያት ለማደር ፈለግሁ:: ለምን? ሰውነቴ ከሄለን ጋራ ለማደር አኮብኩቦ ነበር:: ያኮበኮበ ሁሉ መብረር አለበት:: ሴትዮዋም ቀጥሯት የቀረውን ሰውዬ መበቀል ትፈልጋለች:: ይሄ የቀጠራት ሰውዬ የቀረው የመኪና አደጋ ገጥሞት ይሆናል:: ግን በዕድሜ የገፉች ሴት በዚህ ሰዓት እንዲህ ዐይነት ምክንያት አይገለጥላትም:: ከእርሷ የተሻለ ሴት አግኝቶ እንደ ቀረ ነው የሚታያት:: ስለዚህ ገላዋ እንዳላስፈ.በት ለማረጋገጥ



ከእኔ ጋራ አድራ ማሳየት አለባት፤ አብረን አደርን::

«ነገሩን ያደረግነው ተጠንቅቀን ነው:: ግን ሳልመረመር ከሄለን ጋራ መተኛት እንደሌለብኝ ተሰማኝ:: ስለምወዳት ላጣት አልፈልግም:: ስለምወዳት፣ ውጤቱን ሳላውቅ አብሬያት አልተኛ ም:: ለምርመራ ደግሞ ደግሞ ሦስት ወር መጠበቅ አለብኝ:: እንግዲህ ጥያቄው፣ ሦስት ወር ሙሉ የት ልጥፋ? ለሦስት ወር ለመስክ ሥራ ወጣሁ እንዳልል ሥራ የለኝም:: ምን ወንጀል ብሠራ ነው ሦስት ወር ታስሬ የምፈታው? ብዬ ጠየቅሁት:: ‹ሰው ብትደበድብ ነው፤› አለኝ:: እዚያ ጥግ ላይ ከተቀመጡት ሰዎች አነስ ያለውን መርጬ በቴስታ ልበለው? አብሮት የተቀመጠው ሰውዬ ምስክር ሊሆን ይችላል ብዬኮ ነው::»

«ሌላም አማራጭ አለህ፣» አልሁት፤

«ምን አማራጭ?»

«አንደኛውን ሰውዬ በቴስታ ስትለው፣ ሌላው ጉያህ ላይ ይረግጥህና ሦስት ወር ሙሉ ሆስፒታል ትተኛለኽ፤» ዝም አለ:: ዝም አልሁ:: የለበሰው ሸሚዝ ከፉኛ መጨማደዱን ለመጀመርያ ጊዜ አስተዋልሁ::

በደከመ ድምፅ፣ «እማማ ገንዘብ መላክ ካቆመች ሁለት ወር ሆናት፤» አለ፤

«ሻይ ላሠራልህ;»

«ሻዩን ትተህ ላጭር ጊዜ ስማኝ:: የሄለንን ዐይን የማዬው እንዴት ነው? ለሦስት ወር ያህል ወደ ሰማዩ ማረግ ብችል እንዴት ጥሩ ነበር:: ድሮ ነቢያት እና ጻድቃን ወደ ሰባተኛ ሰማይ ይወጡ ነበር:: ግን በዚህ ዘመን ወደ ሰማይ መውጣት

ለምን ቀረ?;»

«እንጃ . . .የሆነ ጊዜ ላይ ሊፍቱ ሳይበላሽ አልቀረም፤» አልሁት::

ምዑዝ መሣቅ ጀመረ:: ሣቁ ሲያልቅ ታሪኩም አብሮ አለቀ::



# ምዕራፍ 11

የጊዜ ነገር ይገርመኛል:: አዲስ አበባ ውስጥ ጊዜ በሣር በቅጠሉ ውስጥ አድፍጧል:: በግድግዳ ላይ፣ በቴሌቭዥን ላይ፣ በሞባይሌ ላይ ሳይቀር ሰዓት አለ:: በመዲናይቱ የስልክ ግንኙነት ከተዳከመ ወዲህ ሞባይሌ በሲም ካርድ የሚሠራ የኪስ ሰዓት ሆኗል:: ልጅ እያለሁ እንዲህ ያለ ዕድል አልነበረም:: ያኔ፣ ለመደባደብ ካልሆነ በቀር ሰዓት ልይ ብሎ የሸሚዙን እጅጌ የሚሰበስብ ሰው በመንደራችን አልነበረም:: ትዝ ይለኛል፤ ከሰኞ እስከ ዓርብ ማለዳ፣ «የገቢ ምንጫችን፣ ቡና ቡና» ብሎ የሚጀምር ኅብረ ዝማሬ ከሬዲዮኑ ሆድ ሲወጣ፣ እማዬም ተማጅቷ ትወጣና፣ «ተነሥ፣ የትምህርት ሰዓት ደርሷል፤» በማለት ከዕንቅልፌ ትቀሰቅሰኝ ነበር:: ዘወትር ሰባት ሰዓት ላይ እኛ ቤት ቡና ይፈላል:: እናም፣ የቡና ወቀጣ ድምፅ ከእኛ ቤት ሲወጣ መንደርተኞች ከቀኑ ሰባት ሰዓት እንደ ሆነ ያውቃሉ:: የእኛ ቤት የቡና ሙቀጫ በአደባባይ ላይ እንደ ተተከለ የሕዝብ ሰዓት ነው:: በሕይወቴ ለመጀመርያ ጊዜ ቡና የተጫወተው ሚና ጊዜን መጠቆም ነው::

ስለ ጊዜ እና ቡና~ይህንና የመሰለውን በሐሳቤ ሳወጣና ሳወርድ፣ «ቡና እንደ ወረደ አምጣልኝ፤» የሚል የአንድ

ተስተናጋጅ ትእዛዝ አናጠበኝ።

እነሆ ዛሬም፣ በቤትሆቨን ካፌ ውስጥ ከቡና ማለቢያ ማሽኑ ፊት ለፊት ቆሜያለሁ። የካፌው የፊተኛው የመስተዋት በር ሲከፈት፣ መክሊት እና ፍቅረኛዋ አቶ ያን ተከታትለው ገቡ። አቶ ያን ለመክሊት ይዞላት የመጣውን የተጠቀለለ ሹራብ እና በዳመና ጊዜ ራሱን በራሱ የሚዘረጋ አውቶማቲክ ጃንጥላ አቀብሏት፣ ጉንጯን ስሞ ከተሰናበታት በኋላ ደጅ ላይ ወዳቆመው መኪና ተመለሰ። መክሊት የተሰጣትን ስጦታ አንጠልጥላ፣ በብዙ ፈገግታ እና ልበ ሙሉነት ካፌውን መሀል ለመሀል ሠንጥቃ ወደ መልበሻ ክፍል ገብታ ለጊዜው ከተሰወረች በኋላ ዩኒፎርሟን ለብሳ ተመለሰች።

የኋለኛው ክፍል በር ሲጢጥ ብሎ ሲከፈት ማቂጥ የተሳናቸው ሦስት የጀርመን ሴቶች ተከታትለው ገቡ። በነገራችን ላይ፣ «ማቂጥ የተሳናቸው» የሚለውን ሐረግ ከምዑዝ የተዋስሁት ሲሆን? «ቂጥ ማውጣት የተሳናቸው» የሚል ትርጉም አዝሏል። የማዝለ ነገር ከተነሣ ተከታትለው ከገቡት የጀርመን ሴቶች አንደኛ ዋ በጉዲፈቻ የተገኘ ጥቁር ሕፃን አዝላ ነበር። ሕፃኑ በፊት በኩል በመታዘሉ በጉዲፈቻ ከመወሰዱ በፊት ከሚያውቀው አስተዛዘል ስለተለየበት በፊቱ ላይ ግራ መጋባት ይታያል። ከኢትዮጵያውያን በተለየ ፈረንጆች ሕፃናትን እንደ ካንጋሮ በፊት በኩል ያዝላሉ።

አንድ ቀን ምዑዝ፣ «የአስተዛዘል አቅጣጫ፣ ወላጆች ለልጆቻቸው ያላቸውን አመለካከት ይገልጻል፤» ብሎ ነበር። «. . .ሕፃኑን በፊት በኩል ስታዝለው፣ ሕፃኑ አንድም፣ የመጭው ዘመን ሰው መሆኑን እየነገርኸው ነው። አንድም ከእኔ ይልቅ ለአንተ ቅድሚያ እሰጥሃለሁ ማለት ነው. . .።» በመሀል መክሊት



አቋርጣው፣ «እንዳንተ አተረጓጎም ከሆነ ኢትዮጵያውያን እናቶች ልጆቻቸውን በጀርባቸው የሚያዝሉት፣ ከልጆቻቸው ራሳቸውን ስለሚያስቀድሙ ነው።» አለችው።

«አልወጣኝም!» አለ ምዑዝ፤ «ኢትዮጵያውያን እናቶች ልጆቻቸውን ከኋላ በኩል በጀርባቸው የሚያዝሉት፣ ከፊት ለመፍጨት እንዲያመቻቸው ነው።»

ወደ ካፌው ክፍል ልመለስ - ማቂጥ የተሳናቸው ጀርመኖች ከተቀመጡባቸው ሁለት ወንበሮች ቀጥሎ የተቀመጠ፣ ብልጭልጭ የለበሰ ተስተናጋጅ በክፍሉ ውስጥ ላሉ ሁሉ በሚሰማ ድምፅ ጮህ ብሎ፡- «እባካችሁ አስተናጋጆች፣ ቴሌቪዥኖቹን የኢትዮጵያ ጣቢያ ላይ አድርጉልኝ፤ ያገሬን ቴሌቪዥን ካየሁ ዐሥር ዓመት ሆነኝ!» በማለት ተናገረ።

የዚህ ተስተናጋጅ ዓላማ ዐሥር ዓመት ሙሉ ውጭ አገር ኖሮ መምጣቱን ከኋላው ተቀምጠው በርገር ለሚገሩርሱ ሴቶች ማሳወቅ ነው። ከጥቂት ሰከንዶች በኋላ የቴሌቪዥኑ ጣቢያ ሲቀየር፣ እሱ ቴሌቪዥኑን ትቶ፣ ቴሌቪዥኑን የከፈተችውን መክሊትን መመልከት ጀመረ። ባጋጣሚ፣ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የልማት ፕሮግራም ላይ የሚከተለው ዜና እየታየ ነበር። «በአማራ ክልል እናርጅና እናውጋ ወረዳ በሚገኝ አንድ የገጠር ቀበሌ ውስጥ ከዳገት ላይ አዲስ ጅረት ስለ ፈለቀ፣ የቀበሌው ሊቀ መንበር ጅረቱን መርቀው ከፈቱ። የቀበሌው ሊቀ መንበር በጅረቱ ምረቃ ላይ ለተገኙት አርሶ አደሮች እንደ ተናገሩት፣ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ብቻ ሦስት ጅረቶች መፍለቃቸውን አስታውሰው ይህም የመልካም አስተዳደር ውጤት መሆኑን ገልጸዋል።»

የፊተኛው በር እንደገና ተከፈተና፣ አብርሃም አረንጓዴ ማንቆርቆርያውን አንጠልጥሎ ከገባ በኋላ ወደ ጆሮዬ ተጠግቶ፡- «. . . ስማ! እኒህ ፈረንጆች ጎልማሳ ኢትዮጵያዊ በጉዲፈቻ መውሰድ ለምን አይጀምሩም?» በማለት እኔን ጠይቆ በራሱ ቀልድ ራሱ ሥቆ፣ ጎበጥ ጎበጥ እያለ በኋለኛው በር ወጣ፡፡ አብርሃም የቧንቧ ውኃ እጥረት ከተከሠተ ወዲህ በካፌያችን ውስጥ በእጅ አስታጣቢነት ለአጭር ጊዜ ተቀጥሮ ሲሠራ የነበረ ነው፡፡ አብርሃም በረጅም ቁመቱ አጎንብሶ ሲያስታጥብ ስለሚውል ተስተናጋጆች እጅ እንጂ ፊት ያላቸው አይመስለውም፡፡ አብርሃም አጎንብሶ ሲያስታጥብ ስለሚውል፣ ወገቡ ጎብጦ በመጀመርያ ደመወዙ የባሕር ከዘራ ለመግዛት ተገድዷል፡፡

አንድ ቀን፣ «የቧንቧ ችግር ሲቃለል ምን ሠርተህ ልትበላ ነው?» አልሁት፤

«እንጃባቴ፣ ምናልባት ከሕዝቡ እጅ ጋራ የተያያዘ ሌላ ሥራ እሠራ ይሆናል!»

«ምን ትሠራለህ?»

«ምናልባት በመዳፍ አንባቢነት እተዳደር ይሆናል፤»

ከኋለኛው በር አንዲት ሴትዮ፣ በቀሚሷ ሥር የውስጥ ሱሪዋን ወደ ነበረበት እየመለሰች ከገባች በኋላ፣ «ሽንት ቤቱ ችግር አለበት፤» አለችኝ፡፡

«ምንድን ነው ችግሩ፣ እትዬ?»

«ጥሩ፤ ችግሩ ምን መሰለህ? በመጸዳጃ ቤቱ በር ላይ የወንድ/



የሴት የሚል ምልክትም ሆነ ጽሑፍ ስለሌለው የትኛው የወንድ፣ የትኛው የሴት መሆኑን ለማወቅ ያስቸግራል፡፡»

«እትዬ፣ በደንብ አላስተዋሉት እንደሆን እንጂ የወንዱን ሽንት ቤት ከሴቱ የሚለዩበት ሌላ ዘዴ ነበረልዎት፤»

«የምን ዘዴ?»

«ወደ ሽንት ቤቱ ሄደው በሩን ሲያንኳኩት *ሰው አለ* ብሎ የሚመልስልዎት ድምፅ ጎርናና ከሆነ ሽንት ቤቱ የወንዶች ነው ማለት ነው፡፡»

በዚህ ዐይነት ሁሉንም ተስተናጋጅ በትሕትና እና በዘዴ እንደ ዓመሉ ስመልስ ቆይቼ ደከመኝና ቁጭ አልሁ፡፡ መክሊት እየተፍለቀለቀች መጥታ አጠገቤ ተቀመጠችና ለማውራት አፏን አቀባበለች፡፡ ስለ አዲሱ ፍቅረኛዋ ስለ አቶ *ያን* ማውራት ከጀመረች ለማነጻጸርያ የቀድሞው ፍቅረኛዋ እና የቀድሞው የብሔራዊ ቡድን በረኛ ሳሚ መነሣቱ አይቀርም፡፡

«ይገርምሃል» ብላ ጀመረች፣ «. . . *ያን* ደስ የሚለኝ ዋናው ነገሩ ንጽሕናው ነው፡፡ በጣም ጽ. . . ድት ያለ ነው፡፡ የገላው መዓዛ ደስ ስለሚለኝ፣ በቃ ምን ልበልህ ምግብ በልቶ ሽቶ የሚጠጣ ነው የሚመስለኝ፡፡ ሳሚዬ ግን ራሱን ለመከባከብ ያን ያህል ግድ አልነበረውም፡፡ ኳስ ካቆመ ከሁለት ወር በኋላ እንኳ በፀጉሩ ውስጥ የኳስ ሜዳ ሣር አገኝቼበታለሁ፡፡. . .በተለይ አሪፍ ሽታን ከመጥፎ ሽታ ለመለየት በጣም ፈጣን ነኝ፡፡ *አዲስ አበባ ውስጥ አፍንጫ የሚያገለግለው ለመነጽር ማስቀመጫ ነው፤* ያለው ማን ነበር? ምዑዝ መሰለኝ! ይህ አባባል እኔን አይመለከትም፡፡ ከሳሚዬ ጋራ እንዴት እንደ ተዋወቅን ነግሬህ

የለ?»

ነግራኛለች፤ ከዕለታት አንድ ቀን ተፈሪ መኮንን በሚገኘው አሮጌ ፌርማታ ላይ ቆማ ወደ ቤቷ የሚወስዳትን አውቶብስ ትጠባበቃለች። አውቶብሱ እስኪመጣ ድረስ አካባቢውን በማሸተት ጊዜዋን ለማሳለፍ ፈለገች። ፌርማታው፣ ከጠጣር ፊስ የተገነባ ይመስል በጣም እንደሚከረፋ አስተዋለች። ይህ ቦታ የአውቶብስ ማቆሚያ ከመሆኑ በፊት የጎርፍ ማቆሚያ እንደ ነበር አጠገቧ የቆሙ በዕድሜ የገፉ ተሳፋሪ ነገሯት።

ጠረኑ እየባሰበት ሲመጣ፣ መክሊት ከጠረኑ ለማምለጥ ባልጠበቀችው አውቶብስ ውስጥ ተንደርድራ ገባች። በአውቶብሱ ውስጥ መቀመጫ ስላልነበረ፣ ምሰሶውን አጥብቃ ይዛ ቆመች። ካጠገቧ፣ የወደፊት ፍቅረኛዋ ሳሚ ቁጭ ብሏል። «እዚጋ ተቀመጭ፤» አለና የወንበሩን ትራፊ ጋበዛት፤ የወንበሩ ትራፊ ስላልበቃት በከፊል ጭኑ ላይ ለመቀመጥ ተገደደች።

«ሳሚዬ መውረድ የፈለገው ስታድየም ነበር፤ ግን በቃ እኔን ከጭኑ ላለማውረድ እስከ መጨረሻው ፌርማታ ድረስ ሄደ። በዚህች አጋጣሚ ተዋወቅን፤ ፍቅረኛሞችም ሆን። ታዲያ ብዙ ጊዜ ስለ አዲስ አበባ ጽዳት ሲነሣ ሳሚ፦ *ተይው ባክሽ፣ አዲስ አበባ ንጹሕ ብትሆን ኖሮ እኔ እና አንቺ አንገናኝም ነበር።»* ይለኛል።

ከጀርመን የመጣው ተስተናጋጅ ውቃ እንድታመጣለት ስለ ጠየቃት አስተናግዳጡ ተመሰሰች። «አየኸው?» አለችኝ አንገቷ ላይ ያለውን ሐብል እያስጎበኘችኝ፦ «. . .*ያን ነው ትላንት ሰርፕራይዝ* ያደረገኝ። አበሻ ቢሆን ይህን የሚያደርግ ይመስልሃል? የአበሻ ወንድ ከመርዶ በቀር ምን ሰርፕራይዝ ያውቃል? አሁን



ሳሚ በብዙ ነገር ከፉ ሰው አልነበረም፤ ግን በቃ *ሰርፕራይዝ* ምናምን አይገባውም፤ . . .የልደቱ ቀን ያደረገውን ነግሬሃለሁ?»

ነገሩ እንዲህ ነው።

አንድ ቀን የፍቅረኛዋን የሠላሳኛ ዓመት በዓል በማስመልከት መክሊት እና ተዋናይ ወንድሟ ሲያስገርሙት ፈለጉ። ቀን ቤት ሲያጸዳዱ ዋሉ፣ ኬክ በስሙ አስጋገሩ፣ ከዚያ ሦስት ሻማ ገዙ(አንዱ ሻማ ዐሥር ዓመት ይወክላል)፤ ምሽት ላይ ሳሚ በሩን ከፍቶ ገባ። መክሊት እ. . .ቅፍ አደረገችውና፣ «እስኪ ጎበዝ ከሆንክ ይህን ጥያቄ መልስ፤ የዛሬውን ቀን ከሌሎች ቀኖች የሚለየው ምንድን ነው?» አለችው። ሳሚ ፈገግ ብሎ ዙሪያ ገባውን ከቃኘ በኋላ ዐይኖቹ ሻማዎቹ ላይ ሲያርፉ፣ «ok, ዛሬ መብራት ተረኛ ነን፤» አለ።

«እና ይህ ዐይነቱ ልጅ ከእኔ ጋራ ባይቀጥል ይደንቃል?»

ወዲያው ንግግሯ ተቋረጠ። ሰማዩ ላይ ሳይሆን ዛፎች ላይ አድፍጦ የቆየ የሚመስል ድንገተኛ ዝናም መውረድ ጀመረ። ምንጫቸው ያልታወቀ፣ ቡቱቷም ከሲታ ሕፃናት ሎተሪ አዟሪዎች እና ፓርኪንግ የሚሠሩ ሴቶች በካፌው በረንዳ ላይ ተጠራቀሙ። የሚበሉ፣ የሚጠጡ፣ የሚያፈቅሩ እና የሚያጠኑ ተስተናጋጆች ካፌው ውስጥ ቁጭ ብለዋል። በረንዳው ላይ የሚተክዙ እና የሚያዛጉ ድሆች ቆመዋል። በተስተናጋጆች እና ከዝናም በሸሹ ድሆች መካከል ከውኃ የጠራ የመስተዋት ግድግዳ ቆሟል። በድሆች እና በሀብታሞች መካከል ያለውን ርቀት የሚያጠበው ብቸኛ ኀይል ዝናም እንደ ሆነ ገባኝ።

# ምዕራፍ 12

- ዝናሙ እየሣሣ ሲመጣ በክፍሉ ውስጥ ታግቶ የቆየው የተስተናጋጅ ድምር ድምፅ ተለቀቀ። እንደ ወፍ ጉባኤ የተደበላለቀው ሕምሕምታ ቀስ በቀስ እየጠራ መጣ። ተባራሪ የወሬ ግንጣዮች ይሰሙኝ ጀመር።
- ቦምቦሊኗቸው በጣም አሪፍ ነው፤
- «የቦምብ ፍንዳታ ደረሰ፤» የሚባለው እውነት ነው?
- እውነቴን ነው የምልሽ አገሪቱ ያለችበት ሁኔታ ተስፋ አስቆራጭ ነው።
- እኔኮ ያዘዝሁት ተቆራጭ ነው።
- *ቪ ሐይሲን ዚ?*

*ኢህ ሐይሰን፣* ሐሰን፤

በቅርቡ የተቀጠረው አዲሱ አስተናጋጅ አባተ ማስተናገድ ብርቅ ሆኖበት ከጠረጴዛ ጠረጴዛ ይሯሯጣል። ተስተናጋጁ ጠጥቶ ሳይጨርስ አባተ የቡና ብርጭቆውን ያነሣል፤

«እረ ገና ነኝ፤» ሲባል «ላሙቅልዎ ብዬ ነው፤» ብሎ ይመልሳል። ከሽንት ቤት የተመለሰ ተስተናጋጅ ርጥብ እጁን ሲያራግፍ ካየ፣ «ምግቡ እንዴት ነበር?» ብሎ ይጠይቃል። ደግሞ



ከተቀጠረበት ቀን አንሥቶ እስከ አሁን ፈገግታው አልተከደነም። እንዲህ ዐይነቱ ቆሞ ቀር ፈገግታ በድግምት እንጂ በደስታ የሚገኝ አይመስለኝም። አሁን የሆነ ሰውዬ ሲገባ ተንደርድሮ ሄዶ፣ «ምን ላምጣልህ?» አለው። ተስተናጋጁ ጭቁን ፈገግታ እያሳየ፣ «ዐሥር ደቂቃ ልቆይ?» አለ። እንግዲህ ከብዙ ዓመታት የአስተናጋጅነት ልምዴ እንደተገነዘብሁት አንድ ተስተናጋጅ፣ «ዐሥር ደቂቃ ልቆይ፤» ካለ ኪሱ የነጠፈ ችስታ(ኪሰ *በራ*) ነው። ወደ ካፌው የመጣው ዝናም ለማባራት ወይም መሄጃ ስለሌለው ነው። አባተ ግን ይህ አይገባውም። የግድግዳ ሰዓቱን እና ሰውዬውን እያፈራረቀ ሲመለከት ከቆየ በኋላ፣ «ዐሥር ደቂቃ ሞልቷል ምን ላምጣልህ?» ብሎ ድርቅ ይላል።

ከጥቂት ደቂቆች በኋላ ካፌያችን ካለበት ሕንፃ ሰባተኛ ቆጥ ላይ የሚሠራ የሕግ አማካሪ፣ «አምቦ ውኃ ይምጣልኝ፤» ብሎ በስልክ አዘዘ። እውነት ለመናገር ሰባተኛው ቆጥ ላይ የተቀመጠ ሰው ለሰማዩ ስለሚቀርብ ከደመናው ጠልቶ ቢጠጣ ይቀለዋል። መክሊት፣ «ሰውዬው እኔን ስለሚያስቸግረኝ አንተ አስተናግደው፤» አለችኝ። እሺ፣ ከማለቴ ተጸጸትሁ። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት መብራት ስለ ጠፋ የዕርገት ማሽኑ(ሊፍቱ) መሥራት አቁሞ ነበር። ስለዚህ በአንድ እጄ አምቦ ውኃውን ይዤ፣ በሌላ እጄ የመወጣጫውን ድጋፍ ተመርኩዤ በየርምጃው እንደ ታነቀ ሰው በጭንቅ እየተነፈስሁ እወጣ ጀመር። ይህን ፎቅ የሠራው ሰውዬ በሕይወት ካለ ዕድሜው ይጠር! በሕይወት ከሌለ ዘላለሙ ይጠር! ተጨማሪ ርግማን ለማውረድ ፈልጌ ነበር፣ ግን ከአምስተኛው ፎቅ በኋላ እንኳን መርገም ማሰብ ተሳነኝ። ሰባተኛው ቆጥ ላይ ደርሼ የሕግ አማካሪውን ቢሮ ሳንኳኳ «ግቢ!» ተባልሁ። ይሁን እንጂ የሕግ አማካሪው መክሊት እንዳልሆንሁ ሲያይ ተበሳጭቶ የአምቦ ውኃው ማከፈቻ ስላረጀ ቀይረህ ተመለስ

ብሎ አዘዘኝ:: እንደገና ወርዶ መመለስን ሳስብ በቢሮው መስኮት ወደ ውጭ ተወርወር ተወርወር የሚል ሐሳብ መጣብኝ:: ለካ አንዳንድ ወጣቶች ራሳቸውን ከሰባተኛ ፎቅ የሚወረውሩት ወደው አይደለም፤ ለመውረድ ስለሚቀል ነው::

በዚህ ዐይነት «አምቦ ውኃ ቅዳ፣ አምቦ ውኃ መልስ» ስዳፋ ቆይቼ ሳቤን ከግንባሬ ላይ እያለብሁ ወደ ነበርሁበት ቦታ ስመለስ መክሊት ከነበረችበት ቦታ ንቅንቅ ሳትል ቅድም ለኔ የጀመረችልኝን ወሬ ለራሷ ስትጨርስ አገኘኋት::

«ዝም ብሎ ቁጭ ማለት ያዋጣሻል?» አልኳት::

«ምነው እንዳልባረር ፈራህ?» ስትል ጀመረች:: «ካልክስ የምባረርበትን ሰበብ እየፈለግሁ ነው:: ይኸውልህ እንግዲህ፣ በልቤ የያዝሁትን ምስጢር ልታዘረግፈኝ ነው:: ያንየሆነ ፕሮሰስ ጀምሮልኛል፤ ከሦስት ወር በኋላ ይዞኝ ኢ. . .ልም ወደ ጀርመን:: እንዲህ ያለውን ቁም ነገር ዛሬ ማን ያውቀዋል?. . .ለነገሩ ገና ከጅምሩ ለቁም ነገር እንደሚፈልገኝ ዐውቀው ነበር:: ያኔ እንደተገናኘ ን ራት ጋበዘኝና እኔን ለማስደሰት እንጀራ በላ:: እንጀራ ሲቆርስ ብታየው በሣቅ ይገድልሃል:: መቼም እንጀራ ይቧጥጣል እንጂ እንጀራ ይቆርሳል አይባልም:: ያን ቀን ታሞ አደረ:: በመታመሙ ባዝንም የእኔን ባህል ለማክበር፣ እኔን ለማስደሰት ሲል እንጀራ በልቶ ስለ ታመመ ደስ አለኝ:: የሚያፈቅረኝ ሰው አይሙት እንጂ ለእኔ ብሎ ትንሽ ቢሠቃይ ምን ችግር አለው?»

ዝናም ለማባራት በረንዳ ላይ ችፍግ ብለው ቁመው የነበሩት ድሆች የቡትቶ ጠረናቸውን እና ትዝታቸውን ትተው እየተንጠባጠቡ ሲሄዱ፣ ከመካከላቸው አንድ ትንሽ ልጅ ቀርቶ፣ በሩን በዝግታ ከፍቶ ከገባ በኋላ፣ «ጎዳና ነው ቤቴ፣. . .» ብሎ



ጀምሮ፣ «ጥለውኝ ሞተዋል፣ እናት እና አባቴ፤» ብሎ ከማጠናቀቁ በፊት አባተ ደርሶ እጅጌውን ይዞ ወደ በሩ ጎተተው:: ይሁን እንጂ አንዲት የቋንቋ ተማሪ ሴትዮ ከወንበሯ ብድግ ብላ በአባተ ጆሮ የሆነ ነገር ስታንሾካሹክ አባተም ራሱን ሲያነቃንቅ አየሁት:: ከዚያ አባተ ልጁን ብቸኛ ወንበር ላይ ጎልቶት ወደ ጓዳ ገባ:: ልጁ እንደ ተጋበዘ እንጂ ምን እንደተጋበዘ ስላላወቀ በጉጉት ወደ ጓዳው በር ይመለከት ጀመር:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አባተ በቲማቲም የተጠበሰ ሥጋ ይዞ ከወጣ በኋላ በልጁ አቅጣጫ መጥቶ፣ መጥቶ፣ መጥቶ ከልጁ በኋላ በተቀመጠ ተስተናጋጅ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠው:: ልጁ ምራቁን ሲውጥ ጉሮሮው እንደ ቴርሞሜትር ከፍ ዝቅ ስትል ዐየሁ:: አባተ እንደ ገና ወደ ጓዳ ገብቶ ሲወጣ ሻይ እና ጥቂት የተቆረሰለት ዳቦ በትሪ ይዟል:: ልጁ ዳቦውን እና ሻዩን ሲያይ «ይለፈኝ» በሚል ዐይነት ጣራ ጣራውን መመልከት ጀመረ:: አባተ ግን አላለፈውም:: የያዘውን ሳሕን ጠረጴዛው እስኪርድ ድረስ ከፊቱ አስቀምጦለት ሄደ::

ልጁ የቀረበለትን መብላት ሲጀምር ከላይ እስከ ታች ገመገምሁት:: «የጥበብ መጀመርያው እግዚአብሔርን መፍራት ነው፤» የሚል ጥቅስ የተጻፈበት፣ ለዐዋቂ የሚሆን ቲ-ሸርት ለብሶ ነበር:: በርግጥ በጥቅሱ ላይ ያለው፣ «እግዚአ» የሚለው ቃል በእድፍ ስለ ተዋጠ፣ «የጥበብ መጀመርያ. . .ብሔርን መፍራት ነው፤» የሚለው ጽሑፍ ብቻ ይታያል::

አጠገቤ የተቀመጠችው መክሊት ወሬዋን ቀጠለች:: «ከያን ጋራ ወደ ጀርመን ልበር ጥቂት ቀን ሲቀረኝ ለሳሚ ምርር ያለ ደብዳቤ እጽፍለታለሁ፤ ለነገሩ በካሴት ቀርጬ ካልላክሁለት በቀር ደብዳቤዬን አያነበውም:: ንባብ ደመኛው ነው:: ግንኮ ከሚያነቡ ሰዎች የበለጠ ጭንቅላት ነበረው:: አንድ ቀን፣ ሳሚዬ የስፖርት

ጋዜጣ እንኳ አታነብም? ብዬ ጠየቅሁት። የመለሰልኝ መልስ እስከ ሞቴ አይረሳኝም። ምን አለኝ መሰለህ፣ ‹. . .ዐይኔን ለዐይን ባንክ ለመስጠት ቃል ገብቻለሁ፤ የማላነበው ዐይኔን ለመጭው ትውልድ መቆጠብ ስላለብኝ ነው፤› አለኝ - አሪፍ አይደል?»

አሁን ግን ሁሉም አልፏል። አዲስ ሕይወት ውስጥ ገብቻለሁ። ሳሚ ይህን እንዲያውቅልኝ እፈልጋለሁ። ነገ ለመጨረሻ ጊዜ አገኘዋለሁ። እኔጋ ያሉትን ሦስት የልጅነት ፎቶዎቹን እንድመልስለት ይፈልጋል። ለነገሩ ፎቶዎች ሰበብ ሆኑ እንጂ እኔን ለማየት ነው ፍላጎቱ፤ የዛሬ ወር ገደማ ፎቶውን ልሰጠው ተቀጣጥረን ተገናኘን። ግማሽ ቀን ሙሉ ስናወራ ከቆዬን በኋላ ፎቶውን ሳይጠይቀኝ ሄደ። እኔም ረስቼው አላነሣሁበትም። አሁን እንደገና «አምጪ» ብሎ ደወለልኝ . . . ምን አስተያዬት አለህ?»

«በሕፃንነቱ የተነሣው ሦስት ፎቶ ካለው በእውነቱ ዕድለኛ ሰው ነው፤» አልሁ።

«እንዴት?»

«እኔ ሕፃን በነበርሁበት ጊዜ ፎቶግራፍ መነሣት በጣም ከባድ ነበር። እንዲያውም ከዚህ በፊት እንደገለጽሁት፣ በእኛ መንደር ፎቶ ከተነሡት ይልቅ ሞተው የተነሡ ይበዙ ነበር። በተለይ ፎቶ ለብቻ መነሣት እና ጉርድ ፎቶ መነሣት ፎቶውን እንደ ማባከን ይቆጠራል። ካሜራ ያዥ ጋራ የመገናኘት አጋጣሚ ያለው ሰውዬ፣ ዘመድ እንኳን ቢያጣ ከጠመንጃው እና ከውሻው ጋራ አብሮ ይነሣ ነበር። ትዝ ይለኛል የሦስተኛ ክፍል ተማሪ ሳለሁ፣ የትምህርት ቤታችን የመዝገብ ቤት ሐላፊ፣ ‹የወላጅህን ጉርድ ፎቶግራፍ አምጣ፤› ሲለኝ የእንጀራ አባቴ በቁም የተነሣውን ፎቶ ከወገቡ በላይ በመቀስ ቆርጬ ወስጃለሁ። ከእኛ



ቤት ትንሽ ፈንጠር ብለው የሚኖሩ አንድ የሀብታም ቤተሰብ አባላት በሁለት ዓመት አንዴ ፎቶ ይነሡ ነበር። ታዲያ አንድ ቀን ፎቶ አንሺው ካሜራውን ሲያቀባብል፣ በፎቶ ተነሺዎች ጀርባ የማልፍ አስመስዬ እግሬን እያዘገየሁ ተራመድሁና አብሬ ፎቶ ተነሣሁ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ባለቤትዬዋ ለእንግዳ የፎቶ አልበም ሲያስጎበኙ፣ ‹ይህ ባለቤቴ ነው፤ ይህ ልጄ ነው፤ ይህ ደግሞ በስሕተት የገባ የጎረቤት ልጅ ተረከዝ ነው፤› ብለው ያሳያሉ።

ሌላ ጊዜ ደግሞ የፋፋ ዱቄት ፋብሪካ ለፖስተር የሚሆን የሕፃን ምስል ፈልጎ እኛ ሰፈር ሲመጣ ዐይኑን በእኔ ላይ ጣለ።»

«በጣም ወፍራም ሕፃን ነበርህ ማለት ነው?» አለችኝ መክሊት፤

«ወይ ወፍራም! በርግጥ ፋፋ የዱቄት ፋብሪካ ለፖስተር የሚመርጣቸው ሕፃናት ወፍራም ናቸው። በአንድ ወቅት ላይ ግን ለለውጥ ያህል ቀጭን ሕፃን ተፈለገ።»

«እሺ!»

«ከዚያ እኔን አነሡኝና ፖስተሩ ላይ በምስሉ ሥር፣ ‹ፋፋ ያልተመገበ ሕፃን ይህን ይመስላል› ብለው ጻፉበት።»

«ውይ የኔ ጌታ!!» አለችና መክሊት ጉንጬን ሳመችኝ። በጣም ስለ ተደሰትሁ በረንዳው ላይ ፀጉሬ ቀና ብዬ ኮከብ፣ ዝቅ ብዬ ዐደይ ባይኔ ፈለግሁ። ይሁን እንጂ ይህ ስሜት አልቀጠለም።

ከካፌው በረንዳ ፈንጠርጠር ብለው ከቆሙት መኪኖች መካከል ጭንቅላቷን የሸሸገች ዔሊ የምትመስል ቮልስ በጥሩንባ

ጠራችኝ:: ስሄድ በቮልሱ ውስጥ ያለው ሰውዬ ወተት እንዳመጣለት አዘዘኝ:: የመክሊትን ነገር እያሰብሁ ስለነበር የባለቮልሱን መልክ በቅጡ አላስተዋልሁትም:: ለምልክት የያዝሁት ቮልሷን ነው:: ይሁን እንጂ ወተቱን ይዤ ስመለስ ሌሎች ሁለት ነጫጭ ቮልሶች በተርታ ተሰልፈው ቆመዋል:: በቮልሶቹ ፊት ለፊት ለጥቂት ደቂቃ ግራ ተጋብቼ ቆምሁ:: ከሦስቱ ባለቮልሶች መሀል ወተት ያዘዘኝን እንዴት ልለየው? ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ግን መላ መጣልኝ:: ከሦስቱ ባለቮልሶች መሀል ጥጃ የሚመስለውን መርጬ ሄድሁና ወተቱን አቀበልሁት::



# ምዕራፍ 13

የዝንብ ሠራዊት መበርከቱን ሳይ ግንቦት መግባቱን ዐወቅሁ - ግንቦት የዝንብ ቀፎ! መስከረም የመስቀል ወፍን ሲወልድ ዐይቶ እርሱ ዝንብን ይፈለፍላል:: አንዳንድ ባህላዊ ምግብ ቤቶች ግንቦት ሲገባ ለተመጋቢዎች ከቢላዎ እና ከሹካ ጋራ ጭራ ያድላሉ(ዝንብ እጅግ በሚበዛባቸው ሬስቶራንቶች ደንበኞች አጎበር ለብሰው ይበላሉ):: እዚህ ላይ የሥነ ፍጥረት ምስጢር ብልጭ አለልኝ:: ዝንብን በላብራቶሪ ውስጥ የፈጠሩት ጭራ ነጋዴዎች ሳይሆኑ አይቀሩም::

እየመሸ ነው:: ከጎኔ አማተሩ አስተናጋጅ አባተ ቢላዎውን እና ሹካውን አስተባብሮ ፒዛው ላይ አቀርቅሯል:: ፊቱ ላይ ያለውን እንደ አለት የጠነከረ ተመሥጦ እና የለበሰውን ጋዎን አስተባብረህ ስታዬው ቀዶ ሕክምና የሚያደርግ እንጂ የሚበላ አይመስልም:: መክሊት አጠገቡ ቁጭ ብላ፣ አገጯን በእጇ አስደግፋ ትተክዛለች፤ ማካሮኒዋን አልነካችውም:: ወሬ ለመጀመር እንደ ፈለገች ስለ ገባኝ ከሐሳቤ ላለመደናቀፍ ፊቴን አዞርሁ::

ወደ አባተ ዞረችና፣ «ፍቅር ይዞህ ያውቃል?» አለችው፤

«አም!» አለ እንዳቀረቀረ::

«ምግብ የሚከለክል ፍቅር ይዞህ ያውቃል?»

«የምግቡ ዐይነት ይወስነዋል፣እንግዲህ!»

እነሱ እንዲህ ሲያወሩ እኔ ስለ ዝንብ ማሰቤን ቀጥያለሁ:: የሦስተኛ ክፍል *«የሳይንስ እና ሕይወት»* ማስተማርያ መጽሐፍ ላይ የዝንብ ዕድሜ ከሁለት ሳምንት እንደማይበልጥ ማንበቤ ትዝ አለኝ:: ይህቺም ዕድሜ ሆና ነጻነቱን እንነፍገዋለን፤ በበኩሌ እንኳን በወተቴ በሕይወቴ ቢገባ አልፈርድበትም::

እየመሸ ስለሆነ ካፌ ውስጥ ጥቂት ተስተናጋጆች ቀርተዋል:: ከፊት ለፊት በሰልፍ ከተደረደሩት አግዳሚ ወንበሮች በአንዱ ላይ ክብ ፊት ያላት የቋንቋ ተማሪ ተቀምጣ ግድግዳውን በዝምታ ትመለከታለች:: በግራ ጆሮዋ ላይ የዐደይ አበባ ቅርጽ ያለው ጌጥ አንጠልጥላለች:: ከጌጡ ከፍ ብሎ ብዙ የዘመኑ ሴቶች እንደሚያደርጉት የአይፖድ ማዳመጫ ሰክታለች:: የጆሮ ጌጡ፣ ተመልካች መጥሪያ፣ አይፖዱ ደግሞ ማባረርያ ነው:: መክሊት እንደ ነገረችኝ ሴቶች ጆሯቸው ላይ አይፖድ የሚሰኩት በሙዚቃ ለመዝናናት ወይም ፋሽን ለመከተል ሳይሆን የወንዶችን ሰርጎ ገብ ንግግር ለመከላከል ነው::

ይህን ዐውቆ ሳይሆን አይቀርም፣ ከልጅቱ አጠገብ በስተግራ አንድ ጎረምሳ በማመንታት ዐይነት በግማሽ ቂጡ ተቀምጦ ሰረቅ እያደረገ ያያታል:: ጎረምሳው የተራቆተ ቀኝ ክንዱን በልጅቷ ትከሻ አንጻር በወንበሩ መደገፊያ ላይ አጋድሞታል:: የክንዱ አቀማመጥ ልጅቱን ለማቀፍ ያለውን ምኞት ያሳብቅበታል:: በምኞት እና በእውኑ መካከል ያለው ርቀት በወንበሩ መደገፊያ



እና በልጅቱ ትከሻ መካከል ካለው ርቀት ጋራ እኩል ነው::

በነገራችን ላይ ጎረምሳው እንደ አቅሙ ለማጌጥ ስለ ፈለገ በስፖርት ባልዳበረ ቀጭን ክንዱ ላይ ግማሽ ልብ ተነቅሷል:: ይህን የግማሽ ልብ ንቅሳት ሥራ የፈታ ሐያሲ የምን «ትእምርት»/ሲምቦል/ ነው? ብሎ ይመራመር ይሆናል:: የምንም «ሲምቦል» አይደለም:: የንቅሳት ባለሞያው ግማሽ ልብ የነቀሰበት ምክንያት የጎረምሳው ቀጭን ክንድ ሙሉ ልብ ለመንቀስ የሚበቃ ቦታ ስለሌለው ነው፤ አለቀ::

አለፍ ብሎ፣ አንዲት ደርባባ ሴት ሕፃን ልጅ ታቅፋ ተቀምጣለች:: ድንገት ትልቅ ጡቷን በካናቴራዋ የግርጌ ጠርዝ በኩል አውጥታ ልጅዋን ማጥባት ጀመረች:: አእምሮዬ ሕፃኑን ከፍሬሙ ገፍትሮ አውጥቶ ሴትዮዋን እና የተጋለጠ ጡቷን ብቻ ያሳየኝ ጀመር:: ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ሴትዮዋ በአስተያየቴ አፍራ እንገቷን ትደፋለች ብዬ ጠብቄ ነበር:: ወይ ፍንክች! እናትነት ለሴቶች ከሚሰጣቸው መብቶች አንዱ ጡትን ባደባባይ መግለጥ ነው:: ይገርማል! ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ዝንብን የሚያስረጅ እምላክ፣ በዘጠኝ ወር ጊዜ ውስጥ ጡትን ከውበት ወደ መብልነት ያሸጋግራል::

አራተኛው፣ ተስተናጋጅ ሳይሆን ተስፈኛ ነው:: በቅርቡ ካፌያችንን ማዘውተር የጀመረ የቀድሞ ሠራዊት አባል ነው:: «በችግር ምክንያት አብዶ ጨርቁን ጥሎ ዐይተነዋል፤» የሚሉ ሰዎች ገጥመውኛል፤ ተሳስተዋል:: በችግር ምክንያት አንድ ልብስ ብቻ ስላለው፣ ልብሱ ታጥቦ እስኪደርቅ ራቁቱን ዞር ዞር ሲል ዐይተውት ይሆናል እንጂ አላበደም:: አሁን ጥግ ላይ ቁጭ ብሎ መክሊትን ባይኑ ይከታተላታል:: ካፌው ከመዘጋቱ በፊት ብቅ

ሲል፣ ከደንበኞቹ የተረፈውን ምግብ ትሰጠዋለች:: ይህን ስታደርግ ግን የመጽዋችነት ጠባይ አይታይባትም:: «ሻለቃ፣. . . ስለ ጦር ሜዳ ትንሽ አጫውተንና ራትህን ትበላለህ!» ትለዋለች:: የሚሰጠው ፍርፋሪ እንደ ምጽዋት ሳይሆን በተራኪነቱ የሚከፈለው ደመወዝ አድርጎ እንዲቆጥረው ያመጣችው መላ ነው::

በበኩሌ እንዲህ ዐይነቱን መላ፣ ክብርን በመርፌ እንደ መውጋት እቆጥረዋለሁ:: መላውን ለመጀመርያ ጊዜ ያስተዋወቀን ምዑዝ ነው:: ባንድ አጋጣሚ አብረን ስንሽራሽር አራት ኪሎ መንገድ ዳር አንድ ጎልማሳ ነዳይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደራጎኑን ሲገድል የሚያሳይ ሥዕል እግሩ ሥር ዘርግቶ ምጽዋት ሲጠባበቅ ተመለከትነው:: ምዑዝ አጎንብሶ ለጥቂት ደቂቃ ያህል ካተኮረበት በኋላ፣ «ለምነህ በቀን ስንት ብር ታገኛለህ?» ሲል ጠየቀው:: ነዳዩ ትንሽ በተደናገረ አንደበት «ዐሥር ብር» ሲል መለሰ::

«እንደዚህ ከሆነ የጊዮርጊስን ሥዕል በዐሥር ብር ሽጥልኝ:: ዛሬ እንኳ ሠርቼ አገኘሁ ብለህ ደስ ይበልህ!» አለ ምዑዝ:: ነዳዩ ያልጠበቀው ነገር ስለሆነበት እምቢ ለማለት አልቻለም::

አሁን እንግዲህ በተመሳሳይ ሚና መክሊት፣ «ሻለቃ፣ የጦርነቱን ተጋድሎ አጫውተኝና ራትህን ትበላለህ!» ብላ በድጋሚ ጋበዘችው::

«አዬ፣ አገራችን የተሸነፈችበት ጦርነት ምን ያደርግላችኋል? ቢቀር ይሻላል!» አለ ተስፈኛው! አላግደረደረችውም፤ የራሷን ወሬ ለመጀመር ማቅብቀብ ስትጀመር፣ «የግድ አጫውተን የምትሉ ከሆነ ግን የጉና ተራራን ለማስለቀቅ የተደረገውን ተጋድሎ አጫውታችኋለሁ!» አለ ጮህ ብሎ:: ወንበራችንን ስበን ከበብነው::



«የጉና ተራራ ከባሕር ጠለል በላይ አምስት ሺሕ ጫማ ከፍታ ያለው ተራራ ነው!» ሲል ጀመረ::

«በስንት ቁጥር ጫማ ተለክቶ ነው?» አለና አባተ አቋረጠው::

አቤት አባተ፣ ወሬ ማደናቀፍ ሲወድ!! ባለፈው የመክሊት ፍቅረኛ አቶ ያን፣ «የምኖርበት ከተማ ከበርሊን መቶ ኪሎ ሜትር ይርቃል!» ብሎ ሲናገር አባተ ጥልቅ አለና፣ «መቶ ኪሎ ሜትር በኛ ስንት ይሆናል?» ብሎ ጠየቀ:: በጥፊ ብወለውለው ደስ ይለኝ ነበር:: መክሊት ግን ሕፃን ልጅ እንደምታስጠና ሁሉ፣ «የእነሱ መቶ ኪሎ ሜትር በኛም ያው መቶ ነው!» አለችው::

«የዋጋው ግሽበት ያልነካው ኪሎ ሜትሩን ብቻ ነው ማለት ነው?» አላት ትሪውን ይዞ እየሄደ:: ለማንኛውም የቀድሞ ሠራዊት አባል የሆነው ሻለቃ የተረከውን ገድል ከዚህ ቀጥሎ አቀርባለሁ::

* * *

«. . .በ1980 ዓ.ም ባሕር ዳር ከተማ ሠፍሮ የነበረውን ሃያ አንደኛ ሜካናይዝድ ጦር እየመራሁ ወደ ሰሜን ጉዞ ጀመርሁ፤ ደብረ ታቦር ከተማ ስንደርስ የውኃ ኮዳ ለመግዛት ጥቂት መኮንኖችን አስከትዬ ወደ ገበያ ሄድሁ:: ከገበያው ስወጣ ግን የሬዲዮ መገናኛዬን ከኪሴ አጣሁት:: እግዜር ያሳያችሁ፣ ያለመገናኛ ሬዲዮ ጠላት የሚገኝበትን ወረዳ ማወቅ እንደማይቻል ስለ ተረዳሁ ተሸበርሁ:: ቢጨንቀኝ በሬዲዮ መገናኛ ፈንታ ኖርማል ሬዲዮ ገዝቼ ቢቢሲ ስከፍት ዜና አንባቢዋ፣ ‹የኢትዮጵያ መንግሥት ተቃዋሚ ጦር ከጉና ተራራ ጀርባ መሽጓል!› አለች:: እግዜር ይስጥሽ አልሁና፣ ሠራዊቱን እየመራሁ እልም! ወደ ጉና! በጉዞ ላይ የሠራዊቱ ስንቅ ስላለቀ ወታደሮች የጠላት ጦር

እንደሚያደርገው አፈር እና ስኳር ቀላቅለው እንዲመገቡ አዘዝኋቸው። ምን ዋጋ አለው! ስኳር እና አፈር እየቀላቀሉ የተመገቡ ወታደሮች ከወር በኋላ ሽንኮራ አገዳ መጸዳዳት ጀመሩ፤ አይ ያ ጊዜ!!

ጉና በገባን በሁለተኛው ቀን ጠላት ተኩስ ከፈተብን። የወገን ጦር እና የጠላት ጦር ኀምሳ ሜትር በማይሞላ ርቅት ላይ ተቀራርቦ ይተጋተግ ጀመር። ድንገት ከፊት ለፊቴ አንድ የጠላት ወታደር እየተኮሰ ሲመጣ ዐየሁትና ልዘረጋው ዒላማዬ ውስጥ አስገባሁት። በዒላማዬ ውስጥ የገባው መንትያ ወንድሜ መሆኑን ሳውቅ ግን ክላሼን አሽቀንጥሬ ጣልሁት።

አበጋዝ፣ ብዬ ጮህኩ።

እሱም ‹ስንታየሁ› ብሎ ጮኸና መትረየሱን ጣለ።

አንገት ላንገት ተቃቅፈን መላቀስ ጀመርን። ወዲያው ተተኩሶ ሳይፈነዳ ከቀረ የመድፍ ቀለሕ ላይ ጎን ለጎን ቁጭ ብለን ወሬ ጀመርን። የመትረየስ ጥይት እየተንፈቀፈቀ ዩኒፎርማችንን ወንፊት እያደረገው ያልፋል።

‹እንዴት ወደ ወያኔ ጦር ልትገባ ቻልህ?› ብዬ ጠየቅሁት መንትያዬን።

‹እንደምታውቀው እነሱ በቁጥጥር ሥር ባደረጉት አካባቢ በጀማሪ መምህርነት አገለግል ነበር። እና በጊዜው ከመምህር ደመወዝ ይልቅ የታጋይ ደመወዝ ስለሚሻል ትግሉ ውስጥ ገባሁ፤> አለኝና፣ <አንተስ፣ እንዴት ወደ ደርግ ጦር ገባህ?> ሲል ጠየቀኝ። እኔ እንኳ ለዚህ ያበቃኝ ችኩልነቴ ነው። አንድ ቀን፣



አራት ኪሎ መንገድ ላይ የተለጠፈ ክፍት የሥራ ማስታወቂያ ዐየሁ። ለብሔራዊ ውትድርና ለመቀጠር የምትፈልጉ የሚለውን፣ «ለብሔራዊ ቴአትር መቀጠር የምትፈልጉ፣» ብዬ በማንበብ ሄጄ ተመዘገብሁ። ወደ ካምፕ ወስደው የዒላማ ተኩስ ሲያሠለጥኑኝ እንኳ ለብሔራዊ ቴአትር ዘበኝነት እንጂ ለዘመቻ ነው ብዬ አላሰብሁም ነበር፣ ብዬ ነገርሁት።

ወጋችንን በዚህ ዐይነት ቀጠልን። ድንገት ከጠላት የተተኮሰ ላውንቸር ሱሪዬን እንደ ወረቀት ገንጥሎ ወሰደው። በሸርጥ ሆኜ ወጌን ቀጠልሁ።

‹እና በማናምንበት ጦርነት ያንድ እናት ልጆች ተጋድለን ነበር በለኛ!› አልሁት። ሊመልስልኝ አልቻለም። አቅፎኝ በእንባ ታጠበ። እስኪበቃን ካለቀስን በኋላ፣ ‹ልጅ እያለን የምንሠራቸው ሸወዳዎች ትዝ ይሉሃል?› አልሁት፤ ‹እንዴት እረሳቸዋለሁ› ብሎ ለመናፈጥ መሐረብ ከኪሱ አወጣ። ከወገን ጦር የተተኮሰ የ«ቢሃያ ዘጠኝ» መድፍ መሐረቡን ከእጁ ነጥቆ ወሰደበት። ‹እንዴት እረሳቸዋለሁ?› አለ ሌላ መሐረብ እያወጣ።

«እንዲያውም አንድ ጊዜ የሒሳብ መምህራችንን በመልካችን መመሳሰል ሸውጄ ፈተና ተፈትኜልህ ዐውቃለሁ።»

‹አይ አንተ ተንኮለኛ!›

እንደገና ተቃቅፈን በሣቅ እንባ ታጠብን!

‹የኔንም ትዝታ ላስታውስህ፤ ዐሥረኛ ክፍል እያለን አንዲት በጣም የምታፈቅራት ገርል ፍሬንድ አልነበረችህም?› አልሁት።

‹ጸዳለ?›

‹እም፣ ጸዳለ፤›

‹እሺ!›

‹ባንተና በኔ መካከል ያለው የመልክ ልዩነት ይምታታባት ነበር:: ታዲያ አንድ ቀን አንተ አክስታችንን ለመጠየቅ ናዝሬት ስትሄድ እኔ ቤት ይዣት ሳጣጥማት አደርሁ፤. . አይ ልጅነት!!›

‹ተውንጂ?›

‹አልነገርሁህም እንዴ?› አልሁ እየሣቅሁ፤

‹ያለዛሬም አልሰማሁት፤› አለኝ መንትያዬ ገፍትሮ ከእቅፉ እያስወጣኝ:: ፊቱ ደም መምሰሉን አስተዋልሁ::

‹ለማገኛውም ያ ጊዜ አልፏል፤› አልሁት የስሜቱን መለወጥ ተመልክቼ፤

‹ዝ. . .ጋ!!› ብሎ ጮኸብኝ እና የጣለውን መትረየስ አነሣ:: እኔም የጣልሁትን ሽጉጥ ለቀም አደረግሁ::

‹ዋናው ወደ ጦርነት መሄድ ነው፤ የምትዋጋለትን ምክንያት መንገድ ላይ ታገኘዋለህ፤ ይል ነበር አባቴ› አለና ወደ ጠላት ጦር ተቀላቀለ::

ወዲያው ምድር ቀውጢ ሆነች:: በላውንቸር ጥይት ተመትቼ ወደቅሁ:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ስነቃ አካባቢው ድብልቅልቅ ብሏል:: ወደ ቀኝ ዞር ስል ጀግናው ጄነራል ዑመር ገብረ ክርስቶስ በሁለት መቶ የጠላት ወታደሮች ተከቧል:: ጠላቶቹ የከበባውን ቀለበት



እያጠበቁበት ሲሄዱ ከመ[illegible]ረክ ይልቅ ራሱን ማጥፋት መርጦ ሽጉጡን ለመጠጣት እጁን ወደ ስገባው ሲልክ፣ ሽጉጡን በነበረበት ቦታ ዐጣው:: ይሄኔ የከበቡትን ጠላቶቹን በትሕትና እየተመለከተ፣ ‹ከእናንተ መካከል ትርፍ ሽጉጥ የያዘ ይኖራል?› ብሎ ጠየቃቸው:: ሁሉም በአሉታ ራሳቸውን ነቀነቁ:: ይሄኔ የውኃ ኮዳው ውስጥ አንዲት ጥይት ጨምሮ ባንድ ትንፋሽ ጨለጣት::

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከወደቅሁበት ተነሥቼ እያነከስሁ መራመድ ጀመርሁ:: ከፊት ለፊቴ የጠላት ጦር እና የወገን ጦር አስከሬን እንደ ቅጠል ረግፏል:: እየተንቀለቀለ ከሚነደው ታንክ ነበልባል ላይ ሲጃራዬን ለኩሼ አካባቢውን ስቃኝ ‹ጓድ፣ አድነኝ!› የሚል የሥቃይ ጥሪ ሰማሁ:: ድምፁን ወደ ሰማሁበት አቅጣጫ ሮጬ ስደርስ፣ የልጅነት ጓደኛዬ ጀግናው ሻለቃ ጣሰው ታፋው ላይ በጥይት ተመትቶ ቆስሎ ወድቋል:: ከበላዩ አንድ ግዙፍ ቀይ ቀበሮ ጭኑን በክራንቻው ነክሶ ሲዘነጥለው ተመለከትሁ:: ከመ ቅጽበት ካሊበር ሽጉጤን ላጥ አድርጌ፣ በቀይ ቀበሮው ላይ ካነጣጠርሁ በኋላ፣ በአንድ ወቅት በአዲስ *ዘመን* ጋዜጣ ላይ የቀይ ቀበሮዎች ቁጥር እየተመናመነ መምጣቱን የሚገልጽ ሐተታ ማንበቤ ትዝ አለኝ::

ከዚያ ወደ ሻለቃ ጣሰው ቀረብ ብዬ፣ አዝናለሁ ጓድ፣ ባገሪቱ ያለው የቀይ ቀበሮዎች ቁጥር ከሻለቃዎች ቁጥር ጋራ ሲነጻጸር በጣም አነስተኛ ነው:: ስለዚህ ቀይ ቀበሮውን ገድዬ እናት አገሬ በቱሪዝም የምታገኘውን ጥቅም አልጎዳም፣ ብዬ ካስረዳሁት በኋላ ማደንዘዣ ወግቼው ጉዞዬን ቀጠልሁ::»

•

እኔ እና አባተ ስንሥቅ፣ መክሊቱ ለተራኪው ራት ለማምጣት

ወደ ጓዳው ዘለቀች።



# ምዕራፍ 14

በዝናም እና በዝንብ መካከል ያለው ልዩነት አለነገር አልተፈጠረም። እነሆ ግንቦት በዝንብ ታጅቦ ሲወጣ ሠኔ በዝናም ታጅቦ ገባ። ክረምቱ አየሩን ብቻ ሳይሆን የሰዎችን ሞያ ቀየረ። ማስቲካ ያዞሩ የነበሩ ደቂቅ ሕፃናት ማስቲካውን ትተው በአንድ አዳር መኪና አጣቢ ሆኑ። የጉልት ሴቶች ጉልቱን ትተው መንገድ ዳር በቆሎ እየጠበሱ አዲስ አበባን ከመዲናነት ወደ ማድቤትነት አሸጋገሯት። ክረምቱ አየሩን እና ሞያውን ብቻ ሳይሆን ቁሳቁሱን ቀየረው፤ አስፋልቱን ሰው ሠራሽ ወንዝ፣ የአንበሳ አውቶብሱን የኖኅ መርከብ አደረገው። ክረምቱ በር ሆነ፣ መግባት እና መውጣቱም ቀጠለ። አገር ውስጥ የነበሩ ሽሮ እና ትዝታቸውን ይዘው ወጡ። ከአገር ውጭ የነበሩ አይፖድ እና የአሳማ ጉንፋን ይዘው ገቡ።

እኔም ማስተናገዴን ቀጥያለሁ፤

አቤት፣ ስንት ዐይነት ተስተናጋጅ አለ?

የተቀባችው ፓውደር እጅግ ከመብዛቱ የተነሳ ፓውደር ላይ በግንባሯ የወደቀች የምትመስል ሴትዮ፣ እንደ ስድስተኛ ጣት ከመዳፏ የማይለየውን ሲጃራዋን ስባ በጭሱ ተጉመጥምጣ

ጠራችኝ:: አጠገቧ ደርሼ ስቆም፣ «ፈገግ በል እንጂ፣ የምን መኮሳተር ነው - ከፍትፍቱ ፊቱ እንዲሉ አበው፤ ፈገግ በልና ትኩስ ቡና አምጣልኝ - የቡና ስባቱ መፋጀቱ እንዲሉ አበው፤ ደሞ አደራህን ስኒው ንጹሕ ይሁን - ሲያዩት ያላማረ ሲበሉት ያቅራል እንዲሉ አበው፤» በማለት የትእዛዝ እና የተረት እሩምታ አወረደችብኝ:: «ሴትዮ፣ ሱስሽ የቡና ነው ወይስ የአበው? ለምን ቡናውን አበው አይታዘዙሽም?» ብዬ ላሥቅባት ካሰብሁ በኋላ፣ «ከሰው ጋራ ሲኖሩ ሞኝ ሆኖ፣ አህያን ሲጭኑ ሦስት ሆኖ» እንዲሉ አበው በዝምታ ሥራዬን ቀጠልሁ::

በነገራችን ላይ አባባሉን ሁሉ አበው ብቻ ለምን ይሉታል? ሌላውምኮ ሊል ይችላል:: ለምሳሌ፣ «ሁለት ያባረረ አንድ አይዝም» እንዲሉ ፌዴራል ፖሊሶች::

«ሲነጋጋ ሲል ይጨልማል!» እንዲሉ የመብራት ተረኞች::

«ልጅ እና ወረቀት ያስያዙትን አይለቅም፤» እንዲሉ መሠረተ ትምህርት የተማሩ እናቶች::

«ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል!» እንዲሉ የአትሌቲክስ አሠልጣኞች::

«የማይተማመን ባልንጀራ በየወንዙ ይማማላል!» እንዲሉ የናይል ተፋሰስ አገሮች::

«ሳታማሃኝ ብላኝ!» እንዲሉ ለምክንያት ግድ የሌላቸው ምግቦች::

«የባሰ አለ፣ አገርህን አትልቀቅ!» እንዲሉ ወደ ሶማሌ የተሰደዱ የአገራችን ሰዎች::



«ሕልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም!» እንዲሉ የአልቤርጎ አከራዮች::

ለማንኛውም ወደ ካፌው ልመለስ::

ከተስተናጋጆች ጋራ ሰርጋ የገባች የአምስት ዓመቷ ቀሎ ሻጭ ዕንቅቧን ትከሻዋ ላይ አድርጋ በኋላዬ በኩል ውልብ ስትል፣ «ይህ ቀሎ ኤክስፓየርድ ዴት የለውም እንዴ? ከአምስት ዓመት በፊት እናትሽ ይዛው ትዞር ነበር!» የሚል ጩካኝ ድምፅ ሰማሁና ዞርሁ:: የቀድሞው የጥራት ደረጃ ተቆጣጣሪ ከእስተናጋጆች መሀል ተቀምጦ ተመለከትሁት:: መክሊት አጠገቡ ደርሳ፣ «ምን ላምጣልህ?» ብላ ስትጠይቀው ለዐዋጅ በሚበቃ ድምፅ፣ «በርዶኛ ል፣ ነጣ ያለ ጋቢ ልታመጭልኝ ትችያለሽ?» አለና ግራ ቀኙን ቃኘ:: ከሥልጣኑ ከወረደ ወዲህ ማንም ሥቆለት አያውቅም:: የዛሬን አያድርገውና ያኔ በባለሥልጣንነቱ ዘመን የሚደረግለት አቀባበል መስል የለውም ነበር:: መክሊት አዲስ ተስተናጋጅ ሲገባ ጠረጴዛውን ትወለውላለች:: ባለሥልጣኑ ሲመጣ ግን ጠረጴዛውን ትለውጥለታለች::

በየምግብ ቤቱ በር ላይ የሚለጠፈው «ታሽጓል» የሚለው አሳዛኝ ድርሰት ደራሲ ይህ ሰው ነበር:: ያኔ በየማለዳው ወደ አንዱ ዳቦ ቤት ብቅ ይልና በቅርብ ያገኘውን ሙልሙል እንደ ብይ እያጦዘ፣ «ይህ ዳቦ አልመጠን አንሷል:: ሕዝቡን ለማስራብ ነው፤ ይህ ዳቦ አለመጠን ተልቋል፤ የሰፊውን ሕዝብ ሆድ ለመንፋት ነው? መልስልኝ!» ይልና በባለቤቱ ላይ ይደነፋል:: ከዚያም ቀዝቀዝ ባለ ድምፅ፣ «ለማንኛውም በዚህ መደዳ ያሉ ዳቦዎች መጠናቸው አጠራጣሪ ስለሆነ በኤግዚቢት መልክ እኛ ዘንድ ይቆያሉ፤» ይልና በቅርጫት ሞልቶ መኪናው ላይ ያስጭናቸዋል:: በማግሥቱ ቅርጫቱ ብቻውን ይመለሳል::

ይህ ሰውዬ የተባረረበት ምክንያት እንደሚከተለው ነው:: በሥልጣን ላይ እያለ ሁለት ጎረምሳ ልጆቹን በሥሩ ይሾማቸዋል:: የመሥሪያ ቤቱ ገምጋሚ ኮሚቴ ለምን እንደዚያ እንዳደረገ ሲጠይቀው፣ «አንደኛው ልጄ በየምግብ ቤቱ እየዞረ የምግቡን ጣዕም እና ጤንነት የሚያረጋግጥ ቀማሽ ነው:: ሁለተኛው ደሞ፣ ቀማሹ የተመረዘ ምግብ በልቶ ሲወድቅ አዝሎ ሆስፒታል የሚያደርስ ነው!» ብሎ መለሰ::

በሁለተኛው መሥመር በሚገኘው ወንበር ላይ አንድ መነጽራም ወጣት ፀጉሩን እንደ ነጠላ እየቋጨ፣ ከፊት ለፊቱ ከተቀመጠው ጀርመናዊ ጋራ ያወራል:: ወጣቱ የተለያዩ አዲስ ሳይንሳዊ የፈጠራ ግኝቶችን ለዓለም ለማበርከት እንዳቀደ እና ዕቅዱን ለማሳካት የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያስፈልገው ለጀርመኑ እየገለጸለት ነበር:: በአጠገቡ ትሪ ይገፍ ሳልፍ፣ "I am brilliant but a poor inventor" ሲል ሰማሁት:: ስመለስ በሚኖርበት ደሳሳ ጎጆ ውስጥ ያሉትን ዕቃዎች ሲዘረዝር አገኘሁት:: "I have got only a laboratory, a small bed and a chair" እያለ ሲናዘዝ:-

"What about a table;" አለው ጀርመኑ፣

"Well, I have a periodic table, sir!"

ሮዝ በተባለ መጽሔት ፓተንት በሚል ዓምድ ሥር የዚህን መነጽራም ወጣት ታሪክ ታትሞ እንዳነበብሁ ትዝ አለኝ:: ይህ ወጣት መንፈሳዊ መዝሙር ብቻ የሚጫወት ቴፕሬከርደር ከመፈልሰፉም በላይ በጄኔሬተሮች ላይ የሚገጠም ድምፅ ማዳፈኛ (ሳይለንሰር) ለመፈልሰፍ ተሰናድቷል::

አገራችን በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ገና ወጣኒ ናት:: ይህን



ለማስረዳት አንድ ምሳሌ ልጥቀስ:: ከጥቂት ቀናት በፊት ሬዲዮ ሳዳምጥ በእንግድነት የቀረበ የላውንደሪ ባለቤት፣ «በመብራት ኀይል እጥረት ምክንያት በቅርቡ በፀሐይ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ሥራችንን እንቀጥላለን!» ሲል ተናገረ:: ጋዜጠኛውም፣ «በፀሐይ ቴክኖሎጂ በመታገዝ የምትሠሩት እንዴት ነው?» ብሎ ቢጠይቀው፣ «ልብሱን አጥበን ፀሐይ ላይ እናሰጣለን ማለቴ ነው!» ብሎ መለሰ:: ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ እንደ ቀንዳም ፈረስ ተረት በሆነበት አገር ይህ መነጽራም ወጣት ሊታገዝ ይገባው ነበር፤ ግን ከወሬ በስተቀር ማንም ሊተባበረው አልፈቀደም::

ለምሳሌ፣ አባተ የነገረኝ ወሬ እንዲህ ይላል፤ መነጽራሙ ወጣት አገር ቤት እያለ በመጸዳጃ ሳሕኖች ላይ የሚገጠም ኮምፒዩተር ፈልስፎ ነበር:: ኮምፒዩተሩ በሚሞከርበት ቀን የውጭ እና የአገር ውስጥ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ባለሞያዎች በተገኙበት ወጣቱ መጸዳጃ ሳሕኑ ላይ ተቀምጦ ከተጸዳዳ በኋላ "Delete" የሚለውን ክሊክ ሲያደርግ መጸዳጃ ሳሕኑ ላይ የነበረው ፍግ እልም ብሎ ጠፋ:: ወዲያው "perfume" የሚለው ላይ ክሊክ ሲያደርግ መጸዳጃ ክፍሉ በከርቤ እና በሉባንጃ መዓዛ ተሞላ:: በቦታው የነበሩ ታዛቢዎች ክንብንባቸውን አውልቀው ክፍሉን በጭብጨባ አናጉት:: በጭብጨባው የተደናገረው ወጣት ሳይንቲስት በስሕተት "Undo" የሚለውን ክሊክ ሲያደርግ ያለፈው ትውልድ የተጸዳዳው ሳይቀር ወጥቶ አካባቢውን አጥለቀለቀው:: በዚህ የተነሳ መነጽራሙ ወጣት አካባቢን በመበከል ተከሶ የሁለት ዓመት እስራት ተፈርዶበት ለአራት ዓመት ታሰረ::

«ሁለት ዓመት ተፈርዶበት እንዴት አራት ዓመት ይታሰራል?» ብዬ ጠይቄው ነበር፣ ታሪኩን የነገረኝን አባተ:: የሰጠኝ መልስ የሚከተለው ነው:: መነጽራሙ ወጣት ይኖርባት

በነበረችው ክልል ውስጥ የእትት ብሔር እና የእግግ ብሔር ተዳብለው ይኖራሉ:: የፌዴራሊዝም ሥርዐት በሰጣቸው መብት መሠረት የራሳቸውን ፍርድ ቤት እና ወኅኒ ቤት አቋቁመው ነበር:: የእትት ብሔር ፍርድ ቤት መነጽራሙን ወጣት ሁለት ዓመት ሲፈርድበት፣ የእግግ ብሔር ፍርድ ቤት ከተጎራባቹ ብሔር ጋራ ያለውን እኩልነት ለማስመስከር ወጣቱን አስመጥቶ ሌላ ሁለት ዓመት ፈረደበት::

መነጽራሙ ወጣት አንድ ቀን ካፌው ውስጥ ሞተ::

በሞቱ ዋዜማ ሞቱን የሚተነብይ ሕልም ዐይቼ ስለነበር ከሥራ ቀረሁ:: ሕልሙ እንዲህ ነው:: የጥራት ደረጃ ተቆጣጣሪ የነበረው ሰውዬ በካፌያችን በር ላይ ቆሞ የተስተናጋጆችን ልብስ እያየ ያስገባል:: ብዙ ተስተናጋጆች ልብሳቸውን እንደ መታወቂያ እያሳዩ ይገባሉ:: ድንገት መነጽራሙ ወጣት ሰልቫጅ ካፖርት ለብሶ ይመጣል:: የጥራት ደረጃ ተቆጣጣሪው፣ «ሰልቫጅ ለብሰህ ወደዚህ መግባት አትችልም!» ብሎ ይከለክለዋል:: ወጣቱ ግን አሻፈረኝ ብሎ በመታገል የጥራት ደረጃ ተቆጣጣሪውን ከካፌው መዝጊያ ጋራ ደርቦ ይዞት ወደ ውስጥ ይገባል::

ከሕልሜ ስነቃ ሰልቫጅ የሙት ልብስ ስለሆነ ወጣቱ እንደሚሞት ተገነዘብሁ:: እኔም በሞቱ ላለመግባት(ገዳዩ ላለመሆን) ወደ ካፌው ሳልሄድ ቀረሁ:: በሁለተኛው ቀን ወደ ካፌው ስመለስ፣ አስተናጋጁ አባተ በነፍስ ገዳይነት ተጠርጥሮ ወደ ፖሊስ ጣቢያ መሄዱን ሰማሁ:: ምን ደረሰበት? ከመርማሪው ፖሊስ ጋራ ያደረገውን ምልልስ እንደሚከተለው አቀርባለሁ::

* * *



አባተ፣ በወረዳ ምንትስ ፖሊስ ጣቢያ ከመርማሪው ፊት ለፊት ቁጭ ብሏል:: መርማሪው ከፊቱ ያለውን መዝገብ ሲያገላብጥ ከቆየ በኋላ፣ «አቶ አባተ ቤተሰብ አለህ?» ብሎ ጠየቀ::

«አለኝ፣ ማስረጃ ካስፈለገ. . .!» አለና አባተ ከኪሱ ውስጥ አሮጌ አልበም አውጥቶ የመጀመርያውን ገጽ ገልጦ፣ «ከግራ ወደ ቀኝ ይህቺ ምሽቴ ናት፤ ይሄ ልጄ ነው፤ ይሄ ደግሞ አባቴ ነው፤ ይሄ ባዶ ቦታ ነው!» እያለ ሊቀጥል ሲል ፖሊሱ፣ «ልጁ ቁጭ አባትህን ይመስላል!» ብሎ አቋረጠው::

«ቢመስልም አይገርመኝም!. . እኔ ለሥራ ወጣ ስል ጠብቆ አባቴ እኛ ቤት ይመጣ እንደ ነበር ደርሼበታለሁ::»

«አስተናጋጅ ከመሆንህ በፊት ምን ትሠራ ነበር?»

«ከብት አድልቤ እሸጥ ነበር:: ጌታዬ እንደሚያውቁት፣ በአገራችን የክርስቲያን እና የሙስሊም ሥጋ ቤት ብሎ መለየት የተለመደ ነው:: እኔም ልዩነቱን ለምን ከበሬው አንጀምሬውም በማለት የክርስቲያን እና የሙስሊም በሬ እሸጥ ነበር!»

«የክርስቲያን እና የሙስሊም በሬ ልዩነቱ ምንድን ነው?»

«የክርስቲያኑ በሬ ቆዳው ላይ መስቀል ይነቀሳል፣ ጌታዬ!»

«ከከብት አድላቢነት ወደ አስተናጋጅነት ያደረግኸው ሽግግር እንዴት ነው? ትንሽ አልተራራቀም?» አለ ፖሊሱ ፈገግ ብሎ፤

«እንደኤ እንደኤ አልተራራቀም:: ያው ከከብት አድላቢነት ወደ ሰው አድላቢነት ነው የተሸጋገርሁት!»

ከዚህ ማኩብኮቢያ በኋላ ፖሊሱ በቀጥታ ወደ ምርመራው ገባ።

«ከሟቹ ጋራ የነበራችሁን ግንኙነት ብትገልጽልኝ?»

«ሟቹ በሕይወት በነበረበት ጊዜ የነበረን ግንኙነት ያስተናጋጅ እና የተስተናጋጅ ነው!»

«ሟቹ በሞተበት ቀን የነበረውን ሁኔታ ትገልጽልኛለህ?»

«ወደ ካፌያችን መጥቶ ውኃ አዘዘ፤ አቀረብሁለት። በአጠገቡ ተቀምጠው ሻይ ሲጠጡ የነበሩ ሰዎች እንደ ነገሩኝ ወዲያው ከኪሱ ብዙ ክኒኖች አውጥቶ ባቀረብሁለት ውኃ እያወራረደ ዋጣቸው። አይ የቀን ጎዶሎ. . .ምነው ውኃውንም እንደ ክኒኑ ከቤቱ ይዞት በመጣ. . .!»

«በጊዜው በሟች ፊት ላይ የተስፋ መቁረጥ ስሜት አንብበሃል?»

«ንባብ ላይ ያን ያህል ነኝ፣ ጌታዬ!»

«አልገባህም፣ ስትመለከተው ተስፋ ቆርጧል ብለህ ገምተህ ነበር?»

«መቼስ በርገር በሚቀረጠፍበት፣ ኮካኮላ እንደ ውኃ በሚፈስበት ካፌ ውስጥ አንድ ሰው የቧንቧ ውኃ ብቻ ካዘዘ ተስፋ ቢቆርጥ ነው፤ ግና መልሶ እጁን በርሳው ውስጥ ሲከት ሳይ፣ የምሳ ዕቃ ሊያወጣ ነው ብዬ ተዘናጋሁ።»

«ከዚያስ?»



«ከዚያ ልቤን ሲያወልቀው ለነበረ ተስተናጋጅ ስቴክኒ አድርሼ ስመለስ፣ ያ ወጣት ወንበሩን ላይ ዘፍ ብሎ ተኝቷል። አይ ምስኪን! ይሄኔ ሮንድ አድሮ ይሆናል ብዬ ቸል አልሁት።»

«የመጀመርያ ርዳታ አላደረግህለትም?»

«አድርጌለታለሁ፤ ተኝቷል ብዬ ስላሰብሁ ዘፈኑን ቀነስሁለት፤ በተጨማሪም አንገቱን ወደ ወንበር መደገፊያው አቃናሁት። በእኔ ቤት በሥነ ሥርዐት ማስተኛቴ ነበር። ለካ አጅሬ በሥነ ሥርዐት እየሞተ ኖሯል።»

«ሟች ከመሞቱ በፊት የተናገረው ነገር አለ?»

«ሰው ሲኖር መናገሩ መች ይቀራል፤»

«አባባሌ አልገባህም፣ ከመሞቱ ጥቂት ደቂቃዎች በፊት የተናገረው ነገር አለ ወይ?»

«የለም። ባይሆን ከጎኑ የተቀመጠ ተስተናጋጅ ተናግሯል፤»

ፖሊሱ በረጅሙ ተንፍሶ ወደ ወንበሩ መደገፊያ ተንጋሎ ሲያስብ ከቆየ በኋላ፣ «አቶ አባተ፣ ለማንኛውም ሟች ለነገይቱ ኢትዮጵያ ብዙ ምርምሮችን ያበረክታል ተብሎ የታሰበ ወጣት ነበር። ምን ያደርጋል፣ ብዙ የዕንቅልፍ ክኒኖችን በመውሰድ ራሱን አጥፍቷል፤» ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ።

አባተ አንገቱን ደፍቶ ትንሽ ካሰበ በኋላ፣ «ሕእናንተ ባላውቅም. . .» ብሎ ጀመረ። «. . .ሟች የዋጠው የዕንቅልፍ ክኒን ከሆነ ጊዜው ይርዘም እንጂ መንቃቱ አይቀርም፤ ቁርጡ እስኪታወቅ ድረስ መንግሥት አስከሬኑን መቅበር ትቶ በወዶገባ ዘበኛ

ቢያስጠብቀው ይበጃል ባይ ነኝ፡፡»

መርማሪው ፖሊስ አባተን በንቀት ለጥቂት ደቂቃ ካተኮረበት በኋላ መሄድ እንደሚችል ገለጸለት፡፡ አባተ መሄድ ሲገባው አላስፈላጊ ጥያቄ አመጣ፡፡

«ጌታዬ፣ ለመሆኑ በምን አበሳዬ ነው ፖሊሶች ቤቴን እንዲፈትሹ የተደረገው?»

«ቤትህ በመፈተሹ የተጎዳኸው ነገር አለ?» አለ ፖሊሱ፡፡

«ለመጎዳትስ አልተጎዳሁም፡፡ እንዲያው ፖሊሶቹ ቤቴን በጣም ከመፈተሻቸው የተነሳ ለዐሥር ዓመት ያህል ፈልጌ ያጣሁትን የልደት ካርዴን አገኙልኝ፤. . .ብቻ ከሕግ አንጻር ፍተሻው አግባብነት አለው ወይ ለማለት ነው?»

«አቶ አባተ፣» አለ ፖሊሱ፣ «ሟች ራሱን ሲያጠፋ መተባበር ወንጀል መሆኑን አታውቅም?»

«እንዴት አድርጌ ነው የተባበርሁት?» አባተ ጮኸ፡፡ «ውኃ ጠየቀኝ፤ ውኃ አመጣሁለት፤ መቼም ገመድ በትሪ አላቀረብሁለትም፤ ሰው ለመሞት ከተዘጋጀ የሚተባበረው ቀኑ ነው፡፡ አዩ ጌታዬ፣ መቼም በዚህ ዘመን ራስን ለመግደል የሚያበቃ ብዙ ነገር አለ፡፡ በዘመድ ተስፋ ያጣ ሰው በገመድ ተስፋ ቢያደርግ አይገርመኝም፡፡ ያም ሆኖ እንዲህ ዐይነቱ ሰው ሲገጥመኝ ልቡ እስኪጠፋ እመክረዋለሁ፡፡ አንድ ባልንጀራዬ ባለፈው ራሱን ለመግደል የባቡር ሐዲዱ ላይ በጀርባው ተኛ፡፡ የምድር ባቡር ብልሽት ስለ ገጠመው ሥራ ካቋረጠ ዘመን የለውም፤ እዚህ ላይ መተኛት ምንም አይጠቅምህም፤ተነሥ ብዬ ብመክረው፣



«እምቢ፣ ባቡሩ እስኪጠገን ድረስም ቢሆን እጠብቃለሁ፤» ብሎ ድርቅ አለ፡፡ ለካ ቀኑ ደርሶ ኑሯል፡፡ አመሻሽ ላይ ከወፍጮ ቤት የሚመለሱ እህዮች ሐዲዱን ሲያቋርጡ ረግጠው ገደሉት፡፡ ለወሬ የቸገረ ነገር!!»

መርማሪው ፖሊስ ከአባተ ጋራ የነበረው ቆይታ መጠናቀቁን ለማሳየት ሰዓቱን ደጋግሞ ከተመለከተ በኋላ፣ «መሄድ ትችላለህ» ብሎ አጉተመተመ፡፡

አባተ «ጥሩ» ብሎ ከወንበሩ በከፊል ከተነሣ በኋላ ተመልሶ በመቀመጥ፣ «. . .አንድ ነገር ብቻ ልበል፤ እሱም ምንድን ነው? አዎ፣ ፖሊስ ጣቢያ አንዴ ከመጣሁ አይቀር እግረ መንገዴን የምጠቁመው ነገር አለኝ፡፡»

«ምንድን ነው?» አለ መርማሪው ጣራ ጣራውን እያዬ፤

«ምንድን ነው ላሉት፣ ጌታዬ! ነገሩ ወዲህ ነው፡፡ ከጥቂት ቀኖች በፊት አጥቤ ያሰጣሁት ሱሪ ባልታወቁ ሰዎች ተዘርፏል፡፡ የክፍለ ከተማው ፖሊስ ከኅብረተሰቡ ጋራ በመተባበር ሱሪዬን ቢያስመልስልኝ ደስ ይለኛል ጌታዬ፤»

ፖሊሱ በጣም ስለ ተናደደ ለጊዜው ቃል ተሳነው፤ ወዲያው ግን፣ ለዘበት እንደ ተዘጋጀ ሰው እስኪቢርቶውን ካቀባበለ በኋላ፣ «የወገብ ቁጥሩን ልትነግረኝ ትችላለህ?» አለው»

«ዐሥራ ሁለት፣ ጌታዬ!» አለ አባተ፤

«ገምባሌ ነው ወይስ ሱሪ?»

«እኔ እንግዲህ ሱሪ ነው ብያለሁ፣ ጌታዬ!»

«የዬት አገር ሱሪ ነው?»

«የቻይና!»

«የቀለሙ ዐይነት?»

«ከመታጠቡ በፊት ነው ወይስ ከታጠበ በኋላ፣ ጌታዬ?»

«በጠፋበት ጊዜ የነበረውን ቀለም ነው የጠየቅሁህ፤»

«አረንጓዴ»

«ጥሩ!» አለ መርማሪው፣ «ሱሪህን ሌባ ሊሰርቀው ይችላል፤ ዐሥራ ሁለት ቁጥር የቻይና ሱሪ ለሌባው ያን ያህል ይጠቅመዋል ብዬ አላስብም። ለነገሩ ይጠቅመዋል። ቢያንስ ኩባያ ሊለውጥበት ይችላል። በሌላ በኩል ጥጃ በልቶት ሊሆን ይችላል የሚል ጥርጣሬም አለኝ። ዐየህ፣ የአዲስ አበባ ጥጃ ሣር ቢያጣ የሣር ፍራሽ ይበላል። የሣር ፍራሽ ቢያጣ አረንጓዴ ሱሪ ይበላል። ያም ሆነ ይህ ፖሊስ አስፈላጊውን ክትትል ስለሚያካሄድ አንተ ሥራህን እየሠራህ ውጤቱን ተጠባበቅ።»

«ጌታዬ፣» ቀጠለ አባተ፣ «ያለፈው አንዴ አልፏል መቼም። መጭውን ሳስብ ግን ይጨንቀኛል፣ በጣም!! አሁን የለበስሁት ሱሪዬ የመጨረሻው ስለሆነ ይሄ ከተሰረቀ ነገ ቢሮዎት የምመጣው ጋቢ አገልድሜ ነው። ምን ለማለት ፈልጌ ነው፣ ከእንግዲህ በልብስ ማስጫው አካባቢ ጥበቃው ቢጠናከር!»

«አይበቃም?» ፖሊሱ አምባረቀ፣ «ትንሽ አታስብም! ያንተ ሱሪ አስተማማኝ ጥበቃ እንዲደረግለት ከፈለግህ ለምን ቤተ መንግሥት አጥር ላይ አታሰጣውም? አሁን ከዚህ አትነሣም?»

አባተ ከመርማሪው ክፍል ወጥቶ የሮጠ የቤቱ ግድግዳ አቆመው።



# ምዕራፍ 15

ዛሬ መክሊት ወደ ቤትሆቨን ካፌ ብቅ አላለችም። አቶ ያን ፌስታል ሙሉ ስጦታ ይዞ መጥቶ ይጠብቃታል። እየጠበቀ ስልክ ደጋግሞ ቢሞክርም ስልኳ አይመልስም፣ ወይም ተዘግቷል። ግን እሱ ተስፋ ሳይቆርጥ ተግቶ መጠበቁን ቀጠለ። ጥቂት ወዲያ ወዲህ ብዬ ፋታ አግኝቼ አጠገቡ ስቆም፣ በላሊበላ ስላደረገው የማይረሳ ጉብኝት ይተርክልኝ ጀመር። በትረካው መካከል የሴት ጫማ ቋቋታ ከበስተጀርባው ሲሰማ ትረካውን አቋርጦ ይዞርና ይመለከታል። ያ ቋቋታ ከመክሊት ጫማ የመነጨ አለመሆኑን ሲያውቅ እንደገና ፊቱን መልሶ፣ «ምን ላይ ነበርሁ?» ብሎ የጠፉ ቃሎቹን ይፈልጋል። ትረካውን ሲጀምር የላሊበላን ሕንጻዎች በማድነቅ ነበር። ሰዓቱ እየገፋ ሲሄድ፣ መክሊት እንደማትመጣ ቁርጡን ሲያውቅ፣ በላሊበላ ሕንጻዎች ዙሪያ ሰፍረው ቱሪስት ስለሚያስቸግሩ ለማኞች አንሥቶ ያማርር ጀመር።

•

ከሥራ ሰዓት በኋላ መክሊትን ፍለጋ ቤቷ ሄድሁ። ስገባ፣

አልጋዋ ላይ ተንበልብላ ጉንጯን በእጆቿ አስደግፋ በመስኮት በኩል ውጭ ውጩን ስታይ ነበር::

«ምነው?» አልኳት ከጥቂት መፋጠጥ በኋላ፤

«ምነው?» አለችኝ ዞራ ሳታየኝ፤

«ከመሥሪያ ቤት ለምን ቀረሽ?» የሰውዬውንስ ስልክ የማታነሽው በምን ምክንያት ነው? በረጅሙ ተንፍሳ፣ «ትላንት ከኤክስ ቦይፍሬንዴ ከሳሚ ጋራ እንደ ተቀጣጠርን ነግሬህ የለ!»

ራሴን በአዎንታ ነቀነቅሁ:: «ምን ተፈጠረ?»

መክሊት፣ ተንኮለኛ ፈገግታ አሳይታኝ ፊቷን በትራሷ ውስጥ ሸሸገች::

የሆነው ሁሉ ገባኝ::

«እንዴት እንዲህ ልታደርጊ ቻልሽ?. . .ልክ አይደለሽም!»

ተንደቀደቅሁ::

«ነገሩ እንዴት ተጀምሮ እንዴት እንደ ተፈጸመ ሳስበው ሕልም ይመስለኛል፤» ብላ ጀመረች::

ቀጥላ እንደ ነገረችኝ ከሆነ፣ ከሳሚ ጋራ ተቀጣጥረው ከተገናኙ በኋላ ብዙ አንጀት የሚበሉ ነገሮችን ነግሯታል:: «ፍቅርሽን ገፍቼ ከሄድሁ በኋላ አልቀናኝም!» ብሎ ሁለት ሲጃራ አከታትሎ አጨሰባት:: ከእሷ ጋራ ከተለያዩ በኋላ ሥራ ስላጣ በታክሲ ረዳትነት ለመሥራት ሞከረ:: በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ግብ ጠባቂ የነበረ ወጣት፣ አሁን የታክሲ ረዳት



መሆን ስለ ከበደው የኑሮ ግዴታን እና ክብሩን ለማስታረቅ የሆነ ነገር ማድረግ ነበረበት:: ከዚህ በፊት ወያላዎች እንዳደረጉት «ስታዲየም፣ ሜክሲኮ» ብሎ ከመጣራት የቦታ ዝርዝሮችን በካሴት አስቀርጾ በቴፕ ማጫወት እንደሚሻል ሾፌሩን ለማሳመን ሞከረ:: «ወያላ» የሚለው መጠሪያ «የሚኒባስ ዲጄ» በሚል እንዲተካ ሐሳብ አቀረበ:: የሚኒባሱ ባለቤት በግርምት ሲሰሙት ከቆዩ በኋላ፣ «እናስብበትና እንጠራሃለን፤» ብለው አሰናበቱት፤ እስከ አሁን አልጠሩትም::

ችግር ሲጠናበት አገሪቱን ጥሎ ወደ አሜሪካ ለመሄድ መጣር ጀመረ:: ነገር ግን በምን መንገድ ይሂድ? አስቦ አስቦ ዘዴ መጣለት:: አንድ አሜሪካዊ አግኝቶ ሊደበድብ አሰበ:: እንደ እሱ ሐሳብ ከሆነ አሜሪካ በዜጋዋ ላይ በሚደርሰው ጥቃት ትናደድና፣ «ወንጀለኛውን አሳልፈሽ ስጭኝ፤» በማለት ኢትዮጵያን ትጠይቃለች:: በዚህ መሠረት ሳሚ ወደ አሜሪካ ይላክና ፍርድ ቤት ቀርቦ ይፈረድበታል:: ከዚያ እጅግ ምቹ እና ጽዱ በሆነው ወኅኒ ቤት ጥቂት ወራት ታስሮ ይለቀቅና እዚያው አሜሪካ ዘና ብሎ መኖሩን ይቀጥላል:: ነገሩን ሲሞክረው ግን እንዳሰበው አልሆነም:: አሜሪካ ኤምባሲ አካባቢ ያገኘውን ደከም ያለ አርመን በስሕተት ደብድቦ ሲሮጥ ፌዴራል ፖሊሶች በቁጥጥር ሥር ካዋሉት በኋላ ሸዋሮቢት ወስደው ገርፈው ለቀቁት::

ለመክሊት ይህን በነገራት ጊዜ አለቀሰች:: እርሱ ግን በዚህ ተበረታቶ እጅግ ስሜታዊ በሆነ ድምፅ፣ «መክሊትዬ፣ ጆርባዬ ላይ የተጋደመውን ሰንበር ስታይውማ ዕድሜ ልክሽን ታነቢልኛለሽ፤» ብሎ ከኪሱ ውስጥ ቆራጣ ሶፍት ወረቀት አውጥቶ ደረቅ ዐይኑን አበሰ:: አስከትሎም፣ በጄኔሬተር ድምፅ ከተናፈጠ በኋላ፣ «የለም፣ ሹራቤን አውልቄ ካላሳየሁሽ በስተቀር አታምኚኝም)»

ብሎ በአቅራቢያው ወደሚገኝ አልቤርጎ ይዟት ገባ።

ከዚያ ሹራቡን አወለቀ። ቀጥሎ ቀበቶውን ማላላት ሲጀምር፣ «የምታሳየኝ ጀርባህን አይደለም እንዴ?» ብላ ጮኸችበት። «ታፋዬ ላይም ረግጠውኛል፤ እግረ መንገዴን ላሳይሽ ብዬ ነው፤» ብሎ ሱሪውን አወለቀ።

«ርቃኑን ቆሞ ሳየው፣» ትላለች መክሊት ትረካዋን ስታጠናቅቅ፣ «በቃ፣ ምን ልበልህ የድሮው ነገር በሙሉ ተቀሰቀሰብኝ። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ራሳችንን አንሶላ ውስጥ ተቃቅፈን አገኘነው» «በርግጥ ሰውነቱ ላይ የግርፊያ ምልክት ነበረበት?» አልኳት።

«አንተ ደግሞ፣ እንዴት ያለ ጥያቄ ነው የምትጠይቀኝ? በዚያ ሰዓት ይህን እንዴት ላይ እችላለሁ?»

«ታዲያ አሁን የጀርመኑን ነገር እንዴት ልታደርጊ ነው?»

«እንጃ!! በጣም የሚያስጨንቅ ነገር ነው። እሱን እያሰብሁ እያለ ነበር የመጣኸው።»

ከጥቂት ዝምታ በኋላ ተነሥታ መለባበስ ጀመረች።

«ምን ይሻላል ትላለህ?» አለችኝ።

ድንገት የከበደ ሚካኤልን ያላለቀ ግጥም አስታወስሁ፤

*የሰው ልጅ ዕድል ነው፣*

*ወደ ኀጢአት መግባት፣ ከኀጢአትም መውጣት፣*

*ያመነዘረ ሰው፣*

*ገላውን ያጠራል በንስሐ ቅጣት፣*



*ትልቁ ኩነኔ . . . !(የዚህ ስንኝ መድፊያ ቃሎች ጠፍተዋል)*

* * *

በነገራችን ላይ፣ አንጋፋው ደራሲ እና ባለቅኔ ከበደ ሚካኤል ነፍሳቸውን ይማርና በመጨረሻ ዘመናቸው ወደ ካፌያችን ይመጡ ነበር። ገና እንዳየኋቸው ለመክሊት እንዲህ አልኳት፣ «እኒህ ሰውዬ ታላቅ ሰው ስለሆኑ የሚናገሩትን መዝግቢ፤ የሚጥሉትንም ሰብስቢ!» እርሷ ግን አላመነችኝም። አጭር ሰው ታላቅ ይሆናል ብላ መቀበል ከበዳት። ያልሁት አልቀረም። ከበደ ሚካኤል ከሞቱ በኋላ የብሪትሽ ሙዚየም በተወካዩ በኩል ከባለቅኔው ጋራ የተነካኩ ዕቃዎችን እያፈላለገ በውድ ዋጋ መግዛት ጀመረ። እኔም በዚያን ሰሞን የሁለት ወር ውዝፍ ኪራይ ስለነበረብኝ አንድ አፈ ሰፊ ብርጭቆ ወስጄ ባለቅኔው እኛ ካፌ በሚመጡበት ጊዜ ሻይ የሚጠጡት በዚህ ብርጭቆ ነበር፣ በማለት እንዲገዙኝ ጠየቅኋቸው።

የብሪትሽ ሙዝየም ተወካይም፣ «ብርጭቆውን ከመግዛታችን በፊት ከባለቅኔው ጋራ ግንኙነት እንዳለውና እንደሌለው ለማረጋገጥ እንመርምረው!» ብሎ ብርጭቆውን ወደ ላብራቶሪ አስገባው። የላብራቶሪውን ውጤት በተስፋ ተሞልቼ መጠባበቅ ጀመርሁ። ሺሕ ብርጭቆ ሲያመላልሱ ከመኖር፣ አንድ የረባ ብርጭቆ ሸጦ መገላገል ይሻላል፤ አልሁ በልቤ። ከጥቂት ምርመራ በኋላ የሙዝየሙ ተወካይ፣ «የላብራቶሪ ውጤቱ በብርጭቆው ጠርዝ ላይ የታላቁን ሰው የከንፈር አሻራ አያሳይም! ስለዚህ ልንገዛህ አንችልም!» ብሎ አረዳኝ። ላሳምናቸው ሞከርሁ። የታላቁ ሰው የከንፈር አሻራ በብርጭቆው ላይ ያልታየበት ምክንያት ሰውዬው በስትሮ ስለሚጠጡ ነው! ብዬ ለመከራከር ሞከርሁ። በዘበኛ አባረሩኝ።

ትዝ ይለኛል፤ለመጀመርያ ጊዜ አንጋፋው ደራሲ የካፌያችንን ወለል ሲረግጡ ተስተናጋጆች ዐይናቸውን ማመን አቅቷቸው በአቅራቢያቸው ያገኙትን ወረቀት እና ወረቀት ነክ ነገር በሙሉ በመያዝ ሲያስፈርሟቸው ተሽቀዳደሙ:: ታላቁ ሰውም ለጊዜው አድናቂዎቻቸውን በጥንቃቄ ለመያዝ ጣሩ:: ብዕራቸውን በቁንጥ ከደረት ኪሳቸው ላይ ላጥ ያደርጉና ፊርማ ጠያቂውን እና ፊርማ መቀበያ ደብተሩን በፈገግታ አፈራርቀው ከተመለከቱ በኋላ፣ በሠዓሊ የእጅ ጥራት ፊርማቸውን ያሰፍራሉ:: እንዲያውም አልፎ አልፎ ከፊርማቸው አጠገብ፣ «ሕዝባችሁን እንድታገለግሉ አደራ እላለሁ፤» የሚል ምራቂ ማሳሰቢያ ጣል ያደርጉ ነበር::

ቀስ በቀስ ያስፈራሚዎች ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ ግን የአንጋፋው ደራሲ ትዕግሥት እና ብዕር እያለቀ ሲሄድ ይታይ ነበር:: አሁን፣ ከፊት ለፊታቸው የተገተረውን ፊርማ ጠያቂ ቀና ብለው ለማየት ሳይቸገሩ፣ ደብተሩን ከመመንጨቅ በማይተናነስ አሳሳብ ስበው «ከበደ» የሚል የሚነበብ ሳይሆን የሚገመት ፊርማ ያስቀምጡ ጀመር:: አንድ ቀን እንዲያውም ምርር ብለው፣ «. . .በገዛ ፊርማዬ አካኪ አካኪቪች አደረጋችሁኝ፤» ብለው አካኪ ዘራፍ አሉ - (ከጊዜ በኋላ ምዑዝን ጠይቄ እንደ ተረዳሁት አካኪ አካኪቪች በሩሲያ ልቦለድ ውስጥ የሚገኝ ጸሐፊ በመገልበጥ የሚተዳደር ገጸ ባሕርይ ነው፤)

የሆነ ጊዜ ላይ ታላቁ ሰው ተስተናጋጅነታቸውን ሁሉ ሳይዘነጉት አልቀሩም:: አንድ ቀን ከሚያስፈርሟቸው ሰዎች ጋራ ተደባልቄ የተጠቀሙበትን ቢል ባቀርብላቸው ቀና ብለው ሳያዩኝ በቢሉ ላይ ፊርማ እና «በርታ» የሚል ቃል አስፍረው ገፉልኝ::

እየዋለ እየሰነበተ ተስተናጋጆች ታላቁን ሰው ተላመዷቸው::



በአንጋፋ ከያኒነታቸው ሳይሆን በአንጋፋ ተስተናጋጅነታቸው ያስታውሷቸው ጀመር:: በተለይ አንድ ተስተናጋጅ በአንድ እጁ ሞባይሉን ከጆሮ ግንዱ አጣብቆ መልእክት እየተቀበለ፣ በሌላው እጁ ኪሱ ውስጥ ገብቶ የሚጽፍበት ቢያጣ፣ ከፊት ለፊቱ አቀርቅረው ግጥም እየጻፉ ከነበሩት ባለቅኔ እጅ ብዕራቸውን ነጥቆ ወሰደ:: ከዚህ ገጠመኝ በኋላ ባለቅኔው ብዕር መያዝን እርም አሉ:: የድንገቴ ግጥም ሲመጣላቸው መክሊትን አጣድፈው ይጠሯትና «ጻፊ» ብለው ያዟታል:: እርሷም የደንበኞችን ትእዛዝ በምትመዘግብበት ደብተር ግጥማቸውን ትመዘግባለች:: አንድ ቀን ትንሽ ሲያሰላስሉ ቆይተው ጠሯትና የሚከተለውን በቃላቸው ማጻፍ ጀመሩ፤

*የሰው ልጅ ዕድል ነው፣*

*ወደ ኀጢአት ገብቶ፣ ከኀጢአት መውጣት፣*

*ያመነዘረ ሰው፣*

*ገላውን ያጠራል፣ በንስሐ ቅጣት፤*

*ትልቁ ኩነኔ . . .*

ብለው ቤት መድፊያውን ሳይጨርሱ፣ መክሊትን ሌላ ተስተናጋጅ ስለ ጠራት መጻፏን አቋርጣ ሄደች:: በዚህ ምክንያት ታላቁ ሰው ልባቸው ተሠብሮ ወጡ:: ከዚያ በኋላ ወደ ካፌው አልተመለሱም::

ሕይወታቸው ካለፈ ከብዙ ጊዜ በኋላ የስንኙ መደምደሚያ ቃላት ምን ይሆን? በሚለት ራሴን እስጨንቅ ነበር:: እኒያን

የጠፉ ቃላት የት ላግኛቸው? ከጉጉቴ የተነሳ የሙት መንፈስ ጠሪ ደጅ እስከ መጥናት ደረስሁ። ግን የጠፉ ቃሎችን ለማግኘ ት ሳይሳካልኝ ቀረ።

ያን ቀን መክሊት አጠገቤ ሆና ስትለባብስ ከፊል ርቃኗን ገልመጥ እያደረግሁ ሳይ፣ በዐይኗ ብትይዘኝም አለማፈሯን አስተዋልሁ። ልብሷን ስትቀይር ወንድሟን እንኳ እንደምታፍረው ነግራኛለች። ያ ማለት ከወንድሟ ጋራ እንኳ ከዘሃ የቀጠነ፣ ኀቡእ ጾታዊ መሳሳብ አላት ማለት ነው። ይህ ጉዳይ አንድ ትልቅ መርዶ ነገረኝ። በእኔ ፊት ምንም አለማፈሯ ከቁም ሣጥኑ፣ ከአልጋው እና ከወንበሩ ለይታ እንደማትመለከተኝ ገለጸልኝ፤ እናም ተከፋሁ። እነሆ፣ ለብዙ ጊዜ ፈልጌ ያጣኋቸውን የከበደ ሚካኤልን የጠፉ ቃላት በትካዜዬ ውስጥ አገኘኋቸው፤

*የሰው ልጅ ዕድል ነው፣*

*ወደ ኀጢአት ገብቶ፣ ከኀጢአት መውጣት፣*

*ያመነዘረ ሰው፣*

*ገላውን ያጠራል፣ በንስሐ ቅጣት*

*ትልቁ ኩነኔ የሚያፈቅር ማጣት፤*



# ምዕራፍ 16

ይኸው ከመክሊት አጠገብ እየተከዝሁ ተቀምጫለሁ። አጠገቤ ቆማ፣ እኔን ትታ መስተዋቱን እያየች ትለባብሳለች። በተሻለ አነጋገር ለመግለጽ፣ ለጥቂት ደቂቃ ያህል ተገልጦ የቆየውን ሰውነቷን ከፊቴ እየለቃቀመች በጡት ማስያዣዋ ውስጥ፣ በካናቴራዋ ውስጥ፣ በጅንሷ ውስጥ ትከትታለች። እኔ እንደ ግድግዳው፣ እንደ ጣሪያው፣ እንደ መስኮቱ ጋርዷት ቆሜያለሁ። ከአጠገቤ ያለው ገላ ለአቶ ያን እና ለሳሚ እንጂ ለእኔ ሲል ከላይ አልወረደም። ምን ይደረግ? ሕይወት ላንዱ ዕንቁ ለሌላው ዕንቁልልጭ ናት። ይህን እያነሣሁ ስጥል፣ ከመክሊት ጋራ ፍቅር ባልጋራ እንኳ ብስጭት ልጋራ ብዬ የሚያናድዳት ነገር እፈልግ ጀመር።

«አንድ ነገር ልጠይቅሽ፣» አልኋት፤

«ጠይቀኝ»

«ከጆርመናዊው ጋራ ያለሽ ግንኙነት የምር ነው ወይስ የብር ነው?»

ፊቷን ከመስተዋቱ ሳትነቅል፣ «አንተ ደግሞ ብርን ሳታስገባ

ምንም ነገር ማሰብ አትችልም፤» ብላ ጮኸች።

ጩኸቷ ከጠበቅሁት በላይ ስለነበር ለጊዜው የምለው ጠፋኝ።

«ወድጄ አይደለም፤» አልሁ ጥቂት ካመነታሁ በኋላ፣ «በዚህ ዘመን ማንም ሰው ለጥቂት ሰከንዶች እንኳ ብርን ሳያስገባ ማውራትም ሆነ ማሰብ አይችልም፤»

«ለምን አልችልም?»

«አትችይም»

«እችላለሁ፤ከፈለግህ በጎምላ ብር እንወራረድ!»

«ይኸው ራስሽ አመጣሽው፤»

«እናትክን፣ ሠራህልኝ፤» አለችና ሣቀች።

ደስ አለኝ። ቀጥላ፣ ከፊት ለፊቷ የተደረደሩትን መአት የከንፈር ቀለሞች ስታማርጥ ቆየችና፣ «ግን እንዴት እንዲህ ልትል ቻልህ?» ብላ ጠየቀችኝ። በቀላሉ እንደማትለቀኝ ገባኝ። በአንድ ወቅት ጓደኛዬ ምዑዝን፣ ስለ መክሊት እና ስለ ጀርመናዊው ጓደኝነት ምን እንደሚሰማው ጠይቄው ጥቂት ካቅማማ በኋላ ከሚከተለው አንቀጽ ጋራ የሚቀራረብ አስተያየቱን ነገረኝ። «በጥንት ጊዜ አንድ ጻድቅ መነኩሴ ነበር። የኢትዮጵያ ብሔራዊ እምነት በብዙ አማልክት ማመን በሆነበት በዚያ ዘመን፣ መነኩሴው በአንድ አምላክ ስለ ማመን ለሕዝቡ ያስተምር ነበር። በጊዜው የነበረው ንጉሥ ይህን በሰማ ጊዜ መነኩሴውን አስጠርቶ በብዙ አማልክት እንዲያምን፣ አለበለዚያ በአገር ክሕደት ወንጀል እንደሚቀጣው ነገረው። መነኩሴው እምቢ ስላለ ንጉሡ በአደባባይ



አስፈርዶበት ምላሱን አስቆረጠው።

ያ መነኩሴ የተቆረጠ ምላሱን ባፉ፣ የጸና እምነቱን በልቡ ይዞ ሲኖር አንድ ቀን እስከ ዛሬ ሲያምንበት የቆየውን ሃይማኖት ውድቅ የሚያደርግ ሐተታ አግኝቶ አነበበ። ይሄኔ ደነገጠ፤ ተርበደበደ፤ ለማስተካከል የሚችልበት፣ የራእይም ሆነ የዕውቀት አቅም አልነበረውም። ያም ሆኖ መነኩሴው በድሮ እምነቱ ጸንቶ ለመቀጠል ወሰነ። ምላሱን ያህል ነገር የሠዋበት ሃይማኖት እንዴት ሐሰት ሊሆን ይችላል? እምነቱን በከፈለው መሥዋዕትነት መጠን መዘነው። ይኸውልህ አብዛኛው በዓለም ላይ ያለ ፍቅርም ሆነ አይዲዮሎጂ በዚህ ስሜት ላይ የተመሠረተ ነው። አቶ ያንን ውሰድ። መክሊት ከእርሱ ጋራ በሆነችበት አጭር ጊዜ ውስጥ ቢያንስ መቶ ሺሕ ብር ተቀብላዋለች፤ መቶ ሺሕ ብር ከወጣ በኋላ እንደማትወደው ቢሰማው ምን ያደርጋል? ግንኙነቱ ውሸት ነው ብሎ የሚያቆም ይመስልሃል? መቶ ሺሕ ብር የፈሰሰበት ግንኙነት እንዴት ውሸት ሊሆን ይችላል?»

መክሊት በጥሞና ካዳመጠችኝ በኋላ፣ «ምዑዝ ይህን ብሏል?» አለችኝ። በአዎንታ ራሴን ነቀነቅሁ። ከመስተዋቱ ፊቀቅ ብላ አልጋው ጠርዝ ላይ ቁጭ ካለች በኋላ፣ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ያህል ራሷን ስትነቀንቅ ቆይታ፣ «ይህ የብዙ ወንዶች ችግር ነው፤» ብላ ጀመረች፤ «የእኛ ወንዶች አንዲት ሴት ከነጭ ጋራ ስትሄድ ካዩ አውሬ ይሆናሉ። ሌላ ጊዜ አይተውኝ የማያውቁ ሁሉ ከእሱ ጋራ ስሄድ አፍጥጠው ይመለከቱኛል። መመልከት ብቻ አይደለም በግልምጫ አንሥተው ያፈርጡኛል። ምን አገባቸው? የት ያውቁኛል? አንድ ወንድ፣ በአጋጣሚ የአንድ አገር ልጆች ስለሆን ብቻ በገላዬ ላይ የይገባኛል ጥያቄ የማንሣት መብት አለው?. . .ፈረንጅ ሁሉ እንደ ሀብታም፣ ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንደ

ድሃ ስለሚቆጥር ከፈረንጁ ጋራ የተገኘች ያበሻ ሴት ገላዋን በገንዘብ የለወጠች እንደ ሆነች ተደርጋ ትወሰዳለች፤ አለቀ። ሥራ፣ ፍቅር፣ ከጾታ ጋራ ያልተገናኘ ጓደኝነት ከግምት አይገባም፤ አዝናለሁ። ሌላው እንዲህ ቢያስብ አይገርመኝም። አሪፍ ጭንቅላት አለው ብዬ የማስበው ምዑዝ እንዲህ ሲያስብ ግን ያሳዝናል።»

«ማዘን የለብሽም፤ በሌላ ጊዜ ምዑዝ ከዚህ የተለየ ነገር ብሏል!» አልሁ።

«ምን አለ?» አለች በኩሪፊያ ከንፈሯን ጥላ፤

«ከፈረንጅ ጋራ ያላቸው ግንኙነት የረጂ እና የተረጂ ያልሆነ፣ ተፈጥሮ ባጎናጸፈቻቸው ኀይል ተማምነው የሚኖሩ ሁለት ዐይነት ጥቁሮች በአፍሪካ ይገኛሉ። እነርሱም የሶማሌ የባሕር ሽፍቶች እና የኢትዮጵያ ቆነጃጅት ናቸው፤» ብሏል።

«ሊል ይችላል፤ ግን በፊት የተናገረውን የሚክስ አባባል አይደለም፤» ከተቀመጠችበት አልጋ ተነሣችና፣ «በድሃ አገር መኖር ግን እንዴት ጣጣ ነው፤» ብላ ተከዘች።

ይኸው እንግዲህ ትካዜዬን አስረክቤያት ወደ ፈገግታዬ ተሸጋገርሁ። በድሃ አገር ለመኖር የሚደረገው ግብግብ አሥቂኝነቱ ከመቼውም ጊዜ በላይ ጎልቶ ታሰበኝ። አሁን ለምሳሌ በየሳምንቱ የምከታተለው «ጤናችን» የተባለ በብዙ ቅጅ የሚታተም ጋዜጣ አለ። በአገራችን ከጤነኛው በሽተኛው በቁጥር ስለሚበልጥ በሕክምና ዙሪያ የሚጽፍ ጋዜጣ በብዙ ቅጂ ቢሸጥ አይገርምም፤ ግን ሁሌ ፋሲካ የለም።

በአንድ ወቅት ሕዝቡ ከሕክምና ይልቅ ወደ ፖለቲካ ማዘንበል አመጣ። ከፓናዶል ይልቅ የፓናል ውይይትን መምረጥ ጀመረ። ይሄኔ የጋዜጣው አዘጋጅ ከጊዜው ጋራ ራሱን ለማወዳጀት በጤና

ወሬ ውስጥ ጥቂት ፖለቲካ በተን በተን እያደረገ ማተም ጀመረ። በጋዜጣው ታትመው ይወጡ ከነበሩ ዜናዎች ውስጥ የሚከተሉትን አስታውሳለሁ፤

- በወር ቢያንስ አንድ ጊዜ ሰላማዊ ሰለፍ ማድረግ የደም ዝውውርን እንደሚያሻሽል ተገለጸ።

- የብረት ቆብ ከማያደርጉት አድማ በታኝ ፖሊሶች በበለጠ የሚያደርጉት ለጭንቅላት ካንሰር የተጋለጡ መሆናቸው ተመለከተ።

- የተቃዋሚ ፓርቲው መሪ ቀዶ ሕክምና ያደረጉበት ሆስፒታል ሊታደስ ነው።

- ከነምሳ በላይ ሕፃናት በትላንትናው ዕለት ተከተቡ። ከተከታቢዎቹ መካከል የፕሬዝዳንቱ የልጅ ልጅ ይገኙበታል።

ነዋሪነታቸው በባሕር ዳር የሆነው የባህል ሐኪም፣ መሪጊታ በልስቲ አሻግሬ ለመጭው ምርጫ እንደሚወዳደሩ ተጠቆመ።

ይህን ስነግራት መክሊት በምላሹ የሚከተለውን ገጠመኝ አወጋችኝ።

* * *

የዛሬውን አያድርገውና የመክሊት ወንድም በአንድ ወቅት የዐፄ ቴዎድሮስን ገጸ ባሕርይ ወክሎ ለመጫወት ብዙ ጥናት ያደርግ ነበር። የንጉሡን ታሪክ በፍጹም ታማኝነት ለማቅረብ ካለው ቀናዒነት የተነሳ በሕይወት ዘመናቸው ጫማ ያደርጉ ነበር ወይስ ባዶ እግር ነበሩ? የሚለውን ለማጣራት ብዙ የታሪክ

ድርሳናትን ይመረምር ጀመር። የታሪክ ድርሳናቱ ዘገባ ግን እርስ በርሱ የሚቃረን ሆኖ ስላገኘው፣ «ለምን ራሳቸውን ዐፄ ቴዎድሮስን አልጠይቃቸውም?» ብሎ በማሰብ በአገሪቱ ስመ ጥር የሆነ የሙታን መንፈስ ጠሪ ዘንድ ለመሄድ ወሰነ፤ መክሊትም ወንድሟን ለማስደሰት ስትል አብራው ሄደች።

እዚያ ሲደርሱ ከጠበቁት በላይ ቁጥር ያለው ሕዝብ ተከማችቶ ወረፋ ሲጠብቅ አገኙት። መክሊት ከፊት ለፊቷ የተቀመጡትን ጠና ያሉ ሴትዮ ለምን እንደ መጡ ጠየቀቻቸው።

«ባለቤቴ በድንገተኛ ሞት ለኑዛዜ ሳይበቃ ስላረፈ፣ ከመሞቱ በፊት የጡረታ መቀበያ ደብተሩን የት እንዳስቀመጠው ለመጠየቅ ነው!» አሉ ሴትየዋ ሳግ እየተናነቃቸው። ወረፋቸው ሲደርስ መክሊት እና ወንድሟ ወደ ሙት መንፈስ ጠሪው ቢሮ ገቡ። የሙት መንፈስ ጠሪው በጎልማሳነት ዕድሜ ክልል የሚገኝ ወፍራም፣ ጢማም ሰው ነው። ከፊት ለፊቱ ባለው ጠረጴዛ ላይ ከዐፄ ፋሲል ዘመን ወዲህ የሞቱ ሰዎችን ስም ዝርዝር የያዘ ግዙፍ መዝገብ ተቀምጧል።

«የምዝገባ ክፍያ የፈጸማችሁበትን ደረሰኝ ይዛችኋል?» አለ ሰውዬው።

እንዳልያዙ ነገሩት። «ጥሩ፣ እንዲያ ከሆነ መጀመርያ ቢሮ ቁጥር 3 ሄዳችሁ ከፍላችሁ ትመጣለችሁ። ለመሆኑ አከፋፈሉን ዐውቃችኋል?»

ሁለቱም ራሳቸውን በአሉታ ወዘወዙ።

«ክፍያው በሙት ዓመት ሃያ ብር ነው!»

«አልገባኝም!» አለች መክሊት።



ሰውዬው ማብራራት ጀመረ። «ልታነጋግሩት የምትፈልጉት ሰውዬ ከሞተ ዓመት በሞላው ሃያ ብር ትከፍላላችሁ። ሁለት ዓመት ከሞላው አርባ ብር ትከፍላላችሁ። እንዲህ እያለ ይቀጥላል።»

«አከፋፈሉ በዚህ መልክ ለምን ሆነ?» ሲል ጠየቀ ወንድምዬው።

«ጥሩ ጥያቄ ነው!» አለ ሰውዬው፣ « . .ዐየሀ፣ ሟቹ የሞተበት ዘመን እየራቀ በሄደ ቁጥር ኔትወርኩ ያስቸግራል!»

መክሊት ዐፄ ቴዎድሮስ ከሞቱበት ከ1860 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን ሒሳብ ስታስበው አለቅጥ በዛባት።

«ሌላ አማራጭ ፈልግ!» አለችው ወንድሟን።

«ምን ዐይነት አማራጭ?» አለ ወንድሟ።

«ዐፄ ቴዎድሮስን በአካል የሚያውቁ፣ ነገር ግን በቅርቡ የሞተ ሰው አስብ!»

ወንድሟ ትንሽ አሰበና ዐፄ ምኒልክ ትዝ አሉት። ዐፄ ምኒልክ በልጅነታቸው ንጉሥ ቴዎድሮስን በአካል ያውቋቸዋል። በዚህ መሠረት ዐፄ ምኒልክ ከሞቱበት ዘመን እስከ ዛሬ ያለውን በሃያ ብር አስልተው ከከፈሉ በኋላ ደረሰኙን ይዘው ወደ ሰውዬው ተመለሱ።

«ጥሩ!» አለ ሰውዬው ደረሰኙን ተቀብሎ እየመረመረ፣ «አሁን ደግሞ ቢሮ ቁጥር ስድስት በመሄድ ለአስተርጓሚ የሚሆን የማይመለስ አምስት መቶ ብር ትከፍላላችሁ!»

«የምን አስተርጓሚ?» ጠየቀች መክሊት::

«አያችሁ፣ በምኒልክ ዘመን የነበረው አማርኛ ከአሁኑ በጣም የተለየ ነው:: ለምሳሌ:- በዚያ ዘመን ‹ትዳር› የሚለው ቃል ዛሬ ‹ሞያ› ማለት ነው:: በዚያ ዘመን ‹አሽከር› የሚለው ቃል ዛሬ ‹ትንሽ ልጅ› የሚል ትርጉም ይዟል:: ስለዚህ ይህን የሚያስተረጉም ራሱን የቻለ አስተርጓሚ ስላለ ለእሱ የሚሆን አምስት መቶ ብር ትከፍላላችሁ::»

መክሊት እና ወንድሟ የተባለውን ከፍለው ተመለሱ:: ሰውዬው ደረሰኙን ተቀብሎ ወደ ጠረጴዛው መሳቢያ እየከተተ፣ «ጥሩ፣ አሁን ደግሞ የኮቴ ትከፍላላችሁ፤» አለ::

«ከዚህ በኋላ አምስት ሳንቲም አናወጣም፤» አለ ወንድሟ በንዴት ጦፎ::

«ጥሩ፣ አምስት ሳንቲም የማታወጡ ከሆነ እናንተ ከዚህ ቤት ትወጣላችሁ፤» አለ ሰውዬው ወደ በሩ እየጠቆመ:: መክሊት እና ወንድሟ ወደ ቤታቸው ለመሄድ ሰውዬውን ገላምጠውት ዞር ሲሉ ድምፁ ከኋላቸው ተከተላቸው::

«ወደ ቤታችሁ ከመሄዳችሁ በፊት ግን ለመውጫ የሚሆን አምስት መቶ ብር ትከፍላላችሁ!»



# ምዕራፍ 17

ጥቂት ዓመታት ሄዱ፤ ተስተናጋጆች አለመጠን ተበራከቱ፤ የማይተዋወቁ ሰዎች ጠባብ ጠረጴዛ ከብበው እንደ ገበጣ ተጋጣሚ ግንባር ለግንባር ነጥመው ይቀመጣሉ:: ቦታው ከመጥበቡ የተነሳ ጠረጴዛ ተካፍለው የተቀመጡ ሁለት ተስተናጋጆች ባንድ ጊዜ ብርጭቋቸውን ካነሡ አለፈቃዳቸው ያጋጫሉ:: በዚህ መሀል ትከሻ ለትከሻ ሲጋፉ የራሱን አፍ ስቶ ከጎኑ የተቀመጠ ሰው አፍ ውስጥ ጉርሻ የሚጥል አይጠፋም::

ካፌው ቢጨናነቅ አይገርምም፤ አዲስ አበባ አለቅጥ እየሞላች ነው:: ገበሬው ጠፍ መሬቱን ትቶ፣ ሞፈሩን ተሸክሞ፣ ወይፈኑን እየነዳ ከገጠር ወደ መዲናይቱ ይመጣል:: ወይፈኑን ወደ ቄራ ሞፈሩን ወደ ቤተ መዘክር አስናብቶ ሎተሪ ማዞር ይጀምራል::

ሕፃናት ክረምት ከበጋ ሳይመርጡ ተዘርተው ይበቅላሉ፤ ወላጆች የበኩር ልጃቸውን አንደኛ ዓመት የልደት በዓል በግብረ ሥጋ ያከብራሉ:: የዚያው ቀን ሁለተኛ ልጃቸው ይረገዛል:: ዘመናዊ ሴቶች ለርግዝና መከላከያ መርፌ ይወጋሉ:: ይሁን እንጂ የወንድ ዘር በመርፌ የተቀበሉ ይመስል አርግዘው ይታያሉ::

የሚኖረው ከማኖርያው እጅግ በለጠ፤ ያም ሆኖ አዲሳባ

ውስጥ የሐዘን ምልክት አይታይም፤ የደስታ ከተማ ናት - አዲስ አበባ፤ «ደስታ በዕጦት ላይ የበቀለ አበባ ነው፤» ያለው ማን ነበር? አዲሳባን ከፍ ሲል እጥረት፣ ዝቅ ሲል ዕጦት ያዋስናታል። ለምሳሌ፣ የመጓጓዣ እጥረት አለ። ነዋሪዎች ሚኒባስ በሚጠብቁበት ናፍቆት የመድኃኔዓለምን ምጽአት አይጠብቁም። ሚኒባሱ ብቅ ሲል ጎዳናው ዳር የበቀለ የቁልቋል ጫካ የሚመስለው ሕዝብ ድንገት ተንዶ መንጋጋት ይጀምራል። ለኑሮ የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ በሚኒባሱ ታጭቆ የተላከላት ይመስል በታላቅ ጉጉት እየተጋፋ ወደ ሚኒባሱ በር ይሮጣል።

በዚያ ግፊያ ውስጥ የዚህ ሰውዬ እግር እዚያ ሰውዬ ጫማ ውስጥ ይገባል። የዚች ሴትዮ አምባር በዚያች ሴትዮ ክንድ ዙሪያ ይገኛል። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ያንገት ልብስህ የነበረው አሁን እንደ ድግ በወገብህ ዙሪያ ታገኘዋለህ። ከዚያ ግፊያ መሀል ወጥታ፣ ከዚያ የሰው መረብ አምልጣ ሚኒባስ ውስጥ ቦታ ያገኘ ች ነፍስ እንዴት ደስ አይላት?!

ጊዜው ቢሄድም አብሮን የሚሠራው አባት ብዙ አልተሻሻለም። ተስተናጋጅ ገብቶ፣ ወንበር አጥቶ ባይኑ ሲፈልግ አባተ ፈገግ ብሎ በዝምታ ያየዋል። ወንበር ሊስብለት ይገባ ነበር። ግና በልጅነቱ ጉቶ ላይ ሲቀመጥ ስለ ኖረ ተንቀሳቃሽ ወንበር ያለ አይመስለውም። ለምሳሌ፣ አንድ ቀን ሁለት ጀማሪ ፍቅረኛሞች ጭር እስኪል ጠብቀው ጥግ ይዘው ከተቀመጡ በኋላ ለመሳሳም ሲቀራረቡ አባተ አጠገባቸው ቆሞ በተመሥጦ ያፈጥባቸዋል። ፍቅረኛሞቹ ዞር እንዲልላቸው ሰበብ ለመስጠት፣ «ሻይ በሎሚ ታመጣልን?» ሲሉት አባተ ዐይኑን ከላያቸው ላይ ሳይነቅል፣ «መክሊት አንድ ሻይ በሎሚ ይዘሽ ነይ!» ብሎ ትእዛዙን አስተላለፈ። ከሁሉም በላይ ግን ለምን ያለምክንያት



እንደሚያስቆመኝ አይገባኝም። ሞባይል እያወራ ባጠገቡ ካለፍሁ ነጻ በሆነው እጁ አፈፍ አድርጎ ይዞ ይገትረኛል። ምን ሊነግረኝ ነው ብዬ ስጠብቅ ስልኩን አውርቶ ሲጨርስ ይለቅቀኛና ይሄዳል። አንዳንዴ የአምቦ ውኃ ጠርሙስ እንደ ቴርሞሜትር በብብቱ ይዞ ከውስጥ ይወጣል።

ብዙ ዐይነት ተስተናጋጅ መግባት እና መውጣቱን ቀጥሏል። አሁን እዚያ ማዶ የተቀመጠችውን አሮጊት ፈረንጅ እንውሰድ፣ ኬክ ትበላለች፤ ኬኩን በሹካ ወግታ ወደ አፏ ስትወስድ ዐይኗ በጣም ይፈጥጣል፤ ሥሯ ይገታተራል፤ መድኃኒት የምትውጥ እንጂ እህል የምትበላ አትመስልም። በትዕይንቱ ተሣቅቄ ወደ አበሻው ተስተናጋጅ ስዞር ነገሩ የባሰ ነው። በድስት የቀረበለትን ቦዘና ሽሮ እየተመለከተ ያጉተመትማል፤ «ወይ ጉድ! ይሄ ድስት በየጊዜው እያነሰ እያነሰ መጥቶ አሽትሬ አክሎ ቁጭ አለ'ኮ፤ እንጀራውስ ቢሆን? በቀዳማዊ ዐፄ ኀይለ ሥላሴ ጊዜ ምጣዱ ሰፊ ከመሆኑ የተነሣ እናቶቻችን እንጀራውን ሲያሰፉ ዲስክ የሚወረውሩ ይመስሉ ነበር፤ ዛሬ ግን ምጣዱ አንሶ ጠገራ ብር አክሏል፤» እያለ ያማርራል።

ሌላው ሞቅ ያለው ደሞ አጩብጭቦ ይጠራኝና፣ ሄጄ ምን ልታዘዝ ስለው፣ «ሻይ በአረቄ ነፍሴ ነው ይለኛል፤» አረቄ የለም እዚህ ስለው፣ «ማዶ ካለው ካቲካላ ቤት አረቄ ጠጥቻለሁ። እዚህ ሻይ ልደብልቅበት ብዬ ነው፤» ይለኛል። ንዴቴን ውጩ ሥራዬን በትጋት እቀጥላለሁ።

አንድ ቀን ምዑዝ ተመልሶ መጣ። ትልቅ ቀይ ቦርሳ አዝሏል። ለብዙ ጊዜ ለተነፋፈቀ ሰው የማይሆን ግዴለሽ ሰላምታ ከሰጠን በኋላ የተስተናጋጆችን ቦታ ትቶ ባለመስተዋቱን የኬክ ማስቀመጫ ሣጥን ተደግፎ ቆመ። መክሊት ቡና ስታቀርብለት ቡናው

«ያንተስ ልደት መቼ ነው የሚከበረው ምዑዝ?» አለች መክሊት አጠገቡ ስትደርስ፤

«ልደት?» አለ ምዑዝ እንደ መባነን ብሎ፣ «ደሞ ከዚህ በኋላ ልደት ምን ያደርግልኛል?» በወጣትነት ልደት *ሰርፐራይዝ* ሲሆን ወጣትነትን ካለፉት በኋላ ግን መርዶ ነው። እኔ ደሞ የወጣትነትን ጣቢያ እያለፍሁት ነው፤ በጸጋ ከመቀበል ሌላ አማራጭ የለም። እርጅናን በቦዲጋርድ መከላከል አይቻልም!»

«ኧረ ገና ነህ፤» አልሁት እኩያ ስለሆንን ይዞኝ እንዳያረጅ ሰግቼ፤

«አይምሰልህ። በየጊዜው ኮተቴ ሲበዛ ይታወቀኛል፣ እንዲያውም ልንገርህ አንድ ወንድ ማርጀቱን የምታውቀው ዕድሜውን በመቁጠር ሳይሆን በቦርሳው ውስጥ ያለውን ዕቃ በመቁጠር ነው። በቦርሳው ውስጥ ያንገት ልብስ፣ ካፖርት፣ ተጠባባቂ ሹራብ፣ ተጣጣፊ ከዘራ፣ የመድኃኒት ብልቃጥ፣ ኮምፓስ፣ የመሐሙድ አሕመድ የትዝታ ካሴት የሚገኝ ከሆነ የእርጅና ምልክት ነው!»

«ለሠርግህ ለምን አልጠራኸኝም? ሠርግ እና ሞትኮ አንድ ነው፤» አለና አባተ ለጠየቀው ጥያቄ መልስ ሳይጠብቅ ወደ ተስተናጋጆቹ ሄደ።

«ሠርግ እና ሞት አንድ ነው። አቤት፣ እንዴት አሪፍ አባባል ናት። ሠርግ እና ሞት አንድ ከሆነ ፍቺ እና ትንሣኤ አንድ መሆን አለበት!» አለ ምዑዝ ከጥቂት ዝምታ በኋላ ቀጠለ።

«የሠርጌ ቀን ብዙ የሚታወስ ነገር የለውም - ምግብ ነበር፤



እንዲወፍርለት ጠየቀ። ወፍራሙ ቡና ሲቀርብለት ሦስት ማንኪያ ስኳር ጨመረበት(ለምን ስኳር ማስቀመጫው ላይ አይቀዳም)። ይህ ቀላል ለውጥ አይደለም። ድሮ ሳውቀው ቡና ውስጥ ስኳር አይጨምርም ነበር፤ ወፍራም ቡናም አይጠጣም ነበር። ስኳርን አለመጨመር፣ ቡናን አለማወፈር ለጤና የማሰብ አንድ ምልክት ነው። አሁን ያ ሁሉ ጥንቃቄ የት ሄደ?

የምዑዝ ፀጉር በደንብ መስተካከሉ፣ ሰውነቱ እና ልብሱ መጽዳቱ በኑሮው ላይ የተከሠተውን ግዴለሽነት ከማዬት አላገደኝም። ቡናውን እየጠጣ እጅብ በለው የተቀመጡትን ተስተናጋጆች ፍዝዝ ብሎ ሲመለከት ቆየ።

ክፍሉ መሀል ላይ ጥቂት ጓደኛ ተስተናጋጆች ጠረጴዛ ከብበው ተቀምጠው ነበር። ከመካከላቸው አንዱ ብድግ ብሎ ወደ ውስጥ ገባና ትንሽ ቆይቶ መክሊትን አስከትሎ ወጣ። መክሊት በሻማ የተከበበ ትልቅ ኬክ ይዛ፣ በውስጥ ዐዋቂ ፈገግታ ፈገግ ብላ፣ ኬኩን ካንዲት ሴት ፊት ለፊት አስቀመጠችው። ጠረጴዛውን ከብበው የተቀመጡት የልጅቱ ጓደኞች ብድግ ብለው፣ ጎረቤት አገር በሚሰማ ድምፅ፣ *«ሀፒ በርዝደይ ቱ ዩ»* እያሉ መዘመር ጀመሩ። ባለልደቱ ልጅ ነገሩን እንዳልጠበቀችው ለማስመሰል ዐይኗን አፍጥጣ፣ መዳፎቿን አፏ ላይ ጭና ጥቂት የመደናገጥ ትዕይንት ካሳየች በኋላ ብድግ ብላ እየሣቀች ጓደኞቿን ተራ በተራ ትስም ጀመር። በዙሪያው ተቀምጠው ሲበሉና ሲጠጡ የቆዩ ሌሎች ተስተናጋጆች የሁካታውን መንሥኤ ለማጣራት ዞር ብለው ካዩ በኋላ የዕዩን ዕዩን ነገር መሆኑን ሲያውቁ በማዬት ላለመተባበር በፍጥነት ወደ ሳሕናቸው እና ወደ ብርጭቋቸው አቀረቀሩ።

መጠጥ ነበር፤ ተጋባገሮች ብዙ ጥሬ ሥጋ ሲበሉ አይቻለሁ፤ እና የጥንቱ የጀርመን ቋንቋ መምህሬ ተጠርቶ ነበር። ብቻ እሱ ምንም የኢትዮጵያን ባህል ቢያከብር ጥሬ ሥጋ መብላት አልፈለገም፤ እና ምን አደረገ? ከጥሬ ሥጋው ሙዳ ቆርጦ ባፉ ይዞ በላይተር እየጠበሰ በላ፤.. ሌላ ምን ትዝ የሚለኝ ነገር አለ? ... አዎ፣ በኔ እና በሄለን አናት ላይ ነጫጭ ርግቦችን ሲያስቀምጡ ነበር። ጥቂት ቆይተው ግን ሥጋ አንሷል እያሉ ሲንሾካሾኩ ሰማሁ። ርግቦችን አርደው በጎደለ እንዲሞሉ ነገርኋቸው፤ በቃ! በሠርጌ ቀን ሌላ ምን ነበር? አንደኛ ሚዜዬ ከኮቴ ኪስ ውስጥ ሞባይሌን ሰረቀኝ። የሠርጋችንን ቪዲዮ አምስት ጊዜ በተደጋጋሚ በማየቴ ነው ማንነቱን የደረስሁበት! ሄለን ግን ቪዲዮውን በተደጋጋሚ በማየቴ በሠርጋችን ትዝታ የተመሠጥሁ ሳይመስላት አልቀረም።»

እዚህ ላይ ሄድሁ። ስመለስ ምዑዝ ቀጥሏል፤ «... ቀላል የሚባል ሕይወት የለም። ባንድ ወቅት እንደ ዲዮጋን ኮተት ሳላበዛ መኖር አለብኝ ብዬ አሰብሁ። ግን ቆይቶ ቆይቶ ጅልነት ሆኖ ታየኝ። ዲዮጋን የሚኖርበት ቀፎ ነበረው። ውኃ መቅጃ ቅል ነበረው። በቃ! አንድ ቀን አንድ ትንሽ ልጅ በእፍኙ ውኃ ቀድቶ ሲጠጣ ስለ ተመለከተው ‹ትርፍ ነው፣ አያስፈልገኝም› ብሎ ቅሉንም ወረወረው። ቀላል ኑሮ ይሉሃል ይሄ ነው ይሉኛል ፈላስፎች።

«ግን ዲዮጋን ሰው ነው፤ ራት ይበላል፤ ሌሊት ውሃ ከጠማው ምን ሊያደርግ ነው? አሽቀንጥሮ በጣለው ቅል ምትክ ጀሪካን ይገዛል። አልያም ሌሊት ውኃ በጠማው ቁጥር ወንዝ መውረድ ሊኖርበት ነው። ለዚህ ደግሞ ብርድ ልብስ እና ባትሪ ሊገዛ ነው። የሌሊት ውኃ ጥራቱ ስለማያስተማምን የውኃ ማጣሪያ መሺን



መግዛት ሊኖርበት ነው። ከሌሊት ማጅራት መቺዎች ራሱን ለመከላከል ሽጉጥ መግዛት ሊኖርበት ነው. . .ወዘተ፤ ቅሉን በመስኮት በኩል ሲወረውረው ተጨማሪ ቁሳቁስ በበሩ በኩል ይገባበታል።

«ከሄለን ጋራ መኖር እንደ ጀመርን አብረን የምንቀጥል አይመስለኝም ነበር፤ ግን ሳላስበው በኮተት አሸነፈችኝ። አንድ ቀን ትልቅ ቁም ሣጥን ገዛች፤ በማግሥቱ ትልቅ የቴሌቪዥን ማስቀመጫ ወደ ቤታችን ገባ። ከዚያ ብዙ ዐይነት ብርጭቆዎች፣ መአት ዐይነት ማንኪያዎች እና ሳሕኖች ቤቱን ሞሉት። አንድ ቀን ከሄለን ጋራ ምርር ያለ ጠብ ተጣልተን፣ ‹ውጭልኝ› ብዬ ጮሁባት። ‹እሺ!› ብላ ተነሣች፤ ወዲያው ግን ዕቃዋን ለማስጫን የሚወስደው ጊዜ እና የተወሳሰበ ሂደት ሳስብ አብሬያት መኖር የሚቀል ሆኖ ታየኝ።

«አንዳንዬ ሳስበው ዕጣ ፈንታ፣ የሆነ ሸክም ታሸክመኛ ለች። ሸክሙን ለማቅለል ብልጠትም ሆነ ጸሎት ማድረግ ከንቱ ነው። ድሮ ለምሳሌ፣ ብዙ ጉልበት የሚባክነው በሸክም ነበር። አሁን ቴክኖሎጂ ነገሮችን እያሳነሳቸው መጣ። ትንንሽ ነገሮች ደግሞ በቀላሉ ይሰወራሉ። እና ድሮ በሸክም የምናጠፋውን ጉልበት ዘንድሮ በፍለጋ እናጠፋዋለን።

ከሄለን ጋራ በተጋባን በማግሥቱ ከመሥሪያ ቤት ስንመለስ ከግቢያችን ፊት ለፊት አንድ ሰካራም ሽንቱን ይሸናል። መሽኛው ትልቅ በመሆኑ ሽንቶ ሲያራግፍ አጠገቡ የነበረውን የመንገድ መብራት አምፖል አቃጠለው። በአደባባይ የሚሸኑ ወንዶች በአካባቢ ላይ ከሚፈጥሩት ብክለት በላይ በትዳር ላይ የሚፈጥሩት ችግር ይበልጣል። ዐየህ፣ ሚስቶች ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው የባላቸውን መሣሪያ ከሌላው ጋራ ሊያወዳድሩ ይችላሉ። ሰውዬው

ሲሸና ሳይ ዞር ብዬ ሄለንን ባይኔ ፈለግሁ፡፡ አፍጥጣ እየተመለከተችው ነበር፡፡ የተረገመው ሰውዬ አልዓዛሩን አልጋረደም ነበር፡፡ ስለዚህ እኔ የሄለንን ዐይን ከመጋረድ ውጭ የማደርገው ነገር አልነበረም፡፡ በጣም ተናድጄ፣ እዚህ ትሸናለህ? ብዬ ጮሁበት፤

‹እና ጎረቤት አገር ሄጄ ልሸና!› ብሎ ጮኸብኝ፡፡»

ምዑዝ ወሬውን ገታ አድርጎ ወደ በረደው ቡና አቀረቀረ፡፡ እሱ ቡናውን እስኪጨርስ ድረስ እኔ ትረካውን ልቀበለው፡፡

ብዙ ሳይቆይ ምዑዝ ሌሎችን ሴቶች አብዝቶ መጎብኘት ቀጠለ፡፡ ሄለን መጠርጠር ጀመረች፤ እሷ እና ሠራተኛዋ ልብሶቹን ተከፋፍለው ሲያጥቡ፣ ሄለን ሱሪዎቹን ለምን እንደምትመርጥ አይገባውም ነበር፡፡ አንድ ምሽት ከመሥሪያ ቤቱ ወደ ቤቷ ሲመጣ ሄለን የሱሪውን የኪስ ገበር እየበዘበዘች፣ «ይሄ ምንድን ነው?» ብላ አፈጠጠችበት፡፡

«የቱ?» አለ በእጅዋ የያዘችውን የኮንዶም ፓኬት እየተመለከተ፤

«ይሄ ነዋ! ዐይንህ አያይም?»

«ባጭሩ ልንገርሽ፣ ምን መሰለሽ፣ ትላንት ከጓደኛዬ ጋራ ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ውስጥ ስንዋኝ ቆየን፤ በመጨረሻ ሞቅ ብሎን ስለነበር በስሕተት እኔ የእሱን ሱሪ፣ እሱ የእኔን ሱሪ አድርገን ተለያየን፡፡»

«ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ውስጥ መዋኛ ገንዳ የለም፤» አለች ሄለን፤



«ልክ ነሽ፣ መዋኛ ገንዳ የለም ግን በቅርቡ ወንዝ ፈልቋል!»

ሄለን ከዚህ በላይ መቀጠል አልቻለችም፡፡ ማልቀስ ጀመረች፡፡ በልቅሶዋ መሃል ፋታ ስታገኝ፣ «ሌላ ሴት ጋ ሄደሃል!» አለችው፤

«አልሄድሁም!»

«ማልልኝ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ማልልኝ!»

ምዑዝ ቤቱ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሌለ ነገራትና፣ «ከቤተ ክህነት መጽሐፍ መደብር ገዝቼ ልምጣ፣ ፍራንክ ስጭኝ!» አላት፡፡

«ስንት ነው?»

«አራት መቶ ብር»

«አንድ መጽሐፍ ቅዱስ አራት መቶ ብር?»

«እንደዛ ነው ዋጋው!»

«በቃ ተወው፣ እንዲሁ አምንሃለሁ!»

ሌላ ጊዜ አብረው ተኝተው አንገቱ ላይ የጥርስ ምልክት ያለው ቁስል ተመለከተችና፣ «ይሄ ምንድን ነው?» ብላ አፈጠጠችበት፤

«ወድቄ ነው!» አለና ጀርባውን ሰጣት፤

«የጥርስ ምልክት ይታየኛል!» ብላ ጮኸች፤

«እኮ ጥርስ ላይ ወድቄ ነው!» ብሎ መለሰ፤

* * *

በአጠገባችን የነበሩ አንድ አጭር እና ረጅም ተስተናጋጅ ግብግብ ገጠሙ:: ግብግብ የገጠሙበት ምክንያት የሚከተለው ነው:: አጭሩ ተስተናጋጅ ወደ ካፌው ገብቶ ሰው የሚፈልግ አስመስሎ በክፍሉ ውስጥ ዝም ብሎ ይመላለሳል:: ከቆንጆ ሴቶች ቂጥ በማይተናነስ መንገድ ትኩረት የሚስብ ምርጥ ስኒከር ጫማ አድርጎ ነበር:: ረጅሙ ሰውዬ የኮካ ጠርሙሱን እንደ ጨበጠ የአጭሩን ሰውዬ ስኒከር ለረጂም ጊዜ አፍጥጦ ሲመለከት ከቆየ በኋላ፣ «ነፍሱ፣ የጫማ ቁጥርህ ስንት ነው?» ብሎ ጠየቀ፤

«ዐርባ ዘጠኝ» ሲል መለሰ አጭሩ፣

«እኔም ጠርጥሬያለሁ! ለመሆኑ ፖስታ ቤት የሚሠራ ዘመድ አለህ?» ረጅሙ ቀጠለ፤

«ለምን ጠየቅኸኝ?»

«አይ ለክፋት አይደለም፣ ከውጭ አገር ወንድሜ እንደዚህ ያለ ጫማ ልኮልኝ ስላልደረሰኝ ምናልባት በጎን አስቀርቶት ይሆን? የሚል ስጋት ተሰምቶኝ ነው::»

አጭሩ ሰውዬ በቃሉ ምላሽ መስጠት አልፈለገም:: በኀይል ተንደርድሮ የረጅሙን ሰውዬ ወገብ አቀፈው:: ረጅሙ ሰውዬ ብድግ ብሎ ጠርሙሱን በጥንቃቄ አጠገቡ ካለው ጠረጴዛ ላይ ካስቀመጠ በኋላ ጎንበስ ብሎ የአጭሩን ሰውዬ አንገት አነቀ:: ፊቱ ላይ ያለው ፈገግታ ግን ባጭሩ ሰውዬ አንገት ላይ ሜዳሊያ የሚያጠልቅ እንጂ የሚያንቅ አይመስልም ነበር:: በዚህ መሀል በሰላሙ ጊዜ አስተናጋጅ፣ በቀውጢው ጊዜ ቦዲጋርድ በመሆን በካፌው ውስጥ የሚያገለግለው አባተ በደረቱ አየሩን እየገፋ ደረሰና ባንድ እጁ ያጭሩን ሰውዬ ኮሌታ በሌላ እጁ የረጅሙን ሰውዬ እጅጌ ጨምድዶ ይዞ፣ «እዚህ ሰው እየተዝናና ስለሆነ



አትረብሹ፤ ጠብ ከፈለጋችሁ ውጡና ይለይላችሁ፤» ብሎ ወደ በሩ ጎተታቸው:: ጠበኞቹ ፊት እና ኋላ ሆነው ሲወጡ የካፌው ደንበኛ ሁሉ ጠበኞቹን ተከትሎ ግልብጥ ብሎ ወጣ:: ከውጭ የመሸባቸው አልፎ ሂያጆች መንገዳቸውን ገታ አድርገው ፍልሚያውን ለመመልከት በጠበኞች ዙሪያ ከብበው ተደረደሩ:: የካፌው አዋሳኝ በሆነ ፀጉር ቤት ውስጥ ሲስተካከል የነበረ ጎልማሳ የገዛ ፀጉሩ እንደ ጨጎጊት የረገፈበትን ሽርጥ እንደ ለበሰ፣ ግማሽ የተላጨ አናቱን አስቀድሞ ብቅ ካለ በኋላ ጠበኞቹን ባይኑ ይፈልግ ጀመር:: ከጀርባው ፀጉር አስተካካይዋ መንሽ የሚያህል ማበጠርያ ይዛ ተከትላዋለች:: አባተ ካፌው በር ላይ ሆኖ ያልከፈሉ ተስተናጋጆች በግርግሩ መሀል ሾልከው እንዳይሄዱ በዐይነ ቁራኛ ይጠብቃል::

በጥበቃ ላይ የነበሩ ሁለት የፌዴራል ፖሊስ አባላት ግርግሩን አይተው ከወጡ በኋላ ጠቡ የፖለቲካ ጠብ አለመሆኑን አረጋግጠው ሲጨርሱ ከተመልካች መሀል ተቀላቅለው ማዬት ጀመሩ::

አጭሩ እና ረጅሙ ሰውዬ እንደ ተነፋፈቁ ዘመዳሞች ለረጅም ጊዜ ሲተቃቀፉ እና ሲላቀቁ ከቆዩ በኋላ አጭሩ ሰውዬ ሽጉጡን ላጥ አድርጎ ሲያወጣ ረጅሙ ደግሞ ጩቤውን መዘዘ:: ዙሪያውን ከብቦ ይመለከት የነበረው ተመልካች ትንሽ አፈግፍጎ፣ ለዕይታ እና ለሽሽት በሚያመች ቦታ ላይ ተከማቸ:: ባለሽጉጡ ሞባይሉን ከኪሱ አውጥቶ ቁጥሩን ከመታ በኋላ፣ «ሄሎ ግርማቸው፣ እቤት ከሆንህ ከመኝታዬ መሳቢያ ሦስት ጥይት ይዘህልኝ ና ፈጠን በል!» ብሎ ጮኸ:: ባለጩቤው በበኩሉ ከተመልካች መካከል የነበረውን ጓደኛውን ጠርቶ፣ «ስማቸው፣ ይሄን ጩቤ አስሞርደህልኝ ና፣ ፈጠን በል» ብሎ ላከው:: ጠብ ለማየት ጓጉቶ የነበረው ተመልካች ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ተሰላችቶ ወደ ካፌው

መመለስ ጀመረ፤ እኔም ተደርቤ ገባሁ::

ከውስጥ ምዑዝ እና መክሊት አፍ ለአፍ ገጥመው ሲያወሩ እና ሲሥቁ ዐየኋቸው:: መክሊት አሁንም አሁንም በሣቅ እያሳበበች ትከሻው ላይ ስትደገፍ ታዘብኋት:: አጋጣሚውን ተጠቅመው ጭር ያለውን ቤት የድርያ ቤት አድርገውት እንደ ቆዩ ውቃቢዬ ነገረኝ::

ምዑዝ አለወትሮው ካፌው እስኪዘጋ ድረስ ቆየ:: ተስተናጋጆች ቀስ በቀስ ወጥተው የካፌው ባዶ ወንበሮች በደረቀ ወንዝ ወለል ላይ የቀሩ አለቶችን መሰሉ:: መክሊት ልብሷን ልትቀይር ወደ ውስጥ ስትገባ በዐይኑ ሲከተላት ዐየሁት:: እየጠበቃት መሆኑን ጠረጠርሁ:: ለመታጠብ እና ለመልበስ አለልማዷ ረጅም ጊዜ ፈጀባት:: እሷ እስክትወጣ እሱ እኔን በወሬ ጠመደኝ::

«የተወለድሁት መሀል ፒያሳ ነው፤» አለኝ፤ እና ምን አባህ ላድርግህ ልለው አሰኝቶኝ ነበር፤ ግን ከፊቃዴ ውጭ ጆሮዬን ሰጠሁት::

«አባቴ በጊዜው ከአዲስ አበባ ከሚኖሩ ጥቂት ስመ ጥር ሰዎች አንዱ ነበር፣ እንዲያውም *የፒያሳው ብርሃን* ተብሎ ይጠራ ነበር::»

«ሲቅ ነበሩ ማለት ነው!»

«እንዲያውም የፒያሳው ብርሃን የተባለው ላምባ ሻጭ ስለነበር ነው፤»

«ገባኝ!»

«የሆነ ጊዜ ላይ አባቴ ሀብታም ሆነ! ግን የኑሮ ነገር አልሆነለትም፤ መጠጣት፣ ሴት መተኛት፣ መደባደብ ሆነ ሥራው:: አባቴ አጭር እና ቅንዝረኛ ስለነበረ ሰዎች ስንዝሮነቱን እና ቅንዝረኛነቱን አስተባብሮ የሚገልጽ ስም ሰጡት - *ቅንዝሮ* ብለው ጠሩት:: የድሮ ቅጽል ስሙ ተረሳ:: አንድ ቀን በሚጠጣበት ቤት ውስጥ በተፈጠረ ዐምባጓሮ በድንጋይ ተፈንክቶ ሞተ፤ አብሮ አደግ ጓደኛውም በዕለቱ አብሮት ሞተ:: ዐየህ፣ ጓደኛ መስተዋት ነው የተባለው ተረት እና ምሳሌ እውነትነቱ የገባኝ ያኔ ነው:: አዎ! ጓደኛ መስተዋት ነው፣ ከሚወረወር ድንጋይ አያስጥልህም!

«የአባቴ ጓደኛ መቼም በጣም ሊቅ ነበር:: ‹አንድ ሊቅ ከሞተ አንድ ቤተ መጻሕፍት ተቃጠለ› ማለት ነው ሲባል ሳትሰማ አትቀርም:: አባዬ ግን ከመጠጣት በቀር ምንም አያውቅም:: ምን ታደርገዋለህ! አንድ ቤተ መጻሕፍት ሲቃጠል ከጎኑ ያለ ጠጅ ቤት አብሮ መቃጠሉ አይቀርም:: ደከመህ መሰል?»

«እረ እየሰማሁህ ነው!»

«አባዬ ከሞተ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እማማ ታማ ሆስፒታል ገባች:: ወደ ውጭ አገር ሄዳ እንድትታከም ተወሰነ:: ከዚያ፣ አሜሪካ ለሕክምና በሄደችበት በዚያው የፖለቲካ ጥገኝነት ጠየቀች!»

«የፖለቲካ ጥገኝነት እንዴት ተሰጣቸው?»

«Well, ሆስፒታል ውስጥ እያለች *የኢትዮጵያ ሕመምተኞች አብዮታዊ ፓርቲ* የሚባል ድርጅት አቋቁማ ነበር:: ትዝ ይለኛል፣ ልጠይቃት በሄድሁ ቁጥር እሷ ያኔቃቻቸው ሕመምተኞች መድኃኒት መድኃኒት በሚሸት ክፍላቸው ውስጥ ተሰብስበው፣

«እንደ ቼጉቬራ፣ እንደ ቼጉቬራ፣»

· «እንደ ቼጉቬራ፣ እንደ ቼጉቬራ፤»

በማለት በታላቅ ወኔ ይዘምሩ ነበር። ዐየህ፣ ቼጉቬራም በሕይወት ዘመኑ ሙሉ የአስም ሕመምተኛ ነበር!»

ፋታ ለማግኘት በማሰብ ፊቴን ወደ ቴሌቪዥኑ አዞርሁት። የቴሌቪዥኑ ጋዜጠኛ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኒውዮርክ ከተማ በሚደረግ የመሪዎች ጉባኤ ላይ ለመሳተፍ ወደዚያ እንዳመሩ ይዘግባል። ጋዜጠኛው ይህን ሲዘግብ በስቱዲዮ ውስጥ የተንጠለጠለ የዓለም ካርታ ላይ ኒውዮርክን ነጥሎ እየጠቆመ ነበር። ብዙ ጋዜጠኞች ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋራ ወደ ውጭ ሲሄዱ በዚያው ስለሚቀሩ ከዚህ በኋላ እንዳይሄዱ ተወስኗል። ከዚያ ውሳኔ ጊዜ ጀምሮ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዓለምን ሲዞሩ፣ ጋዜጠኞች ደግሞ በስቱዲዮ ውስጥ ያለውን የዓለም ካርታ ይዞራሉ።

«እማማ ውጭ አገር መኖር እመርጣለሁ ካለች ይመቻት!» አለ ምዑዝ እኔ የምመለከተውን እየተመለከተ። ለእኔ ግን ከአገር ወጥቶ መኖር ትርጉም የለውም። ብዙ ሰው ከአገር የሚወጣው ከሆነ ነገር ለማምለጥ ነው። ካልሞተ በቀር ማን አገሩን ያመልጣል? በርግጥ ያገሬ ታሪክ ደስታዬን ሲያደፈርስብኝ ኖሯል። በደካማ አገር ውስጥ ያለ ወንድ ከሴት ጋራ በጥሞና መተኛት እንኳ አይችልም። ያገሬ ካርታ በየአንሶላው ላይ የተለጠፈ ይመስል ዕረፍት የለኝም። እስቲ ራስህ አስበው፣ ከቆንጆ ሴት ጋራ አልጋ ላይ ሆኜ አልዓዛሬ ሲገተር ልጅቷ፣ «ዋው የአክሱምን ሐውልት አይመስልም?» ብላ ስታደንቅልኝ ሳልፈልግ የአክሱም ሥልጣኔ በሐሳቤ ይመጣል።



«እኛ ኢትዮጵያውያን ከሺሕ ዓመታት በፊት አክሱም ላይ ድንቅ ሥልጣኔ መሠረትን። ባሕር ተሻግረን መንግሥታትን አስገበርን። ከዚያ ከብዙ ዓመታት በኋላ በተረገመ ዕለት ቀይ ባሕር እንደ ዛጎል የተፋቸው ሁለት የግሪክ ብላቴናዎች ክርስትናን ይዘው መጡ። ቆይቶ ቆይቶ ግብጾች ወንዛችንን ወስደው በምትኩ አቡን ሰጡን - ዓባይን ወስደው አባሆይን ሰጡን ማለቴ ነው።

ክርስትና ከተፈጥሮ ጋራ ስምረት የነበረውን አረማዊ እምነታችንን አጥፍቶ ሥልጣኔያችንን አሽመደመደው። ይህን ሳስብ አልዓዛሬም አብሮ መሽመድመድ ይጀምራል፤ ወንድሜ፣ ከሴት ጋራ ተኝተህ ሳለ ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወዲህ ያለው ታሪካችን ወደ መኝታ ቤትህ ከገባ አለቀልህ!»

«እና መደሰት አንችልም ማለት ነው?» አልሁት። ፊቱን ወደ ጓዳው በር አዞረው፣ መክሊት ለባብሳ እየወጣች ነበር። የጠየቅሁትን የሰማኝ ስላልመሰለኝ ደገምሁለት።

«ለምን አንችልም?» አለ ምዑዝ በመክሊት ቂጥ ላይ አነጣጥሮ፣ «በበኩሌ እኔም እንደ ጎተ በዓለም ደስተኛ ነኝ - Gefällt mir die welt»

«በአገሬ ደስተኛ የምሆንበት ምስጢርም እየተገለጠልኝ ነው። ይህ ምስጢር ለዘርዐ ያዕቆብም ሆነ ለዘርዐ ቱስትራ አልተገለጠም - ለኔ ብቻ!! ለመደሰት አገራችንን መለወጥ ይኖርብን ይሆናል። ይህን ስል ድልድይ መሥራት፣ ሐዲድ መዘርጋት፣ ነዳጅ ማውጣት፣ ዴሞክራሲ ማስፈን ማለቴ አይደለም። አገራችንን የምንመለከትበትን መንገድ መለወጥ ማለቴ ነው። በመሪዎች መተማመኑን ትተን የልባችንን መሪነት መከተል ይሻላል። ርእዮተ ዓለሞች ሁሉ ሲከስሙ፣ በልባችን ላይ የሚቀረው ርእዮተ ዓለም

ሜታሞርፎሲስ ይባላል፤ የማያድጉ አገሮች ርእዮተ ዓለም አድርጌ መርጨዋለሁ:: በዚህ አማካይነት መከራችንን ወደ ሣቅ፣ ውርደታችንን ወደ ክብር የመቀየር ኀይል ይኖረናል::»

«ለብዙ ዘመናት የምድር አማልክት ጦር እንደ ችቦ ሲናጠቁብን ኖረዋል:: ለፈጠራ እና ለሳይንስ ፋታ አልነበረንም፤ ቢሆንም የመለወጥን ሕግ(ሜታሞርፎሲስን) ተከትለን የሳይንስ ባለቤቶች ያቃታቸውን ሞክረናል:: አንድ ቀን ገጠር ወርጄ ሴቶች ከወደቀ የመድፍ ቀለሕ የቡና ሙቀጫ ሠርተው ቡና ሲወቅጡ ዐይቼ እንባዬን መቆጣጠር አቃተኝ:: የመገለጥ እንባ ነበር:: አውሮፕላን ባለመሥራታችን ኮምፒዩተር ባለመፈልሰፋችን መጸጸት አይገባንም አልሁ:: ዐየህ፣ አውሮፕላን መሥራት ኮምፒዩተር መፈልሰፍ ሰውን የተሻሻለ አላደረጉትም:: በምንጅላቶቻችን ዘመን የነበረውን ክፋት፣ ሞት እና ሽብር አልገሩትም:: የመድፍ ቀለሕን የቡና ሙቀጫ አድርጎ መቀየር ግን፣ የሞቱን ዕቃ ወደ ሕይወት ዕቃነት ማሸጋገር ነውና ቀላል ግኝት አይደለም::

«ወደፊት አንድ ቀን ወይ ኀበዝ ሽፍታ አልያ ኀበዝ ተመራማሪ ወይ ኀበዝ ባል እንደምሆን ጥርጥር የለኝም:: ብቻ የሆነ የላቀ ብቃት ሳላሳይ የካፌው ትውልድ አንድ አባል ሆኜ ብቻ ማለፍ አልፈልግም:: አሁን ብዙ የምፈልጋቸውን ነገሮች በዕድልም በለው በትግል አግኝቻለሁ - ሥራ ማግኘት እፈልግ ነበር አግኝቻለሁ፤ ለዚያውም በአንድ NGO(Non Growth Organization) ውስጥ እሠራለሁ:: መሥሪያ ቤታችን እከክ ላስቸገራቸው አካባቢዎች ልብስ እና ሳሙና አያቀርብም፤ ከዚያ ይልቅ እከክ ላስቸገራቸው አካባቢዎች የማከኪያ ማሽን ያቀርባል:: የነገርኩህን ባታምን አይገርመኝም:: የውጭ አገር ሰው መሆን ገደብ የለሽ



መብት እንደሚያጎናጽፍ አታውቅም:: ኢትዮጵያዊ ከአገሩ የሚወጣው ለምንድን ነው? የውጭ አገር ሰው ሆኖ ለመመለስ ነው:: የውጭ አገር ሰው ሆኖ ሲመጣ በተወላጅነቱ ያላገኘውን መብት ያገኛል::

አንድ የሰፈራችን ሽማግሌ መሬት ለመግዛት ጠየቁ - ጉለሌ:: በካሬ ሜትር የተጠየቁት ገንዘብ ቢያስደነግጣቸው፣ «የጉለሌ መሬት ዑራኒየም አለው እንዴ!!» ብለው ባለሥልጣኑን ጠየቁት:: በአንጻሩ ለውጭ አገር ኤምባሲዎች የሚሰጠው መሬት ግን በጣም ሰፊ ከመሆኑ የተነሣ ወንዝ እና ተራራ ቢገጠምለት ‹አገር› ተብሎ በተ.መ.ድ ምክር ቤት ዕውቅና ይሰጠው ነበር:: በዚህ ረገድ በምሥራቅ በኩል ኢትዮጵያን ሦስት አገሮች ያዋስኗታል - ሶማልያ፣ጅቡቲ እና የጅቡቲ ኤምባሲ::»

. «ከሄለን ጋራ እንዴት ታረቃችሁ?» አልሁት ከዓመታት በፊት የገጠመውን አስታውሼ:: «እነግርሃለሁ» አለና ሲቀጥል ሲል መክሊት አጠገባችን መጥታ ቆመች:: ፊቱ በፈገግታ ተሞልቶ ሲመለከታት የኔ ፊት - ባላየውም - ሲቀላ ታወቀኝ:: ፊቴን ለመደበቅ ወደ መታጠቢያ ቤት ሄድሁ:: ከጥቂት ቆይታ በኋላ ስወጣ መክሊት እና ምዑዝ በክፍሉ ውስጥ አልነበሩም፤ አባተ ብቻ ከመስኮት መስኮት እየዘለለ የመስኮቶችን መዝጋት ያረጋግጣል::

# ምዕራፍ 18

ከጥቂት ጊዜያት በኋላ መክሊት አቶ ያን ቤት ጠቅልላ መኖር ጀመረች:: የአስተናጋጅነት ሥራዋን ጨርሶ አቆመች:: በእሷ ምትክ ለታሪክ የማይበቁ ሁለት ሴት አስተናጋጆች ተቀጠሩ፤ ለጊዜውም ቢሆን ከመክሊት እና ከምዑዝ ጋራ አልፎ አልፎ መገናኘታችን አልቀረም:: አንድ እሑድ አመሻሽ በሠፈራችን በሚገኝ ኢንተርኔት ካፌ በረንዳ ላይ ተቀምጬ መክሊትን እጠብቃለሁ:: በአስተናጋጁ ምትክ መንገድ ለመንገድ የሚዞር መጽሐፍ ሻጭ መጥቶ አጠገቤ ቆመ፤ አልገረመኝም:: የተቀመጥሁበት በረንዳ ከካፌው ይልቅ ለጎዳናው ይቀርባል:: መጽሐፍ ሻጩ በደረቱ ከተሸከመው የመጽሐፍ ነዶ መሀል፣ «ፍቅር እስከ መቃብር» የሚል ወፍራም ጥራዝ ታየኝ:: አቶ ሐዲስ መጽሐፋቸው እንደ አጠና በሸክም ገበያ የሚወጣ መሆኑን ቢያውቁ ኖሮ፣ የገጹን መጠን ያሳንሱት ነበር ብዬ አሰብሁ:: የልጁን ሸክም ለማቅለል ብዬ አንድ ትልቅ ጥራዝ ገዛሁትና ወደ ጎዳናው መመልከት ጀመርሁ:: ጎዳናው ዳር መሄጃ የሌላቸው ወጣቶች ፈንጠር ፈንጠር ብለው ቆመው ከሚያውቁት አልፎ ሂያጅ ሰላምታ እንደ ምጽዋት ይጠብቃሉ:: ችጋር ሣር በል ያደረጋቸው ከሲታ የከተሜ ውሾች የሚቀመስ ፍለጋ አለቱን፣ ዕንጨቱን ያሸታሉ:: የተሠበሩ መኪኖችን የሚያነሣ ላንድሮቨር



የተሰናከለ ቶዮታ እየጎተተ አለፈ:: በሚጎተተው ቶዮታ ጋቢና ውስጥ የተቀመጠው ሾፌር፣ አንዲት እግረኛ ቆንጆ ስታልፍ አይቶ፣ «ላድርስሽ?» ብሎ ጮኸ::

መክሊት አልመጣችም:: በእሷ ምትክ ያልቀጠርሁት ሽንቴ ስለ መጣብኝ ከካፌው ጓሮ ወደሚገኘው ሽንት ቤት ጎራ አልሁ:: እዚያም መጸዳጃ ሳሕኑ ውስጥ ሽልንግ ዐይቼ በዓለም ፍርደ ገምድልነት ተገረምሁ:: ይገርማል! ያልታደለው ቤሳቤስቲን አጥቶ መጽሐፍ በሸክም ያዞራል፤ የታደለው ሽልንግ ያራል:: ከመጸዳጃ ቤቱ ወደ በረንዳው ተመልሼ ብዙም አልቆየሁም:: አንድ በክራንች የሚያነክሱ ለማኝ አጠገቤ ደርሰው ወጌሻ የሆንኩ ይመስል፣ አንድ እግራቸውን ዘረጉልኝ::

«እግርዎት ምን ሆኖ ነው?» አልኋቸው፤

«በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት አደጋ ደርሶብኝ ነው፤» አሉኝ::

«ዘምተው ነበር?»

«አይ አልዘመትሁም፤ ብቻ በኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት ወቅት የቤቴን ጣራ በመጠገን ላይ ሳለሁ ተንሸራትቼ ወደቅሁ::»

መክሊት ከቀጠሯችን ግማሽ ሰዓት አርፍዳ ደረሰች:: ለዘገየችበት ይቅርታ ትጠይቀኛለች ብዬ ሳስብ፣ «ብዙ አልቆይም እሺ? ሌላ ቀጠሮ አለኝ!» አለችና ከፊት ለፊቴ በነበረው ወንበር ላይ ቁጭ አለች::

የተቀባችው ሮዝ የከንፈር ቀለም፣ የተቀባችው እንደ ሉባንጃ የሚያውድ ሽቱ፣ የለበሰችው ሥሥ እና ወንፊታማ ታይት ሱሪ

ለእኔ እንዳልሆነ ገባኝ። አጠገቤ የተቀመጠው አልፎ ሂያጅ ውበት ነው።

«መዘግየትሽ ብዙ አልገረመኝም!» አልሁ ለቀጣይ ወሬ እያሟሟቅሁ፤

«እንዴት?» አለችኝ፤

«ዐየሽ! . . .ሴቶች የጊዜ ዋጋ አይገባቸውም። ከዶሮዎች ወገን እንኳ መንጋቱን የሚያበሥረው አውራ ዶሮ ነው፤» አልሁኝ - ከበደ ሚካኤል ባንድ ወቅት ቤትሆቨን ካፌ ውስጥ ሲናገሩ የሰማሁትን የራሴ አስመስዬ።

«ተሳስተሃል! የሴቷን ያህል ለወንዱ የጊዜ ምስጢር አይገለጥለትም። ሴቶች ከመጀመርያዋ የወር አበባ ጠብታ ጀምሮ የጊዜ ቁራኛ ናቸው። ወንዶች የወር አበባን እና ርግዝናን ስለማያውቁ የጊዜን ርግማን እና ስጦታ አይረዱትም። ካሌንደር የሴቶች የፈጠራ ውጤት መሆን አለበት። በርግጥ ሴቶች በቀጠሮ ሰዓት አይመጡም። ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት የመዘግየትን ፍሬ ጣዕም ስለሚያውቁት ነው!» አለች በአንድ ወቅት ምዑዝ የተናገረውን የራሷ አስመስላ።

«የመዘግየት ፍሬ. . . » የሚለው ሐረግ ትርጉሙ ባይገባኝም አንዳች ምስጢራዊ ስሜት አሳደረብኝ። ምናልባት አንድ ቀን ፍቺው ይገለጥልኝ ይሆናል። አስተናጋጁ ሲመጣ ቡና አዘዝሁ። መክሊት፣ «ቶሎ የሚደርስ ነገር ምንድን ነው?» ብላ ጠየቀችው - መቸኮሏን እንዳልዘነጋው ማሳሰቧ ነው።

ቡና እየጠጣሁ ቶሎ የደረሰ ማኪያቶ እየጠጣች፣ ስለ አዲሱ



ቤቷ እንድትነግረኝ ጠየቅኋት። «ምን ልበልህ? በጣም አስጨናቂ ምቾት አለው!» ከማለት ባሻገር ተጨማሪ ልትነግረኝ አልፈለገችም። የቤቱን ምቾት በዝርዝር የገለጸልኝ በቅልውጥና(እሱ በእንግድነት ይላል) ቤቱን የሚያውቀው ምዑዝ ነው።

እንደሱ አገላለጽ የቤቱ ግቢ በጣም ሰፊ ሆኖ በውስጡ ዐደይ አበቦች፣ ጤዛ ያዘሉ ሣሮች እና ከቀጠሳቸው እኩል ወፎችን ያቀፉ ዛፎች ሞልተውበታል። የግቢውን በር ከፍተህ ስትወጣ ግን አዲስ አበባ አቧራ እና ጠጠር አንጥፋ ትቀበልሃለች። የአቶ ያን ግቢ ከዋናው የጽጌ ወር ተገንጥሎ የቀረ የጽጌ ፋርጎ ይመስላል።

ቪላው፣ የቀድሞ አየር ወለድ አባል በሆነ ዘበኛ ይጠበቃል፤ በተጨማሪም ከውሻ የሚተልቁ ከአንበሳ የሚያንሱ ድልብ ውሾች ለግቢው ዘብ ቆመዋል።

ቤቱ እጅግ ንጹሕ በመሆኑ እንግዳ ወይም ቀለዋጭ ጫማውን አውልቆ እንዲገባ ይገደዳል። ድንገት ተሳስቶ ከነጫማው ከገባ የረገጠውን ምንጣፍ ጠቅልሎ እንዲወስድ ይፈረድበታል። ምንጣፉ የሚያምር የፋርስ ምንጣፍ ቢሆንም እንደ ፎጣ ተጠቅሞ ለመጣል የተሰናዳ ነው። በቪላው ውስጥ ባሉ ክፍሎች ውስጥ ቴሌቪዥኖች እና ቴፕሬከርደሮች በነፍስ ወከፍ ይገኛሉ። ዐየህ፣ ጀርመኖች ሲጸዳዱ እንኳ በሙዚቃ ታጅበው ነው። ጀርመኖች በጣም ኩሩ ሕዝቦች በመሆናቸው ከሚጸዳዱበት ክፍል የሲምፎኒ እንጂ የፈስ ድምፅ እንዲወጣ አይፈልጉም።

ምሳ ይጋብዙሃል። ምሳ ቢሉህ፣ እንጀራ በወጥ በልቶ መሄድ እንዳይመስልህ፤ አበላሉ የሚከተለው ይመስላል። በመጀመርያ የአትክልት ሾርባ ያመጡልሃል - ማሕጋጊያ ይሉታል። ቀጥሎ አይብ ያመጡልሃል፤ አይቡን ማዘናጊያ ይሉታል። ቀጥሎ የተቀቀለ

የዓሣ ዕንቁላል ያመጡልሃል - መታደጊያ ይባላል:: ቀጥሎ የፍራፍሬ ፍርፍር ያመጡልሃል፤ ይሄ ማሳረጊያ ይባላል:: ቁንጣን ያስቸግርሃል:: ወደ ምግብ ጠረጴዛው በእግርህ መጥተህ፣ ወደ ሶፋው በዳዴ ትመለሳለህ:: ከዚያ በረንዳው ላይ ቁጭ ብለህ ፒፓ እያጨስህ ኮከብ ታያለህ:: ኮከቡ ከራቀ ቴሌስኮፕ ያመጡልሃል:: ከዚያ በኋላ ግን ምን ዋጋ አለው? በአውቶማቲክ ማዛጋት ትጀምራለህ::

በዚህ ዓለም የማይለመድ ነገር ቢኖር ምቾት ነው:: ወዲያው ዕረፍት የለሽ ትሆናለህ:: የሀብታሞች ቤት ብዙ ክፍል የሚኖረው ያለምክንያት አይደለም:: አቶ መሰልቸት ከአንዱ ክፍል ሲያባርርህ፣ ወደ ሌላው ክፍል ገብተህ እንድታመልጠው ነው::

ይህን የምሁዝን ዘገባ አሁን ለመክሊት ስነግራት፣ «. . .ትንሽ አጋነነውንጂ ልክ ነው!» አለቺኝ፤ ቀጠለችናም፣ «ምቾትን መልመድ ከባድ ነው፣ ያለው በጣም በጣም ብዙ እውነት አለው!» አለቺኝ::

«ግን ለምንድን ነው?» አልኳት፤

«እንጃ!» አለችኝ ቀጠለችና፣ «. . .ምናልባት አብዛኛው ኑሯችን በዕጦት የተሞላ ስለሆነ አባቶቻችን ዕጦትን እንዴት እንደምንቋቋም እንጂ ከምቾት ጋራ እንዴት እንደምንኖር አላሠለጠኑንም ይሆናል::»

ይህ ንግግር ከርሷ የፈለቀ ይሁን ከምዑዝ የተገኘ ማወቅ አልቻልሁም:: እኔም አንዳንዴ ከምዑዝ ያጠራቀምሁት ሐሳብ በጊዜ ብዛት የእኔ ይመስለኝና በልበ ሙሉነት እተረትረዋለሁ::



አቶ ያን ለዕረፍት ወደ አውሮፓ ሲሄድ እሷ የምቾት ግዞተኛ ሆና ተቀመጠች::

«ታውቃለህ፣ ሲሰለቸኝ ጊዜ ምዑዝን ልጋብዘው ፈለግሁ፤ አብሮኝ እንዲውል ስደውልለት ሳያቅማማ መጣ፤ ከዚያ አብሮኝ ዋለ::»

ሣቀች፣ የዚህን ሣቅ ትርጉም ዐውቀዋለሁ፤

«ወሲብ ያን ያህል ቀላል ነው?» አልሁ ቅናት በተጠናወተው ድምፅ፤

«አይደለም፣ እኔ ራሴን እንደ ልቅ ሴት አልቆጥርም፤ እንደሚፈልጉኝ ወንዶች ብዛት ካየኸው በጣም ቁጥብ ነኝ:: አንድ ወንድ በጣም ስለሚያምር ወይም ዘናጭ ስለሆነ፣ ወይም ስለ ወሲብ በግልጽ ስለሚያወራ ስሜቴን ሊያነሣሣው አይችልም፤ ስሜቴን የሚያነሣሣው አስማተኛ ወንድ ነው::»

«አስማተኛ?»

«አስማተኛ ስልህ፣ አለ አይደል፣ በተዘጋ በር የሚገባ፣ ያልጠበቅኸውን ነገር የሚያሳይህ፣ እኔን የማያስደንቅ ነገር ሳገኝ ነው የምሸፍድ፤»

«አልገባኝም!» አልሁ በኩርፊያ፤ ነገሩን በዝርዝር ባቀረበችው ቁጥር የመከራዬ መጠን እያየለ ሲሄድ ይታወቀኛል::

«ምዑዝ እቤቴ ሲመጣ. . .» ቀጠለች መክሊት፣ «ትንሽ አውርቶ ይመለሳል ብዬ ነው:: ትዝ ይለኛል፣ በጣም ዘንጦ መጣ:: ቆንጆ ሽቶ ተቀብቷል፣ ግን ይሄ ላንዲት ሴት በግልጽ

የሚታይ ማስጠንቀቂያ ስለሆነ አልተዘናጋሁለትም፤ እና እያንዳንዱን ነገር ነቃ ብዬ ተከላከልሁት። ትንሽ ቆይቶ ግን አዘናጋኝ እና ሶፋ ላይ ጋደም ብሎ ራሱን እንዳመመው ሰው እጁን ግንባሩ ላይ ጣል አድርጎ፣ «ቡና አፍይልኝ፤» አለኝ። «ታዲያ የኮረንቲ ቡና አልፈልግም። የመሺን ዓላማ ቡናውን በፍጥነት ማድረስ ነው። እኛ እንደ ፈረንጆች የሚያስቸኩል ነገር የለብንም። የምንጠብቀው፣ የቀጠረን መሲሕ የለም። ስለዚህ እንደ አገራችን ባህል በጀበና አፍይልኝ፤» አለ። ለጊዜው ጓዳ ገብቶ መንጎዳጎዱን ስላልፈለግሁ «የቡና ዕቃ የለም አልሁት። ታዲያ እሱ ምን እንዳለኝ ታውቃለህ፣ አንቺ ሙቀጫ እና ጀበና ፈልጊ፣ እኔ ዘነዘናውን ይዤ መጥቻለሁ አለኝ። እሺ ብዬ ጓዳ ከገባሁ በኋላ ግን የዘነዘናው ትርጉም ገባኝ። ባለጌ አይደል? በጣም እየሣቅሁ ማቀራረብ ጀመርሁ።

«ዐየህ፣በኛ ቤት ቡና እንደ ታቦት የሚፈራ እና የተቀደሰ ነገር ነበር። ጀበና ከወረደ በኋላ ልጆች ሳሎን ውስጥ እንዲሯሯጡ አይፈቀድላቸውም፤ ምክንያቱም ቡና የተቀደሰ ነገር ነው። ገብቶሃል የምልህ?»

የገባኝ መሰለኝ። ያኔ ደብረ ማርቆስ ሳለሁ ለብሔራዊ ውትድርና በምሰናዳበት ወቅት አባ ገብረ መስቀል የተባሉ ባሕታዊ ከዱር ወደ ከተማችን መጡ። በተለያየ ጊዜ ከዱር ወደ ከተማ የሚመጡ ባሕታውያን በዱር አምሳል የተሠሩ(ፀጉራቸው እንደ ቅጠል የተንዠረፈፈ፣ ሰውነታቸው በገመድ እና በመቁጠርያ ሐረግ የተተበተበ ስለሆነ) እንግዳ የሆነ ግርማ ሞገስ ነበራቸው። አባ ገብረ መስቀል ወደ ከተማ እንደ ገቡ፣ ቡና የክርስትና ደመኛ መሆኑን ሰበኩ። የከተማው ምእመናን ጀበናቸውን እንደ ጠላት ቆጥረው ባንድ ሌሊት ሠባብረውት አደሩ። እማዬ ግን፣ ‹ጠላትን



ከማውደም የሚገኝ ትርፍ የለም› ብላ ጀበናውን በመንደራችን ለሚኖር ሸክላ ሠሪ በቅናሽ ሸጠችው። ሸክላ ሠሪው በበኩሉ ጀበናውን አፍርሶ እንጀራን የሚከለክል ባሕታዊ እስኪመጣ ድረስ የሚያገለግል ምጣድ አበጀበት። በጊዜው ባሕታዊው በቡና ላይ እንዲያ ያመረሩበት ምክንያት አልገባኝም ነበር። አሁን መክሊት ከፊቴ ቁጭ ብላ፣ «ቡና የተቀደሰ ነገር ነው!» ስትለኝ፣ ጀበና የሰማዩን እግዜር የሚቀናቀን ምድራዊ እግዜር መሆኑ ተገለጠልኝ። ቤተ ክርስቲያን አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ እንዳላት፣ ጀበናም አቦል(አብ - ወል)፣ ቱና እና በረካ የሚባል ‹ሥላሴ› አለው። ቤተ ክርስቲያን ማዕጠንት አላት፣ ጀበናም በዕጣን ይታጀባል። ቤተ ክርስቲያን ቁርባን አላት፣ ጀበናም ቡና ቁርስ አለው። ቤተ ክርስቲያን ነቢያት አሏት፣ ጀበናም በስኒ ትንቢት የሚናገሩ ንግርተኞች አሉት።

«እና እንዳልኩህ፣ ቡና የተቀደሰ ነገር ነው!» ስትል ቀጠለች፤ መክሊት፣ «. . ምዑዝ ግን ቡና የወሲብ ትርጉም እንዳለው ሊያሳየኝ ፈለገ። ‹ፍቅር እስከ መቃብር ሲተረክ ሰምተሻል? እዚያ ውስጥ ያሉ ሴቶች ቡን ፈልቷል ሲሉ ለስርቆሽ መዘጋጀታቸውን በኮድ መናገራቸው ነው። የቡና ዕቃዎችን እስቲ እያቸው፣ ሁሉም የወሲብ አካል አላቸው፤> አለኝ። ወዲያው የቡና ዕቃዎቼን አውጥቼ ስደረድር ነገሮች ተደበላለቁብኝ፤ እውነትም ጀበናውን ሳየው የቆመ ብልት አለው። በዚያ ላይ አምላክ ነው፤ ይታይህ። ከዚያ በቃ ሐሳቤን ማባረር እንደማልችል ገባኝ። እስቲ አስበው፣ ቤተ መቅደስ ውስጥ የብልግና ሐሳብ ቢመጣብህ አትፈራም፤ ግን ምን ያደርጋል፣ የሚያስፈራ ነገር ያሻፍዳል።»

«እሺ!» አልሁ፣ ለምን እንዳልሁ ሳይገባኝ።

«ከዚያ በቃ ማምለጫ ስፈልግ፣ አንተኮ ባለትዳር ነህ፣

ምናምን አልሁት! ምን እንዳለኝ ታውቃለህ፣ ታዲያ ምን ችግር አለው፤ «እያንዳንዱ ባለትዳር ከቤቱ ሲወጣ ወንደላጤ ነው፤ አለኝ። ከዚያ ቀጠለና ደሞ፣ አትጨነቂ፣ ሚስቴ አትቀናም እንዲያውም የጻፈችልኝን የድጋፍ ደብዳቤ ላንብብልሽ› አለና ባዶ ወረቀት አውጥቶ እየፈጠረ ያነብልኝ ጀመር።»

ለ፦ተወዳጇ ለባለቤቴ ውሽማ፣

*ጉዳዩ፦ ትብብርን ይመለከታል፤*

*ይህን ደብዳቤ ይዞ የሚመጣው ጎልማሳ የሕግ ባለቤቴ ነው። ከእሱ ጋራ ጥቂት ዓመታት ስንቆይ አንድ ሌሊት እንኳ ተቀያይመን አናውቅም። ባለቤቴ አልጋ ላይ ጀግና ነው፤ ትጉህ ነው፤ በራስጌ ነው ሲሉት በግርጌ መገኘት ልማዱ ነው። በዚህ የተነሳ የእኔ እመቤት፣ በቤታችን ከሚገኙት ዕቃዎች ውስጥ ብርጭቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ የመሻገር ዕድል ሲኖረው አልጋችን ግን ከአንድ ሌሊት ያለፈ ዕድሜ የለውም።*

*ውድ የባለቤቴ ውሽማ፣ ብዙ ወንዶች ከወሲብ በኋላ አንድ ዐመል አያጡም - ጡት መሀል ተኝቶ የሚያለቅስ አለ፤ የተረሳ ዘፈን የሚዘፍን አለ፤ ሲጃራ የሚጠጣም አለ። ባለቤቴ በዚህ በዚህ በኩል ነጻ ስለሆነ የሚያሰጋሽ ነገር አይኖርም። ከእንድገም በቀር ሌላ ዐመል የለውም። በተጨማሪም ራቱን ከእኔ ዘንድ ተመግቦ ስለሚመጣ ድስት ልጣድ፣ ምጣድ ላግም ብለሽ አትጨነቂም። ይህንና የመሳሰለውን ከግምት በማስገባት አስፈላጊውን ሁሉ እንድታደርጊለት እጠይቅሻለሁ።*

ከሰላምታ ጋራ

የሰማኒያ ሚስቱ

በከንፈር ቀለም የታተመ ማሕተም አለው



ያም ሆነ ይህ ምዑዝ እና መክሊት አልጋ ውስጥ አብረው አመሹ። ማታ ላይ ምዑዝ ወደ ቤቱ ለመሄድ ሲዘጋጅ መታጠቢያ ቤት ገብቶ ዘጋ(መክሊት ስትነግረኝ)፣ ከመታጠቢያ ቧንቧው የሚወርደው ውኃ ሽሽሽሽ የሚል ድምፅ ሲያሰማ ከየት መጣ የማይባል ንዴት ሰንጎ ያዛት። ምዑዝ ወደ ሚስቱ ከመመለሱ በፊት የእሷን ጠረን ከገላው እያባረረ እንደ ሆነ ገባት። ሊታጠብ ሲነሣ፣ እንዳይታጠብ ለምን አልከለከልኩትም፤ ሻወሩ ተበላሽቷል ብዬ ለምን አልዋሸሁትም፤ ብላ ተጸጸተች። ያለበትን ሁኔታ ለመረዳት አላቃታትም። እሷን እሷን እየሸተተ ቢሄድ ከሚስቱ ጋራ ሊጣላ ነው፤ ትዳሩ ሊፈርስ ነው፤ መክሊት ይህ እንዲሆን አትፈልግም። ግን የሚስቱን ስሜት ለመጠበቅ ሲል የእሷን ክብር ማቁሰል፣ ትዳሩን ለማዳን ሲል የእሷን ቤት መድፈሩ ተሰማት።

ሽሽሽሽ የሚለው ድምፅ ሲቀጥል ፍቅሯ ከገድፍ ጋራ በመታጠቢያው ሳሕን በኩል ወርዶ ሲወገድ ያየች መሰላት፤ «በሕይወቴ አንድ ከማላውቀው ስሜት ጋራ ስፋጠጥ ተሰማኝ፤ ይገባሃል የምልህ?»

አልመለስሁላትም፤ እኔም ሽሽሽ የሚል የወራጅ ውኃ ድምፅ የሰማሁ መሰለኝ። መክሊት ከአዲስ ስሜት ጋራ የተፋጠጠችበት ሁኔታ እኔም ከዕድሜዬ አንድ ጣቢያ ጋራ የተፋጠጥሁበት ገጠመኝ ጋራ ተገጣጠመ። ነገሩ እንዲህ ነው።

ልጅ እያለሁ፣ በየዓመቱ ጳጉሜ ሦስት የቅዱስ ሩፋኤል ቀን ልጆች በዝናም የሚጠመቁበት ልማድ አለ። የዚያን ቀን አየሩ ሲቀዘቅዝ፣ እንደ ዕፉዬ ገላ ሲባክኑ የዋሉ ነጫጭ ቀሊል ደመኖች መርጋት እና መጥቆር ሲጀምሩ፣ ርጥብ ነፋስ ቅጠሎችን ከዛፎች ነጥሎ እንደ ቢራቢሮ ሲነዳቸው ድሆች ዳባቸውን፣ ባለጸጎች

ካባቸውን ከልብስ ማስጫ ገመድ ላይ ሲለቅሙ ልጆች በበኩላችን እጀ ጠባባችንን አሽቀንጥረን እየተጯጯህን ወደ መስክ እንወርዳለን::

ከላይ መንደር፣ ከታች መንደር የመጣ የራቁት ልጆች ገላ እንደ ናዳ እየተግተለተለ ወርዶ መስኩን ይሞላዋል:: ልጆች እንዲህ በዶፍ መሀል ስንሯሯጥ፣ ከዐዋቂዎች መሀል መስኮት ያላቸው በመስኮታቸው፣ መስኮት የሌላቸው መጠኑ ከመስኮት በማይተናነስ ሽንቁራቸው ብቅ ብለው ይመለከቱናል(የዚያን ቀን ዝናም ዝም ብሎ ዝናም አይደለም:: ‹የቅዱስ ሩፋኤል ጠበል ነው› ብለው ስለነገሩን አመንናቸው:: አድገን ነገሩን ስናስበው ግን፣ አባቶቻችን በቅዱስ ሩፋኤል ስፖንሰር አድራጊነት በዓመት አንዴ በጅምላ እያጠቡን እንደ ነበር ገባን)::

ከዓመታት ባንዱ ዓመት፣ በሩፋኤል ቀን፣ እንደ ልማዴ ከሕፃናቱ ጋራ ለመቀላቀል ቁምጣ ሱሪዬን ሳወልቅ፣ ከላባ የሣሣ ወጣኒ ፀጉር ጉያዬን ወርሶት ዐየሁና ደነገጥሁ:: ልጅነቴ ማክተሙን መቀበል አቃተኝ:: ለራሴም ለሌሎችም ልጅ አክዬ እታይ ነበር:: ለካ ችግር በተፈጥሮ ላይ አይሎ እንደ ልጅ ሐውልት ባንድ ቁመት ወስኖኝ ኖሯል:: እና በዚያች ቅጽበት ያወለቅሁትን ሱሪዬን መልሼ አጥልቄ፣ ደጃፌ ላይ ቁሜ፣ በዝናም መሀል የሚርመሰመሱትን ሕፃናት እያየሁ ተከዝሁ::

ዓመታት አልፈው ተከራይቼ በምኖርበት ግቢ ውስጥ በሚገኘው የጋራ መታጠቢያ ክፍል ውስጥ እገባና ልብሴን አወላልቄ፣ የውኃውን ማውረጃ መዘውር ሳልከፍት አንጋጥጬ ለረጅም ጊዜ እቆማለሁ:: የውኃ ማውረጃው ወንፊት በብዙ ዐይኖቹ ቁልቁል ያየኛል:: እኔም በበኩሌ በመስቀያ ምሶሶ ሥር እንደ ቆመ ሰው



ቀና ብዬ በሽብር ዐየዋለሁ:: ምን አሸበረኝ? ውኃው ድሮም ቢሆን ቀዝቃዛ ነው፤ ግን ቅዝቃዜው የተሰማኝ ሰሞኑን ነው:: ውኃው ካልተቀየረ የተቀየርሁት እኔ ነኝ ማለት ነው:: ድርጃ ቆዳዬ እንደ ተወሰደ፣ በምትኩ የቀዝቃዛ ውኃ ጠብታን እንደ መርፌ የሚፈራ ሥሥ ቆዳ ተተክቶልኛል:: እዚህ ላይ ድሮ በሦስተኛ ክፍል የሳይንስ መጽሐፍ ላይ ያነበብሁት ታሪክ በከፊል ትዝ አለኝ:: በመጽሐፉ ውስጥ እንደ ተገለጠው፣ አንድ የጥንት ተመራማሪ እየታጠበ ሳለ አንድ ግኝት ተገለጠለት:: የግኝቱን ምንነት ዘንግቼዋለሁ:: ምናልባት ሳሙና ሳይሆን አይቀርም:: ተመራማሪው ግኝቱ ብልጭ ሲልለት፣ «ዩሬካ ዩሬካ! አገኘሁት አገኘሁት!» በማለት እየጮኸ ከመታጠቢያ ቤቱ ወጥቶ ሮጠ፤ እኔም ይኸው በጋራ መታጠቢያ ቤቱ ውስጥ እርጅናዬን አገኘሁት እናም አገኘሁት! አገኘሁት! እያልሁ ወጥቼ ለመሮጥ አስቤ ነበር፤ ነገር ግን የመታጠቢያ ቤቱ ወረፋ በቀላሉ ስለማይገኝ አደብ ገዝቼ መቆዬቱ የተሻለ ሆኖ ታዬኝ::

«. . .እንደኔ ዕድለኛ የለም፤ ፕሮሰስ አለቀልኝ፣ አልነገርኩህምንዴ? ያን ከጀርመን ከመጣ በኋላ ጥቂት ቆይተን አውሮፓ እንሄዳለን:: ያን በጣም. . .በጣም ጥሩ ሰው ነው፤ ግን ዕድለኛም ብሆንም እፎይ ብዬ አላውቅም:: ከጥቂት ሳምንት በፊት የነበረው ጭንቀቴ ቪዛ አይሰጡኝ ይሆን የሚል ነበር:: አሁን እሱ ሲሟላ ደሞ አውሮፕላኑ በሰላም ይደርስ ይሆን? የሚል ጭንቀት ውስጥ ገብቻለሁ፤» በማለት መክሊት ከሐሳቤ መለሰችኝ::

«ከምዑዝ ጋራ ነው ቀጠሮሽ?» አልኳት::

«አዎ! ምነው?» መልሳ ጠየቀችኝ::

«ጣማችሁ፣ ልትደግሙት ነው?»

«ሰእሱ አይደለም፤» አለች መክሊት፣ «እንደ ነገርኩህ ባለፈው ነገሩ የተጠናቀቀበትን መንገድ አልወደድኩትም:: ዐየህ፣ እኔ የሚወዱኝ ሰዎች ከፈለግሁ እረሳቸዋለሁ፤ ሳሚን ሳይቀር:: እነሱ ግን እንዲረሱኝ አልፈልግም፤ እና ከመሄዴ በፊት በምዑዝ ላይ አሻራዬ እንዲኖር እፈልጋለሁ:: ምን አደርጋለሁ? ምናልባት እቧጭረው ይሆናል፤ አልያም እነክሰው ይሆናል:: መስተዋት ፊት ቆሞ የጥርሴን ምልክት ሲያይ አስቦኝ ፈገግ እንዲል እፈልጋለሁ:: ያ ካልሆን ደሞ ምናልባት ካደረግን በኋላ በካናቴራዬ ርጥበቴን አስነካና እሰጠዋለሁ፤ እንዳያጥበው አሳስበዋለሁ:: እንጃ፣ ብቻ የሆነ ነገር. . .ዐየህ፣ እኔ ለአገሬ ብዙ ደንታ የለኝም፤ ግን ከምወደው ሰው ልብ መደምሰስ ያስፈራኛል:: ይገባሃል የምልህ?»

ከዚህ በኋላ አብራኝ እንድትቆይ ፍላጎት አልነበረኝም፣ «የቀጠሮሽ ሰዓት አልፏል!» አልኳት ክንዷን አንሥቼ ሰዓቷን እያየሁ::

«ቆይ ትንሽ ይጠብቅ! ቀጠሮ ማክበር ለመሥሪያ ቤት እንጂ ለፍቅር አይጠቅምም:: ትንሽ መናፈቅ፣ ትንሽ መስጋት፣ ትንሽ መበሳጨት፣ ትንሽ መቁነጥነጥ አለበት:: በሬዲዮ ግጥም ሲያነቡ ሰምተሃል? አንድም ቀን ስለ ቀጠሮ አክባሪ ሴት የተጻፈ ግጥም ሰምቼ አላውቅም:: ግጥም እንዲጻፍላት የምትፈልግ ሴት መዘግዬት ወይም መቅረት አለባት!»

ተሰናብታኝ ከሄደች በኋላ አስተናጋጁ መጥቶ በእግር እና በእግሬ መሀል መጥረጊያ አስገብቶ በረንዳውን መጥረግ ጀመረ:: ወደ ውስጥ ገባሁና በመስኮቱ አጠገብ ተቀመጥሁ::



እየመሸ ነው:: በማስታወሻዬ ላይም መሸበት:: በመስኮቱ በኩል ስመለከት፣ ከውጭ ያሉት ሕንፃዎች፣ ዛፎች እና አጥሮች ቀለማቸው እና ዝርዝራቸው ተውጦ ንድፋቸው ብቻ ቀረ:: ማዶ ካለው ቀለበት መንገድ ላይ መኪኖቹ እንደ አብሪ ጥይት በጨለማው ውስጥ ውር ውር ሲሉ ታዩኝ:: ከምሥራቅ ሰማይ በኩል አንድ ጉማጅ ብርሃን እየተጎተተ ብቅ አለ:: የአውሮፕላን ፍሬቻ ወይም እግዜር በዛለ ክንዱ የወረወረው ኮከብ ይሁን አላወቅሁም:: ጆሮዬ ትዝ አለኝ:: አንጉል ከሩቅ ይሰማል:: ከኋላዬ ከካፌው ወጥተው ወደ ቤተ ጋለሞታ ለመሄድ የተሰናዱ ደንበኞች ንግግር ይሰማኛል::

«ኮንዶም ታውሰኛለህ?»

«አውስሃለሁ! ግን ተጠቅመህ ትመልሳለህ!»

በመስኮት በኩል ለረጅም ጊዜ ማፍጠጤ ትዝ ሲለኝ እንደታከተኝ ገባኝ:: አዎ፣ ምዑዝ ባንድ ወቅት እንደተናገረው፣ «የናፈቀ ሰው በር በሩን፣ የታከተ ሰው መስኮት መስኮቱን ያያል!»

ተፈጸመ